
# የዓለማችን ሁኔታዎችና

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች

በዶክተር ቻርለስ ዳየር
*Dr. Charles Dyer*



ተርጓሚ
መጋቢ አሸናፊ ከተማ

መቅድም

መግቢያ

ምዕራፍ 1. የወደፊቱን ለመረዳት ያለፈውን ታሪክ መመርመር

ምዕራፍ 2. ተስፋዎች

ምዕራፍ 3. አዲሱ ፍልሰት

ምዕራፍ 4. ሠላም የሚጠይቀው ዋጋ

ምዕራፍ 5. ሦስተኛው ቤተ መቅደስ

ምዕራፍ 6. የፍጻሜው እልቂት

ምዕራፍ 7. ሩሲያ እንበሳው ጥርስ አልባ ሆኗል?

ምዕራፍ 8. ነዳጅ ዘይት፥ የምዕራባዊው ሥልጣኔ መጠቂያ

ምዕራፍ 9. እስልምናና የዓረቦች አንድነት አፈ ታሪክ

ምዕራፍ 10. ሳዳም ሁሴንና የባቢሎን መግነን

ምዕራፍ 11. ቱርክ፥ ኢራን እና የእስላማዊው ኅብረት በእስራኤል ላይ ማበር

# የዓለማችን ሁኔታዎችና የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች

በዶክተር ቻርልስ ዳየር
Dr. Charles Dyer

ተርጓሚ
መጋቢ አሸብር ከተማ

ልዩ ረዳት
ትፍስህት ለማ

ኤዲተር
ገበየሁ አየለ

Published by
የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን
LAPSLEY/BROOKS FOUNDATION
Dallas, Texas --- Addis Ababa

U.S.A. Ethiopia

2003 - 1995

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

All Rights Reserved

2003

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው

‘‘World News and Bible Prophecy’’

by Charles H. Dyer

Copyright 1993

Tyndale House Publishers

Carol Stream, Ill. U.S.A.

ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን

የታተመውም በደራሲው ፈቃድ ነው።

የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን

ስልክ 201464 ፖስታ 41221

አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

Publisher

Lapsley/Brooks Foundation

Dallas, Texas, U.S.A.

2003 A.D. - 1995 ዓ.ም.

# የመጽሐፍ ማውጫ


- መቅድም ........................................ 6
- መግቢያ ........................................ 7

**ክፍል አንድ፡ እስራኤል፡ በዓውሎ ነፋስ መካከል** ............. 11

- 1. የወደፊቱን ለመረዳት ያለፈውን ታሪክ መመርመር ............. 14
- 2. ተስፋዎች ........................................ 21
- 3. አዲሱ ፍልሰት ........................................ 26
- 4. ሠላም የሚጠይቀው ዋጋ ........................................ 49
- 5. ሦስተኛው ቤተ መቅደስ ........................................ 56
- 6. የፍጻሜው እልቂት ........................................ 68

**ክፍል ሁለት፡ መካከለኛው ምሥራቅ፡ የነዳጅ ዘይት፥ እስላም እና አዲሱ ናቡከደነፆር** ........................ 76

- 7. ሩሲያ አንበሳው ጥርስ አልባ ሆኗል? ........................ 79
- 8. ነዳጅ ዘይት፥ የምዕራባዊው ሥልጣኔ መጠቂያ ................ 88
- 9. እስልምናና የዓረቦች አንድነት አፈ ታሪክ .................. 95
- 10. ሳዳም ሁሴንና የባቢሎን መግነን ......................... 104
- 11. ቱርክ፥ ኢራን እና የእስላማዊው ኅብረት በእስራኤል ላይ ማበር ... 120

**ክፍል ሦስት፡ አውሮፓ፡ ወታደራዊ ኃይልና አዲሱ የዓለም ሥርዓት** 138

- 12. አውሮፓ፡ ወታደራዊ ኃይልና አዲሱ የዓለም ሥርዓት ......... 140
- 13. የሰላም ሰው/የሥልጣን ሰው ................................ 157
- 14. የአውሬው ውበት ........................................ 166
- 15. አርማጌዶን፤ የመጨረሻ ግብ ................................ 172

**ክፍል አራት፡ ትንቢት፤ የነገዎቹ አርእስተ ዜናዎች የዛሬዎቹን ፍላጎቶች የሚያረኩት እንዴት ነው** ........................ 182

- 16. እግዚአብሔር በእርግጥ የወደፊቱን ሁኔታ ይተነብያል? ........ 184
- 17. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶችን ማጥናት የሚኖርብኝ ለምንድነው? .202
- 18. ቢሆንስ ታዲያ? ........................................ 211

**አባሪዎች**

- የእንግሊዝኛ ቃላት ዝርዝር ................................ 220
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማውጫ ........................... 223
- ካርታዎች ........................................ 229
- የአሳታሚው ማስታወሻ ................................ 233

# ምስጋና

ይህ የትርጉም ሥራ ዳር እንዲደርስ ሞያዊ እርዳታ በመስጠት ረገድ የተሳተፉትን ኢትዮጵያውያን በሙሉ፥ በተለይም እንግዳሸ ማርቆስ፥ አስቴር ተመስገን፥ ፍራንክ ኪንስማን፥ ሸርሊ ኩክ፥ ፓት ቶምፕሰንና ሊዝ ገንተር ላደረጉት አስተዋጽዎ ከልብ እናመሰግናለን።

# የዓለማችን ሁኔታዎችና የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች

# መቅድም

ፈሪሳውያን የጊዜውን ምልክቶች ለማየት ባለመቻላቸው ክርስቶስ ዕውሮች ብሎ የገሠጻቸው መሆኑ ማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 16፥1-4 ውስጥ ተገልጧል። ክርስቶስ በተተነበየለት መሠረት እውነተኛው መሢሕ መሆኑን የሚያረጋግጡ ድርጊቶችን ሲፈጽም እየተመለከቱ አለማመናቸው ነበር ፈሪሳውያንን ያስገሠጻቸው።

የዘመናዊው ዓለም የሃይማኖት መሪዎችም በተመሳሳይ ከእግዚአብሔር ትንቢታዊ ፕሮግራም ጋር የተዛመዱ ሁኔታዎች ሲከናወኑ ላለማየት ልክ እንደ ፈሪሳውያን ታውረዋል። የዚህ ምክንያቱ ባመዛኙ፥ አለማመናቸውና መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን በትክክል ያለመረዳታቸው ችግር ነበር።

የጌታን ዳግም ምጽአት የሚጠቁሙ ምልክቶችን በተመለከተ፥ የጠራ አሳብ ሊኖረን ይገባል። ቀጣይ ክንውን የሆነው የቤተ ክርስቲያን መነጠቅን የሚጠቁም ምልክት አልተሰጠም። ዛሬ በዓለም ላይ የምናያቸው ሁኔታዎች ከመነጠቅ በኋላ የሚመጡና በመቃረብ ላይ ያሉ መከራዎች ምልክት ናቸው። ከእነዚህ ጥቂቶቹ፥ ማለት ወደ መጨረሻው የዓለም መንግሥት ምሥረታ የሚደረገው እንቅስቃሴ፥ በመካከለኛው ምሥራቅ ችግር ላይ ትኩረት የማድረጉ ጉዳይና በመጨረሻው ዘመን ለሚኖረው የዓለም መንግሥት መምጣት ሁኔታዎችን የሚያመቻቸው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እድገት የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። አነስተኛ ምልክቶችን በተመለከተ የሚኖሩ አመለካከቶች ቢለያዩም፥ ዋናው ነጥብ ግልጥ ሆኗል። ምንም እንኳን ጊዜው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይገለጥ፥ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በጣም የቀረበ የመሆኑ እውነት በአንዳንድ የማያምኑ ወገኖች ዘንድ እንኳን ግንዛቤ አግኝቷል። ይህ መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ከዘመናችን ሁኔታዎች ጋር ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ የተደረገ የብዙ ማስረጃዎች ጥልቅ ጥናት ነው። አንባቢያን መጽሐፉ ውስጥ በሚገኙ ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ ላይ አይስማሙ ይሆናል። ዋናው ማጠቃለያ ግን ግልጥ ነው። ከትንቢታዊ እውነቶች ጋር በተዛመደ መልኩ የዓለም ዜናዎች ወይም የዘመናችን ሁኔታዎች፥ ታላቅ ቁም ነገር አላቸው። ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለወንጌሉ ሥራ እንዲተጉና የቤተ ክርስቲያንን በክብር መነጠቅ የሚያበስረውን የመለከት ድምፅ ነቅተው እንዲጠብቁ ሊያነሣሣቸው ይገባል።

አንባቢዎች ይህን መጽሐፍ የአሁኗን ዓለማችንን ሁኔታዎች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ጋር በሚያዛምዱ እውነቶችና ዝርዝር ጉዳዮች የታመቀ፥ እንዲሁም የፍጻሜው ዘመን ጉልህ ትንቢታዊ ምስሎችን በወጉ ደርድሮ የሚያሳይ ሆኖ ያገኙታል።

ጆን ኤፍ ዋልቮርድ

የ"አርማጌዶን የነዳጅ ዘይትና የመካከለኛው ምሥራቅ ውዝግብ" መጽሐፍ ደራሲ

# > መግቢያ <

# የአዲሱ ሺህ ዓመት ጎህ መቅደድ

"ቡለቲን ኦፍ ዘ አቶሚክ ሳይንቲስት" የተሰኘ መጽሔት ቺካጎ በተባለው የአሜሪካን ግዛት ውስጥ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ህዳር 27 ቀን 1991 እአአ በወጣው እትሙ ሽፋን ላይ አንድ የሰዓት ምስል ይዞ ነበር። የዚህ "የክፉ ቀን አመልካች" ተብሎ የተሰየመ ሰዓት የጊዜ አመልካች ቀስቱን ወደ ኋላ በመመለስ ከምሽቱ 5፥43 ሰዓት ላይ አሳርፎታል። ይህ ጊዜ ዓለማችን ወደ "የኒውክሊየር ውድቅት" ወይም ክፉ ቀን ለመድረስ የቀራትን ርቀት ነበር የሚያመለክተው። የዚሁ መጽሔት ተጓዳኝ የሆነ አንድ ጽሑፍ ስለ ክፉው ቀን መዘግየት የተሰማውን የተስፋ ለውጥ ሲገልጥ፥ "አሮጌው ጦርነት አበቃ። በምሥራቁና በምዕራቡ አህጉራት መካከል ለ40 ዓመት የቆየው የኒውክሊየር ጦር መሣሪያ ፉክክር አከተመ" ብሎ ነበር።

በጊዜው የነበሩት የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሶቪየት ኅብረት ውስጥ ተሞክሮ ያልተሳካውን የመንግሥት ግልበጣ አስመልክተው ሲናገሩ፥ "ዛሬ በምንገነዘባቸው ሁኔታዎች ላይ በመመሥረት አዲሱ የዓለም ሥርዓት ምን እንደሚመስል መተንበዩ አዳጋች አይደለም. . . ጊዜውን ከተጠቀምንበትና የዓለም ሕዝቦች አሳባቸውን ዘላቂ ወደሆነ የሠላም መዋቅር እንዲመልሱ ካደረግን ታሪካዊ ምዕራፍ ይጀመራል" ብለዋል።

ሰዎች "ሠላምና ደኅንነት ነው ሲሉ፥ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል፤ ከቶም አያመልጡም" (1ኛ ተሰ. 5፥3)።

ዓለም ወደ አዲሱ ሺህ ዓመት (Millennium) በመገስገስ ላይ ናት። ከፊታችን ምን አዲስ ነገር ይጠብቀን ይሆን? መጪው ዘመን ሠላምና ብልጥግናን ለዓለም ያመጣ ይሆን? ወይስ ዓመቶቹ የተስፋ መቁረጥ ይሆኑ? መጪውን ዘመን በተስፋ ዓይን የሚያዩ ሰዎች የኮሙኒዝምን መፈራረስ፥ የቀዝቃዛውን ጦርነት እየሟሸሸ መሄድ እያመለከቱ፥ ወደፊት መልካም ጊዜ እንደሚመጣ እነዚህ ሁኔታዎች ይጠቁማሉ ይላሉ። ክፉ ነገር የሚታያቸው ደግሞ የዘረኝነት ግጭቶችን፥ የአካባቢ መበከልን፥ በድሀና በበለጠጉ አገሮች መካከል እየሰፋ የሚመጣውን ልዩነትና የኒውክሊየር ጥበብን እያደገ መምጣት እየጠቆሙ ዓለም ለጥፋት ተቃርባለች ይላሉ።

ወደፊት የሚሆነውን ነገር ሊተነብይ የሚችል ሰው አለ? ከአሜሪካኑ የንግድ ማዕከል እስከ ምሥራቅ አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ ያሉ ጠቢባን ወደፊት ይሆናል የሚሉትን ነገር ለመተንበይ ሞክረዋል። የብዙዎቹ ትንበያ አልሆነም። በ1980ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት የአሜሪካን መንግሥት በታሪኩ ከፍተኛ የሆነውን የሠላም ወቅት ወታደራዊ ግንባታ አከናውኗል። የወታደራዊ ግንባታው ዓላማ፥ "ዕኩዩን አምባገነን መንግሥት" ማለት፥ ግዙፉን የሶቪየት ኅብረት መንግሥት ለመከላከል ነበር። ያን ጊዜ የምሥራቅ አውሮፓ ወይም የሶቪየት ኅብረት መንግሥታት ይወድቃሉ ብሎ የተነበየ አልነበረም። በ1987 እአአ የአሜሪካን፥ የምዕራብ አውሮፓ፥ የሳውዲት ዓረብ እና የኩዌት መንግሥታት የሳዳም ሁሴንን ወታደራዊ ኃይል ግንባታ በምስጢር ይረዱ ነበር። ታዲያ ሳዳም ሁሴን* በሦስት ዓመት ውስጥ ኩዌትን ወረው ዓለም ወረራውን የሚያወግዝ መሆኑን ማን ተነበየ? የዓለምን ሁኔታ አስመልክቶ በየጊዜው የተሰነዘሩ ትንቢቶች ስሕተት በመሆናቸው፥ ጠቢባኑ አፋቸውን እንዲይዙ አድርገዋቸዋል። ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን ለመተንበይ እንችላለን? ወይስ ይህን አስመልክቶ የሚደረጉ ሙከራዎች ሁሉ ከንቱ ናቸው?

የወደፊቱን እናውቃለን የሚሉ ሁሉ በዓለም ታሪክ ውስጥ መልካም ስፍራ የላቸውም። ከንቱ በሆኑ ትንበያዎች ሁሉ መካከል ግን አንድ የተለየና ጉልህ ነገር አለ-መጽሐፍ ቅዱስ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በዘመናት ስለሚሆኑ ነገሮች የተናገራቸው ትንቢቶች ተጽፈዋል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች አንድ አራተኛው፥ ሁነቶች ከመከናወናቸው በፊት የሚተነብዩ ናቸው። እግዚአብሔር ደግሞ ተሳስቶ አያውቅም! የእግዚአብሔር ትንቢቶች ፍጹም ትክክልና እውነት መሆናቸውን በዘመናት ሁሉ ታሪክ አረጋግጧል። እግዚአብሔር የአንድን ነገር ፍጻሜ ከጅማሬው ስለሚያውቅ (ዓለማትን ሁሉ የሚቆጣጠርም ስለሆነ)፥ እርሱ ብቻ ነው ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች በትክክል ለመናገር የሚችል።

የእግዚአብሔር ቃል የወደፊቱን ይተነብይ ይሆናል፤ መጽሐፍ ቅዱስን ለማይከታተሉ ወይም ለማያጠኑ የሚሰጠው ጠቀሜታ ግን ጥቂት ነው። አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ያነቡና ትርጉም የሌላቸው በቅፅበት የሚለዋወጡ ምስሎች የሚመለከቱ ይመስላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ለዘመናት የሚሆን ዕቅድ አለው? ወይስ በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ሰዎች የተጻፉና ያልተያያዙ መጻሕፍት ስብስብ ነው?

---

* የዚህ መጽሐፍ አሳታሚዎች ይህን መጽሐፍ ለማሳተም የመጨረሻ ዝግጅት በሚያደርጉበት ሰዓት በኢራቅ የሳዳም ሁሴን አገዛዝ አብቅቷል። ሳዳም ሑሴን በአሁኑ ሰዓት ያሉበት አይታወቅም።

የመጽሐፍ ቅዱስና እውስጡ ያሉት ትንቢቶች ደራሲ እግዚአብሔር እራሱ መሆኑ እንዲህ ተገልጧል፦ "ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም። ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" (2ኛ ጴጥ. 1፡20-21)። የመጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛ ደራሲ እግዚአብሔር፥ ንግግሩም ግልጥ ነው።

የጊዜያችንን ጋዜጦችና መጽሔቶች ማንበብ፥ ለመገጣጠም የሚያስቸግሩ ቁርጥራጭ ነገሮች (Jigsaw Puzzle) ያሉበት ጠረጴዛን እንደመመልከት ነው። እያንዳንዱ ነገር ለየብቻው ደስ ይላል፤ ነገር ግን በዙሪያው ካለ ነገር ጋር አልተሰካካም ወይም አልተያያዘም። ቁርጥራጮቹን ነገሮች እርስ በርሳቸው ለማሰካካት ብቸኛው መፍትሔ፥ በሳጥናቸው ላይ የተጻፈውን ምስል ወይም መግለጫ መከተሉ ነው። የምስሉን መግለጫ በመመልከት እያንዳንዱ ቁርጥራጭ በአጠቃላዩ ቅርፅ ወይም ዕቅድ ውስጥ የት መግባት እንዳለበት ለመረዳት ይቻላል። በተመሳሳይ ሁኔታ አጠቃላዩን የእግዚአብሔር ቃል ዕቅድ በመረዳት፥ በዓለም የሚከናወኑ አያሌ ሁነቶችን ለመመዘንና፥ እግዚአብሔር ለታሪክ ባለው ዕቅድ ውስጥ የትኛው ነገር የት እንደሚገባ ለመወሰን ይቻላል።

ብዙ ሰዎች የመረዳት ችሎታ የለንም ብለው ስለሚያምኑ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ትንቢቶችን ማጥናቱን ይፈሩታል። መልካም ዓላማ ያላቸው ሰባኪዎች እና ምሁራን የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃቀም ዘዴ፥ የብዙዎችን በራስ የመተማመን ድክመት ሊረዳ አልቻለም። አንዳንዶቹ ግልጥ ያልሆኑ ጥቅሶችን ተዛማጅነት ከሌላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይወስዱና አሁን ላሉት ሁኔታዎች እግዚአብሔር የሰጣቸው መገለጦች ናቸው ይላሉ። ምንባቦቹን ለመመልከት ድፍረት ያገኙት ደግሞ ከዚህ ቀደም ፈጽሞ ያልሰሟቸው ስሞችና ቦታዎች ይገጥሟቸዋል። በዚህ ጊዜ በትክክል ሊያነቧቸው እንኳን የማይቻላቸውን ስሞች የተረዱ ይመስል እራሳቸውን ይነቀንቁና በቀስታ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ይዘጋሉ። ከአንባቢው ሕዝብ አማካይ የሚሆኑት መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት አይቻልም በሚል እምነት የንባብ ሙከራቸውን ያቆማሉ።

እግዚአብሔር ግን፥ መጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ቋንቋ እንደተጻፉ የሳይንስ መጻሕፍት አብዛኛው አንባቢ የማይረዳው ሆኖ እንዲጻፍ አላደረገም። መጽሐፍ ቅዱስን፥ ትንቢትንም ጨምሮ ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው ሁሉ ዛሬ እንዲረዳው አድርጎ ነው የሰጠው። በዚህ መጽሐፍ፥ በእግዚአብሔር ትንቢታዊ ቃል ውስጥ ዋነኛ ሁነቶችን እያነሣሁ መጽሐፍ

ቅዱስ ስለሁነቶቹ የሚለውን እገልጣለሁ። እግረመንገዴንም ትንቢቶቹን ከአሁኑ የዓለማችን ሁኔታዎች ጋር አገናዝባቸዋለሁ።

ይህን መጽሐፍ በአራት ክፍሎች መድቤዋለሁ። የመጀመሪያው ክፍል፥ በፍጻሜው ዘመን ሁኔታዎች ውስጥ እስራኤል በሚኖራት ሚና ላይ ያተኩራል። እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ዕቅድ፥ ለዓለም ባለው ዕቅድ ውስጥ ዋነኛውን ስፍራ ይይዛል። ሁለተኛው ክፍል ሌሎቹ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች፥ ማለት ሩሲያ፥ ቱርክ፥ ኢራን እና ኢራቅ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ውስጥ ያላቸውን ሚና ይመረምራል። ነዳጅ ዘይትና እስልምና በእግዚአብሔር ትንቢታዊ ትዕይንት ውስጥ ያላቸው ሚና ምንድነው? ሦስተኛው ክፍል አውሮፓ የሚኖራትን ሚና ይፈትሻል። የአውሮፓ አገሮች አንድ ይሆናሉ? ከሆኑስ እንዴት ነው ይህ አዲስ የዓለም ሥርዓት መካከለኛው ምሥራቅና በሌላው ዓለም ላይ ተጽዕኖ የሚያደርገው?

የመጽሐፉ አራተኛ ክፍል ትኩረቱን ወደፊት ከሚሆኑ ነገሮች ያነሣና በአሁን ሁነቶች ላይ ያደርጋል። እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን በትንቢት ስለመግለጡ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን? የገለጠ ከሆነስ፥ ትንቢቶቹ ዛሬ ላለነው ሰዎች የሚሰጡን ጥቅም ምንድነው?

ዛሬ ያሉት ሁነቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ፍጻሜዎች አለመሆናቸውን ልብ ይበሉ። "የባቢሎን ትንሣኤ" በሚለው መጽሐፌ እንደገለጥኩት፥ እግዚአብሔር ለዚህ ዘመን ያለው የመጨረሻ ትንቢት ገና አልተጀመረም። የፍጻሜው መጀመሪያ ዝግጅት በመደረግ ላይ መሆኑን ግን ልብ እንላለን። እግዚአብሔር የፍጻሜውን ክንውን በተገቢው ቦታ በማዘጋጀት ላይ ነው። የክንውኑ ተዋናዮችም ስፍራ ስፍራቸውን በመያዝ ላይ ናቸው። ሁሉም ነገር ስፍራ ስፍራውን እንደያዘ፥ የትንቢቱ ፍጻሜ ይጀምር ዘንድ እግዚአብሔር ይፈቅዳል።

የዓለማችንን የአሁን ሁነቶች ስናይና ስንመረምር፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ትንቢቶች ይጀምሩ ዘንድ ሁነቶቹ ያላቸውን ሚና ልንረዳ ይገባል። እንዲሁም ዓለም በመለወጥ ላይ እንደመሆኗ መጠን፥ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑንም መዘንጋት የለብንም። የዘመናችንን ሁነቶች በሌላ በምንም መንገድ ሳይሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ መነጽርነት ነው መመዘን የሚገባን። በመሆኑም የዘመናችን ሁነቶች ያላቸውን ሚና በጥበብ ለመገንዘብ ይቻለን ዘንድ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶችን መረዳትና ማወቅ አለብን።

እንግዲህ ቆጭ ብለን መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንግለጥና ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች እግዚአብሔር በትንቢቶቹ ያለውን እንመርምር።

# > ክፍል አንድ <

# እስራኤል፣

## በዓውሎ ነፋስ መካከል

በመንገዱ ግራና ቀኝ እንደ ሰልፈኛ በቆሙ ሕንጻዎች መካከል ያለፈው የፀሐይ ብርሃን ነጣ ባለው ድንጋያማ መንገድ ላይ የብርሃን ኩሬ ሠርቷል። በአእላፋት ሰዎች እርምጃ የሚሸሸውና የፀሐይ ብርሃን የተንጣለለበት ይህ መንገድ የደማስቆ በር ወደተባለው ስፍራ ያመራል። እስራኤልን ለመጎብኘት የሚመጡ ሰዎች በነዚህ መስቀለኛ ክፍልፍል መንገዶችና ጠባብ መተላለፊያዎች እየተጓዙ ነው በትዝታ ወዳለፉት ዘመናት በመመለስ፥ የእስራኤልን ትዕይንቶች፥ ድምፆችና መዓዛዎች የሚያጣጥሙት። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን የመሰሉ ነጋዴዎችና ቸርቻሪዎች፥ ልዩ ልዩ ቅርፃ ቅርፆችንና ምግብ በመያዝ በየመንገዱ ዳር ሆነው ተላላፊው እንዲገዛቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጣራሉ።

በዛሬው ጠዋት ግን አንድ ችግር ያለ ይመስላል። ቸርቻሪዎችና ነጋዴዎች ሸቀጣቸውን ደርድረው በመሸጥ ፈንታ፥ ዕቃቸውን በጥድፊያ እየሰበሰቡና መደብሮቻቸውን እየዘጉ በጠባቦቹ መንገዶች ሲሰወሩ አየሁ። እስራኤልን በመቃወም የሚደረገው ንቅናቄ ወይም "ኢንቲፋዳ" በየግድግዳዎቹ ላይ በሚሰፍሩ ጽሑፎችና በምሳሌያዊ ጥላቻ ይገለጣል። ዛሬ ግን የተቃውሞ ዕለት አይደለም። ተማሪዎቼ በጣም በቅርቤ ሆነው እየተጓዝን መንገዱ ወደ ግራ ከሚታጠፍበት ስፍራ ደረስን። እዚያ ሆነን ነው ለመደብሮቹ በጥድፊያ መዘጋት ምክንያት የሆነውን ነገር የተመለከትነው።

ሁለት ተቀናቃኝ ቡድኖች ሀያ ሜትር ያህል ተራርቀው ተፋጠዋል። ወደኛ ቀረብ ያሉት እንጨት ላይ የታሠረ የእስራኤል ባንዲራ ይዘዋል። ከእኛ የራቁት ደግሞ፥ ጥቁርና ነጭ ነጠብጣብ ያሉበት ፎጣ መሰል ልብስ እራሳቸው ላይ ጠምጥመዋል። ሰዎቹ የፍልስጥኤም ነጻ አውጭ ድርጅት (P.L.O./ፒ.ኤል.ኦ.) አባላት መሆናቸውን ጥምጥሙ ያመለክታል። ተቃውሟቸውን ከፍ ባለ ድምፅ የሚገላለጡት በዓረብኛና በዕብራይስጥ ቋንቋዎች ቢሆንም፥ ፊታቸው ላይ የሚታየውን መልእክት በማየት ብቻ የቃላቶቻቸውን ትርጉም ለመረዳት ይቻላል።

ከፊት ለፊቴ ባለው ጠባብ መተላለፊያ ላይ የሚታየውን ያልተለመደ ትርዒት በጥሞና እየተመለከትኩ ቆምኩ። ተቀናቃኞቹ ቡድኖች መፈክሮቻቸውን አንዱ ወደ ሌላው በቃላት ይወረውራሉ። ያን ተከትሎ ድንጋይ መወናጨፉ ይጀመር ይሆን? ያ መሆን አለመሆኑን እዚያው ቆመን መጠበቅ የለብንም ብዬ ከተማሪዎቼ ጋር ከአካባቢው ራቅን። ትንሽ እንደተጓዝን፥ የደማስቆ በር ወደሚባለው ስፍራ ከሚያመራው መንታ መንገድ ደረስን። ሸማቾች መንገዱን ሞልተውታል። ነጋዴዎች መደብሮቻቸው በር ላይ ተቀምጠው፥ ወደ ውስጥ ገብተን ጌጣ ጌጦችን እንድንገዛቸው ይጋብዙናል። ተቀናቃኞቹ ቡድኖች ከተፋጠጡበት ስፍራ ንግዱ አካባቢ ለመድረስ የወሰደብን ጊዜ ሦስት ደቂቃ ነው። በጣም የሚገርመው ነገር፥ ከሦስት ሳምንት ቆይታችን በኋላ በእስራኤል ይህ ሁሉ ነገር በጣም የተለመደና የሚያስደንቅ አለመሆኑ የተረጋገጠ ነው።

እስራኤል። ዘመናዊቷ አገር፥ ገና የኀምሳኛ ዓመት ልደቷን የምታከብር ጨቅላ መንግሥት ብትሆንም፥ የዓለም ክንውንን መካከለኛ መድረክ ይዛለች። የእስራኤልን እንደ መንግሥት የመኖር መብት አስመልክቶ የተደረገው ትግል፥ በአገሪቱ ስፋት፥ ሕዝብ ወይም ሀብት ላይ ያደርሳል ተብሎ ከተገመተው ይልቅ፥ በዓለም ላይ ያደረሰው ተጽዕኖ ይበልጣል። በ1972 እአአ ሚውኒክ (ጀርመን) ውስጥ በተደረገው የኦሎምፒክ ጨዋታ ወቅት፥ እስራኤላውያን እስፖርተኞች በታገቱና በተገደሉ ጊዜ፥ የዓለም ሕዝቦች ዓይን በዓረባውያን ሽብርተኞች ላይ አተኮረ። በ1973 እአአ በእስራኤልና በዓረቦች መካከል ጦርነት በተቀሰቀሰ ጊዜ፥ የዓለም ሕዝቦች ነዳጅ ለመግዛት መሰለፍ ነበረባቸው። በ1991 እአአ ሳዳም ሁሴን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኢራቅ ጉዳይ ላይ የነበረውን ኅብረት ለማናጋት ስከድ ሚሳይል የተሰኘውን አውዳሚ መሣሪያ በቴል አቪቭ (የእስራኤል ከተማ) ላይ ተኮሱ። ለምንድነው እስራኤል በዓለም ጉዳይ ውስጥ እንዲህ ያለ ጠቃሚ ሚና የምትጫወተው?

አንዳንዶች፥ በአይሁዳውያን ባለጠጋዎችና ዓለምን በሚቆጣጠሩ የሥልጣን ደላላዎች አማካይነት የሚካሄድ ምሥጥራዊ ሴራ አለ ብለው ያን ለማግኘት ይጥራሉ። እንዲህ ያለው መሠረተ ቢስ ግምት ፀረ-ፅዮናዊነትን ያመለክታል። የራሺያውያን ፀረ-አይሁዳዊነት፥ ሂትለር የደነገገው "የመጨረሻው መፍትሔ"፥ መገናኛ ብዙሃኗ "በፅዮናዊነት የሚመራ ነው" በማለት በአሜሪካን ላይ የሚሰነዘረው ነቀፋ፥ ሁሉ ተደምሮ ለግል ችግራቸው አይሁዳውያንን ተጠያቂ የሚያደርጉ ግለሰቦች ዓለም አላጣችም። የእስራኤል በዓለም ውስጥ ልዩ ጠቀሜታ ያለው ስፍራ መያዝ ግን፥ የጥቂት ባለጠጋ አይሁዳውያን ሴራ ውጤት አይደለም። ይህን

የምለው በሁለት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው፥ እንዲህ የሚያሴር ቡድን የለም። ሁለተኛ፥ መልሱ በጣም ጥልቅና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው!

እስራኤል በዓለም ማዕከላዊ መድረክ ላይ የመገኘቷ ምክንያት፥ አይሁዳውያን በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች መሆናቸው ነው። በዓለም ታሪክ ውስጥ መሠረታዊ ሚና ትጫወት ዘንድ እግዚአብሔር እስራኤልን መርጧታል። የዓለም ሁኔታ እንደ አውሎ ነፋስ በሚፈጥኑ ድርጊቶች በሚለዋወጥበት ጊዜ፥ እስራኤል ግን በዚህ ሁሉ መካከል በስፍራዋ ጸንታ ትኖራለች።

ለዘመናት ባለው ዕቅዱ ውስጥ እስራኤል ዋናይቱ ተዋናይ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ፈቅዷል። በፍጻሜው ዘመን ክንውን ውስጥም እንደገና ማዕከላዊውን መድረክ ትይዛለች። እስራኤል በታሪክ ውስጥ የተሰጣትን ሚና ያልተረዳ ሰው የዓለማችንን የወደፊት ሁኔታ ሊገነዘብ አይችልም። የእግዚአብሔርን ትንቢታዊ እንቅቅልሾች ለመረዳት ከፈለግን፥ ወደ ኋላ ተመልሰን እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር "ቃል ኪዳን ከገባበት" ጊዜ መጀመር ይኖርብናል። እስቲ ክንውኑን ወደጀመረው የቃል ኪዳን ሥርዓት እናምራ።

> ምዕራፍ አንድ <

# የወደፊቱን ለመረዳት ያለፈውን ታሪክ መመርመር

የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን የዘፍጥረት መጽሐፍን ብዙ ጊዜ “የጅማሬ መጽሐፍ” ይሉታል። የመጽሐፉ የመጀመሪያ አሥራ አንድ ምዕራፎች ግን “የሰው ልጅ ውድቀት” መጽሐፍ ሊባል ይገባል። እነዚህ ምዕራፎች ስለ ሰው ልጅ ብሩህ የሆነ የመጀመሪያ ታሪክ ሥዕል አይደለም የሚያሳዩን። አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሰው፥ የእርሱን ፍጡራን ፍጹምነት አናጉት። በኃጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔር ከኤደን ገነት አባረራቸው። በእነዚህ የሰው ዘር መጀመሪያ ቅድመ አያቶች የተሠራውና፥ የነፍስ ደዌ የሆነው ኃጢአትም የሰውን ዘር ከእግዚአብሔር ለየው። የሰው ዘርም በኃጢአት ድርጊቱ እጅግ ወደላቀ ደረጃ በመድረሱ፥ እግዚአብሔር ዓለምን መቅጣት ነበረበት። ኖኅ እና ቤተሰቡ ብቻ ነበሩ ምድርን ከደመሰሳት የጥፋት ውኃ የተረፉት። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ከሰው ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት እንደገና በኖኅና በልጆቹ በኩል ጀምሮ ነበር። እነርሱም ቢሆኑ ከአዳም የወረሱት ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ነበረባቸው። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ለሰው ዘር የነበረው ታላቅ ዕቅድ ባቢሎን ግንብ ሥር ተቀበረ። ሰው እግዚአብሔርን ለመከተል ፈቃደኛ ያለመሆኑን እንደገና አሳየ።

እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ ይህን የባቢሎን ግንብ የሁካታና የግራ መጋባት መድረክ በማድረግ ነው የሰው ልጆችን ዐመፅ የቀጣው። ቋንቋቸውን በመደበላለቅ የግንቡ ሥራ እንዲቆም አደረገ። ውጤቱም አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ቤተሰቦች የተለያዩ ሕዝቦች በመሆን ወደተለያየ አቅጣጫ መጓዝ ሆነ። ማንም በዕድሜ የበሰለና ሌላ ቋንቋ ለመማር የሞከረ ሰው፥ እነዚህን ሰዎች በተመለከተ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን ያህል ውጤታማ እንደነበር ይረዳል። የሰው ዘር በቋንቋ መለያየት ሌላም ችግር አስከትሏል። እንዴት ነው እግዚአብሔር ከነዚህ አዲስ ሕዝቦች ጋር ሊገናኝና ለአዲስ በረከቱ እንደገና ሊያስተባብራቸው የሚችለው?

## አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ

እግዚአብሔር ለዚህ ችግር የሰጠው መፍትሔ፥ በትውልዱ አማካይነት ለሌላው ዓለም “መልእክተኛው” የሚሆን አንድ ሰው መምረጥ ነበር። በዚሁ መሠረት አብርሃምን መረጠና እምቢ ሊል የማይቻለውን ስጦታ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ አቀረበለት።

> "ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ" (ዘፍጥ. 12፡2-3)።

የመጀመሪያ ስሙ አብራም የነበረው አብርሃም፥ በቀረበለት ጥሪ ውስጥ የነበረውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሙሉ ለሙሉ ባይረዳም፥ ለእግዚአብሔር ታዘዘ። ከቤተሰቡና ከወዳጆቹ ተለይቶም ወደማያውቀው አገር ተጓዘ። አብራም በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆኑ ከችግር ነጻ አላደረገውም። ከርሃብ፥ ከቤተሰብ ችግር፥ ከወራሪዎችና አንዳንዴ ከሚገጥመው የእምነት ማወላወል (ዘፍጥ. 12፡14) ጋር ታግሏል። ያም ቢሆን በእግዚአብሔር ተስፋ ታምኖ ነበር።

ዘፍጥረት 15 አብራም በሕይወቱ አጋማሽ ላይ ማለት በ85 ዓመቱ የገጠመውን ችግር ይገልጣል። እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ "ታላቅ ሕዝብ" እንደሚያደርገው ቃል ገብቶለታል፤ አብራም ያኔ የሰባ አምስት ዓመት ሰው ነበር (ዘፍጥ. 12፡4)፥ ሚስቱ ደግሞ የስድሳ አምስት ዓመት ሴት ነበረች። ቤተሰብ እንዲኖረው እጅግ ቢጓጓም፥ ሚስቱ መካን በመሆኗ በጋብቻቸው ዘመን ሁሉ ልጅ ልትወልድለት አልቻለችም (ዘፍጥ. 11፡30)። ቢሆንም እግዚአብሔር በሣራይ ሕይወት ተአምር ሠርቶ ወላድ እንደሚያደርጋት ያምን ነበር። ነገር ግን፥ ዘፍጥረት ምዕራፍ 15 ውስጥ የተመዘገበው ጊዜ ሲደርስ፥ ተስፋው በአሥር ዓመት አልፏል፥ ሣራ የተባለችው ሣራይም ልጅ የመውለጃ ዕድሜዋ አልፎ ነበር።

የአብራም ተስፋ መቁረጥ የታየው፥ ምዕራፍ 15 መጀመሪያ ላይ፥ "አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ ምንን ትሰጠኛለህ? እኔም ያለ ልጅ እሄዳለሁ፤ የቤቴም መጋቢ የደማስቆ ሰው ይህ ኤልዔዘር ነው አለ። . . . አብራምም ለእኔ ዘር አልሰጠኸኝም፤ እነሆም በቤቴ የተወለደ ሰው ይወርሰኛል አለ" (15፡2-3) ባለበት ሁኔታ ውስጥ በነበረ ጊዜ ነው። ከአሥር ዓመታት ጥበቃ በኋላ የእግዚአብሔር ተስፋ ከመቼውም ይልቅ የራቀ መሰለ።

እግዚአብሔር የሰጠው መልስ ከአብራም አእምሮ በላይና አስደናቂ ነበር። "ይህ [ኤልዔዘር የተባለው አገልጋይ] አይወርስህም፤ ነገር ግን ከጉልበትህ የሚወጣው ይወርስሃል. . . ወደ ሰማይ ተመልከት፥ ከዋክብ ትንም ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ቁጠር . . . ዘርህ እንዲሁ ይሆናል አለው" (ዘፍጥ. 15፡4-5)።

የአብራም መልስ እና የእግዚአብሔር አጸፋ እጅግ ድንቅ ናቸው። "አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት" (ዘፍጥ. 15፡6)። አብራም ከውጫዊ ሁኔታዎች ይልቅ በእግዚአብሔር ተስፋ

አመነ። ይህ በእግዚአብሔር ተስፋዎች ማመኑ ነው ከእግዚአብሔር ጋር ወደነበረው ትክክለኛ ግንኙነት ያመጣው። አብራምን ጻድቅ ያደረገው ምንድነው? ሥራዎቹ፥ ሀብቱ፥ ወይም መሥዋዕቶቹ አይደሉም። እግዚአብሔር አብራምን ጻድቅ ያለው እርሱ የነገረውን ለማመንና ለመቀበል በመምረጡ ነው።

እንስማማ

ከእምነት ጉዳይ ጋር ይታገል የነበረ አንድ ሰው፥ አንድ ጊዜ ኢየሱስን እንዲህ ሲል ተማጠነው፥ "አምናለሁ፥ አለማመኔን እርዳው!" (ማር. 9፡24)። ስለ እርስዎ አላውቅም፥ ለኔ ግን የዚህ ሰው ግራ መጋባትና መማጠን፥ በመንፈሳዊ ጉዞዬ የገጠሙኝን ትግሎች ያስታውሰኛል። በእግዚአብሔር አምናለሁ፥ ይሁን እንጂ አሁንም ስለ እምነቴ ጥልቀት ወይም ቅንነት ካለኝ ጥርጥር ጋር በመታገል ላይ ነኝ። በእግዚአብሔር አምናለሁ፥ በርሱም የበለጠ ለመደገፍ እፈልጋለሁ፥ በእምነት ለመራመድ ግን እፈራለሁ።

ልክ እንደኛው፥ አብራምም ታግሎ ነበር። በጥርጥር የተሞላ የሕይወት ትግል የነበረበት ቢሆንም፥ በመጨረሻ ግን እምነቱ ድል አድርጓል። በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ የነበረውን እምነት ከነበረበት ሁኔታ ጋር ሊያስታርቅ የቻለው ግን እንዴት ነበር? የኖረበትን ምድር እግዚአብሔር ነበር በገባለት ተስፋ መሠረት (ዘፍጥ. 13፡14-17) የሰጠው። ነገር ግን ባላንጣዎች ተነሥተው አብራም ከያዘውም ምድር በላይ የኛ ነው አሉ። ልጅ እንደሚሰጠው እግዚአብሔር ተስፋ ገብቶለት ሳለ (ዘፍ. 15፡4-5)፥ ሚስቱ ግን መካንና የመውለጃ ዘመኗ ያለፈባት ሴት ነበረች። አብራም ከአለበት አስቸጋሪ ሁኔታ ባሻገር በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ አብሮት እንዲሆን ከእግዚአብሔር ዋስትናን ጠየቀ። እርሱም በቃል ኪዳን አረጋገጠለት።

ዓለም ስምምነትና ውሎችን እጅግ ትወዳለች። የከርሠ-ምድር ተመራማሪዎች በአብራም ዘመን ይደረጉ የነበሩ ስምምነቶችን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች በቁፋሮ አግኝተዋል። እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን እውነተኛነት ለአብራም ያረጋገጠለት፥ ልክ አንድ ሰው ሕጋዊ ግዴታ ኖሮበት ውሉን እንደሚፈጽም ያህል ነበር። ዝርዝር ሁኔታው ዛሬ ለኛ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም፥ በዘፍጥረት 15፡9-17 ውስጥ ባለው ክፍል ኪዳኑ እንዴት እንደተከናወነ ያመለክተናል። በጊዜው ሥርዓት መሠረት፥ ሁለት ተዋዋዮች ብዙ እንስሳትን ካረዱና ሥጋቸውን ሁለት ላይ ከከፈሉ በኋላ፥ ለቃል ኪዳናቸው ማረጋገጫነት በሥጋው መካከል አብረው ያልፉ

ነበር። ያን በማድረግም "ቃል ኪዳናችንን ጥሼ ብገኝ እንደነዚህ እንስሳት አድርገኝ [ገድለህ ሥጋዬን እንዲህ ለያየው]" በማለት ቃል ይገባባሉ። ሰዎች ይህን ቃል ኪዳን ከማድረጋቸው በፊት በነገሩ በሚገባ ያስቡበት ነበር።

አብራም እንስሳቱን ካረደና ሥጋቸውን ሁለት ላይ ከከፈለ በኋላ፥ ከባድ እንቅልፍ መጣበት (ዘፍጥ. 15፡9-17)። ፀሐይ ከገባች በኋላ ሲነቃ "የምድጃ ጢስና፥ የእሳት ነበልባል በዚያ በተከፈለው መካከል አለፈ"። እዚህ ላይ ሦስት ነገሮችን ልብ ማለቱ እጅግ አስፈላጊ ነው። የመጀመሪያው፥ አብራም በተከፈለው የእንስሳት ሥጋ መካከል አላለፈም። ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ይህን ቃል ኪዳን በተመለከተ አብራምን ምንም ሕጋዊ ግዴታ ውስጥ ያላስገባው መሆኑን ነው። ሁለተኛው፥ የምድጃው ጢስና የእሳቱ ነበልባል እግዚአብሔርን ወክሏል። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ መገኘቱን የገለጠው፥ በእሳትና በጭስ ነው። በዚህ ሁኔታ ከሚጠቀሱት መካከል፥ ለሙሴ በሚቃጠለው ቁጥቋጦ መገለጡ (ዘፀ. 3፡2)፥ ሲና ተራራ ላይ እሳትና ጭስ መታየቱ (ዘፀ. 19፡18)፥ በምድረ በዳ ቀን ደመና፥ ሌሊት ደግሞ የእሳት አምድ ከእስራኤላውያን ጋር መጓዙ (ዘኍ. 9፡15-16) ይገኙበታል። ሦስተኛው፥ በታረዱት እንስሳት መካከል ያለፈው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ ነው። ከዚህ እንደምንረዳው፥ ቃል ኪዳን ተደርጓል! ቃል ኪዳኑን ያረጋገጠው ወይም ያጸናው ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ከአብራም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን እንደሚፈጽም ቃል የገባው በሕይወቱ ነው።

ይሁንና፥ እግዚአብሔር ያደርግ ዘንድ የተስማማው፥ "ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቻለሁ" (ዘፍጥ. 15፡18) በማለት ነበር። አብርሃም ልጆች እንደሚኖሩት ብቻ ሳይሆን፥ ልጆቹ ወይም ትውልዶቹ ምድሪቱን የሚወርሷት መሆኑንም ነበር እግዚአብሔር በመሃላ ያረጋገጠለት። እውነተኞቹ የአብራም ልጆች፥ እውነተኛይቱን የእስራኤል ምድር የሚወርሱ መሆኑን ነበር እግዚአብሔር በሕይወቱ ዋስትና ያረጋገጠላቸው። ምን ያህል ታላቅ ነው ይህ ቃል ኪዳን? መልሱ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለተጠቀሱት ሌሎች ቁም ነገሮች መሠረት ነው የሚል ይሆናል። ነቢዩ ሚኪያስ የእስራኤል ሕዝብ በመጨረሻው ዘመን በመንፈስና በአካል እንደገና የሚታደስ መሆኑን ለማረጋገጥ፥ ይህን ጥቅስ ከ1300 ዓመታት በኋላ ተጠቅሞበታል። ይህ የእስራኤል ሕዝብ የሚሰባሰበው፥ ገና ወደፊት መሆኑን ነቢዩ ትንቢተ ሚክያስ ምዕራፍ 7 ውስጥ ገልጧል። "ቅጥርሽ በሚሠራበት በዚያ ቀን ድንበርሽ ትሰፋለች" (ሚክ. 7፡11)። ግንቡ እንደገና ሽቅብ ያድጋል፥ ድንበሩም ይሰፋል። የእስራኤል ከተሞች

መታደስ ግን በመንፈሳዊ መታደስ የሚታጀብ ይሆናል። “ተመልሶ ይምረናል፤ ከፋታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል” (ሚክ. 7፡19)። እግዚአብሔር እስራኤልን በመንፈስም ሆነ በአካል እንደገና የሚያድሳት ስለመሆኑ “ከቀድሞ ዘመን ጀምረህ ለአባቶቻችን የማልህላቸውን እውነት፥ ለያዕቆብ ምሕረትንም ለአብርሃም ታደርጋለህ” (ሚክ. 7፡20) በማለት ለአብርሃም ከገባለት ቃል እርግጠኛ ለመሆን ይቻላል። ይህን ተስፋ የሰጠ እግዚአብሔር ስለሆነ ሚክያስ ይታመንበት ነበር።

ከ800 ዓመታት በኋላ ደግሞ፥ የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ይህን እግዚአብሔር ለአብርሃም የማለለትን መሃላ አረጋግጧል።

> “እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ ‘በእውነት እየባረክሁ እባርክሃለሁ፥ እያበዛሁም አበዛሃለሁ’ ብሎ፥ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ፥ በራሱ ማለ”. . .ሰዎች ከነርሱ በሚልቅ ሰው ይምላሉ፥ መሃላውም የተባለውን ነገር ያረጋግጥና አወዛጋቢው ነገር ሁሉ ያበቃል። እግዚአብሔር ተስፋ የተደረገውን ነገር ለሚወርሱት ግልጥ ሊያደርግላቸው ስለፈለገ፥ የማይቀየር ዓላማውን በመሃላ አጸናው” (ዕብ. 6፡13-17)።

እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ የገባውን ቃል ሊፈጽም ዐቅዷል።

## በረከትና መርገሞች

እግዚአብሔር የእስራኤልን ምድር ለአብርሃምና ለዘሩ ለመስጠት ቃል የገባ ከሆነ፥ ለምንድነው ሕዝቡ በምድሩ በመኖር ፈንታ፥ ብዙውን ጊዜ ሌላ ስፍራ የሚያሳልፍ የሚመስለው? መልሱ በሙሴ ጊዜ በእግዚአብሔርና በእስራኤል ሕዝብ መካከል በተደረገውና ከአብርሃም ጋር ከተደረገው ስምምነት በተለየ ስምምነት ውስጥ ይገኛል። አብርሃምና ሌሎቹ አባቶች የእስራኤል ሕዝብ ዘር የወጣባቸው ከሆኑ፥ ግብፅ ደግሞ ያ ሕዝብ እስከ ልደቱ ድረስ ያደገባት ምድር ናት። ሰባ ሆነው ግብፅ የገቡት ሰዎች በ400 ዓመታት ውስጥ በሙሴ መሪነት ከግብፅ የወጡ ታላቅ ሕዝብ ሆኑ።

የዚህ ከተለያዩ ጎሣዎች የተሰባሰበና ውሕደት ያልነበረው ሕዝብ ቁጥር፥ ሁለት ሚሊዮን ተኩል ቢሆንም፥ በመንግሥት የሚመራ አልነበረም። ለዚህ አዲስ ሕዝብ እግዚአብሔር ሲና ተራራ ላይ ዘጸአት፥ ዘሌዋውያንና ከፊል ዘኍልቁ መጻሕፍት ውስጥ የተጻፉትን ሕግጋትና መመሪያዎች ሰጠው። ከአርባ ዓመታት በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለተቃረበው አዲስ ትውልድ በሕግጋቱ ላይ አንዳንድ ተጨማሪ ትእዛዛትን

በማከል፥ በመቀየር ላይ ስላሉ ነገሮች ዳግመኛ ነገረው። ይህ "በድጋሚ የወጣ" ሕግ የኦሪት ዘዳግም መጽሐፍ ነው።

ሕግጋቱን በሰጠባቸው በሁለቱም ጊዜያት፥ የእግዚአብሔር አደራረግ እንደመልካም ወላጅ ነበር። ከሕዝቡ የሚጠበቀው የጽድቅ ባሕርይ ምን መምሰል እንዳለበት ከገለጠ በኋላ፥ ተከታታይ በረከቶችን ወይም በመታዘዝ የሚገኙ ስጦታዎችን አስገነዘባቸው። ባለመታዘዝ ምክንያት የሚመጡ እርግማኖችንና ቅጣቶችንም ነግሯቸዋል። እግዚአብሔር መጀመሪያ ሕጉን በሰጠ ጊዜ፥ ዘሌዋውያን መጽሐፍ ምዕራፍ 26 ውስጥ መርገምና በረከቱን ገልጧል። ለሁለተኛ ጊዜ ሕጉን ሲሰጥ ደግሞ፥ ዘዳግም 28 ውስጥ የተጠቀሱትን መርገምና በረከቶች አስገንዝቧል።

በሁለቱም ምዕራፎች እንደተመለከተው፥ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት ተገቢ ያልሆነ ባሕርያቸውን ባይለውጡ፥ ቅጣቱ ከባድ እንደሚሆን ነው የተነገራቸው። የመጨረሻው ቅጣት፥ ባለመታዘዛቸው የተነሣ በእስራኤላውያን ላይ የሚመጣ ነው። ያም ከሚገቡባት ምድር ለጊዜው መባረር ነበር። "እናንተንም ከአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ፥ ሰይፍንም አስመዝዝባችኋለሁ፤ ምድራችሁም የተፈታች ትሆናለች፥ ከተሞቻችሁም ባድማ ይሆናሉ" (ዘሌ. 26፡33)። "...ትወርሱአትም ዘንድ ከም ትገቡባት ምድር ትነቀላላችሁ። እግዚአብሔርም ከምድር ዳር እስከዳርቻዋ ድረስ ወዳሉ አሕዛብ ሁሉ ይበትንሃል" (ዘዳግ. 28፡63-64)።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ምንም እንኳን "የመጨረሻውን ቅጣት" ቢቀጣቸው፥ እስራኤልን ሙሉ በሙሉ አልተዋቸውም። ዘሌዋውያን 26 ውስጥ እንደተገለጠውም፥ ሕዝቡ ከኃጢአቱ እስኪመለስ ድረስ እግዚአብሔር የሚጠብቀው መሆኑን በቅድሚያ ተናግሯል። እንዲህ ይላል፥ "ከያዕቆብ፥ ከይስሐቅና ከአብርሃም ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን አስባለሁ፤ ምድሪቱንም ለሕዝቤ ለመስጠት የሰጠሁትን የተስፋ ቃል አድሳለሁ። ... ይሁን እንጂ፥ በጠላቶቻቸው አገር ሳሉ እንኳ እስከመጨረሻው አልተዋቸውም ወይም አልደመሰሳቸውም፤ ይህማ ቢሆን ኖሮ ከእነሱ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን እስከመጨረሻ ባልጠበቅሁም ነበር፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው ነኝ" (ዘሌ. 26፡42፥44 የ1980 እትም)። ከአርባ ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ይህንኑ እንደገና አስታወቀ። እስራኤላውያን ተማርከው ባሉበት ሆነው እንኳን የእግዚአብሔርን ፊት ቢሹ፥ "አምላክህ እግዚአብሔር ምርኮህን ይመልሳል፥ ይራራልህማል፤ አምላክህም እግዚአብሔር አንተን ከበተነበት ከአሕዛብ ሁሉ መካከል መልሶ ይሰበስብሃል" (ዘዳ. 30፡3) በማለት ቃል ገብቶላቸዋል።

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን ያረጀ ይመስል ይሆናል፤ ነገር ግን አሁንም አልተሻረም። አንድ የጥንት ንጉሥ በለዓም የተባለ ባለ ራእይ ጠርቶ፥ ገና ያልጠነከረውን የእስራኤል ሕዝብ እንዲረግም አዘዘው። ንጉሡም ቋጥኛማ ወደሆነው ተራራ ወጥቶ፥ የእስራኤል ሕዝብ ድንኳን የተተከለበትን ሰፍራ ቁልቁል ሲያይ፥ በለዓም በዚያ ሕዝብ ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያወርድበት ለመሆኑ እርግጠኛ ሆነ። የበለዓም መልስ ግን ንጉሡን አስደነገጠው። "ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም። ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን? እነሆ ለመባረክ ትእዛዝን ተቀብያለሁ፤ እርሱ ባርኮአል፥ እመልሰውም ዘንድ አልችልም" (ዘኁል. 23፡19-20) የሚል ነበር መልሱ። እግዚአብሔር የእስራኤልን ምድር ለአብርሃምና ለዘሩ እንደሚሰጥ ተስፋ ሰጥቷል። እርሱ በፍጹም ቃሉን አያጥፍም። ይሁን እንጂ፥ እነዚህ ተስፋዎች ተፈጽመዋል ወይስ እስራኤል ገና ወደፊት የምትጠብቀው ተስፋ አለ?

> ምዕራፍ ሁለት <

# ተስፋዎች

እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ታላላቅ ተስፋዎች በአብርሃም ዕድሜ አልተፈጸሙም። እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘር እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደሚያበዛ ቃል ገብቶ ነበር። አብርሃም ያየው ግን ከሚስቱ ከሣራ የአንድን "ኮከብ" የይስሐቅን መወለድ ነው። የከነዓንን ምድር እንደሚያወርሰውም ቃል ገብቶላታል። ያገኘው ግን እርሱና ሚስቱ የተቀበሩበትን ምድር ብቻ ነው። የዕብራውያን መጽሐፍ ደራሲ፥ የአብርሃምንና የሣራን ታላቅ እምነት ሲያደንቅ ቀጥሎ ያለውን እውነት ያስገነዝባል። "እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፥ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት፥ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ" (ዕብ. 11፡13)።

የአብርሃም ዘር ግን ወደ ሕዝብነትና የእስራኤልን ምድር ለመውረስ ወደሚችልበት ደረጃ ማደጉ አልቀረም። በዳዊትና በሰሎሞን አገዛዝ ዘመን እስራኤላውያን እግዚአብሔር በተስፋ የሰጣቸውን ምድር እስከመውረስ ደርሰው ነበር (1ኛ ነገ. 4፡20-21)። ይህ ጉዳይ አንድ ጥያቄ ያስነሣል። እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን ዘላለማዊ ነው ወይስ የሚቋረጥ? በሌላ አባባል፥ እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ሕዝብነት ካሳደገና ምድሪቱን ካወረሳቸው በኋላ፥ በርሱ በኩል ያለውን ቃል ኪዳን እንዳበቃ ቆጥሮታል ወይስ ኪዳኑ ይቀጥላል?

ልዩነቱን በምሳሌ ላመልከት። ዕድሜዋ የገፋና ባል አልባ የነበረች አንዲት ሴት የመጀመሪያ ልጇን ልትጠይቀው ሄደች። ልጇ ግዙፍ የግል ድርጅት ያለው ባለጠጋ ነበር። በዚህ ሰው ባለጠጋ መሆን እናቱ ደስ ተሰኝታለች። ታናሽ ወንድሙ ግን እንደርሱ ያልታደለና ቀላል አካለ ስንኩልነት ያጠቃው ከመሆኑም በላይ፥ በዕድሜ ከገፋች እናቱ ጋር ነው የሚኖረው። በወደፊት ዕድሉ ጉዳይ እናቱ ትጨነቃለች። "እኔ ብሞት ማን ይንከባከበዋል?" ትል ነበር። ይህንኑ ጭንቀቷን ለትልቁ ልጇ ነገረችው። "አትጨነቂ እማዬ፥ ሥራም ሆነ መኖሪያ ቤት እኔ እሰጠዋለሁ" አላት ልጇ። እናቲቱም "አሁን ልትረዳው እንደምትወድ አውቃለሁ፤ ነገር ግን እኔ ከሞትኩ በኋላ እየጎበኘህ የሚያስፈልገውን ነገር ታደርግለታለህን?" ብላ ጠየቀችው። ይህ ልጇ የገባው የበጎ ሥራ ግዴታ የአንድ ወይስ የረጅም ጊዜ ነበር? በዚህ ዓይነቱ ግዴታ ውስጥ ለሚገባ ሁሉ የጉዳዩ ግልጥ መሆን እጅግ አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ተስፋ ምድሩ ካስገባና፥ የራሳቸው እንዲሆን ካደረገ በኋላ፥ ለአብርሃም የገባለትን ቃል "አበቃ"

ብሏል? ወይስ አብርሃማዊው ቃል ኪዳን እግዚአብሔርን ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በረጅም ጊዜ ግንኙነት ያቆራኘ ነው? እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባው ቃል ኪዳን፥ ሕዝቡ የተስፋይቱን ምድር በወረሰ ጊዜ እንዳላበቃ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

አንደኛ፥ አብርሃም የተጠራበትና ምድሪቱን ያወረሰበት ዓላማ እስከ ዳዊትና ሰሎሞን ዘመን ድረስ ብቻ አልነበረም። እግዚአብሔር አብርሃምንና ዘሩን የመረጠበት የላቀ ዓላማ፥ አሕዛብን ሁሉ በእነሱ መባረክ ነበር፥ "የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ" (ዘፍ. 12፥3)። እግዚአብሔር ዓለምን ለመባረክ የገባው ቃል ኪዳን፥ በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን አልተፈጸመም።

ሁለተኛ ከዳዊትና ከሰሎሞን ጊዜ በኋላ የዘገቡ ሌሎች የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች፥ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እስከነርሱ ዘመን ድረስም የተጠበቀ ወይም ዋጋ ያለው እንደነበር አምነዋል። ነቢዩ ሚክያስ ትንቢቱን የጻፈው፥ ከዳዊትና ከሰሎሞን ጊዜ ሦስት ምዕተ ዓመታት ያህል ዘግይቶ ቢሆንም፥ የእስራኤልን ወደ ፊት በምድራዊም ሆነ መንፈሳዊ ሁኔታ እንደገና መታደስ መነሻ ያደረገው፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለትን ቃል ኪዳን ነው። "ከቀድሞ ዘመን ጀምረህ ለአባቶቻችን የማልህላቸውን" (ሚክ. 7፥20)። መዝሙር 105ን የጻፈው ያልታወቀ ደራሲም፥ የእግዚአብሔር ተስፋ በአንድ ትውልድ ያላበቃ መሆኑን ተረድቷል።

> "ቃል ኪዳኑን ለዘላለም፥ እስከሺህ ትውልድ ያዘዘውን ቃሉን አሰበ፥ ለአብርሃም ያደረገውን፥ ለይስሐቅም የማለውን ለያዕቆብ ሥርዓት እንዲሆን ለእስራኤልም የዘላለም ኪዳን እንዲሆን አጸና፤ እንዲህም አለ፡- 'ለአንተ የከነዓንን ምድር የርስታችሁን ገመድ እሰጣለሁ'" (መዝ. 105፥8-11)።

መዝሙረኛው ከዳዊትና ከሰሎሞን በኋላ እንኳን ጽኑ ስለሆነው ተስፋ እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

ሦስተኛ፥ አዲስ ኪዳን እንኳን እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን የጸና መሆኑን ይገነዘባል። ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት እናቱ ማርያም ሊወለድ በነበረው ሕፃን በኩል በሚያከናውነው ነገር እንኳን እግዚአብሔር ለእስራኤል ታማኝ መሆኑን ተገንዝባ እንዲህ ብላለች፥ "ለአባቶቻችን እንደተናገረ ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱ ትዝ እያለው እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶአል" (ሉቃስ 1፥54-55)። እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ተስፋ፥ በዳዊትና በሰሎሞን ጊዜ ሕዝቡ የተስፋይቱን ምድር በወረሰ ጊዜ አላበቃም።

## ይህ የአንተ ምድር ነው

እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ የገባለት ምድር ትክክለኛ ድንበሮቹ የትኞቹ ናቸው? ዘፍጥረት 15፡18 ውስጥ ጠቅላላ ድንበሮቿን እግዚአብሔር ገልጿል። "ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ትልቁ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቼአለሁ"። ከአባይ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ! ያ እጅግ ሰፊ ምድር ነው። የግብፅን፥ የእስራኤልን፥ የዮርዳኖስን፥ የኢራቅን፥ የሶሪያንና የሊባኖስን ምድር ያጠቃልላል። ይህ ሁሉ የእስራኤል ነውን? በሦስት ምክንያቶች መልሱ አይደለም ይሆናል።

አንደኛው፥ የእግዚአብሔር ድንበሮች ውሱን ሳይሆኑ፥ አጠቃላይ ናቸው። በሁለቱ ታላላቅ ወንዞች መካከል የሚገኘውንና በጊዜው የሰለጠነ ይባል የነበረውን ምድር ነው ለአብርሃም እንደሚሰጠው እግዚአብሔር የተናገረው። የግብፅ ሥልጣኔ በአባይ ወንዝ ዳርና ዳር የበለጠገ ነበር። የሜሶፓታሚያ ሥልጣኔ ደግሞ በጤግሮስና ኤፍራጥስ ወንዞች ዳርቻ አለፍ አለፍ ብሎ የነበረ ነው።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም በተስፋ የተሰጠውን ምድር፥ እዚያ ከሚኖሩ ሰዎች አኳያም ይገልጣል። ለእስራኤል ተስፋ የተገባላት ምድር "ቄኔያውያን፥ ቄኔዛውያንንም፥ ቀድሞናውያንንም፥ ኬጢያውያንንም፥ ፌርዛውያንንም፥ ራፋይምንም፥ አሞራውያንንም፥ ከነዓናውያንንም፥ ጌርጌሳውያንንም፥ ኢያቡሳውያንንም" (ዘፍጥ. 15፡19-21)። እያለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚዘረዝራቸው ሕዝቦች የሚኖሩበትን አገር ሁሉ ይጨምራል። ከታሪክ እንደተረዳነው፥ ከነዚህ ሕዝቦች ብዙዎቹ የእስራኤል በሆነው ምድር ውስጥ ይኖሩ ነበር (ዘኁል. 13፡29፤ ኢያሱ 11፡1-3)።

ሦስተኛ፥ እግዚአብሔር ለእስራኤል ተስፋ የገባላትን ምድር ትክክለኛ ድንበር፥ እንዲሁም የየአቅጣጫውን ስፋት እንዲህ በማለት በኋላ አስታውቋል "ወደከነዓን ምድር በገባችሁ ጊዜ፥ ርስት ትሆናችሁ ዘንድ በዕጣ የምትደርሳችሁ ምድር፥ በዳርቻዋ ያለች የከነዓን ምድር ይህች ናት" (ዘኁል. 34፡2)። ከዚህ በኋላ የእስራኤል ድንበር በስተደቡብ ከጨው ባሕር (አሁን ሙት ባሕር የሚባለው)፥ ከግብፁ ዋዲ (ምናልባት ሲና ባሕረ-ሰላጤ ውስጥ የሚገኘው ዋዲ አል አሪሽ የተባለው ስፍራ ይሆናል- ዘኁል. 34፡3-5)። ምዕራባዊው ድንበር፥ የሜድትራኒያን ባሕር (ዘኁል. 34፡6 ላይ ታላቁ ባሕር የተባለው) ነው። እግዚአብሔር ያመለከተው መሥመር፥ ወደ ሰሜን፥ ዛሬ ሊባኖስና ሶርያ የተባሉትን አገሮች ያጠቃልላል (ዘኁል. 34፡7-9)። በስተምሥራቅ ያለው ድንበር እስከ ገሊላ ባሕር (የኪኔሬት ባሕር የተባለው) ይዘልቃል። ከዚያ ወደ ደቡብ

እስከዮርዳኖስ ወንዝና ሙት ባሕር ይዘልቃል (ዘኁል. 34፡10-12)። ይህ ነው ለእስራኤል ተስፋ የተገባላት ትክክለኛ ምድር።

ብዙ ጊዜ ልብ ሳይባል ይታለፋል እንጂ፥ ነቢዩ ሕዝቅኤል ለእስራኤል ተስፋ የተገባላትን ምድር በተመለከተ የዘገበው አስደናቂ ምንባብ አለ። በመጽሐፉ መጀመሪያ፥ የይሁዳ ሕዝብ በኃጢአት ሳቢያ የሚወድቅ መሆኑን አስጠንቅቋል። ይሁን እንጂ፥ የኢየሩሳሌም መውደቅ ዜና በምርኮ ለነበሩ ሕዝቦች በደረሳቸው ጊዜ፥ የሕዝቅኤል መልእክት ተለወጠ። ሕዝቅኤል በመጽሐፉ ከምዕራፍ 33 እስከ 48 ባለው ክፍል የተስፋ መልእክት ነበር የሰበከው። በመልእክቱም እስራኤልና ይሁዳ ወደምድራቸው በመመለስ፥ በተስፋው በረከት የሚኖሩ መሆኑን ገልጧል።

ሕዝቅኤል የመጽሐፉን የመጨረሻ ምዕራፎች መልእክት፥ እስራኤል መጀመሪያ ከግብፅ ሲወጡ ከነበረው ሁኔታ ጋር ያመሳስለዋል። በመልእክቱ መሠረት፥ እግዚአብሔር ልክ በሙሴ ዘመን እንዳደረገው የመረጠውን ሕዝብ ሰብስቦ ወደ ተስፋይቱ ምድር ያመጣ ነበር። በዚህ ጊዜ ግን፥ ማንኛውም ነገር ከመጀመሪያው ፍልሰት የተሻለ እንደሚሆን እግዚአብሔር ቃል ገብቷል። ሕዝቅኤል፥ ምዕራፍ 39ን ያጠቃለለው፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመመለስ ማቀዱን በመግለጥ ነበር "አሁን የያዕቆብን ምርኮ እመልሳለሁ፥ ለእስራኤልም ቤት ሁሉ እራራለሁ" (ሕዝ. 39፡25)።

በመጀመሪያው ፍልሰት ወቅት፥ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ነጻ ካወጣቸውና ወደ ሲና ከመራቸው በኋላ፥ በሕዝቡ መካከል ይኖር ዘንድ የማደሪያ ድንኳን እንዲሠሩለት ዕቅድ በመስጠት ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት መሠረተ (ዘፀ. 20-40)። ሕዝቡ በታዘዘው መሠረት ሠርቶ ሲያበቃ፥ "የእግዚአብሔር ክብር ማደሪያውን ሞልቶት ነበር" (ሕዝ. 40፡35)። ሕዝቅኤልም ይህን አሠራር በመከተል ተናግሯል። እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚሰበስብ ከተናገረ በኋላ፥ አዲሱ መቅደስ እንደሚሠራ ገልጧል። በዚህም ጌታ በሕዝቡ መካከል እንደሚኖር ተናገረ (ሕዝ. 40፡43)። የሰጠው ፕላን ልክ የማደሪያው ድንኳንን በተመለከተ የሰጠውን ዝርዝር መመሪያ ይመስላል። በመቅደሱ አሠራር ላይ ካተኮረ በኋላ፥ መልእክቱን የጨረሰው፥ "...እነሆም የእግዚአብሔር ክብር መቅደሱን ሞልቶት ነበር" በማለት ነው (ሕዝ. 43፡5)።

እግዚአብሔር የማደሪያውን ድንኳን ዕቅድ ለሙሴ ከነገረው በኋላ፥ ሕዝቡ እንዴት ሊያመልከው እንደሚገባ ገለጠለት። የዘሌዋውያንና ዘኁልቁ መጻሕፍት እግዚአብሔር ስለ አምልኮ የሰጠውን "የእንቅስቃሴ መመሪያ" ይዘዋል። ሕዝቅኤል የተከተለው ያን መመሪያ ነው። አዲስ

ስለሚሠራው ቤተ መቅደስ አስተናነጽ ዕቅድ ከሰጠ በኋላ፥ ቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚደረገውን አምልኮ በተመለከተ የእግዚአብሔርን መመሪያ ይገልጣል (ሕዝ. 43፡13-44፡31)።

የዘኍልቁ መጽሐፍ ያበቃው፥ የእስራኤል ሕዝብ መጀመሪያ ስለሚገባበት የተስፋ ምድር ድንበሮች እግዚአብሔር የሰጠውን መግለጫ በማቅረብ ነው። ሕዝቅኤልም ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚደረገውን አዲስ መሰባሰብ አስመልክቶ እግዚአብሔር የገለጣቸውን ድንበሮች በተመሳሳይ ሁኔታ ያመለክታል። የሚያስደንቀው ነገር፥ ድንበሮቹ ተመሳሳይ መሆናቸው ነው። እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ የገባለትና ዘኍልቁ 34 ውስጥ ለሙሴ በግልጥ ያስታወቀው ምድር፥ በባቢሎን ከፈራረሰች በኋላም ቢሆን እንኳን ለእስራኤል በተስፋ የተጠበቀች ናት። በሌላ አባባል፥ በግልጥ የተነገሩት ድንበሮች አልተለወጡም።

ኢያሱ መጀመሪያ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደገባ፥ ምድሪቱን ለእስራኤል ነገዶች ከፋፍሎ ሰጣቸው (ኢያሱ 14-21)። ሕዝቅኤል መጽሐፉን የሚደመድመው፥ ምድሪቱ ለእስራኤል ነገዶች ለሁለተኛ ጊዜ የተከፋፈለችበትን ሁኔታ በመግለጥ ነው (ሕዝቅኤል 48)። ድንበሮቹ ያው ናቸው፤ ለነገዶቹ የተከፋፈሉት ቦታዎች ግን ይለዋወጣል።

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን አድርጓል። በዚሁ መሠረት በይስሐቅ በኩል የአብርሃም ትውልድ የተስፋውን በረከት ለሌላው ዓለም ያደርስ ዘንድ የተመረጠ ሕዝብ መሆን ነበረበት። እግዚአብሔር ልዩ በሆነ ስፍራ ላይ የሚከናወን ቋሚ ስመርስት (ሰነድ) ለአብርሃም ትውልዶች ሰጥቷቸዋል። ክልሉ በአባይና በኤፍራጥስ ወንዝ መካከል የሚገኝ ምድር መሆኑ በአጠቃላይ የተገለጠ ሲሆን፥ የታወቁ ሕዝቦችን የያዘና የታወቀ ድንበር ያለው ምድር ነበር። በዚህ ዘመን ያለችው እስራኤል፥ እግዚአብሔር ከሰጣት የተስፋ ምድር በአብዛኛው ላይ ናት እንጂ፥ ሁሉንም አልያዘችም። በሕዝቅኤል ትንቢት መሠረት ግን፥ አንድ ቀን ሕዝቡ ርስቱን ሁሉ የራሱ ያደርጋል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ታዲያ መቼ ነው?

> ምዕራፍ ሦስት <

# አዲሱ ፍልሰት

ዝቪ የተባለ ሰው ወላጆች ከጀርመን የሸሹት፥ ከአገር የመውጫው ፈቃድ በር ከመዘጋቱ በፊት ነበር። በዘመናዊው ፍልሰት መሠረት በእግር፥ በመኪናና በጀልባ ተጉዘው በ1930ዎቹ መገባደጃ ላይ ፍልስጥኤም ምድር ደረሱ። የገቡበት ምድር ምንም የሌለበት ጠፍ ነበር። በየጠረፉ ከነበረው ረግረግ የተፈጠረው ወባ እና የንጽሕና ጉድለት በስፍራው ያለውን ኑሮ አስከፊ አድርጎታል። በአካባቢው ካሉት ጠላቶችም ለሕይወት የሚያሠጋ አደጋ ነበር። የዝቪ ወላጆች ቴል አቪቭ በተባለው ስፍራ በመሰባሰብ ላይ ከነበረው ሕዝብ ጋር በመቀላቀል፥ በጥንት ትውልዳቸው ምድር ላይ አዲስ ሕይወት የመመሥረቱ ዕድል ተሳታፊ ሆኑ።

ዝቪ ወላጆች ምንም እንኳ አውሮፓ ውስጥ ቤተሰቦቻቸውን በማጥፋት ላይ ከነበረው እልቂት* ቢያመልጡ፥ በገቡባት ምድር ለመኖር ግን መታገል ነበረባቸው። በሌላ በኩል ደግሞ፥ የፍልስጥኤምን ምድር የያዙት የእንግሊዝ ወታደሮች ተከላካይም፥ አሳዳጆችም ሆነውባቸዋል። አይሁዶች ከእንግሊዞች ጋር በመሆን በሰሜን አፍሪካ በኩል ከጀርመኖች ይመጣ የነበረውን አደጋ ተከላክለው ነበር። ነገር ግን፥ አይሁዶች ከዓረብ ጎረቤቶቻቸው ጥቃት በተሰነዘረባቸው ጊዜ፥ እነዚያ የእንግሊዝ ወታደሮች ሊረዷቸው አልፈለጉም። በነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ሳቢያ፥ ነጻ የእስራኤል መንግሥት የመመሥረቱ አሳብ የደበዘዘ ሆነ። ዝቪ ቤተሰብ ውስጥ ግን የሚያድግ የነጻነት ተስፋ ነበር።

ጦርነቱ ሲያበቃ፥ ከሂትለር የሞት ፍርድ እሥር-ቤት የተረፉ በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዶች በሕዝባቸው ላይ የደረሰው ጥፋት እጅግ ብዙ መሆኑን ተረዱ። በመሆኑም የፍልስጥኤምን ምድር እንደ መሸሸጊያና ተገን ቆጠሩትና በሺሆች ሆነው አደገኛውን ጉዞ ወደዚያው ተያያዙት። እስፍራው ሲደርሱ ግን፥ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገቡ በእንግሊዝ ወታደሮች ታገዱ። ከአውሮፓ እሥር-ቤቶች ሲወጡ እንደገና ቆጵሮስ ደሴት ላይ በሚገኘው የእንግሊዞች እሥር-ቤት ውስጥ ታጎሩ።

ዝቪ የተወለደው በዚህ ነውጥና ግራ መጋባት በበዛበት ጊዜ ነበር። የእንግሊዝ ወታደሮች ለቁጥጥር በሚዘዋወሩበት፥ በሌላ በኩል ደግሞ በምስጢር የሚሠሩ አይሁዳውያን በአካባቢው የነበሩትን እንግሊዞች

---

* በግምት ስድስት ሚሊዮን የሚሆኑ አውሮፓውያን አይሁዶች በዚህ ጊዜ ተገድለዋል።

ከሥልጣን ለማስወገድ፥ እንዲሁም አይሁዳውያንንና የጦር መሣሪያን ወደ እስራኤል ለማስገባት በሚጥሩበት ከተማ ውስጥ አደገ። በጊዜው ለመዋጋት ገና ልጅ ቢሆንም፥ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1948 አዲሱ የእስራኤል መንግሥት ሲመሠረት ተመልክቷል። እስራኤልን ከተዋጊ የዓረብ ወታደሮች ለመከላከል የሚደረገውን መራራ ትግልም ተለማምዶታል። ዛሬ ከቴል አቪቭ ወደ ኢየሩሳሌም በሚወስደው ጎዳና የወዳደቁትን የእስራኤል ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች በኩራት ይመለከታል። እነዚያ የተሽከርካሪ ስብርባሪዎች፥ ለእርሱ ዘመናዊውን የእስራኤል መንግሥት ለመመሥረት የተከፈለውን መሥዋዕትና የተፈጸመውን ጀግንነት የሚያመለክቱ ናቸው።

እስራኤል ደካማ ከነበረችበትና ለሕልውናዋ ትታገልባቸው ከነበሩ የቀደሙ ዓመታት ዛሬ በጣም ትለያለች። እንደ ዘመናዊ ወታደራዊ ኃይልነቷ ዘመናዊ ትጥቅና የጦር መሣሪያ ያላት መሆኗንም በልበ ሙሉነት ትገልጣለች። እድገትና ብልጥግናዋ ተአምር ይመስላል። የአገሪቱ መወለድና እድገት ግን የአይሁዳውያን ብርታትና ቁርጠኝነት ውጤት ነው፥ ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ክንዋኔ ውጤት ጭምር?

## የደረቁ አጥንቶች የሞሉበት ሸለቆ

ከሁለት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በፊት አንድ ሌላ እስራኤላዊ ወጣት ከወገኖቹ ጋር ቴል አቪቭ ውስጥ ኖሯል። ይህች ቴል አቪቭ የተባለች ስፍራ ግን ያን ጊዜ እስራኤል ውስጥ ሳይሆን፥ ባቢሎን ውስጥ ነበረች (ሕዝ. 3፥15)። የዚያ ወጣት ስም ሕዝቅኤል የሚባል ሲሆን፥ በሀያ አምስት ዓመት ዕድሜው በምርኮ ወደ ባቢሎን ተወሰደ። ናቡከደናፆር ሕዝቅኤልንና ሌሎች 10,000 አይሁዳውያንን በምርኮ ወደ ባቢሎን የወሰዳቸው፥ በ605 ዓመተ ዓለም ነበር። ሕዝቅኤል ለአምስት ዓመት እሥር-ቤት ከቆየ በኋላ፥ ባቢሎን ውስጥ ለነበሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በነቢይነት ያገለግል ዘንድ እግዚአብሔር ጠራው። በምርኮኞች መካከል የነበረው አገልግሎት ቀላል አልነበረም። ምክንያቱም፥ ከእግዚአብሔር ይሰጠው የነበረ መልእክት በቅርቡ ሊመጣ ስላለው ጥፋትና ፍርድ ነበር። ምርኮኞቹ ወደ ምድራቸው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ የሚፈቀድላቸውን ዕለት በናፍቆት በመጠበቅ ቀኑን ይቆጥራሉ። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ነው ወደ ምድራቸው እንደማይመለሱ ሕዝቅኤል የነገራቸው። እንደውም ኢየሩሳሌም እንደምትወድምና ቅሪቶቿም በምርኮ ወደ ባቢሎን እንደሚመጡ ገለጠላቸው።

ሕዝቅኤል ሰቆቃዊ ትንቢቱን መናገር በጀመረ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ልሳኑን ዘጋው (ሕዝ. 3፡26-27)። ከእግዚአብሔር መልእክት ካልተሰጠው በቀር ለመናገር የማይችል ዲዳ ሆነ። የርሱ ለመናገር አለመቻል ለእስራኤል ሕዝብ የሚያስደንቅ ምልክት ነበር። ይህ ሁኔታ ዘግየት ብሎ ሕዝቅኤል ላይ ሊደርስ ካለው ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር ደግሞ የሚያስደነግጥ ሆነ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ታህሣስ 15 ቀን 588 ዓመተ ዓለም፥ በኢየሩሳሌም ላይ የሚደረገው የመጨረሻ ወረራ ተጀመረ። በዚህ ወቅት እግዚአብሔር የሕዝቅኤልን ሚስት ወሰዳት (ሕዝ. 24፡1-2፥ 15-27)። የሴቲቱን ያለጊዜዋ መሞት እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል የገለጠለት፥ "የዓይንህን አምሮት" በማለት ነበር። ይህ ሁኔታ በምርኮ ያሉ ሁሉ የኢየሩሳሌምን መፍረስ በሚሰሙ ጊዜ ለሚደርስባቸው አስከፊ ሀዘን እንደ መጀመሪያ ሆነ።

ከሦስት ዓመት በኋላ፥ ቴል አቪቭ ውስጥ የነበሩ ምርኮኞች የሕዝቅኤልን ሚስት አሳዛኝ ምልክትነት በግል ተረዱ። ታህሣስ 8 ቀን 585 ዓመተ ዓለም፥ የመጀመሪያው የምርኮኞች ቡድን ከኢየሩሳሌም ቴል አቪቭ ገባ። ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ቅጥር የጣሱት፥ ሐምሌ 18 ቀን 586 ዓ.ዓ. ነበር (2ኛ ነገሥት 25፡2-4)። ነሐሴ 14 ቀን የመከላከያ ምሽጎች በሙሉ ተደመሰሱና የተደበቁ ሰዎች ሁሉ ከየሥርቻው ተማረኩ። የባቢሎን የጦር አዛዦች ደህና ወደነበረችው ኢየሩሳሌም ገብተው የማፈራረሱን ሂደት ቀስ በቀስ ተያያዙት። የባቢሎን ሠራዊት በዚሁ መሠረት የሚፈልገውን ከዘረፈ በኋላ፥ የከተማይቱን ሕንፃዎች በሙሉ አቃጠላቸው፤ ግንቦቿንና የመጠበቂያ ስፍራዎችን ሁሉ አፈራረሰ፥ ዋጋ ያለው ነገር ሁሉ እየተመረጠና እየተሰበሰበ ወደባቢሎን ተወሰደ።

የባቢሎን ወታደሮች ኢየሩሳሌምን በደመሰሱ ጊዜ በሕይወት የነበሩ አይሁዳውያንን ሁሉ ማረኩ። የምርኮኞቹን ሁኔታ ለማጣራትም ከኢየሩሳሌም ሰሜን ስድስት ማይሎች ያህል ርቃ ወደምትገኘውና ራማህ ወደተባለች ስፍራ ወሰዷቸው። በማጣራቱ ጊዜ፥ የዐመፁ መሪዎች መሆናቸው የተደረሰባቸው ሰዎች ወዲያው ተረሸኑ፥ ወይም ለመጨረሻ ፍርድ ወደ ናቡከደናፆር ተወሰዱ። የቀሩት ደግሞ ለባርነት የባቢሎንን ረዥም ጉዞ ተያያዙት። ባቢሎናውያን ነጻ ያደረጓቸው፥ ድሆች፥ ሽባዎችና በዕድሜ የገፉ ሰዎች ብቻ ነበሩ። እንዲህ ያሉት እፈራረሰችው ይሁዳ ውስጥ እንዲኖሩ ተፈቀደላቸው።

ወደባቢሎን ይደረግ የነበረው ጉዞ አስቸጋሪና ዝግ ያለ ነበር። የባቢሎን ወታደሮች ምርኮኞቹን በእግራቸው ሲያስኬዷቸው፥ የተማረኩ ዕቃዎችን ግን በጋሪዎች አጓጓዙ። በባቢሎን ሩቅ መንደሮች ውስጥ የነበሩ

አይሁዳውያን፥ አዲሶቹ ምርኮኞች ዜናውን እስካመጡላቸው ድረስ የኢየሩሳሌምን መደምሰስ አልሰሙም ነበር። በዚሁ መሠረት ታህሣስ 8 ቀን 585 ዓመተ ዓለም፥ የኢየሩሳሌም ቅጥር በፈረሰ በስድስት ወር ማለት ነው፥ ቴል አቪብ ውስጥ የነበሩት የሕዝቅኤል ወገኖች እስከፊ የሆነውን የሕዝቅኤል የቀድሞ ትንቢት እውነትነት አረጋገጡ፤ ኢየሩሳሌም ፈራረሰች።

እንዲህ ያለውን ኀዘን ለምርኮኞች ያመጣው ዕለት፥ በሕዝቅኤል ላይ ግን አዲስ ለውጥ አመጣ፥ "ያመለጠውም ሳይመጣ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ነበረች፥ በነጋውም ወደእኔ እስኪመጣ ድረስ አፌን ከፈተ፤ አፌም ተከፈተች ከዚያም በኋላ እኔ ዲዳ አልሆንሁም" (ሕዝ. 33፥22)። የሰባት ዓመት ተከታታይ የዝምታ ጊዜ አበቃ! ምርኮኞች ስለ ኢየሩሳሌም መደምሰስ ሲያዝኑ ሳለ፥ እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል አዲስ መልእክት አመጣለት። መልእክቶቹ በኢየሩሳሌም ወደፊት እንደገና መሠራት ላይ ያተኮሩ ነበሩ።

ሕዝቅኤል ለእስራኤል ያመጣው አዲስ መልእክት፥ የቀድሞ ትንቢቱንና ያስከተለውን ውጤት ያሰላስሉና ያዝኑ በነበሩት ዘንድ እንደ ቀድሞ መልእክቱ ለማመን የሚያዳግት ሆነባቸው። የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥትና የደቡቡ የይሁዳ መንግሥት በምርኮ ተወስደዋል። የኢየሩሳሌም ከተማም የፍርስራሽ ክምር ሆናለች። ሰሎሞን የሠራው ቤተ መቅደስ ፈራርሷል። አመጣጡ ከዳዊት ሥርወ መንግሥት የሆነው ንጉሥ በሰንሰለት ታስሮ ጭለማ ቤት ውስጥ ይማቅቃል። ማንኛውም ነገር ያበቃለት ይመስላል። ሕዝቅኤል ግን የምርኮኛውን ሕዝብ እንደገና ወደ ምድሩ መሰብሰብ እንዲህ እያለ ይተነብይ ጀመር፥ "ከአሕዛብ መካከል አወጣችኋለሁ፥ ከየአገሩም ሁሉ እሰበስባችኋለሁ፤ ወደ ገዛ ምድራችሁም አመጣችኋለሁ...። ለአባቶቻችሁም በሰጠኋት ምድር ትኖራላችሁ፤ ሕዝብም ትሆኑኛላችሁ፥ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ" (ሕዝ. 36፥24፥28)።

ይሁንና መቼ ነው ይህ መሰባሰብ የሚከናወነው? ይህ ክንውን እውን መሆኑን እስራኤል እንዴት ታውቃለች? ሕዝቅኤል በቅርብ በተናገረው ቃሉ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሆኑ ብዙ ጥቆማዎችን ይሰጣል። ይህ ቃል ወይም ጥቅስ የሚፈጸመው፥ እስራኤላውያን በአካልም ሆነ በመንፈስ ወደ ምድሪቱ በሚመለሱ ጊዜ መሆኑን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡-

> "ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ፥ እናንተም ትጠራላችሁ፥ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ። አዲስም

ልብ እሰጣችኋለሁ፥ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከውስጣችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ፥ በትእዛዜም እስኬዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ፥ ታደርጉትማላችሁ'' (ሕዝ. 36፡25-27)።

ሕዝቅኤል፥ አድማጮቹ የእስራኤልን መንፈሳዊና አካላዊ መሰባሰብ እንዳይስቱ እንዲህ በማለት በድጋሚ ያስገነዝባቸዋል፥ ''ከኃጢአታችሁ ሁሉ ባነጻኋችሁበት ቀን በከተሞች ሰዎችን አኖራለሁ፥ ባድማዎችም ስፍራዎች ይሠራሉ። ባድማ የነበረች በመንገደኛም ሁሉ ዓይን ዘንድ ባድማ የነበረች ምድር ትታረሳለች'' (ሕዝ.36፡33-34)።

እንዴት ነው ይህ የሚሆነው? እስራኤል ይህን አስደናቂ ትንሣኤ የምታገኘው እንዴት ነው? ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ቅጥር በጣሱ ጊዜ የእስራኤል መንግሥት ጠፍቷል። ናቡከደነፆርም ሆነ የርሱ ትውልዶች፥ አይሁዳውያን ወደ ምድራቸው እንዲመለሱ አይፈቅዱላቸውም ነበር። እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ሕልውና ሊመልሳት ይችል ነበር?

ሕዝቅኤል የትንቢቱን እውነትነት ለማረጋገጥ ሁለት ምሳሌያዊ መግለጫዎችን አቅርቧል። በመጀመሪያው ራእይ፥ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን አጥንቶች በሞሉበት ሸለቆ መካከል አኖረው። እነዚያን አጽሞች እንዲመለከት ካደረገው በኋላ፥ ''የሰው ልጅ ሆይ እነዚህ አጽሞች በሕይወት ይኖራሉን?'' (ሕዝ. 37፡3) በማለት ከባድ ጥያቄ አቀረበለት። የሞተና የፈራረሰ ነገር እንደገና በሕይወት ሊኖር ይችላል? ሕዝቅኤል ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው መልስ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነትና፥ በሌላ በኩል ደግሞ ግራ መጋባቱን የሚያመለክት ነበር። ''እኔም ጌታ እግዚአብሔር ሆይ አንተ ታውቃለህ አልሁ'' (37፡3) ይላል። ከሰው ግንዛቤ አኳያ ሲታይ፥ የሞተ ነገር እንደገና በሕይወት ሊኖር አይችልም፥ ለእግዚአብሔር ግን የሚሳነው የለም።

ለአጥንቶቹ ትንቢት እንዲናገር እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን አዘዘው። እንደታዘዘው ባደረገ ጊዜ፥ አጥንቶቹ ይገጣጠሙ ጀመር። እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት ሁኔታ አጥንትና ሥጋ ተገጣጥመው አካል ሆኑ። ከዚያም ''ትንፋሽም ገባባቸው፥ ሕያዋንም ሆኑ'' (ሕዝ. 37፡10)። ''ትንፋሽ'' የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ''ነፋስ'' ወይም ''መንፈስ'' ተብሎ ሊተረጎም የሚችልና፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ስለመፍጠሩ በተገለጠ ጊዜ ያገለገለ ቃል ነው። ''እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለበት ሆነ'' (ዘፍጥ. 2፡7)።

ሕዝቅኤል የአዲስ ፍጥረት ሥዕል፥ ማለት ሞት ወደ ሕይወት ሲቀየር ይመለከታል። ምንድነው የዚህ ምሳሌ ቁም ነገር? ከሕዝቅኤል 37፡11 ጀምሮ እግዚአብሔር እንዲህ በማለት ፍቺውን ይገልጣል፥ "እነዚህ አጥንቶች የእስራኤል ቤት ሁሉ ናቸው"። እግዚአብሔር የሕዝቅኤል 36ን መልእክት ለመግለጥ አጥንቶች የሞሉበትን ሸለቆ እንደ ምሳሌ ሲጠቀምበት እናያለን። እስራኤላውያን እንደ ብሔር ሙታን መሆናቸው ተሰምቷቸዋል። ስለሆነም ነበር፥ "አጥንቶቻችን ደርቀዋል፥ ተስፋችን ጠፍቶአል ፈጽመንም ተቆርጠናል" ያሉት። እንደገና ስለመሰብሰባቸው ምንም ተስፋ አልታያቸውም።

ነገር ግን ልክ አጥንቶች ሲሰበሰቡና የእግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስ ሲገባባቸው፥ ሕዝቅኤል በተመለከተው አኳኋን የእስራኤል ሕዝብ ይሰበሰባል፥ የእግዚአብሔርን መንፈስም ይቀበላል። የአጥንቶቹ መገጣጠምና ሥጋ መልበስ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደምድሩ የመመለሱ ተምሳሌት ነው። እስራኤልን እንደ ብሔር ከመቃብር አውጥቶ ያቆማታል። "መቃብራችሁን እከፍታለሁ፥ ከመቃብራችሁም አወጣችኋለሁ፥ ወደ እስራኤል ምድር አገባችኋለሁ" (ሕዝ. 37፡12)። የሕይወት እስትንፋስ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን በአካልም ሆነ በመንፈስ ባደሳቸው ጊዜ፥ በውስጣቸው የሚያድር መንፈስ እንደሚሰጣቸው የገባላቸው ተስፋ ተምሳሌት ነው። ቃሉ እንዲህ ይላል፥ "መንፈሴን በውስጣችሁ አሳድራለሁ፥ እናንተም በሕይወት ትኖራላችሁ፥ በገዛ ምድራችሁም አኖራችኋለሁ" (ሕዝ. 37፡14)።

የሕዝቅኤል የመጀመሪያ ምልክት፥ እግዚአብሔር የማይቻልን ነገር በማድረግ፥ ሕዝቡን በአካልም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ወደ ምድሩ ሊያከማቸው የሚችልና የሚፈቅድም መሆኑን የሚያመለክት አስደናቂ ገለጣ ነበር። የመጀመሪያው ምልክት ዓላማ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚመልስበትን ሁኔታ መግለጥ ከሆነ፥ ሁለተኛው ምልክት ደግሞ፥ በዚህ ተአምራዊ መሰባሰብ ውስጥ የሚካተተው ማን መሆኑን ማመልከት ነበር።

ሕዝቅኤል ሁለት በትሮች ወስደና፥ በአንደኛው ላይ እንዲህ በማለት ጻፈ፤ "ለይሁዳና ለባልንጀሮቹ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ" (ሕዝ. 37፡16)። በሁለተኛው በትር ላይ ደግሞ "የኤፍሬም በትር ለዮሴፍና ለባልንጀሮቹ ለእስራኤል ቤት ሁሉ" (ሕዝ. 37፡16)። ከዛም አንድ በትርም እንዲሆኑ አንዱን ከሁለተኛው ጋር አጋጠመው። ሕዝቅኤል ይህን ሲያደርግ የተመለከቱ ሰዎች "ይህ ምን ማለት ነው?" እያሉ በሹክሹክታ እንደሚነጋገሩ ለመገመት ይቻላል።

ሞርሞን* የተሰኘው እምነት ተከታዮች፥ ይህን የምንባብ ክፍል መጽሐፍ ቅዱስ ወደፊት ስለሚጻፈው የሞርሞን መጽሐፍ የተናገረው ትንቢት እንደሆነ አድርገው ይጠቀሙበታል። መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ከይሁዳ ትውልድ የወጡ ሰዎች ነበሩ። አንደኛው ጆሴፍ ስሚዝ የተባለና የሞርሞንን መጽሐፍ እንዲተረጉም እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው እንደ ነበር ይናገራሉ። በዚሁ መሠረት ሕዝቅኤል እንደተናገረው፥ እግዚአብሔርስ ሁለቱን በትሮች አጋጥማለሁ ያለው መፈጸሙን በማስተማር፥ የእነሱ ቤተ ክርስቲያን ጅማሬን የሚያሳይ እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል። ብዙ ቅን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲህ ባለው የተሳሳተ መንገድ የመጠቀም ሰለባ ሆነዋል። የምልክቶቹን ትርጉም እግዚአብሔር ካልገለጠልን በቀር፥ የሕዝቅኤል ምልክቶች በብዙ አቅጣጫ የሚተረጎሙ ናቸው። እግዚአብሔር የምልክቶቹን ትርጉም አንዴ ከሰጠ ግን፥ ማንኛውም ዓይነት ሌላ ትርጉም ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም። እግዚአብሔር ምልክቶቹን ካሳየ በኋላ ወዲያውኑ ትርጉማቸውን ይገልጣል፡-

> “እነሆ የእስራኤልን ልጆች ከሄዱባቸው ከአሕዛብ መካከል እወስዳለሁ፥ ከስፍራም ሁሉ እሰበስባቸዋለሁ፥ ወደገዛ ምድራቸውም አመጣቸዋለሁ፤ በምድር ላይ በእስራኤል ተራሮች ላይ አንድ ሕዝብ አደርጋቸዋለሁ፥ አንድ ንጉሥም በሁላቸው ላይ ይነግሣል፤ ከዚያ ወዲያም ሁለት መንግሥታት ሆነው አይለያዩም” (ሕዝ. 37፡21-22)።

ንጉሥ ሰሎሞን በ930 ዓ.ዓ. እንደ ሞተ፥ የእስራኤል ሕዝብ ሁለት ላይ ተከፈለ። አሥሩ ነገዶች ከኤፍሬም ወገን የሆነውን ኢዮርብዓምን ተከትለው የእስራኤልን መንግሥት መሠረቱ። ሁለቱ ነገዶች ግን የሰሎሞን

* ዮሴፍ ስሚዝ (1805-1844) ኒዮርክ በሚባል የአሜሪካን ግዛት ውስጥ የኖረና ተከታዮቹን ከዚህ ስፍራ ወደ ምዕራብ ይዞአቸው የተጓዘ መሆኑ ይነገራል። ይህ ሰው እግዚአብሔርና ጌታ ኢየሱስ በ1820 ዓ.ም. እንደተገለጡለት ተናግሯል። በዚህ ልምምዱ በወቅት የነበሩ ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ የተሳሳቱ እንደሆኑና እርሱን ንጹሕ የሆነውን ወንጌል እንደገና እንዲያነሣ የተነገረው መሆኑን ይገልጣል። ስሚዝ በ1823 “ሞሮኒ” የተባለ መልአክ ወደ አንድ ስፍራ እንደመራውና ከዛም ወርቃማ በሆኑ ገጾችና ባልታወቀ ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ እንዳገኘ ይገልጣል። ይህ ሰው አንድ ድንጋይ እንደተሰጠውና ድንጋዩም ይህን መጽሐፍ ሊተረጉም እንዳስቻለው ተናግሯል። ያገኘው መጽሐፍ “እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል” እንደያዘ ሲገልጥ፥ ይህ መጽሐፍ ወደ ደቡብ አሜሪካ ተሰደው በነበሩ አይሁዶች በ600 ዓ.ዓ. ገደማ ተጽፎ እንደ ነበር ይገልጣል። ስሚዝ ይህን መጽሐፍ እንደተረጎመ፥ መጽሐፉም አሁን “የሞርሞንስ መጽሐፍ” በመባል እንደሚታወቅና ይህን “ወርቃማ መጽሐፍ ለመልአኩ መልሶ እንደሰጠው ይናገራል። (የግርጌ ማስታወሻው በተከታዩ ገጽ ይቀጥላል።)

ልጅ የሮብዓም ታማኞች በመሆን የይሁዳን መንግሥት መሠረቱ። እነዚህ ሁለት ጎረቤት መንግሥታት የትብብርና የግጭት ጊዜያትን ቢያሳልፉም፥ እንደተናጠል መንግሥት ኖሩ እንጂ እንደ አንድ መንግሥት ተዋሕደው አያውቁም። በ722 ዓ.ዓ. ሶርያ የሰሜኑን የእስራኤል መንግሥት በምርኮ ወሰደች። ከ140 ዓመታት በኋላ ደግሞ፥ የደቡቡ የይሁዳ መንግሥት በባቢሎን መውደሙን ሕዝቅኤል መዝግቧል።

በሕዝቅኤል የተሰጠው ምልክት ምን ያህሉ የእስራኤል ሕዝብ የሚመለስ መሆኑን ያመለክታል። የእስራኤል ሕዝብ ወደ ምድሩ የሚመለሰው በከፊል አይደለም። እግዚአብሔር ተስፋ የሰጠው ሁለቱንም ማለት፥ በሰሜኑና በደቡቡ መንግሥታት የነበረውን ሕዝብ በሙሉ ለመመለስ ነው።

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮች ልብ ሊባሉ ይገባል። አንደኛው፥ እነዚህ የሕዝቅኤል ትንቢቶች ገና አልተፈጸሙም። ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የእስራኤል ቅሪቶች ሁሉ አይደሉም ወደ ምድራቸው የተመለሱት። የተመለሱትም ቢሆኑ፥ በብሔራዊ ደረጃ የኃጢአት ይቅርታን፥ ያድር ባቸዋል የተባለላቸውን መንፈስ ቅዱስ እና የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ በረከት ገና አላገኙም። ወደ ምድራቸው የተመለሱ አይሁዳውያን ቀደምት ወገኖቻቸው ከነበሩባቸው መሰል ችግሮች ጋር በመታገል ላይ መሆናቸውን ለመረዳት፥ ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ዕዝራን፥ ነህምያን፥ ትንቢተ ሐጌን፥ ትንቢተ ዘካርያስን ወይም ትንቢተ ሚልክያስን ማንበቡ ይበቃል።

ሁለተኛ፥ ሕዝቅኤል በዚህ ምንባብ፥ "የሁለት ጊዜ" መመለስን ትንቢት አልተናገረም። የደረቁ አጥንቶች በሞሉበት ሸለቆ ትዕይንት፥ አጥንቶቹ መጀመሪያ ሕይወት ወደሌለው አካልነት ተለወጡ። ከዚያም ሕይወትን ለመስጠት መንፈስ ቅዱስ ወደ አካላቱ ገባ። አንዳንዶች ከዚህ ትዕይንት የተረዱት፥ የእስራኤላውያን ወደ ምድራቸው መመለስ የሚከናወነው ሁለት ጊዜ፥ ማለት ወደ ምድሪቱ ከሚደረገው መመለስ በፊት በመንፈሳዊ ተሐድሶ ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱበት ሁኔታ መኖሩን ነው። ይህ ዓይነቱ መረዳት ያላቸው ወገኖች፥ የመጀመሪያው

---

በዚህ ሰው ትምህርት ውስጥ በርከት ያሉ ግራ የሚያጋቡ አስተምህሮዎች አሉ። ለምሳሌ ያህል ይህ ሰው ከአንድ በላይ ሚስት የማግባትን መልካምነት ያስተምራል። ለዚህ ምክንያቱ እግዚአብሔር ሰዎች ሰማይን እንዲሞሉ የሚፈልግ ጌታ ነው የሚለው እምነቱ ነበር።

በዚህ ሰው ጉዞ ውስጥ ብዙ አመጾች ተነሥተው ነበር። በመጨረሻም በ1844 ዓ.ም. በተነሣው ዐመፅ ይህ ሰው ተገደለ። ሞርሞንስ (የመጨረሻው ዘመን ቅዱሳን) በብዙ ቡድኖች ተከፋፈሉ። አሁን በምዕራብ አሜሪካ ሶልት ሌክ ከተማ ውስጥ አብዛኞዎቹ የሞርሞን ተከታዮች ይገኛሉ።

ክፍል መመለስ፥ እስራኤል በ1948 እአአ መንግሥቷን በመሠረተች ጊዜ ተከናውኗል ይላሉ። የሕዝቅኤል ራእይ የሚያስተምረው ይህን ነው?'

የሕዝቅኤል ራእይ የሚገልጠው፥ የእስራኤልን አካላዊና መንፈሳዊ ተሐድሶ አስመልክቶ በመጽሐፉ ምዕራፍ 36 ውስጥ የተመለከተውን እውነት ነበር። ተሐድሶው ሁለት ደረጃ ያለው ክንውን መሆኑን ሕዝቅኤል ምዕራፍ 36 አያመለክትም። በደረቁ አጥንቶች ራእይ ውስጥም፥ የሁለት ደረጃው ክንውን ሕዝቅኤል ገለጣ ውስጥ ብቻ ነው የተመለከተው። እግዚአብሔር እንዳውም ደረጃዎቹን በትርጉሙ ያዟዙራቸዋል፥ "መንፈሴንም በውስጣችሁ አሳድራለሁ። እናንተም በሕይወት ትኖራላችሁ፥ በገዛ ምድራችሁም አኖራችኋለሁ" (ሕዝ. 37፡14)። የሕዝቅኤል መጽሐፍ ምዕራፍ 37 የእስራኤል ሕዝብን ወደ ምድሩ መመለስ ይተነብያል። ይህ መመለስ በ1948 (እአአ) የሚከናወን መሆኑን ግን በግልጥ አይናገርም።

## በሚቀጥለው ዓመት ኢየሩሳሌም ውስጥ እንገናኝ

ጸደይ በመጣ ቁጥር አይሁዳውያን በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው የጥንት እስራኤላውያን እንደሚያደርጉት ሁሉ፥ የተጠበሰ የጠቦት ሥጋና እርሾ ያልገባበት ዳቦ እየተጋበዙ፥ የመንፈሳዊ ሥርዓታቸውን መታሰቢያ ያደርጋሉ። በዚህ ጊዜ በዕድሜ ከሁሉ የሚያንስ እስራኤላዊ ወጣት ለሚያቀርበው ጥያቄ መልስ እየሰጡ የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ባርነት ነጻ የወጣበትን ሁኔታ ያስታውሳሉ። በሥርዓቱ ወቅት ከመሢሑ ቀድሞ እንደገና ይመጣል ብለው የሚያስቡትን ነቢይ፥ ኤልያስን የሚጠብቅ አንድ ባዶ ወንበር ይኖራል። የግብዣው ሥርዓት ሲያበቃ፥ የግብዣው ተሳታፊዎች ሁሉ አሳብ የሚያተኩረው፥ "በሚቀጥለው ዓመት ኢየሩሳሌም እንገናኛለን!" በሚለው የብሔርተኝነት ግብ ላይ ነው። ይህ አባባል፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተስፋ በገባለት ምድር እና ከተማ አዲስ የእስራኤል መንግሥት ለማቋቋም በተሰጠው ተስፋ መሠረት እንዲሆን መመኘትን ወይም ጽዮናዊነትን ያነሣሣል።

አይሁዳውያን አንድ ቀን ወደ ምድራቸው በመመለስ ምድራቸውንና የወደሙ ከተሞቻቸውን እንደገና ለመሥራት ማለም የጀመሩት፥ ገና በጦርነት የፈራረሰችው ኢየሩሳሌም ቃጠሎ የመጨረሻ ፍም ሳይጠፋ ነበር። ወራሪዎቹ ሮማውያን በ73 እአአ መሳዳ በተባለው ስፍራ ይገኝ የነበረውንና የመጨረሻውን የአይሁድ የመከላከያ ምሽግ እንደጣሱ ነው፥ ዐመፀኛዋን መንግሥት መደምሰሳቸውን ይፋ ያደረጉት።

ከ60 ዓመት በኋላ ሮማውያን እንደገና ሠራዊታቸውን ወደ ይሁዳ ልከው፥ በዚያ የተነሣውን ባር ኮክባ* የተሰኘውን ዓመፅ እስኪደመስሱ ተዋግተዋል።

ሮማውያን የአይሁድነት መለያዎችንና ባለቤትነትን በማጥፋት ነው በቀላቸውን የገለጡት። የዋና ከተማይቱን ስም ለወጡት። ኢየሩሳሌም፥ ኤሊያ ካፒቶሊና ተባለች። አይሁዳውያን ወደአገራቸው እንዳይገቡ ታገዱ። የምድሪቱም ስም ተለውጦ ይሁዳ ከመባል ይልቅ ፍልስጥኤም ሆነ። ዓመታት እየተፈራረቁ በሄዱ ቁጥር ግን፥ የሮማውያን ገናናነት ሚሸሸ። አይሁዳውያን ግን፥ ምንም እንኳን ተስፋቸው በዓለም ሁሉ ቢበተን ብርታታቸው የጸና ነበር።

በቀጠሉት 1500 ዓመታት አይሁዳውያን በተደጋጋሚ ወደ ምድራቸው ቢመለሱም እንደገና ተባረዋል። ጸሎታቸው "በሚቀጥለው ዓመት ኢየሩሳሌም እንገናኝ" የሚል ቢሆንም፥ እስካለፈው ክፍለ ዘመን ፍጻሜ ድረስ ያን ምኞት ተግባራዊ የሚያደርግ ንቅናቄ አልነበረም። ቴዎዶር ኸርትዝል የተባለ የፈረንሳይ ጋዜጠኛ፥ ድሬይፈስ በተባለው ፈረንሳያዊ አይሁዳዊ ላይ በፍርድ ቤት የቀረበን ክስ በዘገበ ጊዜ፥ "ዘመናዊው" አውሮፓ በሚለው ስም ውስጥ የተሸሸገውን፥ አይሁዳዊነትን የተመለከተ ጥላቻ ተረዳ። በመሆኑም የጽዮናዊነትን፥ ማለት ለአይሁድ ሕዝብ መኖሪያ አገር ማስገኘትን ዓላማው ያደረገ ትግልን ጀመረ።

ኸርትዝል ለዓላማው የመሠረተው ቡድን ከኬንያ እስከ አውስትራሊያ ያሉ ብዙ አገሮችን በመጎብኘት ለአይሁዶች ክልልን ለማዘጋጀት ታላቅ ጥረት አድርጓል። ይህ ሲሆን ሳለ፥ የኸርትዝል ቡድን አባላት በአሳባቸው ለአይሁዶች እግዚአብሔር ወደሰጣቸው የተስፋ ምድር ይጓዙ ነበር። በተናጠል ይደረግ የነበረው የአይሁዶች ወደ ምድራቸው መመለስም፥ ከ1948 ዓ.ምህረቱ. ከእስራኤል መንግሥት ምሥረታ በኋላ፥ ግድቡን የጣሰ ጎርፍ መሰለ። ከ2000 ዓመታት በኋላ አይሁዳውያን እንደገና የራሳቸው አገር ኖራቸው።** ይህ ማለት ግን ማንኛውም ነገር መልካም ነበር ማለት አይደለም።

---

* ሲሞን ባር ኮህከባ በጣም ታዋቂ የአይሁድ መሪ የነበረ መሲሕ ነኝ የሚልና በሮማውያን ላይ የተነሣውን አመጽ የመራ ነበር። ኢየሩሳሌምን በ132 ዓ.ም. ከሌሎች በአካባቢዋ ካሉ ከተሞች ጋር በቁጥጥር ሥር አደረገ። የሮማው ንጉሠ ነገሥት ሐድሪያን ወደ ይሁዳ ጦሩን በ135 ዓ.ም. ልኮ ኢየሩሳሌምን ያዘ፤ ባር ኮህከባንም ገደለው። አይሁድም ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይገቡ በመከልከል ቅጣት ተወሰነባቸው።

** በጽዮናዊነት እንቅስቃሴ ጅማሬ ላይ 50,000 ያህል አይሁዶች ፍልስጥኤም ውስጥ ይኖሩ ነበር። በ1929 ዓ.ም. ቁጥራቸው ወደ 157,000፥ በ1934 ደግሞ ወደ 283,000 አድጎ ነበር።

የእስራኤል መንግሥት፥ ለአይሁዳውያን በጥላቻ ባሕር የተከበበ ደሴት ይመስላቸው ነበር። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የእስራኤል መንግሥት ይመሠረት ዘንድ በ1948 እአአ በድምፅ ብልጫ ሲወስን፥ በፍልስጥኤም ምድር 600,000 ያህል አይሁዶችና 1,200,000 ዓረቦች ይኖሩ ነበር። የእስራኤል መንግሥት መመሥረቱን በዙሪያዋ ያሉ አገሮች ተቃወሙ። ይህ ሁሉ ቢሆንም፥ ከናዚ መንግሥት (ጀርመን) ጭፍጨፋ የተረፉ አይሁዳውያን ከአውሮፓ፥ በየሥርቻው ወድቀው የነበሩት ደግሞ ከባግዳድ፥ የነጻነት ጮራ ወደፈነጠቀባት ምድር ይመለሱ ጀመር። በ1960ዎቹ እአአ እስራኤል ውስጥ የነበሩ አይሁዳውያን ብዛት ከሁለት ሚሊዮን ጥቂት ከፍ ያለ ነበር።

የእስራኤል አስደናቂና ከፍተኛ ዓላማ እውን የሆነው፥ በ1967ቱ የስድስት ቀን ጦርነት ነው። በነዚህ ስድስት ቀናት ውስጥ፥ ሰፊውን ጥንታዊ ምድሯን ጎረቤቶቿ ከሆኑ ዓረቦች በኃይል ወሰደች። ይሁን እንጂ፥ ያኔ ወታደራዊ ድል ባገኘች ጊዜ፥ በውስጧ የጎዘንና የተቃውሞ ዘር ዘርታ ነበር። ይኸውም በያዘችው ምድር ብዙ ዓረቦች መኖራቸው ነው። ከዚህ ጋር የእስራኤል ሕዝብ ብዛት በየጊዜው ይጨምር ነበር።

የ1960ዎቹ ዓመታት እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ ኃያል የጦር ኃይል ያላት መሆኗን አመልክተዋል። የ1973 ዓመተ ምህረቱ ዮም ክፑር ጦርነት ግን፥ የእስራኤልን አትደፈሬነት አስተሳሰብ ሻረው። ግብፅና ሶርያ ከሁለት አቅጣጫ በእስራኤል ጦር ላይ ድንገተኛ ወረራ ሰነዘሩ። በዚህ ሳቢያ እስራኤል ፈተና ገጠማት። ቢሆንም በመጨረሻ ድል አድርጋለች። ድሉ የተገኘው ግን፥ ብዙ መሥዋዕትነትን ከፍላና ለድል ተቃርቦ በነበረው ድንገተኛ ወረራ የጀግንነት ቅስሟ ተጎድቶ ነው።

1970ዎቹ ዓመታት ወደ 1980ዎቹ በሚሸጋገርበት ወቅት እስራኤል ተዳክማ ነበር። እርግጥ ጦርነቱን አሸንፋለች። ነገር ግን በዙሪያዋ ይጫር የነበረው "ቀዝቃዛ ጦርነት" ኢኮኖሚያዊና ሥነ-ልቦናዊ ችግር አስከትሎባታል። በ1982 ሊባኖስን በወታደራዊ ኃይል በመውረር ከዚያ ይደርስባት የነበረውን ችግር በመጠኑም ቢሆን ገታች። በሚገባ የለየለት ዓላማና ግብ የሌለው ይህ ጠላትን የማዳከም ጦርነት አታካች ሆነ። ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ለጦርነቱ የነበረው ሕዝባዊ ድጋፍ ተነነ። በመሆኑም የእስራኤል ጦር ተጎሣቁሎ ከሊባኖስ ወጣ። የአገሪቱ ኢኮኖሚ በከፍተኛ የምንዛሪ መውደቅ ተናጋ፥ ፖለቲካዋም አገሪቱን የሚያስተሣሥር ብርቱ መሪ አጣ። የጽዮናዊነቱ ሕልም ቅዠት እየሆነ ስለመጣ ወደ አገራቸው የሚመለሱ አይሁዳውያን ቁጥር ቀነሰ። ወደ አገር ከሚገቡት የላቁ እስራኤላውያን ከአገራቸው ይወጡ ጀመር።

አንዳንድ እስራኤላውያን ግን ወደ አገራቸው ለመመለስ ይፈልጉ ነበር። በቀድሞይቱ ሶቪየት ኅብረት ውስጥ ይኖሩ የነበሩና በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን እዚያ የተፈጠረውን ሁኔታ በመሸሽ ወደ ሌላ አገር፥ በተለይም ወደ እስራኤል መሄድን ፈለጉ። የሶቪየት ኅብረት መንግሥት ፖሊሲ ግን የአይሁዳውያኑን ፍላጎት በተመለከተ ቀና አልነበረም። በ1979 እአአ 51,320 አይሁዳውያን ከሶቪየት ኅብረት ምድር እንዲወጡ ተፈቅዶላቸው ነበር። በ1986 እአአ ግን ይህ ቁጥር ወደ 914 ዝቅ አለ። ከዚህም የተነሣ ወደ አገራቸው ለመመለስ የተሰለፉ በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን አንዳች ተአምር ካልመጣ በቀር ከሶቪየት ኅብረት የማይወጡ ሆኑ።

ያን ተአምር ያመጡት ሚካኤል ጎርባቾቭ የተባሉት የአገሪቱ አዲስ መሪ ናቸው። "ግላስኖይት" (ግልጥነት) የተሰኘው የኚህ ሰው ፖሊሲ፥ የሶቪየት አይሁዳውያንን ከአገር የመውጣት ዕድል አሻሻለው። በዚሁ መሠረት በ1987 እአአ 8,011 አይሁዳውያን ከሶቪየት ኅብረት እንዲወጡ ተፈቀደላቸው። ወደ ምድራቸው የሚገቡ አይሁዳውያን ብዛትም እጅግ ጨመረና በ1989 እአአ ብቻ ወደ 71,000 አደገ። በ1990 እአአ ደግሞ ሶቪየት ኅብረት ውስጥ የነበረው የኢኮኖሚ ችግር ከፀረ-አይሁዳዊነት ተቃውሞ ጋር ተደመረና 200,000 አይሁዳውያን ከዚያ እንዲወጡ አደረገ። ከነዚህ ብዙዎቹ ወደ እስራኤል ነው የተጓዙት።

## ዘመቻ ሙሴ እና ዘመቻ ሰሎሞን

አይሁዶች ባለፉት ሀያ ዓመታት ከቀድሞይቱ ሶቪየት ኅብረት የወጡበትና ወደ ምድራቸው የተመለሱበት ሁኔታ አስደናቂ ነው ሊባል ይችላል። ከሶቪየት ኅብረት ብቻ አልነበረም አይሁዳውያን ወደ እስራኤል ምድር የተመለሱት። በ1984 እና በ1991 እአአ ወደ እስራኤል በተደረገው የአየር ጉዞ፥ ከኢትዮጵያ ወደ እስራኤል የተመለሱት አይሁዳውያን ብዛትና የጉዞ ሁኔታ ለመገመት ከሚቻል በላይ ነበር።

ብዛታቸው ወደ 30,000 የሚጠጋ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ዝርያቸውን ከንግሥት ማከዳ ጋር ከመጡ አይሁዳውያን ጋር በማጣቀስ፥ በኢትዮጵያ ምድር ይደርስባቸው ከነበረ ችግር ጋር ሲታገሉ ኖረዋል። የእስራኤል መንግሥት በ1973 እአአ የነዚህን አይሁዳውያን ትውልድ ወደኋላ እስከብሉይ ኪዳን ዘመን ድረስ ከመረመረ በኋላ፥ አይሁዳዊነታቸውን አረጋገጠ። ከዚህ በኋላ ዘመቻ ሙሴ በሚል ስያሜ እነዚህን አይሁዳውያን በአይሮፕላን በምስጢር የማጓጓዙ ሂደት በ1984 እአአ ተጀመረ። ይህ የማጓጓዝ ሂደት ሌላው ዓለም ከማወቁ በፊት 12,000

አይሁዳውያንን ከኢትዮጵያ ወደ እስራኤል አጓጉዞአል። በኋላ ግን ከሙስሊም ጎረቤቶቿ በደረሰባት ተጽዕኖ ሳቢያ፥ ኢትዮጵያ የማጓጓዙን ፕሮግራም አገደችው።

በ1989 እአአ ማጓጓዙ እንደገና ተጀመረና፥ በየወሩ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች በሰላም ወደ እስራኤል ተጓጓዙ። ይሁን እንጂ፥ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰቱ ሁኔታዎች በዕቅዱ ላይ ለውጥ እንዲደረግ አስገደዱ። ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ሕዝባዊ ጦርነት በ1991 እአአ ወደ ፍጻሜ ተቃረበ። የኤርትራ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር ለ30 ዓመታት ያደረገውን የነጻነት ውጊያ ከዳር በማድረስ፥ የክፍለ አገሪቱን ዋና ከተማ ያዘ። በተመሳሳይ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ወደ አዲስ አበባ ተቃረበ። ይህ ጦርነት ወደ እስራኤል ለመጓጓዝ አዲስ አበባ ለተከማቹት ከ16,000 የሚበልጡ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ወጥመድ ሆነባቸው።

ግንቦት 17 ቀን 1991 እአአ እስራኤል ዘመቻ ሰሎሞን የተሰኘውን ፕሮግራም ጀመረች። በዚሁ መሠረት፥ ቀጥሎ በነበሩት ሁለት ተከታታይ ቀናት በየግማሽ ሰዓቱ ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን የጫነ አንድ አይሮፕላን ከአዲስ አበባ ይነሣ ነበር። የመጨረሻው አይሮፕላን ከአዲስ አበባ በተነሣ ጊዜ፥ አይሁዳውያን በኢትዮጵያ የኖሩበት ከ2000 ዓመታት በላይ የሆነው ጊዜ ፍጻሜ ሆነ። በዚህ ሁኔታ የአይሁድ ዘር የሆኑ ሌሎች ወገኖችም ወደ ተስፋይቱ ምድር ተመለሱ። ደመላሽ አይሸሽን የተባሉት አይሁዳዊ በጉዞው ፍጻሜ እንዲህ አሉ፦

> “የኢሳይያስ ትንቢት ተፈጸመ፤ እስራኤላውያን ሁሉ አሁን የአባቶቻችን ምድር ወደ ሆነችው ወደ ከነዓን ሊመለሱ ይችላሉ።”

## የእስራኤል መወለድ፤ የትንቢት ክንውን ፍፃሜ ወይስ ጅማሬ?

እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም ወደሰጠው የተስፋ ምድር እንደሚመለሱ ሕዝቅኤል ተንብይዋል። በመንፈስም የአብርሃም አምላክ ወደ ሆነው እግዚአብሔር ይመለሳሉ ብሎ ነበር። ዛሬ ብዙ አይሁዳውያን በአካል ወደ ምድራቸው በመመለስ ላይ ቢሆኑም፥ ወደ አምላካቸው በመንፈስ አልተመለሱም። ስለዚህ የአይሁዳውያን ወደ ምድራቸው መመለስ የሕዝቅኤል ትንቢት ፍጻሜ አይደለም። ታዲያ የአሁኑ የአይሁዳውያን መመለስ፥ ሕዝቅኤል መጽሐፍ ውስጥ ከ36-37 ባለው ክፍል የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ ካልሆነ፥ ትንቢታዊ ጠቀሜታ አለው?

መልሱ አዎ እንደሚሆን አምናለሁ። የሕዝቅኤል ትንቢት ኢየሱስ ወደ ምድር እስኪመለስ የማይፈጸም እንደ መሆኑ፥ ከመሢሑ መመለስ በፊት ቢያንስ ጥቂት አይሁዳውያን በምድሪቱ የሚቀመጡበት ጊዜ እንደሚኖር ሌሎች ነቢያት ያመለክታሉ። በተለይ ሁለት ግልጥ የምንባብ ክፍሎች ይህን ከኢየሱስ ዳግም ምጽአት በፊት የሚደረግ ከፊል መመለስ ይጠቁማሉ።

## መቼ ነው?

ብዙ ቅን ሰዎች ትንቢተ ዳንኤልን ሲያነቡ ይደነግጣሉ። ዳንኤል ስለ ሀውልቶችና አራዊት ያየው ራእይ ትርጉም ዛሬ ለኛ አይገባንም። የሚያቀርባቸው ምስሎች አሮጌ ተረቶች ወይም ታሪኮች ውስጥ የሰማናቸውን አስፈሪ ገጸ-ባሕሪያት ያስታውሱናል። ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች በዝርዝር ጉዳዮች ጥልቅነት ይዋጡና ሕልሙንም ሆነ ፍቺውን ለዳንኤል የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ይዘነጋሉ።

ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 9 የእስራኤል ሕዝብ የጊዜ ሰሌዳ ሲሆን፥ የምዕራፉ መነሻ የሙሴ ሕግጋት ናቸው። ሕዝቡ እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው የኃጢአታቸውን ፍሬ አጭደዋል። እስራኤላውያን በተከታታይ የጣሱት ስለ "ሰንበታዊው ዓመት" የተነገራቸውን አንድ ትእዛዝ ነበር። ይኸውም ምድሪቱ በየሰባቱ ዓመቱ ማረፍ አለባት የሚለው ነው (ዘሌ. 25፡1-5)። ይህን ባያደርጉ በአሕዛብ መካከል እንደሚበትናቸውና ምድሪቱ በሰንበታዊው ዓመት እስክታርፍ ድረስ እዚያው እንደሚቆዩ አስጠንቅቋቸዋል (ዘሌ. 26፡33-35)። ዘዳግም ምዕራፍ 30 ውስጥ ሕዝቡ በምርኮ አገር እንዳሉ፥ በንስሐ ወደ እርሱ ሲመለሱና ኃጢአታቸውን ሲናዘዙ ብቻ ወደ ምድራቸው እንዲመለሱ የሚፈቅድላቸው መሆኑን እግዚአብሔር አስገንዝቧቸዋል።

ዳንኤል ትንቢተ ኤርምያስን ሲያጠና ምዕራፍ 25፡11-12 እና ምዕራፍ 29፡10 ውስጥ አይሁዳውያን ባቢሎን ውስጥ በምርኮ የሚቆዩት ለሰባ ዓመት መሆኑን አንብቦ ነበር። በ605 ዓመተ ዓለም ናቡከደናጾር ዳንኤልን በምርኮኛነት ወደ ባቢሎን ወሰደው። ዳንኤል ዳሪዮስ በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ነበር ይህን የኤርምያስ መጽሐፍ ያነበበው። ዓመቱ 538 ዓ.ዓ. ነበር። በዳንኤል በተጠቀሰው የዘመን አቆጣጠር ላይ በመመሥረት ስናጤነው፥ እርሱ በምርኮ ከተወሰደ ስድሳ ስምንተኛ ወይም ስድሳ ዘጠነኛ ዓመቱ መሆኑን እንረዳለን። ያ የሚያመለክተው፥ የኤርምያስ ትንቢት መፈጸሚያ ጊዜ በጣም የተቃረበ መሆኑን ነበር። ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ቢመለስና ኃጢአቱን ቢናዘዝ ኑሮ፥ እግዚአብሔር ምናልባት

ዘዳግም 30 ውስጥ ለሙሴ በገባለት ቃል መሠረት ለመጨረሻ ጊዜ ሕዝቡን ወደ ምድሩ ይመልሰው ነበር።

ዳንኤል ተንበርክኮ ስለአመጸኛ ወገኖቹ የጸለየበትን ሁኔታ እንዲህ በማለት ገልጦታል፥ "ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኜ ስጾም እጸልይና እለምን ዘንድ ፊቴን ወደ ጌታ ወደአምላክ አቀናሁ" (ዳን. 9፡3)። ኀዘንና ትካዜውን በገሀድ ለመግለጥ የሚፈልግ ሁሉ ማቅ ለብሶ እራሱ ላይ አመድ ይነሰንስ ነበር። ለምሳሌ ያዕቆብ ልጁን ዮሴፍን የዱር አራዊት የበሉበት መስሎት ባዘነ ጊዜ ማቅ ለብሷል (ዘፍጥ. 37፡31-35)። እንዲሁም እግዚአብሔር ኢዮብ በችኮላ ስለተናገረው ቃል በተከራከረው ጊዜ ኢዮብ እንዲህ ብሏል። "መስማትንስ በጆሮዎቼ ሰምቼ ነበር፥ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤ ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ" (ኢዮብ 42፡5-6)።

ዳንኤል ስለ እስራኤላውያን ወገኖቹ ሊማልድ ፈለገ። የእግዚአብሔርን ጻድቅነትና የእስራኤልን ኃጢአት ስለተረዳ ነበር ይህን ያደረገው። "በሙሴ ሕግ የተጻፈው መሃላና እርግማን ፈሰሰብን" (ዳንኤል 9፡11) የሚለውን ቃል በጠቀሰ ጊዜ፥ ወገኖቹ ለስደት የተዳረጉበትን ምክንያት የተረዳ መሆኑን ገልጧል። እግዚአብሔር ከምድራቸው የሚያስወጣቸው መሆኑን በመግለጥ አስጠንቅቋቸው ነበር፤ የተናገረውን በትክክል አደረገ።

በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር 15 ጀምሮ ግን፥ ዳንኤል ካለፈው ጊዜ ወደ አሁኑ ይመለሳል። ከቁጥር 15-19 ባለው ክፍል ስለሁለት ጉዳዮች ይጸልያል። መጀመሪያ "ከኢየሩሳሌም፥ ከቅዱስ ተራራህ" (ቁ. 16) ብሎ ይጸልያል። የእስራኤል ዋና መዲና ኢየሩሳሌም ፈራርሳለች "ቅዱሱ ተራራ" ሰሎሞን የሠራው ቤተ መቅደስ የነበረበት የኢየሩሳሌም ተራራ ነው። ከቁጥር 17-18 ባለው ክፍል ዳንኤል በጣም ግልጥ በሆነ ጸሎት እንዲህ በማለት፥ እግዚአብሔርን ጠይቆታል፥ "በፈረሰው መቅደስህ ላይ ስለአንተ ስትል ፊትህን አብራ... ዓይንህን ገልጠህ... ስምህ የተጠራበትን ከተማ ተመልከት"። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን እንደነበረች እንዲሠራትና ቤተ መቅደሱንም መልሶ እንዲያንጸው ነበር የዳንኤል ፍላጎት።

ዳንኤል የጓጓው ከፈረሰው መቅደስ መገንባት ለላቀ ነገር ነበር። ጸሎቱ ያተኮረው፥ በሁለቱም ማለት በሰዉና በምድሩ ላይ ነው። እግዚአብሔርን የጠየቀው፥ "ኢየሩሳሌምንና ሕዝቡን" (9፡16) እንዲረዳ ነበር። ልመናውንም ሲያጠቃልል፥ "አቤቱ ስማ፥ አቤቱ ይቅር በል፥

አቤቱ አድምጥና አድርግ፤ አምላኬ ሆይ ስምህ በከተማህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቶአልና ስለራስህ አትዘግይ” (9፡19) ብሏል።

እግዚአብሔር የዳንኤልን ጸሎት ለመመለስ መልአኩን ላከ፤ እርሱም “በልመናህ መጀመሪያ ላይ ትእዛዝ ወጥቷል፥ እኔም እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ” (9፡23) አለው። ከዚህ ቀጥሎ የሚታየው ራእይ፥ ዳንኤል ለኢየሩሳሌምና ለአይሁዳውያን ለጸለየው ጸሎት የመጣ መልስ ነው። ይሁን እንጂ፥ የእግዚአብሔር መልስ በመጀመሪያ ግልጥ አይመስልም። “በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ* ተቀጥሯል” (9፡24) ይላል።

የእግዚአብሔር መልስ ኢየሩሳሌምና አይሁዳውያን በመጨረሻ እንደገና የሚመሠረቱበትን በማሳወቅ ችግሩን ይፈታዋል። ይሁን እንጂ “ሰባ ሱባዔ” (ሰባ ሰባቶች) ምንድነው?

እግዚአብሔር “በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቀጥሮአል” ባለ ጊዜ፥ ዳንኤል ትርጉሙ የገባው እንዴት ነው? “ሰባ ሱባዔ” የሚለውን ለማስረዳት ታሪካዊ መነሻውን በምዕራፉ መጀመሪያ ባሉ ሁለት መስመሮች ውስጥ ይገልጣል። ዳንኤል የኤርምያስን መጽሐፍ እና ወደ ባቢሎን ስለሚደረገው የሰባ ዓመት ምርኮ የተነገረውን ትንቢት ያጠና እንደነበር እናውቃለን። ለምንድነው የሰባ ዓመቱ ምርኮ የሆነው? “በኤርምያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል እንዲፈጸም ምድሪቱ ሰንበትን በማድረግዋ እስክታርፍ ድረስ፥ በተፈታችበትም ዘመን ሁሉ ሰባ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ፥ ሰንበትን አገኘች” (2ኛ ዜና 36፡21)። በባቢሎን ምርኮ የሚያልፈው እያንዳንዱ ዓመት፥ እስራኤላውያን በኢየሩሳሌም በነበሩ ጊዜ ያላከበሯቸውን የሰንበት ዓመታት ይወክላል። ቀደም ሲል እንደተገለጠው የሰንበት ዓመት በየሰባት ዓመቱ የሚመጣ ሲሆን፥ በዚያ ዓመት እስራኤላውያን ምድሪቱን ማሳረፍ ነበረባቸው። እስራኤል በታሪኳ ውስጥ ቢያንስ ሰባ ጊዜ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጣስዋ እርግጥ ነው። ይህም 490 ያለመታዘዝ ዓመታትን ይወክላል።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ምድራቸው መመለሱን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ “ሰባ ሱባዔ” ማስፈለጉን ሲያስታውቅ፥ በዳንኤል አእምሮ የነበረው መለኪያ ምን ነበር? ተገቢው መልስ ዳንኤል ሰባ ያህል (ሰባት) የሰንበት ዓመታት ያስብ ነበር የሚል ይሆናል። እግዚአብሔር ለዳንኤል ይነግረው የነበረው፥ እስራኤልን እንደ መንግሥት ሙሉ በሙሉ

---

* “ሰባ ሱባዔ” የሚለው ቃል ስሌትን የሚያመለክት ነው። በሌላ አገላለጥ ሰባ ጊዜ ሰባት ማለት ነው።

ወደ ምድሯ ከመመለሱ በፊት "የሰባው ሱባዔ" ዓመት መፈጸም ያለበት መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምንና አይሁዳውያንን እንደነበሩ የሚመልስበትን የጊዜ ሰሌዳ ለዳንኤል ይሰጠው ነበር።

"ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት . . ." (ዳን. 9፡25) የሚለው እስኪፈጸም ድረስ፥ የእግዚአብሔር የትንቢት ሰዓት መቆጠሩን አይጀምርም። የዳንኤል ትኩረት አሁንም በከተማይቱ ላይ ነው። ኢየሩሳሌምን እንደገና የመገንባቱ ትእዛዝ የወጣው መቼ ነበር? ዳንኤል የእግዚአብሔርን ተስፋ ከመዘገበ አንድ መቶ ዓመት ያህል እስኪፈጸም ድረስ ምንም አልሆነም። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ445 ዓ.ዓ.፥ ኒሳን በተባለው የዕብራውያን ወር (በመጋቢት ማለት ነው)፥ ንጉሥ አርጤክስስ፥ ነህምያ የሚባለው ጠጅ አሳላፊ (Cupbearer) አይሁዳዊ በለመነው መሠረት አዋጅ አስነገረ። ምንም እንኳን ከዘጠና ዓመት በፊት አይሁዳውያን ወደ እስራኤል ምድር በመመለስ ላይ ቢሆኑም፥ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ማፈራረስ የቀጠለ መሆኑን በሰማ ጊዜ ነህምያ አዝኖ ነበር። ለንጉሡ እንዲህ አለው፥ "የአባቶቻችን መቃብር ያለባት ከተማ ተፈትታለችና በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋልና ፊቴ ስለምን አይዘን?" (ነህ. 2፡3)። በመጨረሻም ንጉሡን እንዲህ ሲል ጠየቀው፥ "ንጉሡን ደስ ቢያሰኝህ፥ ባሪያህም በፊትህ ሞገስ ቢያገኝ፥ እሠራው ዘንድ ወደ ይሁዳ፥ ወደ አባቶቼ መቃብር ከተማ ስደደኝ" (ነህ. 2፡5)።

"ስለዚህ እወቅ፥ አስተውልም፤ ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሢሑ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል" (ዳን. 9፡25)። አዋጁ የወጣው፥ ከክርስቶስ ልደት 445 ዓ.ዓ. በፊት፥ በመጋቢት ወር ነው። አዋጁ ከወጣበት እስከ መሢሑ (የተቀባው) ዘመን ድረስ ሰባት ሲደመር ስድሳ ሁለት የተለያዩ ሰባት ዓመቶች ያህል ይቆያል። ሰባት ሲደመር ስድሳ ሁለት፥ ስድሳ ዘጠኝ ነው የሚሆነው። ታዲያ ለምንድነው ዳንኤል ስድሳ ዘጠኝን ሁለት ላይ የከፈለው? ይህን ያደረገው፥ ኢየሩሳሌምን እንደነበረች ለማድረግና እንደገና ለመገንባት፥ የመጀመሪያውን ክፍል ማለት (ሰባት "ሰባቶች") የሚወስድ መሆኑን ለማመልከት ነው። ያም ሆነ ይህ በትእዛዙ መውጣትና በመሢሑ መምጣት መካከል ስድሳ ዘጠኝ ሰባቶችን ያህል ዓመታት እንደሚያልፉ ነው ዳንኤል ያመለከተው። ስድሳ ዘጠኝ ጊዜ ሰባት 483 ዓመታት ናቸው።

እንዴት ነበር አይሁዳውያን ጊዜን ይቆጥሩ የነበሩት? ባጠቃላይ በሀያ ዘጠኝና በሠላሳ ቀናት የሚለዋወጡ አሥራ ሁለት ወራት፥ እንዲሁም የጨረቃን ዑደት ይከተሉ ነበር። ከጊዜ (seasons) ጋር እንዲስማማ

ለማድረግ ሲሉም፥ በእያንዳንዱ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ሰባት ጊዜ አንድ ተጨማሪ ወር በጊዜ ቀመራቸው ውስጥ ያስገባሉ። እንደማንኛችንም መደበኛ የጊዜ ቀመር ነበራቸው። መሬት በፀሐይ ዙሪያ ከምታደርገው ሽክርክሪት ጋር ለመስማማት ሲሉም በጊዜ ቀመራቸው ላይ አስፈላጊውን ማስተካከል ሁሉ ያደርጉ ነበር።

አይሁዳውያን ጊዜን የተገነዘቡበትን ሁኔታ ማወቁ ዳንኤል ምዕራፍ ዘጠኝን ለመረዳት ይጠቅማል። ሰባ ሱባዔ የሚመጣ መሆኑን እግዚአብሔር ባሳወቀ ጊዜ፥ እንዴት ነው አይሁዳውያን በወራትና በቀን ቆጠራ ይህን አሠራር የተረዱት? መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቁመን ነገር አለ?

ሌሎች ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሚያስገርም ሁኔታ የዳንኤል ምዕራፍ ዘጠኝን አንድ ክፍል ለመግለጥ ይረዳሉ። እነዚህን ክፍሎች ዘግየት ብለን በዝርዝር እንመረምራቸዋለን። ነገር ግን ለማነጻጸሪያነት ይረዱ ዘንድ ክፍሎቹን ወይም ምንባቦቹን ለመጥቀስ ይቻላል፡-

> ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባዔ ያደርጋል። የሱባዔውን እኩሌታ መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል፤ በርኩሰትም ጫፍ ላይ አጥፊው ይመጣል። እስከ ተቆጠረውም ፍጻሜ ድረስ መቅሠፍት በአጥፊው ላይ ይፈስሳል" (ዳን. 9፡27)።

> ላይ ቃልን ይናገራል፥ የልዑልንም ቅዱሳን ይሰብራል፥ ዘመናትንና ሕግን ይለውጥ ዘንድ ያስባል፤ እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም በእጁ ይሰጣሉ" (ዳን. 7፡25)

> ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደነበረው ስፍራ ወደ በረሃ ሸሸች።" (ራእይ 12፡6)

> ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፤ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው" (ራእይ 13፡5)።

ወደፊት በሰይጣን ገፋፊነት የሚነሣው የዓለም መሪ፥ በእግዚአብሔር ላይ ካለው ጥላቻ ሳቢያ በሚቀሰቅሰው ጦርነት፥ አይሁዳውያንን ከምድር ገጽ ለማጥፋት ይሞክራል። ይህንኑ ነው ከላይ የተጠቀሱት ምንባቦች የሚገልጡት። ጊዜው ዳንኤል ምዕራፍ 9 ውስጥ እስከተጠቀሰው የመጨረሻ "ሰባት" አጋማሽ ድረስ ይቀጥላል። ያም ሦስት ዓመት ተኩል ይሆናል። የዚህ ጊዜ ልክ ዳንኤል ምዕራፍ ሰባት ውስጥ ፡- "እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም" ተብሎ ከተጠቀሰው እኩል ነው። ይሁን እንጂ፥ ጊዜው በወራትና በቀናት ሲሰላ

በትክክል ስንት ነው? ራእይ 13 ውስጥ ጊዜው 42 ወራት ወይም ሦስት ዓመት ተኩል እንደሆነ ነው የሚያሳየው። ይህ ጊዜ 1260 ቀናት መሆኑ ራእይ 12 ውስጥ ተገልጧል። ያ እውነት ሊሆን ይችል የነበረው፥ ጸሐፊው ጊዜውን እያንዳንዳቸው ሠላሳ ቀናት ባላቸው ወራት ቢያሰላው ነበር። እያንዳንዳቸው ሠላሳ ቀናት ያሏቸው አርባ ሁለት ወራት በትክክል 1,260 ቀናት ይሆናሉ።

ንጉሥ አርጤክስስ ኢየሩሳሌም እንደገና እንድትሠራ ካዘዘበት አንሥቶ እስከ መሢሑ መምጣት የሚኖረው ጊዜ፥ 483 ዓመት ነበር። ይህ ደግሞ እያንዳንዱ ዓመት አሥራ ሁለት ወራት፥ እያንዳንዱም ወር ሠላሳ ቀን ነበር። ትእዛዙ ከወጣበት እስከ መሢሑ መምጣት የነበረው ጊዜ 173,880 ቀናት ነው።

አንዳንድ ምሁራን ኢየሱስ በአህያ ውርንጫ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው፥ ንጉሥ አርጤክስስ በነህምያ መጽሐፍ የሰፈረውን ትእዛዝ ካወጣበት ቀን አንሥቶ ልክ በ173,880 ቀናት ነው ይላሉ። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው፥ ዘካርያስ፥ መሢሑ ይመጣል ብሎ በመዘገበው መሠረት (ዘካ. 9፡9) በአህያ ውርንጫ ነው። ቀኑም መሢሑ ይመጣበታል ብሎ ዳንኤል የመዘገበው ነበር። ይህ የሚያመለክተን፥ ቀኑ ሁለት ታላቅ የሆኑ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች የተፈጸሙበት ዕለት መሆኑን ነው።

ከዚያ ቀጥሎ እግዚአብሔር ለእስራኤል ባለው የጊዜ ሠሌዳ ላይ አንድ ክፍተት መኖሩን ዳንኤል ይገልጣል። በዚህ ክፍተት ወቅት ሦስት በግልጥ የሚታወቁ ሁነቶች መከናወን አለባቸው። መጀመሪያ "መሢሑ ይገደላል፤ በእርሱም ዘንድ ምንም የለም" (ዳን. 9፡26)። መሢሑ፥ ማለት ለእስራኤል ተስፋ የተገባለት ንጉሥ እንዲነግሥና የሚገባውን ስፍራ እንዲይዝ አይፈቀድለትም፤ ይህ ብቻም አይደል፥ ይገደላል። "ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ" ብለው ያሞገሱት ሰዎች በጥቂት ቀናት ውስጥ ሙገሳቸውን "ስቀሉት!" (ማቴ. 27፡22) ወደሚለው የጥላቻ ጩኸት ለወጡት።

ሁለተኛው ሁነት የሚከናወነው፥ በርሱ የጊዜ ሠሌዳ ወቅት መሆኑን እግዚአብሔር ለዳንኤል እንዲህ በማለት ነግሮታል፥ "የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ፥ ፍጻሜውም በጎርፍ ይሆናል" (ዳን. 9፡26)። "የሚመጣውም አለቃ" የሚለው ቃል፥ ቀጥሎ ባለው ቁጥር በዝርዝር የተገለጠውንና በመጨረሻ የሚነሣውን ክፉ ገዥ ያመለክታል። ይህ መሪ የሚወጣበት የመጨረሻ መንግሥት፥ ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን ያፈራርሳል። የኢየሱስ ተቃዋሚዎች በመሢሐቸው ሞት ካላገጡ ከአርባ ዓመት ባነሰ ጊዜ ይህ አስከፊ ሁኔታ ደርሷል። በ70 እአአ ሮማውያን የኢየሩሳሌምን ቅጥር

አፍርሰው ከተማይቱን በዘበዙ። ትንቢቱ በኢየሩሳሌም ከተማና መቅደስ እንደገና የመታነጽ ታሪክ ሲጀምር፥ ፍጻሜው ደግሞ በከተማዋና በመቅደሷ መውደም ተፈጸመ።

ዳንኤል በዚህ የጊዜ ክፍተት የሚከናወኑ ሦስተኛ ነገሮችን ሲገልጥ፥ "እስከ መጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል፥ ጥፋትም ተቀጥሮአል" ብሏል (ዳን. 9፡26)። በቀረው ጊዜ አይሁዳውያን ስደት፥ ችግርና ሥቃይ ይደርስባቸዋል። ይህ ሁኔታ ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት አይሁዳውያን ያለፉበት ሥቃይ፥ እንዲሁም ስደት አሳዛኝና ትክክለኛ ምስል ነው።

ነቢዩ የጊዜ መቁጠሪያውን ዳንኤል 9፡27 ላይ ያቆምና በዛው ክፍል ሁለተኛውን ክንውን መግለጥ ይጀምራል። የመጨረሻው የሰባቱ ዓመት ጊዜ የሚጀምረው፥ በሌላ ግልጥ ክንውን ማለት "እርሱም ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባዔ ያደርጋል" (ዳን.9፡27) በሚለው ነው። "እርሱም" የሚለው ቃል "የሚመጣውም አለቃ" (ቁ. 26) ተብሎ ከኋላ የተገለጠውን ሰው ነው የሚያመለክተው።

ሮማውያን ኢየሩሳሌምን አፈራርሰዋታል። "የሚመጣው አለቃ" የሚወጣውም ከእነርሱ ነው። በአንድ ወቅት በሮማውያን ሰፊ ግዛቶች ከነበሩት ክልሎች አንድ ሰው ዓለምን ለመግዛት ይነሣል። ሰውዬው ለሰባት ዓመት የሚቆይ አንድ ስምምነት ከእስራኤል ጋር ያደርጋል። የዚህ ስምምነት መነሻ ዕለት፥ የመጨረሻው የሰባት ዓመት ጊዜ የሚጀምርበት ነው።

ከእስራኤል ጋር የሚደረጉት ስምምነቶች ዝርዝር ወደ ፊት ባለው ምዕራፍ የሚታይ ይሆናል። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር፥ ይህ ስምምነት ከመፈረሙ በፊት እስራኤል በምድሯ ላይ በመንግሥትነት መመሥረት ያለባት መሆኑ ነው። እስራኤል እንደ መንግሥት በምድሯ ከሌለች፥ ይህ ገዥ ቃል ኪዳን ወይም ስምምነት ሊያደርግ አይችልም። የሰባቱ ዓመት የመጨረሻ ጊዜ ከመጀመሩ በፊት፥ እስራኤላውያን ቢያንስ በግማሽ ወደ ምድራቸው መመለስ አለባቸው።

## የመጨረሻው የኢየሱስ ስብከት

ዳንኤል ትንቢቱን በተናገረ በሰባት ምዕተ ዓመታት ገደማና ትንቢቱ በተነገረለት ዕለት ኢየሱስ በአህያ ውርንጭላ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ። በተከታዮቹ ዕለታት ሃይማኖት መሪዎችን ስለ ኃጢአታቸውና ስለ ግብዝነታቸው ተቃወማቸው። በቅርቡ የሚሞት መሆኑን በመግለጥም ደቀ

መዛሙርቱን ግራ አጋባቸው። ኢየሱስ የመጣው በመጀመሪያ ዓለምን ለማዳን እንጂ፥ ገዢ ለመሆን አለመሆኑን ሲነግራቸው፥ ገለጣው ሙሉ በሙሉ አልገባቸውም ነበር። በጊዜው ለኢየሱስ መንግሥት ጓግተው ተደስቱ እንጂ፥ የመስቀሉን ሥራ አስፈላጊነት አልተገነዘቡም ነበር።

የመስቀያው ዋዜማ በነበረው የመጨረሻ ሳምንት ደቀ መዛሙርቱን እያስከተለ በኢየሩሳሌምና በቢታንያ መካከል ይዘዋወር ነበር። ምሽቶቹንም ያሳልፍ የነበረው እዚያው ነው። ደቀ መዛሙርቱ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ እየወጡ በታላቁ ሄሮድስ የታነጸውን ውብ ቤተ መቅደስ ቁልቁል ይመለከቱ ነበር። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ "እውነት እውነት እላችኋለሁ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም"(ማቴ. 24፡2) ስላላቸው ደነገጡ። ይህ የሚሆነው ግን እንዴት ነበር? የኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በድል መግባት የአሕዛብ ዘመን ማብቂያና የመሢሑ መንግሥት ዘመን መጀመሪያ ምልክት አልነበረምን?

ደቀ መዛሙርቱ ማብራሪያ በመፈለግ ቆም አሉ። በተለይ ለሁለት ጥያቄዎች መልስ ፈልገዋል። የመጀመሪያው ጥያቄ "ይህ መቼ ይሆናል?" (ማቴ. 24፡3) የሚል ነው። የኢየሩሳሌምን የመፍረሻ ጊዜ እና የወደፊት ክብሯን ለማወቅ ነው የፈለጉት። እነዚህ ነገሮች መቼ እንደሚፈጸሙ ለማወቅ ጓጉ። ሁለተኛው ጥያቄያቸው "የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክትስ ምንድነው?" (ማቴ. 24፡3) የሚል ነበር። ለዚህ ጥያቄ መነሻ ምክንያት የደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ መንግሥቱን ለመመሥረት መምጫው በሚቃረብበት ጊዜ የሚከሠቱትን ሁኔታዎች አውቀው ለመጠባበቅ መፈለግ ነበር።

ኢየሱስ እነዚህን በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱ ሁለት ጥያቄዎች እንደመለሰ አምናለሁ። በትክክለኛው አይሁዳዊ ዘይቤ፥ በተቃርኖ በመናገር የመለሰላቸው እንዲህ ነው። በ24፡ 4-31 ለቀረበለት ሁለተኛ ጥያቄ "የመምጣትህ ...ምልክትስ ምንድነው?" ጌታ "የሰው ልጅ ... በሰማይ ደመና ሲመጣ" በማለት መልሷል።

ቀጥሎም በ24፡32-51 "ይህ መቼ ይሆናል?" ለሚለው ጥያቄ ነበር መልስ የሰጠው። መልሱ ጠቅለል ያለ አሳብን ያዘለ ነበር፥ "ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደቀረበ እወቁ" (24፡33)። በዓለም የሚከናወኑ ነገሮችን ልብ ብሎ ማጤኑ፥ ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን የመመለሻ ጊዜ እንዲገምቱ ይረዳቸዋል። ይሁን እንጂ፥ ትክክለኛውን ጊዜ ሊያውቁ እንደማይችሉ በማስገንዘብ፥ "ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ" (25፡13፥36፥42፥44) ብሏቸዋል።

ኢየሱስ መንግሥቱን ለመመሥረት መምጫው መቃረቡን የሚጠቁሙ ሁኔታዎችንና ምልክቶችን ለደቀ መዛሙርቱ ባሳወቀ ጊዜ፥ ከመምጣቱ በፊት ስለሚከሠተው የመከራ ጊዜም ገለጠላቸው። ይህ ጊዜ የሚጀምረው፥ ቤተ መቅደሱ ውስጥ አንድ ሐውልት ከመታነጹ ጋር ነው። ኢየሱስ "እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፤ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ" (ማቴ. 24፥15-16) ብሏል። ወደኋላ መለስ ብሎ ዳንኤል ምዕራፍ 9 ውስጥ የተነገረውን ትንቢት ነበር ለደቀ መዛሙርቱ የሚያስታውሳቸው። የሚነግሠው ገዥ የሰባት ዓመት ስምምነት እንደሚያደርግ ዳንኤል ጽፏል። ነገር ግን በስምምነቱ መካከል ውሉን አፍርሶ "መሥዋዕትና ቁርባን ማቅረብን ይከለክላል፤ በቤተ መቅደሱም ማዕከላዊ ስፍራ ላይ አስጸያፊ የሆነ የጥፋት ርኩሰት እንዲቆምበት ያደርጋል" (ዳን. 9፥27 1980 ዓ.ም እትም)።

ኢየሱስ ሊፈጸሙ ያላቸውን ነገሮች ለደቀ መዛሙርቱ በመግለጥ ላይ እያለ የዳንኤልን ትንቢት አስታወሳቸው። ያ ትንቢት ወደፊት የሚፈጸም ነበር። ሁለት ነገሮችን ነው ይሆናሉ ያለው። መጀመሪያ የተናገረው፥ ቤተ መቅደሱ (ቀደም ሲል ስለ መፍረሱ የተናገረው)፥ እንደገና የሚታነጽ መሆኑን ነው። "በቤተ መቅደሱ ማዕከላዊ ስፍራ ላይ አስጸያፊ የሆነ የጥፋት ርኩሰት እንዲቆም" ቤተ መቅደሱ መታነጽ አለበት። በሁለተኛ ደረጃ ያረጋገጠው፥ ይህ ሁኔታ በሚከናወንበት ጊዜ፥ አይሁዳውያን እስራኤል ምድር ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸውን ነው። በጊዜው እዚያ መኖር አለባቸው፤ ምክንያቱም "በይሁዳ ያሉ" የጥፋቱ ርኩሰት ሲሠራ ለድነታቸው ይሸሹ ዘንድ ኢየሱስ አስጠንቅቋቸዋል።

## የመጀመሪያዎቹ ደረጃዎች

እስራኤል በእግዚአብሔር ተስፋ የተገባላትን በረከት አንድ ቀን ታገኛለች። አይሁዳውያን ወደ አገራቸው በመመለስ ምድራችን ብለው ይጠሯታል። መመለሳቸው በአካል ብቻ ሳይሆን፥ በመንፈስም ይሆናል። ወደ ምድራቸው በመመለስ ኢየሱስን እንደ መሢሐቸው ያውቁታል፥ ለኃጢአታቸውም ይቅርታን ያገኛሉ። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያም ይሆናሉ። ይህ ጊዜ ሕዝቅኤል ባየው ሸለቆ ውስጥ የነበሩ ደረቅ አጥንቶች ሕይወት የሚዘሩበት ይሆናል። ዳንኤል ስለ እስራኤል የተናገረው የጊዜ ሠሌዳ የሚፈጸመውም ያኔ ነው።

እነዚህ ተስፋዎች ዛሬ በእስራኤል በመፈጸም ላይ አይደሉም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለዘመኑ መጨረሻ የወሰናቸው ሆነው በምድሪቱ

አሉ። የመጨረሻው የሰባት ዓመት የእግዚአብሔር የጊዜ ሠሌዳ ከመጀመሩ በፊት፥ እስራኤላውያን ቢያንስ ከፊሉ ወደ ምድራቸው መመለስ አለባቸው። ከዚያም ወደፊት ከሚመጣው የመከራ ዘመን ሰው ጋር ቃል ኪዳን ያደርጋሉ። ይህ ሰው በሰባቱ ዓመት የስምምነት ውል አጋማሽ፥ ስምምነቱን ይሽርና ጀርባውን ይሰጣቸዋል።

የእስራኤላውያን በ1948 እአአ ወደ ምድራቸው መመለስ፥ ለመጨረሻው የእግዚአብሔር ትንቢታዊ ክንውን መድረኩን አዘጋጅቷል። ወደ ምድሪቱ የመመለሳቸው ሂደት በከፊል ተጀምሯል፥ የመጨረሻው ዘመን የሚጀምርበት ሁኔታ ሁሉ ተመቻችቷል። የሕዝቡ ወደ ምድሪቱ መመለስ መጨረሻ ሂደት ግን፥ መሢሑ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት ወደ ምድር እስኪመጣ አይከናወንም። ያኔ ነው እስራኤል አጥብቃ የምትሻው የመጨረሻ ሠላምና ጸጥታ ሊኖር የሚችለው። ብዙዎች ግን የጸና ሠላም በሚለው አሳሳች አሳብ ላይ በመመሥረት ሠላም ለማምጣት መጣራቸውን አላቋረጡም።

> ምዕራፍ አራት <

# ሠላም የሚጠይቀው ዋጋ

እስራኤል በመንግሥትነት የተወለደችው ግንቦት 14 ቀን 1948 እእአ አርብ ዕለት ነው። የመወለዷ ሁኔታ ግን ችግር አልባ አልነበረም፤ የአይሁዳውያን መንግሥትን መወለድ የሚቃወሙ ሰባት መንግሥታት በዙሪያዋ ነበሩ። የእስራኤል መንግሥት ከተመሠረተበት ዕለት አንሥቶ አገሪቱ (ከግብፅ በስተቀር) ሕልውናዋን ከሚቃወሙ አብዛኛዎቹ የዓረብ አገሮች ጋር በጦርነት ላይ ናት።

በእስራኤል መንግሥትነት ዋዜማ፥ መሪዎቿ ከጠላቶቿ ጋር ሠላም ለመመሥረት ያልተሳካ ጥረት አደረጉ። እጅግ ብርቱ የነበሩትና ኋላም የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት ሚስ ጎልዳ ሜኢር፥ ወደ አማንና ዮርዳኖስ ምስጢራዊ ጉዞ አድርገው ነበር። በዓረባዊ ልብስ ሆነውና ፊታቸው ተሸፍኖ እስራኤልና ዮርዳኖስ በሠላም የሚኖሩበትን መላ ለመሻት ከአገሪቱ ንጉሥ አብዱላህ ጋር ተነጋገሩ። ሁለቱም ሠላም ለማምጣት ፈልገው ነበር፤ ነገር ግን ንጉሡ እራሳቸውም ብዙዎቹን ዓረቦች ወደተጠናወታቸው የጦርነት አስተሳሰብ ወጥመድ ስለገቡ፥ ጥረቱ አልተሳካም። ሚስ ጎልዳ ሜኢር ከንጉሡ የሰሙትን የመጨረሻ አሳዛኝ ቃል ያስታውሱታል። እንዲህ የሚል ነበር፥ "እዝናለሁ! ደም መፋሰስና ጥፋትን አወግዛለሁ። እንደገና እንደምንገናኝና ወዳጅነታችንም እንደማይሻክር ተስፋ እናድርግ"። ይሁን እንጂ ዳግመኛ አልተያዩም።

## መጀመሪያ ባይሳካልዎ

በእስራኤልና በዓረቦች መካከል ሠላም እንዲኖር በመጣር ረገድ ሚስ ጎልዳ ሜኢር የመጀመሪያዋ ይሆኑ ይሆናል፤ የመጨረሻዋ ግን አልነበሩም። የመንግሥታት መሪዎች በመካከለኛው ምሥራቅ ሠላም ለማስፈን አያሌ ዕቅዶችንና አሳቦችን ቢያቀርቡም፥ አንዳቸውም ሙሉ በሙሉ አልተሳካላቸውም። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ሄንሪ ኪሲንጀር፥ በ1973 እእአ ዮም ኪፐር በተባለው በዓል ቀን ከተደረገው ጦርነት በኋላ ያልተቋረጠ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አድርገዋል። በእስራኤልና በግብፅ መካከል የጦርነት ማቆም ስምምነት እንዲደረግ ቢጥሩም፥ ለመካከለኛው ምሥራቅ ዘላቂ ሠላም አላመጡም።

የግብፁ ፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳት ከእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚናሂን ቤጊን ጋር ፊት ለፊት ተገናኝተው ለመነጋገር፥ በ1977 እእአ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረጉት ታሪካዊ ጉዞ፥ ለመካከለኛው ምሥራቅ የመጨረሻና ዘላቂ ሠላም ያስገኛል የሚል ተስፋ ፈጥሮ ነበር። በሚቀጥለው ዓመት ሁለቱ

ሰዎች አሜሪካ ውስጥ፥ ካምፕ ዴቪድ በተባለው ስፍራ ከአገሪቱ ፕሬዝዳንት ከጂሚ ካርተር ጋር ለአሥራ ሦስት ቀን ተነጋግረው የመስከረም 17 ቀን 1978 እአአ የሠላም ስምምነት አስገኙ። መጋቢት 25 ቀን 1979 እአአ ስምምነቱን አጸደቁና እስራኤል እንደ መንግሥት ሕልውና ያላት መሆኗን በማወቅ ረገድ ግብፅ የመጀመሪያይቱ ዓረባዊት አገር ሆነች። ሌሎቹ የዓረብ አገሮች ግን የግብፅን ውሳኔ እንከተልም አሉ። ከዚያ ይልቅ ግብፅን አገለሏት፤ አንዋር ሳዳትም በሰው ተገደሉ።

የ1991 እአአ የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት የሠላሙን ሂደት እንደገና አንቀሳቀሰው። ኢራቅ ድል ከሆነች በኋላ የአሜሪካኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፥ ጀምስ ቤከር በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አራት የተለያዩ ጉዞዎች አደረጉ። ረጅሙ የሠላም ጥረታቸው፥ እስራኤል እንደ መንግሥት ከተመሠረተች ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ በርሷና ጎረቤቶቿ በሆኑ ዓረቦች መካከል ፊት ለፊት ንግግር እንዲደረግ አስቻለ። ሌሎቹ ሁሉ ያልሆነላቸው ለአሜሪካ ይሳካላት ይሆን? ወይስ እነዚህ ውይይቶች ሊፈታ የማይቻለውን ግጭት ለመፍታት የሚደረጉ ሌላ ጥረቶች ናቸው?

*ሠላም መሰል ወቅት*

ዓለም፥ በተለይም መካከለኛው ምሥራቅ፥ ጊዜያዊ ሠላም የሚሰፍንበት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይተነብያል። ይህም የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዘመን ክንውን መግቢያ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ተሰሎንቄ ከተማ ውስጥ ለነበረች አንዲት አዲስ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ደብዳቤዎች ጻፈ። በሁለቱም ደብዳቤዎቹ እነዚያ አማኞችና ሌላው ዓለም ወደፊት ስለሚጠብቃቸው ነገር ገለጠ። 1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 5 ውስጥ፥ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዘመን ፍርድ የሚመጣበትን ሁኔታ ሲያስገነዝብ እንዲህ ብሏል፥ "የጌታ ቀን ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና፤ ሠላምና ድኅነት ነው ሲሉ፥ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል፥ ከቶም አያመልጡም" (1ኛ ተሰ. 5፡2-3)።

የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዘመን ፍርድ ዓለም ባላሰበው ጊዜ የሚመጣ መሆኑን ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ገለጠላቸው። የዓለም ሕዝብ በሐሰተኛ ሠላም ተዘናግቶ በሚዝናናበት ጊዜ የእግዚአብሔር የመከራ መዓት፥ እንደ ማዕበል ይመጣበታል። በጊዜው የሚደረጉት የሠላም አዋጆች የፍርድ መቃረቢያዎች ናቸው።

ዛሬ እስራኤል ውስጥ እንደ ሠላም የሚቆጠር ነገር ቢኖር፥ ጦርነት ወይም ሽብር አለመኖሩ ነው። ከኀምሳ ዓመታትና ከአምስት ዋና ዋና ጦርነቶች በኋላ አገሪቱ አልተዘናጋችም፥ ጥበቃዋንም አላላላችም። ይህን ጉዳይ እንድገነዘብ የረዱኝ፥ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የተመለከትኳቸው ሁለት የሕይወት ትዕይንቶች ናቸው። የመጀመሪያው ትርዒት፥ ዮርዳኖስ አማን ውስጥ አንድ መደብር ውስጥ የተመለከትኩት ነው። መደብሩ ውስጥ የዕንቁ ሣጥኖችን በመመልከት ላይ ሳለሁ፥ ራቅ ባለ ግድግዳ ላይ በከፊል የተሸሸገ ካርታ ተመለከትኩ። ጠጋ ብዬ በዓረብኛና በእንግሊዝኛ የተጻፈበት የመካከለኛው ምሥራቅ ካርታ መሆኑን ተረዳሁ። ካርታው እስራኤልን በጥቁር ቀለም ቢያመለክትም፥ እስራኤል የሚል ቃል የለበትም። በዚያ ፈንታ "የተያዘ የዓረብ ግዛት" የሚል ቃል በጥቁሩ ቀለም ላይ ጎልቶ ይታያል።

ሁለተኛው ትርዒት የገጠመኝ፥ ቴልአቪቭ ውስጥ ቤን ጎሪዮን አይሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ነው። አንድ ዓረባዊ በጸጥታ መቆጣጠሪያው በር ለማለፍ ከፊቴ ተሰልፎ ነበር። ፈታሹ የጸጥታ ተቆጣጣሪ የሰውዬውን ሻንጣ ከፈተና፥ ውስጡ የነበረውን ዕቃ ጠርጴዛ ላይ ዘረገፈው። እያንዳንዱን ልብስ በሚገባ ከፈተሸ በኋላም አንድ ላይ ከመረው። በዚህም አላበቃ፤ ራጅ በሚባል መሣሪያ ለመመርመር ሻንጣውን ይዞት ሄደ። ከዚህ በኋላ ነው መከረኛው መንገደኛ ዕቃዎቹን እየሰበሰበ ሻንጣው ውስጥ መክተት የጀመረው። በእስራኤላውያንና በዓረባውያን መካከል ያለው ጥላቻና አለመተማመን ይህን ይመስላል።

እስራኤል በጣም የተለየ ሁኔታ የሚገጥማት መሆኑን ነቢዩ ሕዝቅኤል ገልጧል። እስራኤል "ከሰይፍ የተመለሰች ምድር" ተብላ የምትጠራበትንና፥ ሕዝቧም "ከብዙ ሕዝብ ውስጥ ተሰብስቦ. . . ሳይፈራ የሚቀመጥበትን" ጊዜ ነቢዩ ተመለከተ (ሕዝ. 38፡8)። ሕዝቅኤል ከዚህ ምዕራፍ ጥቂት ቁጥሮች በኋላ የሠላሙን ጊዜ ምስል ያመለክታል። በዚያ ምንባብ "ቅጥር የሌላቸው መንደሮች. . . ተዘልለው የሚኖሩ. . . ሳይፈሩ ያለቅጥርና ያለመወርወሪያ ያለመዝጊያም የሚኖሩ" (38፡11)፥ በማለት ሕዝቡን ይገልጣቸዋል። ይህ የሠላም ወቅት፥ ተዘናግታ በተቀመጠችው እስራኤል ላይ መንግሥታት በቡድን ሆነው በድንገት ወረራ በሚሰነዝሩባት ጊዜ ያከትማል።

በሕዝቅኤል የተገለጠው ራእይ እስከዛሬ በታሪክ አልተፈጸመም። ታዲያ መቼ ነው ለእስራኤል እውን የሚሆነው? የትንቢቱን ፍጻሜ ጊዜ አጥብበን የምንመለከትበትን ፍንጭ ሕዝቅኤል ይሰጠናል። በመጀመሪያ ሕዝቡ ወደ ምድሩ ተመልሶ በሠላም ስለመኖሩ ይገልጣል። ቀጥሎ ደግሞ፥

በትንቢቱ የዘረዘራቸው ነገሮች አይሁዳውያን ተጠቃለው ወደ ምድራቸው ከመመለሳቸው በፊት በአንድ ወቅት እንደሚከናወኑ ያስረዳል። የሚከሸፈው ወረራ አንዱ ውጤት የአይሁዳውያን ተጠቃለው ወደ እስራኤል መመለስ ይሆናል። ሕዝቅኤል በእስራኤል ላይ የሚመጡባትን ወራሪዎች እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያጠፋቸው ከገለጠ በኋላ፥ እርሱ ራሱ ይህን ድል አይሁዳውያንን ሁሉ ወደ ምድራቸው ለመመለሻነት የሚጠቀምበት መሆኑን እንደተናገረ ሲገልጥ፥ "አሁን የያዕቆብን ምርኮ እመልሳለሁ፥ ለእስራኤልም ቤት ሁሉ እራራለሁ፥ ስለ ቅዱስ ስሜም እቀናለሁ" (39፡25) ብሏል።

ሁለተኛ፥ ሕዝቅኤል እንደሚያስገነዝበው፥ በእነዚህ ምዕራፎች የተገለጠውና የወረራው አንድ ውጤት፥ የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ወደማወቅ የሚመለስ መሆኑ ነው፥ "ከእንግዲህ ወዲያ፥ የእስራኤል ቤት እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው እንደሆንሁ ያውቃሉ" (39፡22)። እስራኤል ወደ አምላኳ ስትመለስ፥ እርሱ ደግሞ በሕዝቡ ላይ መንፈስ ቅዱሱን ያፈስሳል። "ፊቴንም ከእነርሱ ከእንግዲህ ወዲህ አልሸሽግም፤ መንፈሴን በእስራኤል ቤት ላይ አፍስሻለሁና፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር" (39፡29)። ሕዝቅኤል 36-37 ውስጥ (ምዕራፍ 3 ውስጥ ተነጋግረንበታል)፥ እግዚአብሔር መንፈሱን በሕዝቡ ላይ እንደሚያፈስና ሁሉን ወደምድራቸው እንደሚመልሳቸው ገልጧል። ይህ የሚሆነው፥ እግዚአብሔር መንግሥቱን በምድር ላይ በሚመሠርትበት ጊዜ ነው። ከሕዝቅኤል 38-39 ባለው ክፍል የተገለጡት ሁነቶች ከላይ ከተገለጠው ክንውን መቅደም አለባቸው።

ታዲያ ሕዝቅኤል 38-39 ውስጥ የተጠቀሱት ሁነቶች የሚከናወኑት መቼ ነው? አይሁዳውያን ወደ ምድራቸው በመመለስ የእስራኤልን መንግሥት ከመሠረቱ በኋላ፥ እንዲሁም ሠላምና ጸጥታ ያላቸው በሚመስላቸው ጊዜ ነው። ሁነቶቹ የሚከናወኑት ግን፥ እስራኤል በአካልና በመንፈስ ሙሉ በሙሉ ከመመለሷ በፊት ይሆናል። እንደውም በእነዚህ ምዕራፎች የተገለጡት ሁነቶች ናቸው አይሁዳውያን አምላካቸውን በቅርብ እንዲያውቁት፥ እርሱም ለመጨረሻ ጊዜ ሕዝቡን ሙሉ በሙሉ ወደ ምድሩ እንዲመልስ የሚያደርጉት። ለእነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሚሆነው ወቅት፥ ዳንኤል 9፡27 ውስጥ የተጠቀሰውና፥ ከመጨረሻው ሰባት ዓመት ውስጥ የመጀመሪያ ሦስት ዓመት ተኩል ነው።

በሠላም የምትኖረው እስራኤልን አስመልክቶ ሕዝቅኤል የሚቀርፀው ምስል ዛሬ እሩቅ ይመስላል። ታዲያ ሕዝቡ ይህን የመሰለ ሠላም ያለው ሆኖ ከሚሰማው ደረጃ የሚደርሰው እንዴት ነው? መልስ የሚመስል ቃል ዳንኤል 9፡27 ውስጥ እንዲህ ተጽፏል፥ "እርሱም ከብዙ

ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባዔ ያደርጋል፤ በሱባዔውም እኩሌታ መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል"።

እስራኤል መንግሥቷን ለመመሥረት ከምትጠብቅባቸው 480 ዓመታት ውስጥ የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት የሚጀምሩት፥ በቃል ኪዳኑ ስምምነት ነው። ቁጥር 27 ውስጥ "እርሱ" የሚለው ቃል፥ ቁጥር 26 ውስጥ የተጠቀሰውን "የሚመጣውም አለቃ" የሚለውን ያመለክታል። ሮማውያን በ70 እአአ ኢየሩሳሌምን አፈራረሷት። እነዚህ ወራሪዎች "የሚመጣው አለቃ ሕዝብ" ነበሩ። ስለዚህ ወደፊት "የሚመጣው አለቃ" ከዋናው የሮም ግዛት የሚመጣ መሆን አለበት።

ይህ መሪ ከእስራኤል ጋር የሰባት ዓመት "ቃል ኪዳን" ወይም ስምምነት ያደርጋል። ከስምምነቱ አንዱ ክፍል፥ እስራኤል ቤተ መቅደሷን እንድታንጽና እንስሳት የማቅረብ መሥዋዕቷን እንድትቀጥል የሚፈቅድ ይሆናል። ቃል ኪዳኑ ከዚህም ሌላ ለእስራኤል ሕዝብ ድነትና ከለላ የሚሰጥ መሆን አለበት። በዚህ ስምምነት መሠረት፥ እስራኤል በመጨረሻ የተከበረ ድንበርና ዘለቄታ ያለው ሠላም ያገኘች ትመስላለች። የሚመጣው መሪ፥ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ማለት ሄንሪ ኪሲንጀር፥ ጂሚ ካርተር፥ እና ጀምስ ቤከር ያልተሳካላቸውን ተግባር ያከናውናል። ለኖቤል ሽልማትም ሳይታጭ አይቀርም። እርሱ ነው የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚሆነው!

እስራኤል የመካከለኛው ምሥራቅ ክቡር ሀብት የሆነውን ሠላም ትናፍቃለች። የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት በ1991 እአአ እስከተቀሰቀሰ ድረስ እስራኤል ነጻነቷን ለመጠበቅ በራሷ ብቃትና ወታደራዊ ኃይል ትመካ ነበር። የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት ለመጀመሪያ ጊዜ የርሷን ጦርነት ሌሎች ይዋጉላት ዘንድ፥ እንድትፈቅድ ያደረጋት መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም። ፓትሪዮት የተባሉ ተወንጫፊ መሣሪያዎችን የተኮሱላት የአሜሪካ ወታደሮች ነበሩ። ባግዳድን በቦምብ ይደበድቡና የተወንጫፊ መሣሪያዎች መተኮሻ ስፍራዎችን ያድኑ የነበሩ አይሮፕላኖች የመጡት፥ ከአሜሪካንና ከአጋሮቿ እንጂ፥ ከራሷ ከእስራኤል አልነበረም። እስራኤልን ከጥቃት ለመከላከል ሌሎች አገሮች ተዋጉ።

በአሜሪካን መንግሥት አማካይነት የተጀመረው የሠላም ንግግር በእስራኤልና ጎረቤቶቿ በሆኑት ዓረቦች መካከል ዘላቂ ሠላም ያመጣ ይሆን? ሲ.ቢ. ኤስ ለተባለው የዜና ድርጅት የመካከለኛው ምሥራቅ ጋዜጠኛ የሆነው ዴቪድ ዶላን በእስራኤልና በዓረቦች መካከል ያለው ግጭት የቅርብ ተመልካች ነው። ይህ ሰው፥ "በዓረቦችና በእስራኤላውያን መካከል ላለው የከረረ ግጭት ሰው-ሰራሽ ሠላም ሊፈጠር እንደማይችል ወዳጅም ሆነ ጠላት ሊቀበለው መዘጋጀት አለበት። ግጭቱን ከየአቅጣጫው ለአሥር

ዓመት ያህል በየዕለቱ ካጠናሁ በኋላ፥ የደረስኩበት መሠረታዊ ድምዳሜ ይህ ነው”፥ በማለት ስለ ጉዳዩ ያለው ተስፋ የመነመነ መሆኑን ገልጧል።

እስራኤልና ዓረቦች እርስ በራሳቸው ስለማይተማመኑ፥ በፈቃዳቸው ወደመስማማት አይደርሱም። እስራኤልና ጎረቤቶቿ ዓረቦች የሠላሙን ስምምነት ቢተገብሩት እንኳ፥ አሁን መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ላለው ግጭት “የመጨረሻ መፍትሔ” እና ለእስራኤል የሠላም “ዋስትና” ሊያስገኝላት የሚፈቅድ የውጭ ኃይል ይኖራል? ከእስራኤል ጋር የሚደረገው “ቃል ኪዳን” ምን እንደሚመስል ዳንኤል 9፡27 ውስጥ በግልጥ አልተጠቀሰም። ስምምነቱን የሚያደርጉት ወገኖች፥ ሙሉ ሰባት ዓመት እንዲቆይ የሚሹ መሆናቸውን ግን ምንባቡ በግልጥ ያመለክታል። እስራኤላውያን ወደ ምድራቸው ከተመለሱ ወዲህ ሠላምና ድኅነት የሚሰማቸው በዚህ ሰባት ዓመት መጀመሪያ ክፍል ነው። በዓለም አቀፍ ሰላም አስከባሪ ኃይል አማካይነት በእስራኤልና በዓረብ ጎረቤቶቿ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል የታለመው የሰባት ዓመት የሰላም ስምምነት፥ ለድንበሮቿ መከበር ዋስትና ይሆን ይሆን? ይህ ነው ወደፊት የሚሆን የሚመስል አንድ ነገር።

## *ሠላም የሚመጣው መቼ ነው?*

ዓለም ሠላምን ትናፍቃለች። ታዲያ በእግዚአብሔር ተስፋ የተሰጠው ሠላም የሚመጣው በእርግጥ መቼ ነው? ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ለዚህ ጉዳይ እግዚአብሔር የሚሰጠውን መልስ ይነግሩናል። የትንቢተ ኢሳይያስ የመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለት ምዕራፎች ግን እጅግ አሳማኙን ቃል ይገልጣሉ። በመጀመሪያዎቹ አምስት ምዕራፎች ኢሳይያስ ይሁዳን በምስክርነት በመጥራት ራሱን እንደ እግዚአብሔር ጠበቃ ቆጥሮ ይቆማል። እግዚአብሔር ደግሞ ምዕራፍ አንድ ውስጥ እንደተጠቀሰው፥ በእስራኤል ላይ ሦስት ግልጥ ክሶች ያቀርባል። የሕዝቡ ዋና ኃጢአት፥ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ሲሆን፥ እንዲህ ይነበባል፥ “ልጆች ወለድሁ አሳደግሁም፤ እነርሱም ዓመፁብኝ” (ኢሳ. 1፡2)። ሕዝቡ ግን ትምህርቱን ሳይቀበሉ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ በመምሰል በግብዝነት ይመላለሳሉ። በመሆኑም እግዚአብሔር እንዲህ ይላቸዋል “እጃችሁን ወደ እኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ፥ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም። እጆቻችሁ ደም ተሞልተዋል” (ኢሳ. 1፡15)። የሕዝቡ ዓመፅ ከዚህም ሌላ ወገኖቻቸውን በመበደል እና ፍርድን በማጣመም የተገለጠ መሆኑ እንዲህ ተጠቅሷል፥ “አለቆችሽ ዓመፀኞችና የሌቦች ባልንጀሮች ሆኑ። ሁሉ ጉቦ ይወዳሉ ዋጋም ለማግኘት ይሮጣሉ። ለድሀ አደጉ አይፈርዱም፤ የመበለቲቱም ሙግት ወደ እነርሱ አይደርስም” (ኢሳ. 1፡23)።

እግዚአብሔር ሕዝቡን በማንኛውም ሁኔታ እንደበደለኛ ቆጠረ። የእርሱ ዓላማ ግን ለዚህ ሁሉ ቅጣት ሳይሆን፥ ፈውስ ነበር። ሕዝቡን በርኅራኄ ወደራሱ ለመመለስ እንዲህ ይላቸዋል፥ "ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፥ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች (ኢሳ. 1፡18)። ኢሳይያስ እግዚአብሔር እስራኤልን ወደዚህ ይቅርታና በረከት የሚያመጣበትን ጊዜ ምዕራፍ ሁለት ውስጥ፥ "በመጨረሻው ዘመን" ብሎ ካመለከተ በኋላ፥ ያኔ በዓለም ሁሉ በረከቱን እንደሚያወርድ ሲገልጥ፥ "በአሕዛብም መካከል ይፈርዳል፥ በብዙ አሕዛብም ላይ ይበይናል፤ ሰይፋቸውንም ማረሻ፥ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ፤ ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፥ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም" ብሏል (ኢሳ. 2፡4)።

የተባበሩት የዓለም መንግሥታት ኒውዮርክ በሚገኘው ድርጅታቸው ሕንጻ ላይ የኢሳይያስን ቃል አስፍረዋል። ይሁን እንጂ፥ ዓለም እስከ ዛሬ ድረስ ያላት ብዙ ሰይፍ እና ጥቂት ማረሻ ነው! መቼ ነው እግዚአብሔር የጦርነት ሥጋት ለተጋረጠባት ዓለም ሠላም የሚያመጣላት? ያ ሠላም የሚመጣው፥ ከአንድ ሕፃን መወለድ ጋር እንደሚሆን ኢሳይያስ መዝግቧል። ነቢዩ ከምዕራፍ 7-12 ባለው ክፍል ሠላም የሚያመጣ ሕፃን የሚወለድ መሆኑን ተንብዮአል። የሕፃኑ ስም አማኑኤል "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" (ኢሳ. 7፡14) የሚል ነው። ደግሞም "ጻድቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ" (ኢሳ. 9፡6) ይባላል። ይህ ሕፃን እግዚአብሔርም፥ ንጉሥም ነው። "ከዛሬ ጀምሮ እስከዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ፥ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነት ይበዛል፥ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም" (ኢሳ. 9፡7)።

ይህ እግዚአብሔርም፥ ሰውም የሆነ ጌታ፥ በዳዊት ዙፋን ላይ በመንገሥ ለዓለም ሠላም ያመጣል። ኢሳይያስ አራዊት እንኳን አብረው በፍቅር የሚኖሩበትን ይህን የተትረፈረፈ ሠላም ሲገልጥ እንዲህ ብሏል፥ "ተኩላ ከበግ ጠቦት ጋር ይቀመጣል፥ ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል፤ ጥጃና የአንበሳ ደቦል፥ ፍሪዳም በአንድነት ያርፋሉ፤ ታናሽም ልጅ ይመራቸዋል። . . . በተቀደሰው ተራራዬ ላይ ሁሉ አይጎዱም፥ አይጠፉፉምም፥ ውኃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለችና" (ኢሳ. 11፡6-9)።

እውነተኛው የዓለም ሠላም የሚመጣው፥ የሠላም ልዑል መንግሥቱን በምድር ላይ ለመመሥረት ሲመጣ ነው። የቱንም ያህል ቅንነት ቢኖርባቸው፥ ሌሎች ጥረቶች ዘላቂ ሠላም ሊያመጡ አይችሉም።

> ምዕራፍ አምስት <

# ሦስተኛው ቤተ መቅደስ

ኢየሩሳሌም፥ ጥቅምት 8 ቀን 1990 እእአ። ኢራቅ ኩዌትን ከወረረች ስድሳ ስምንት ቀን ነበር። የአሜሪካን መንግሥት በኢራቁ ፕሬዝዳንት ሳዳም ሁሴን ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ሌሎች መንግሥታትን በጥንቃቄ በማስተባበር ላይ ነው። አሜሪካን ሁልጊዜ ዋናይቱ የእስራኤል አጋር በመሆኗ፥ ሌሎች የዓረብ አገሮችን የሚያካትት ኅብረት ለመፍጠር ውይይቱ በጥንቃቄ መካሄድ ነበረበት። ይሁን እንጂ፥ ከአሮጌይቱ ኢየሩሳሌም ደቡብ ምሥራቅ በሚገኘው ስፍራ የሚከናወኑና ለቁጥጥር ያዳገቱ ሁኔታዎች ኅብረቱን እስከ መፈራረስ አድርሰውት ነበር።

የኢየሩሳሌም ከተማ መካከለኛው ምሥራቅን ችግሮች ውስጥ የሚጨምሩ ነገሮች የሚነሣሡባት ከተማ ናት። የግጭትና የቅራኔ ከተማ በመሆን ትታወቃለች። ንጉሥ ዳዊት የቆረቆራት ጥንታዊቷ ኢየሩሳሌም፥ ከአሁኑ የ"አሮጌው ከተማ" የግንብ ቅጥር በስተውጭ ነበረች። የኤል አክሳ መስጊድና ለእስልምና እምነት የተቀደሱት ባለዓለት ጉልላት ሕንጻዎች፥ ታላቁ ሄሮድስ ለኢየሩሳሌሙ ቤተ መቅደስ ማሳነጫ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ባስገነባው ከፍታ ስፍራ ላይ ቆመዋል። ጥንታዊቱን የኢየሩሳሌም ከተማና የቤተ መቅደሱን ክልል ለመግለጫነት ያገለገለው፥ "የጽዮን ተራራ"፥ ዛሬ መጠሪያው ከእነዚህ ቦታዎች ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ስም ሆኗል። ያ ስም ከዳዊት ዘመነ መንግሥት 250 ዓመታት በኋላ በነገሠው ንጉሥ ሕዝቅያስ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ክልል የተጨመረ አንድ ተራራ መጠሪያ ሆኗል።*

ጥቅምት 8 ቀን 1990 እእአ ዋሽንግተን ዲ.ሲ. ውስጥ የነበሩ የመንግሥታት መሪዎች ምን ይፈጠር ይሆን? በሚል ጭንቀት ውስጥ ነበሩ። የዓለም ሕዝብ ዓይኖች ትኩረት፥ ለጊዜው ከኩዌት ወደ ኢየሩሳሌም ተዛወረ። ለጥቂት ጊዜያት አሜሪካን ሁሉን የሚያስተባብር ኅብረት ለመፍጠር ትችል ይሆንን? የሚለው ጥያቄ ብዙዎችን አሳስቧቸው ነበር። አሜሪካን ያስተባበረችውን ኅብረት ወደ መፈራረስ አቅርቦት የነበረ ሌላ ነገር፥ ጥቂት አይሁዳውያን ለመሠረት የሚሆን ድንጋይ ይዘው በመውጣታቸው የተፈጠረው ብጥብጥ ነበር።

---

* ገጽ 67 ላይ ያለውን ካርታ ይመልከቱ።

## የተራራው ላይ እልቂት

"የቤተ መቅደሱ ተራራ ታማኞች" የተሰኘና ጥቂት አይሁዳውያን የተሰባሰቡበት አንድ ቡድን፥ ቀድሞ ቤተ መቅደሱ ወደነበረበት ተራራ፥ አሁን ግን የዓለቱ ጉልላት እና የኤል አቅሳ መስጊድ ወዳለበት ስፍራ ተጓዘ። የቡድኑ ዓላማ ሦስተኛውን የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ለመሥራት የመሠረት ድንጋይ ማኖር ነው። ሰሎሞን የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ ያሳነጸው፥ ሞሬ ተራራ ላይ ነበር። ተራራው አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ለመሠዋት የተጓዘበትና፥ ንጉሥ ዳዊት ከሠራት የኢየሩሳሌም ከተማ ሰሜን የሚገኝ ነው። ባቢሎናውያን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ586 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌምን ባቃጠሏት ጊዜ፥ ሰሎሞን የሠራውን ቤተ መቅደስ አፈረሱት። ከሰባ ዓመት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት የአይሁድ ቅሬቶች ሁለተኛውን ቤተ መቅደስ ሠሩ። ታላቁ ሄሮድስ ይህን ቤተ መቅደስ በሚገባ አሻሽሎት ነበር። ከዚህም የተነሣ፥ ኢየሱስ በምድር በተመላለሰበት ጊዜ ቤተ መቅደሱ ዓይን የሚያርፍበትና የተዋበ ነበር። ሮማውያን በ70 እአአ ኢየሩሳሌምን ባፈራረሷት ጊዜ፥ ሁለተኛውን ቤተ መቅደስ እንደገና አወደሙት። አሁን በስፍራው ያለው፥ ቤተ መቅደሱ አርፎበት የነበረ የመሠረት ፍርስራሽ ብቻ ነው።

አይሁድ ሃይማኖተኞች፥ መሢሑ ዳግም መጥቶ እስራኤልን ሙሉ በሙሉ በምድሯ ላይ በሚመሠርትበት ጊዜ የሚሠራውን ሦስተኛ ቤተ መቅደስ በመጠበቅ ላይ ናቸው። አንዳንዶች መሢሑ እስኪመጣ ድረስ ቤተ መቅደሱ አይሠራም ሲሉ፥ ሌሎቹ ደግሞ አይሁዳውያን ቤተ መቅደሱን ሠርተው እስኪያጠናቅቁ ድረስ መሢሑ አይመጣም ይላሉ። ለዚህ ነው "የቤተ መቅደሱ ተራራ ታማኞች" ቡድን ከሌሎች አይሁዳውያን ጋር በመሆን የቤተ መቅደሱን ሥራ በፍጥነት ለመጀመር የሚፈልገው።

እስራኤል ውስጥ ሮሽ ሀሸና የተባለውና በዕብራውያን አቆጣጠር በ5750 የተጀመረው በዓል መከበር የሚጀምርበት ዕለት ጥቅምት 20 ምሽት ላይ ነበር። ከዘጠኝ ቀናት በኋላ ደግሞ፥ ጥቅምት 29 ቀን ማለት ነው፥ አይሁዳውያን የዓመቱ ቅዱስ ቀን የሆነውንና ዮም ኪፑር የተባለውን የሥርየት በዓል አከበሩ። ከአምስት ቀን በኋላ፥ ኅዳር 4 ቀን ምሽት ቲሺር በተባለው የአይሁዳውያን ወር የሚከበረውን የድንኳን በዓል ማክበር ጀመሩ። ይህ የሰባት ቀን በዓል፥ የመከር ወራት ማብቂያ በዓል ነው። በዓሉ በተጨማሪም እስራኤላውያን ከሙሴ ጋር በምድረ በዳ የነበሩበትን ጊዜ ያስታውሳል። ይህ ጊዜ ገና ወደ ተስፋይቱ ምድር ያልገቡበት ነበር። በዓሉ ወደፊት እስራኤላውያን ምድራቸውን ሙሉ በሙሉ ወደሚወርሱበት

ጊዜም ያመለክታል። "የቤተ መቅደሱ ተራራ ታማኞች" ቡድን ለሦስተኛው ቤተ መቅደስ መሠረት ለማኖር የመረጠው፥ በዚሁ የድንኳን በዓል አማካይ ጊዜ ነበር። ይህ በዓል የእስራኤላውያንን ለመጨረሻ ጊዜ ወደምድራቸው መሰባሰብ ይጠባበቃል።

እንዲህ ያለው ሁኔታ የሚያስከትለውን ችግር የፈሩት የእስራኤል ባለሥልጣናት፥ የሦስተኛው ቤተ መቅደስ ሥራ ቡድን አባላት ለመሠረት የሚሆነውን ድንጋይ ወደ ስፍራው እንዳያጓጉዙ ከለከሏቸው። ይሁን እንጂ እስራኤላውያን የቤተ መቅደሳቸውን የመሠረት ድንጋይ ሊያኖሩና የእስላሞችን ቅዱስ የማምለኪያ ስፍራ ለመድፈር የመምጣታቸው ዜና በዓረቦች ዘንድ ተሰምቷል። በመሆኑም፥ በዜናው የተቆጡ ዓረቦች ቅዱሱን የማምለኪያ ቦታ ከታሰበው አስፈሪ ድርጊት ለመከላከል በስፍራው ተሰበሰቡ። ቅዱሱን የማምለኪያ ስፍራ የሚደፍርባቸውን ማንኛውንም ሰው ለመውገርም ቋጥኝና ድንጋይ ሰበሰቡ። ዓረቦች በዚህ ሁኔታ ከላይ ባለው ከፍተኛ ስፍራ ሲሰባሰቡ፥ ይህን ያልጠረጠሩት እስራኤላውያን ደግሞ፥ በስተምዕራብ ካለው ግድግዳ ፊት ለፊት በሚገኘው አደባባይ ተከማቹ። ይህ ግድግዳ በታላቁ ሄሮድ የተሠራና በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ነው። በታው ለብዙ መቶ ዓመታት ማንኛውም አይሁዳዊ ወደ መቅደሱ የሚመጣበት ቅርቡ ስፍራ ሲሆን፥ ከማንኛውም ስፍራ ይልቅ የተቀደሰም ነው።

የአይሁዳውያን ከታች በሚገኘው አደባባይ ላይ፥ እንዲሁም የዓረቦች በኮረብታው ላይ መሰባሰብ አሥጊ ሁኔታን ፈጠረ። እንዴት እንደተጀመረ የተለያዩ ምክንያቶች ቢሰጡም፥ አንድ ግለሰብ ወይ ሌላ አካል ያነሣሣቸው ዓረቦች ከግርጌያቸው ወደሚገኘው አደባባይ የድንጋይ ናዳ ያወርዱ ጀመር። በዚህ ጊዜ ነበር የአይሁዳውያን አድማ በታኝ ፖሊሶች አካባቢውን ለጥበቃ ያጥለቀለቁት። ዓመፁ ባበቃ ጊዜ፥ አሥራ ሰባት ዓረቦች መሞታቸው ተረጋገጠ፤ ይህ ቁጥር በመጨረሻ ወደ ሀያ አንድ ከፍ ብሏል።

በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ አስከባሪው ምክር ቤት፥ በተፈጸመው ሁኔታ ከመከረ በኋላ፥ እስራኤልን የሚያወግዝ ውሳኔ አስተላለፈ። የአሜሪካ መንግሥትም ከሳዳም ሁሴን ጋር የነበረውን አንድነት ለመጠበቅ ሲል ውሳኔውን ደገፈ። የተፈጠረው ነገር አንድነቱን ባያናጋውም፥ የዓለም ሕዝብ ትኩረት ወደ እስራኤል፥ በዓረቦችና በእስራኤል መካከል ያለው ግጭት ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ወደመሆኑና የቤተ መቅደሱ ተራራ ጉዳይ የልዩነቱ እምብርት ወደ መሆኑ እንዲያተኩር አደረገው።

# አይሁዳውያን ቤተ መቅደስ ይፈልጋሉን?

ቤተ መቅደስ መሥራቱ ለምን አስፈለገ? እስራኤላውያን በምርኮ ወደ ባቢሎን ከተወሰዱ ጀምሮ፥ ምኩራብ የአይሁዳውያን እምነት የትኩረት ስፍራ ሆነ። ሁለተኛው ቤተ መቅደስ በ70 እአአ በመደምሰሱና አይሁዳውያን በመላው ዓለም በመበተናቸው፥ ምኩራብ ብቸኛው የማምለኪያ ስፍራቸው ሆነ። እስራኤል ቤተ መቅደስ ካጣች ከ1900 ዓመታት በላይ ሆኗታል። በመሆኑም አንድ ማዕከላዊ የማምለኪያ ስፍራ የማግኘት ጉጉቷ እንዳለ ነው።

ቤተ መቅደሱን እንደገና መልሶ የማነጹ ፍላጎት የነበረ ቢሆንም፥ እስከ 1967 እአአ ድረስ ከነበሩት ሁኔታዎች የተነሣ የማነጹ ጉዳይ የሚታሰብ ነገር አልነበረም። ላለፉት አንድ ሺህ ሦስት መቶ ዓመታት በአካባቢውና ቤተ መቅደሱ በነበረበት ስፍራ ገኖ የኖረው የእስልምና ሃይማኖት ነው። በመስቀል ጦርነት ከነበረው አጭር ጊዜ በቀር* እስላሞች ናቸው አካባቢውን የያዙት። አይሁዳውያን ቤተ መቅደሱ እነበረበት ስፍራ ላይ እንዳያመልኩ እስላሞች ከለከሏቸው። ወደ አካባቢው እጅግ ቀረቡ ቢባል በስተደቡብ ምዕራብ እስካለው ስፍራ ድረስ ብቻ ነበር። በስተምዕራብ ያለው ወይም “የዋይታ ግድግዳ” የሚባለው፥ የፈረሰውን ግድግዳ የማይተካና ብቁ ያልሆነ ነበር።

በ1967 እአአ ግን ሁሉም ተለወጠ። እስራኤላውያን በስድስት ቀኑ ጦርነት አሮጌዋን ኢየሩሳሌም በመያዝ ጥንታዊት መናገሻ ከተማቸውን በእጃቸው አደረጉ። ይሁን እንጂ፥ ቅዱስ ጦርነት የሚባለው ውጊያ ይቀሰቀስ ይሆናል ከሚል ሥጋት በቅዱሶቹ ስፍራዎች ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ አላደረጉም። ቤተ መቅደሱ የነበረበትን ስፍራ እስከ ዛሬ የሚያስተዳድሩት እስላሞች ናቸው። ብዙዎቹ አይሁዳውያን ግን ቤተ መቅደሱን እንደገና እስራኤል ውስጥ ለመሥራት ይፈልጋሉ። በ1983 እአአ በአንድ ጋዜጣ አማካይነት ከተሰጠው ድምፅ ለመገንዘብ እንደተቻለው፥ 18.3 በመቶ የሚሆኑት እስራኤላውያን የቤተ መቅደሱ መሠሪያ ጊዜ ደርሷል የሚል አሳብ አላቸው።

የእስራኤል የሃይማኖት ጉዳዮች ሚኒስቴር በ1989 እአአ የቤተ መቅደስ ጥናት ስብሰባ አዘጋጅቶ ነበር። በሚሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉ አልባሳትና ቁሳቁሶችን በተመለከተ ደንብ የሚያዘጋጁ ቡድኖች በወቅቱ ተመሠረቱ።

---

* የመስቀል ጦርነቶች የተጀመሩት በ1096 ዓ.ም. ሲሆን እስከ 1291 ዓ.ም. ድረስ ቆይተዋል። ነገር ግን የኢየሩሳሌም ከተማ ከ1099 ዓ.ም. እስከ 1187 ዓ.ም. እአአ ብቻ በክርስቲያኖች እጅ ነበረች።

እነዚህ ቁሳቁሶች፥ ኢየሩሳሌም በሚገኘው የቤተ መቅደስ ጉዳይ ተቋም ውስጥ ለእይታ ቀርበዋል። ይህ የቤተ መቅደስ ጉዳይ ተቋም፥ ቤተ መቅደሱ እንደገና ስለ መሠራቱ እጅግ የጓጓ መሆኑን በገለጠበት አነስተኛ መጽሐፍ እንዲህ ብሏል:-

> "ቤተ መቅደሱን የመሥራቱ ሕልም እስከ 50 የአይሁዳውያን ትውልድ፥ እስከ አምስቱ አህጉራትና ከቁጥር በላይ ወደሆኑ ባሕሮችና ውቅያኖሶች የሰፋ ነው። ...በእግዚአብሔር እርዳታ ቤተ መቅደሱን በቅርቡ ኢየሩሳሌም ውስጥ የራሱ በሆነና በተቀደሰው ተራራ ላይ እንሠራዋለን። በዚህም ወደ ሠላምና መግባባት፥ ፍቅርና መዋደድ ዘመን እንሸጋገራለን። ይህ ዘመን እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ንጉሥ፥ አንድ አምላክ፥ ስሙም አንድ የሚሆንበት ይሆናል"።

ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ቀይ ጊደር (ለመሥዋዕት የምትሆን) ማርባቱ፥ እንዲሁም አስፈላጊዎቹን ቁሳቁሶችና አልባሳት የማዘጋጀቱ ተግባር ቀጥሏል። አንዳንድ እርግጠኛ ያልሆኑ ዘገባዎች፥ እስራኤል ለግንባታው የሚሆን እብነበረድና የተጠረቡ ድንጋዮችን በምስጢር በማከ ማቸት ላይ ናት ይላሉ። ዘገባዎቹ መሠረተ ቢስ ይመስላሉ። በሌላ በኩል ግን ምንም እንኳን አናሳ ክፍሎችን የሚወክሉ ቢሆኑ፥ ቤተ መቅደሱን ለመሥራትና በውስጡም አምልኮ ለመጀመር ከልባቸው የሚዘጋጁ አንዳንድ ቡድኖች አሉ። ይሁንና በሙስሊሞች ማምለኪያ መስጊድ በተያዘ ስፍራ ላይ ቤተ መቅደስ ሊሠራ የሚችለው እንዴት ነው?

እናደርገዋለን

አክራሪ አይሁዳውያን የቤተ መቅደስ ተራራ በተባለው ስፍራ ዝር እንዳይሉ ይከለከላሉ። የዚህ ምክንያቱ፥ ቤተ መቅደሱ የነበረበት ትክክለኛ ስፍራ ገና አለመታወቁ ነው። አንድ አይሁዳዊ ባለማወቅ የቃል ኪዳኑ ታቦት ወዳረፈበት ቅዱስ ወይም ቅድስተ ቅዱሳን ስፍራ ዘው ይል ይሆናል፥ ብለው የአይሁድ መምህራን ይሠጋሉ። ቤተ መቅደሱ እንደገና ከመሠራቱ በፊት ትክክለኛ ስፍራው በተራራው ላይ መታወቅ አለበት። ይሁን እንጂ፥ በስፍራው ላይ ምንም ዓይነት የከርሠ-ምድር ቁፋሮ እንዲካሄድ ዓረቦች አይፈቅዱም፤ በተለይም ቁፋሮው የአይሁዳውያን ቤተ መቅደስ ወደነበረበት የሚያመራ ከሆነ።

ቤተ መቅደሱ ወደነበረበት ተራራ ለመሄድ ሙሉ ፈቃድ ባይኖርም፥ ቤተ መቅደሱ የት እንደነበር ለመለየት ሌላ ዘዴ እንዲጠቀሙ ከማድረግ አንዳንዶችን አላገዳቸውም። ቁፋሮው የሚከናወነው በቤተ መቅደሱ ተራራ ጎን ነው። መሬቱን ውስጥ ለውስጥ በመቆፈር የተሠራው

መሽሉኪያ የመምህራን መተላለፊያ የሚባል ሲሆን፥ የምዕራቡን ግድግዳ ተከትሎ በከተማይቱ ሥር 300 ሜትር ያህል ተዘርግቷል። ሌሎቹ ተመራማሪዎች ደግሞ፥ የቤተ መቅደሱን ስፍራ በትክክል ለመለየት ሲሉ ጆሴፈስ* የተባለውን ሰው የጥንት ጽሑፎች ጨምሮ፥ የሙት ባሕር ጥቅል የተባለውን ጽሑፍ መርምረዋል። እነዚህ ተመራማሪዎች፥ ቤተ መቅደሱን ተራራው ላይ እንዲያገኙ የሚረዳቸው በቂ ታሪካዊ መረጃ እንደሚያገኙ ተስፋ ያደርጋሉ።

ከስኮትላንድ የተመለሰውና አሼር ካውፍማን የተባለ አይሁዳዊ ስደተኛ፥ አለ የተባለውን ታሪካዊ መረጃ ሁሉ አጥንቷል። "ቢቢሊካል አርኪዮሎጂ ሪቪው" በተባለው መጽሔት ባሰፈረው ጽሑፍ፥ ጥንታዊው የቅድስተ ቅዱሳን ስፍራ "የዓለት ጉልላት" በተባለው ስፍራ ላይ አልነበረም ሲል ተከራክሯል። በእርሱ አባባል፥ ቅድስተ ቅዱሳኑ የነበረው ቤተ መቅደስ ተራራ ላይ፥ "የዓለት ጉልላት" ከተባለው ስፍራ 100 ሜትር ያህል ወደ ሰሜን ርቆ ነበር። ይህ ሰው አባባሉን የሚያረጋግጠው በጽሑፍ ምንጮች ቢሆንም፥ አስተያየቱን የሚደግፉለት የከርሠ-ምድር ግኝቶችንም አቅርቧል።

ከዋና ዋናዎቹ የከረሠ-ምድር ተመራማሪዎች መካከል የዚህን አይሁዳዊ አስተያየት አሳማኝ ሆኖ ያገኘ ማንም የለም። ጉዳዩ እዚህ የተነሣው፥ የሰውዬው አስተያየት ትክክል ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመከራከር አይደለም። ብዙ መሠረታውያን አይሁዶች ቤተ መቅደሱ የነበረበትን ትክክለኛ ቦታ ለማወቅ ማንኛውንም የማስረጃ ቁርጥራጭ በጥንቃቄ በመመርመር ላይ ናቸው። የአሼር ካውፍማን አቋም ከግኝቶች ጋር ይስማማል ከሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሱ፥ በተባለው ስፍራ ላይ ቤተ መቅደሱን ይሠራሉ። የሃይማኖቱ ማኅበረሰብ ይህን አመለካከት ካልተቀበለው ግን፥ ከከርሠ-ምድር ተመራማሪዎች ግኝት ይልቅ፥ ጥንታዊውን የጽሑፍ ባሕል በራሳቸው መንገድ በመተርጎም ቤተ መቅደሳቸውን ይሠራሉ። ባሕልና የከርሠ-ምድር ግኝቶች ሲቃረኑ፥ ይህ

---

* የታወቀ አይሁዳዊ የታሪክ ተመራማሪ የሆነው ጆሴፈስ፥ የተወለደው በግምት በ37 ዓ.ም. ሲሆን፥ የሞተው ደግሞ በ100 ዓ.ም. ገደማ ነበር። ከታወቁት መጻሕፍቱ መካከል አንዱ "አንቲኪቲስ ኦፍ ዘ ጂውስ" (Antiquities of the Jews) የሚባለው ሲሆን፥ ይህ መጽሐፍ ከፍጥረት ጀምሮ አይሁዶች በ66 ዓ.ም. በሮም ላይ እስካስነሱት አመጽ ድረስ የሚያጠቃልለውን የአይሁድ ሕዝብ ታሪክ ይገልጣል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስ፥ መጥምቁ ዮሐንስ፥ እንዲሁም የኢየሱስ ወንድም የሆነው ያዕቆብ ተጠቅሰዋል።

ሌላው መጽሐፍ "የአይሁድ ጦርነት" (The Jewish war) የተሰኘው ሲሆን፥ ይህም ከአንጦኪዮስ ኤጲፋነስ (175-163 ዓ.ዓ.) ጀምሮ እስከ የኢየሩሳሌም ውድቀት (ከውድቀቱም በኋላ ያለውን የተወሰነ ጊዜ ይጨምራል) ድረስ ያለውን የአይሁድ ታሪክ ይገልጣል።

የመጀመሪያ ጊዜያቸው አይደለም። ምንም እንኳን የከርሠ-ምድር ተመራማሪዎች ሁሉ ነገሩ የሚታመን አይደለም ቢሉ፥ አይሁዳውያን የዳዊት መቃብር መሆኑ በሚነገርለት ስፍራ ላይ ዛሬ ምኩራብ (የማምለኪያ ስፍራ) አላቸው።

ሌሎች ምሁራን የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ የነበረው ዛሬ የዓለት ጉልላት ባለበት ስፍራ ነው ብለው ያምናሉ። የሥነ-ሕንጻ ምሁር፥ የከርሠ-ምድር ተመራማሪና የታሪክ አዋቂ የሆኑት ሊን ሪት ሚይር፥ ከከርሠ-ምድርና ከታሪክ ምርምር የተገኙ ምንጮችን በማገናዘብ፥ ቤተ መቅደሱ የነበረበትን ስፍራ በተመለከተ ከምርምሮች ሁሉ የቅርቡ የሆነውን ንድፈ-አሳብ ለማቅረብ ሞክረዋል። በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ታቦቱ ያረፈበት ትክክለኛ ስፍራ፥ ኤል ሻክራ በተባለ ቦታ በተሠራው መድረክ ላይ ነበር በማለት በአሳማኝ ሁኔታ ተከራክረዋል። ይህ ስፍራ የዓለቱ ጉልላት የነበረበትና ቅርፁ በጉልህ የሚታይ ነው። የኚህ ሰው ግኝት ከታመነበት፥ ቤተ መቅደሱ ከመሠራቱ በፊት የዓለቱ ጉልላት መፍረስ ይኖርበታል።

## ቤተ መቅደስ እንዲሠራ ዓረቦች ይፈቅዳሉን?

ቤተ መቅደሱን በነበረበት ስፍራ ላይ የመሥራቱ ተስፋ ዛሬ የመነመነ ይመስላል። አንድ የአይሁዳውያን ቡድን የመሠረት ድንጋይ ሊያኖር መጣ የሚለው ወሬ ብቻ እንኳን በሺህ የሚቆጠሩ ተቃዋሚዎችን በቁጣ ሊያስነሣ ይችላል። ሦስተኛውን ቅዱስ ስፍራ በየትኛውም የሙስሊሞች ምድር ላለማሠራት እስከ መጨረሻው ዓረባዊ የደም ጠብታ ድረስ ለመፋለም ዓረቦች ዝተዋል። ጥቂት የአይሁዳውያን ቡድኖችም ሦስተኛውን ቤተ መቅደስ በነበረበት ስፍራ ላይ ለመሥራት ያንኑ ያህል ቆርጠዋል። እንዴት ነው ይህ ፍጥጫ የሚያከትመው?

እግዚአብሔር ሁኔታዎች የሚያበቁበትን መንገድ በዝርዝር አይገልጥም። አዲስ ቤተ መቅደስ ስለ መሠራቱ ግን በግልጥ አስታውቋል። ቤተ መቅደሱ የግድ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የወሰነው የመጨረሻ የሰባት ዓመት ፕሮግራም የጊዜ ደውል ከማቃጨሉ በፊት መሠራት አይኖርበትም። በሰባት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ግን መሠራት አለበት። እግዚአብሔር ለቤተ መቅደሱ መሥሪያ የሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ ሰጥቷል።

ዳንኤል 9 (በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 3 እና 4 ውስጥ በመጠኑ በዝርዝር ተገልጧል) ውስጥ እስራኤል ስለሚኖራት 490 ዓመት ነቢዩ ይገልጣል። ይህ ጊዜ ኢየሩሳሌም እንደገና እንድትታነጽ ትእዛዝ ጊዜ

አንስቶ፥ ከወጣበት የእግዚአብሔር መንግሥት ተስፋ እስከሚፈጸምበት ድረስ ያለው ነው። የመጨረሻው የሰባት ዓመት ጊዜ ገና ወደፊት ሲሆን፥ የሚጀምረውም የዓለም መሪ ሆኖ የሚነሣው ሰው ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን ወይም ስምምነት ሲያደርግ ነው። ነገር ግን ቃሉ፥ "በሱባዔውም እኩሌታ መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል። ከርኩሰትም ጫፍ ላይ አጥፊው ይመጣል" (ዳን. 9፡27) ስለሚል፥ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ፥ የመሥዋዕቱ ሥርዓት ከመተግበሩ ጋር ቤተ መቅደሱ መሠራት አለበት።

ዳንኤል ትንቢቱን ከተናገረ ከአምስት ምዕተ ዓመታት በላይ ቢሆንም፥ ትንቢቱ ገና አልተፈጸመም። ትንቢቱ ገና ወደፊት የሚፈጸም መሆኑን ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ በማለት ነግሯቸዋል፥ "እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ አንባቢው ያስተውል፤ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደተራራዎች ይሽሹ" (ማቴ. 24፡15-16)። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚያስታውሳቸው፥ ለእስራኤል ሕዝብ የመጨረሻ መከራ በዳንኤል ትንቢት የተነገረው ድርጊት ጀማሪ የሚሆንበት ወቅት መሆኑን ነበር። ምልክቱ "በተቀደሰችው ስፍራ" የሚጀምር መሆኑን ነው ኢየሱስ ለይቶ የተናገረው። ይህ በግልጥ የሚያመለክተው፥ ያኔ ቤተ መቅደሱ የሚኖር መሆኑን ነው።

ኢየሱስ የመጨረሻውን ዘመን አስመልክቶ ለደቀ መዛሙርቱ ማብራሪያ ከሰጣቸው ከሀያ ዓመታት ያህል በኋላ፥ ሐዋርያው ጳውሎስም ግሪክ ውስጥ ለነበረው አዲስ የአማኞች ቡድን ተመሳሳይ ገለጣ አድርጓል። ጳውሎስ በሁለተኛ ተሰሎንቄ መልእክቱ አንባቢዎቹ ገና በመጨረሻው ዘመን ውስጥ እንዳልሆኑ አስረድቶአቸዋል። አንድ ሰው በዳንኤልና በኢየሱስ የተተነበየው የመጨረሻ ዘመን የደረሰ መሆኑን በመግለጥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ደብዳቤ የጻፈ መሆኑ ግልጥ ነው። ስለሆነም ጳውሎስ 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡2 ውስጥ፥ "ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱም ስለመሰብሰባችን፥ በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት፡- የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ በአእምሮአችሁ እንዳትናወጡ፥ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን" በማለት አንባቢዎቹን አስገንዝቧል።

ጳውሎስ ከዚህ በመቀጠል ቀደም ሲል በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተገለጡትን ሁኔታዎች እንዲህ በማለት ይጠቅሳል፡-

> *"ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው፥ እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ አይደርስም። እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ*

መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው” (2ኛ ተሰ. 2፡3-4)።

አሁንም ቅደም ተከተሉ ግልጥ ነው። በትንቢታዊው ክፍለ-ጊዜ ጅማሬ ላይ “የዓመፁ ሰው” ይገለጣል። ይህ ሰው ኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተ መቅደስ ይሄድና አምላክ ነኝ ብሎ ያውጃል። ይህ ድርጊቱ ነው የመጨረሻውን የሦስት ዓመት ተኩል መከራ የሚጀምረው።

ዳንኤል፥ ኢየሱስና ጳውሎስ አንዱን ታሪካዊ ክሥተት አመልክተዋል። ክሥተቱ ሮማውያን በ70 እአአ ኢየሩሳሌምን በደመሰሱ ጊዜ ተፈጽሞ ይሆን? ሐዋርያው ዮሐንስ ለዚህ ጥያቄ አሉታዊ መልስ አለው። ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ከጻፈ ከአርባ ዓመታት በኋላ (እና ኢየሩሳሌም በሮማውያን እጅ ከወደቀች ከሀያ ዓመታት በኋላ)፥ ሐዋርያው ዮሐንስ የዳንኤል፥ የኢየሱስና የጳውሎስ ትንቢቶች ገና ወደፊት የሚፈጸሙ መሆናቸውን ገልጧል።

ዮሐንስ ራእይ ከምዕራፍ 12-13 ባለው ክፍል ውስጥ፥ በመጨረሻው ዘመን ምድርን የሚያሠቃዩዋትን ሦስት አካላዊ ፍጡራንን ይገልጣል። የዚህ ተግባር የበላይ አስፈጻሚ “ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ፥ እርሱም የቀደመው እባብ” ነው (ራእይ 12፡9)። ምዕራፍ 12 ውስጥ ደግሞ በመጨረሻዎቹ ቀናት መንፈሳዊ ኃይላት ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ መሆናቸውን ለአንባቢዎቹ ያስረዳል። ሰይጣን የእስራኤልን ሕዝብ ለማሳደድ ይነሣል። በሴት ተምሳሌትነት የተገለጠችው እስራኤል ወደ “በረሃ ለመሸሽ” ትገደዳለች። ይህ ምድረ በዳማውን የይሁዳ አካባቢ ወይም የሲናን ባሕረ-ሰላጤ በረሃማነት ለመግለጥም የተጠቀሰ ሊሆን ይችላል። እስራኤል በዚህ “ለ1260 ቀናት” (ራእይ 12፡6) በሚቆየው ስደት ወቅት መለኮታዊ ጥበቃ የሚደረግላት መሆኑን ዮሐንስ ጽፎአል። ይህን ሲያደርግ፥ የዕብራይስጥን የጊዜ ስሌዳ በመጠቀም ለሦስት ዓመት ተኩል (ለ1260 ቀናት ወይም እያንዳንዳቸው 30 ቀናት ላላቸው 42 ወራት) ስለሚቆየው የስደት ጊዜ መግለጡ ነበር።

ከሦስቱ የሥቃይ አካላዊ ፍጡራን የመጀመሪያው ሰይጣን ከሆነ፥ ሁለተኛው ማነው? ከሦስቱ አካላዊ ፍጡራን ሁለተኛው፥ ከሰይጣን ኃይልን የሚታጠቀውና የወደፊቱ የዓለም መሪ እንደሚሆን ዮሐንስ በጽሑፉ ያስረዳል። ይህንኑ መሪ “አውሬ” ሲል ይገልጠዋል። አገላለጡ ከዳንኤል ምዕራፍ 7 የተወሰደ ነው። ይህ መሪ፥ በመጨረሻው ዘመን ከፍተኛ ወታደራዊ ኃይል ወደመሆን ያድጋል። ዓለም በሞላው፥

"አውሬውን ማን ይመስለዋል፥ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል?" ሲል ይጠይቃል (ራእይ 13፡4)። አሁንም ዮሐንስ ይህን አውሬ ዳንኤል ከገለጠው የመጨረሻ ዘመን መሪ ጋር ያዛምደዋል። ይህ መሪ፥ የሰባት ዓመት ስምምነት እንደሚፈርም፥ በመካከሉ ስምምነቱን እንደሚጥስና በቀሪው ጊዜ እስራኤልን እንደሚያሳድዳት ዳንኤል ተንብዮአል። ዮሐንስም ይህንኑ እንዲህ ይገልጠዋል፦

> "ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፤ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው። እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ። ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፤ በነገድና በወገንም፥ በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው" (ራእይ 13፡5-7)።

አርባ ሁለት ወራት፥ 1260 ቀናት፥ ሦስት ዓመት ተኩል፦ ይህ የሚያመለክተው፥ ዳንኤልና ዮሐንስ ያንኑ አንድ ሁኔታ መግለጣቸውን ነው።

ዮሐንስ በመቀጠል የሚገልጠው ከሦስቱ የክፋት አካላዊ ፍጡራን ሦስተኛውን ነው። "ሌላ አውሬ. . . የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት፤ እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር" ይለዋል (ራእይ 13፡11)። ይህ የመጨረሻው የክፋት አካል፥ የዋህና ክርስቶስን የሚመስል (በግ መሰል) የሃይማኖት ሰው ይመስላል። ዳሩ ግን፥ መልእክቱንና ኃይሉን የሚያገኘው (ዘንዶን ከሚመስለው) ከሰይጣን ነው። የዚህ ግለሰብ ሚና የዓለም ሕዝብ ወደፊት የሚመጣውን መሪ እንዲያመልክ ማበረታታት ይሆናል፦ "ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል" (ራእይ 13፡12)። ይህን ተግባራዊ የሚያደርገው ግን እንዴት ነው?

ዮሐንስ የዳንኤልን፥ የኢየሱስንና የጳውሎስን መልእክቶች ዘርዘር አድርጎ በማብራራት፥ ይህ ሦስተኛ የክፋት አካል ምድርን የሚያስታት መሆኑን እንዲህ ይገልጣል፥ "በአውሬው ፊት ያደርግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሣ በምድር የሚኖሩትን ያስታል። የሰይፍም ቁስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል። የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ፥ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፥ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው" (ራእይ 13፡14-15)።

"የጥፋት ርኩሰቱ" (ማቴ. 24፡15-16) የወደፊቱ የዓለም መሪ ሐውልት ሲሆን፥ ኢየሩሳሌም ከተማ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ይተከላል።


ሐውልቱ በሰይጣናዊ አስመሳይ ተአምር አማካይነት ሕይወት ያለው ወደ መሆን የሚለወጥ ይመስላል። ከዚሁ ሐውልት የሚወጣው ድምፅ ይህንኑ የዓለም መሪ ሕዝቡ እንደ አምላክ እንዲያመልከው ያዛል። ትእዛዙን አሻፈረኝ የሚል ሁሉ ይገደላል። ታዲያ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለዚሁ ሁኔታ ከገለጠላቸው በኋላ፥ የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰችው ከተማ ሲቆም "ወደ ተራሮች እንዲሸሹ" ማስጠንቀቁ ያስደንቅ ይሆን? ዕቃቸውን ለመሰብሰብ ወይም ልብሳቸውን ለመቀየር ጊዜ መውሰድ አልነበረባቸውም።

እነዚህ ነቢያት በሰባት ዓመቱ የመጨረሻ አጋማሽ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚከሠቱትን ድርጊቶች በመግለጥ ረገድ አንድነት አላቸው። ቤተ መቅደሱ በመጀመሪያው የሰባት ዓመት አጋማሽ ላይ ተሠርቶ አገልግሎት መስጠት የሚጀምር ይመስላል። ቅዱሱ ስፍራ ይታነጽና የእንስሳት መሥዋዕቱ ይቀጥላል። ቤተ መቅደሱን ለማነጽ ታዲያ የሦስት ዓመት ተኩሉ ጊዜ በቂ ነው?

የመጀመሪያው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ የተሠራው በሰባት ዓመት ነበር (1ኛ ነገ. 6፡38)። ከሰሎሞን ቤተ መቅደስ መፍረስና የባቢሎን ምርኮ በኋላ በ536 ዓ.ዓ. አይሁዳውያን ቤተ መቅደስ መሥራት ጀመሩ። መሠረቱ ከተጀመረ በኋላ ከአካባቢው ተቃውሞ በመነሣቱ ሥራው ተቋረጠ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ያበረታቱ ዘንድ ሐጌንና ዘካርያስን በ520 ዓ.ዓ. እስካስነሣ ድረስ አልተሠራም። ከመስከረም 21 ቀን 520 ዓ.ዓ. ጀምሮ (ሐጌ 1፡15) የቤተ መቅደሱ መሠረት እንደገና ተጣለና በሦስት ዓመት ተኩል፥ መጋቢት 12 ቀን 516 ዓ.ዓ. የቤተ መቅደሱ ሥራ ተጠናቀቀ። የዘመናችንን የሕንጻ ግንባታ ዘዴዎችና የሥራውን አስፈላጊነት ስናጤን፥ በሦስት ዓመት ተኩል ተሠርቶ አገልግሎት ለመስጠት የሚችለውን ቤተ መቅደስ ምንነት ለመገመት ይቻላል።

ወደፊትም አንድ ቀን፥ ቤተ መቅደሱ ይታነጻል። የሚሠራበት ተራራ ሁለት የእስልምና ማምለኪያዎች የሚገኙበት ስፍራ ነው። ታዲያ እንዴት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል? ለዚህ ጥያቄ እግዚአብሔር የሰጠው መልስ ስለሌለ፥ የትኛውም አስተያየት ግምታዊ ይሆናል። ምናልባትም የማምለኪያ ትቋማቱን የምድር መንቀጥቀጥ ያፈራርሳቸው ይሆናል። ወይም አይሁዶች የዓረቦች ቁጣ የሚያስከትለውን ነገር ሁሉ በመቋቋም፥ ያፈራርሷቸው ይሆናል። ምናልባትም የአሸር ካውፍማን አመለካከቶች ትክክል ይሆኑና፥ የሙስሊሞችን ቅዱሳት ስፍራዎች ሳያውክ ቤተ መቅደሱ የሚሠራበት ሁኔታ ይፈጠር ይሆናል።

ከሁሉም ይልቅ ሊሆን የሚችል የሚመስለው አስተያየት፥ ወደፊት የሚነሣው የዓለም መሪ ከሰባት ዓመቱ ስምምነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ አይሁዳውያን ቤተ መቅደስ የሚያንጹበትን መንገድ የሚያመቻች መሆኑን የሚናገረው ነው። እስራኤል ቤተ መቅደስ ለማነጽ ፈቃድ የምታገኝበትን ሁኔታ የእግዚአብሔር ቃል አይነገረን እንጂ፥ ቤተ መቅደስ የምታንጽ መሆኗን ግን አበክሮ ይተነብያል። የጥፋት ርኩሰት የሚቆመው፥ ወደፊት በሚታነጸው ቤተ መቅደስ ውስጥ ነው። "የእግዚአብሔር ቤት" ለሦስቱ የጥፋት አካላዊ ፍጡራን ዋና ጽሕፈት ቤት በመሆን ያገለግላል።




ኢየሩሳሌም ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ

> ምዕራፍ ስድስት <

# የፍጻሜው እልቂት

አውቶቡሳችን የእስራኤል እልቂት መታሰቢያ በሚገኝበትና፥ ያድ ቫሽም በሚባለው ጎዳና ላይ በማምራት ላይ እንዳለ ነው ፀሐይ ወደ መጥለቂያዋ የተቃረበችው። ዕለቱ ጥድፊያ የበዛበት ቢሆንም፥ አስደሳች ነበር። በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ ጥንታዊቱ ኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ ስንዘዋወር ቆየን። ጉዞው፥ በምድር ውስጥ ለውስጥ በሚሄደው የሕዝቅያስ መንገድ መነሻ ከሆነው የግዮን ምንጭ አጠገብ ሲደርስ አበቃ። በጥንታዊቱ ኢየሩሳሌም ከተማ ሥር በሚሽሎከለከው የምድር ውስጥ መተላለፊያ በምንጓዝበት ጊዜ፥ ውኃው እስከ ግማሽ አካላችን ያሰምጠን ነበር። ከምሳ በኋላ፥ ሁለተኛው የኢየሩሳሌም ሞዴል ወደሚገኝበትና፥ "ሆሊ ላንድ" ወደሚባለው ሆቴል ተጓዝን። የሰማዩ ጥራት ውብ መሆንና በስፍራው የነበረው ሕዝብ ቁጥር አነስተኛነት፥ ለቡድናችን መልካም አጋጣሚ ሆነለትና፥ ሞዴሉን ፎቶግራፍ አነሣነው። በመሆኑም የቀኑን ተግባራችንን ስንፈጽም ቡድናችን ድካም ቢሰማውም፥ ደስተኛ ነበር።

ከአውቶቡሱ ወርደን ሽቅብ ወደ ሕንጻው በማምራት ላይ እያለን፥ በአቅራቢያው የነበረ አንድ አስደናቂ ምስል ትኩረቴን ሳበው። ምስሉ፥ መጀመሪያ ኢየሩሳሌም በ70 እአአ በሮማዊው ቲቶ በተደመሰሰች ጊዜ በጸጥታ ተሰልፈው የነበሩትን ዘበኞች ምስል መሰለኝ፥ ግድግዳው ላይ ትኩር ብዬ ስመለከት ግን፥ ሽቦ አጥር ውስጥ የታጎሩና በናዚ ወታደሮች የሚነዱ ሰዎች መሆናቸውን ተረዳሁ። ሰዎቹ ወደ ምርኮ ሳይሆን፥ ወደ መሰቀያ ስፍራ በመጓዝ ላይ ነበሩ።

የያድ ቫሺም (የአይሁዳውያን ሰማዕታት መታሰቢያ)፥ ቀላል አሠራር አስደነቀኝ። የትኛውም ዘመናዊ የኮምፒውተር ፈጠራ እንዲያ የተዋበ ሥራ አልሠራም። ያን ከተመለከትን በኋላ፥ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በፊትም ሆነ በኋላ የነበረውን የናዚ ስደት እውነተኛ ታሪኮችን ለመረዳት፥ ፖስተሮችንና ሥዕሎችን እንመለከት ዘንድ አቅጣጫችንን ለወጥን። ናዚዎች የአንድን አስከፊ በሽታ ከምድር ገጽ መጥፋት ታሪክ ይመዘግቡ ይመስል፥ የጭካኔ ተግባራቸውን በፊልምና በፎቶግራፍ ማቆየታቸው የተፈጸመውን በደል ይበልጥ አጎላው።

የምመለከተውን ነገር አሰቃቂነት ይበልጥ ለመረዳት እየሞከርኩ ኢግዚቢሽኑን ጎበኘሁት። አይሁዳውያን ሆነው መወለዳቸው ብቻ፥ እንደ ኃጢአት ተቆጥሮባቸው በተጨፈጨፉት በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ምክንያት የተሰማኝን ኀዘንና ቁጣ ለመግታት እየታገልኩና ስሜቴን እየተቆጣጠርኩ ጉብኝቴን አበቃሁ። ከኤግዚቢሽኑ ስፍራ ከመውጣቴ

በፊት፥ በናዚ ዘመን በተለያዩ አገሮች የተገደሉትን አይሁዳውያን ቁጥር በጉልህ የሚያመለክተውን መግለጫ ለማንበብ ቆም አልኩ። በመጨረሻ የአየሁት፥ የአንድ እግር ጫማ ያለበት የመስታወት ዕቃ ነው። ጫማው የሕፃን ልጅ ነበር። ከመስታወቱ በላይ የተጻፈው መግለጫ በእልቂቱ ጊዜ አንድ ሚሊዮን ተኩል ሕፃናት መገደላቸውን ያስረዳል። ጫማው ለትልቁ ልጄ ልክ የሚሆነው ይመስላል። በጣም ስለምወደው ልጄ ማሰብ ስጀምር፥ የተፈጸመው ነገር አሰቃቂነት ዘገነነኝ።

ቡድናችን መጓጓዣ አውቶቡሱ ላይ የተሣፈረው፥ በዝምታ ተውጦ ነበር። እንዳላለቅስ ስለፈራሁ፥ ስለተመለከትኩት ነገር ለመናገር አልቻልኩም። ጉዞ ስንጀምር፥ የእስራኤል መንግሥት ከውጭ ለሚመጣበት ማንኛውም አስፈሪ ነገር ቅፅበታዊ አጸፋ ስለሚሰጥበት ምክንያት የበለጠ መረዳት ያገኘሁ መሰለ ተሰማኝ። ያ ሁሉ ሥቃይ የደረሰባቸው ሰዎች ያለፈው ነገር እንዳይደገም ለመከላከል ቆርጠዋል።

## ፀረ- ፅዮናዊነት - ሰይጣናዊ መነሻ

አይሁዳውያን ለምንድነው ለዘመናት የተሠቃዩት? እንዲህ ላለው ውስብስብ ጉዳይ ቀላል መልስ መስጠቱ ችግር አለው። እርግጥ በእስራኤል ላይ የደረሰው ያለፈ ሥቃይ ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር የነበራት የቃል ኪዳን ግንኙነት ነበር። እስራኤል ሲና ተራራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ተጋብታለች። እግዚአብሔርም ለሕዝቡ ግልጥ መመሪያ ደንግጓል። ዘሌዋውያን 26 ውስጥ እንደተመለከተው፥ ሕዝቡ ቢታዘዙት በረከት እንደሚሰጣቸው፥ ባይታዘዙት ግን እንደሚረግማቸው ወይም እንደሚቀጣቸው እግዚአብሔር ገልጧል። ይህንኑ የበረከትና የመርገም ዝርዝር ዘዳግም 28 ውስጥ ለአዲሱ ትውልድ በድጋሚ አስገንዝቧል።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ስለመርገሞቹ ያስጠነቀቀበት ዓላማ፥ ከርሱ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ባይጠብቁ፥ ክፉ ነገር የሚደርስባቸው መሆኑን ለማስታወስ ነበር። የመጨረሻው የርግማን ማስጠንቀቂያ፥ ሕዝቡ ቃል ኪዳኑን ባይጠብቅ ከእስራኤል ምድር ተሰዶ በባዕድ ምድር በሌሎች መንግሥታት የሚሠቃይ መሆኑን እንዲህ በማለት አስገንዝቧል፥ "እግዚአብሔርም ከምድር ዳር እስከ ዳርቻዋ ድረስ ወዳሉ አሕዛብ ሁሉ ይበትንሃል፥ . . . በነዚያም አሕዛብ መካከል እረፍት አታገኝም፥ ለእግርህ ጫማ ማረፊያ አይሆንም" (ዘዳ. 28፥64-65)። በአጭሩ ለመግለጥ ያህል፥ እስራኤል ላይ ከደረሱባት ሥቃዮች አንዳንዶቹ፥ ለእግዚአብሔር ካለመታዘዝ ሳቢያ የመጡ ናቸው። ይሁንና፥ አይሁዳውያን እስከዛሬ የተሠቃዩበትን ምክንያት ይህ አባባል ይገልጠዋል?

ክርስቲያን ነን የሚሉ አንዳንድ ወገኖች አይሁዳውያንን በክርስቶስ ስም አሳደዋቸዋል። እነዚህ ቀናዒ ሃይማኖቶች ማቴዎስ 27፡25 ውስጥ የተጠቀሱትንና፥ "ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን" ያሉትን ሰዎች አባባል በተሳሳተ አቅጣጫ በመተርጎም፥ ለክርስቶስ ሞት አይሁዳውያንን ተጠያቂዎች አደረጓቸው። እነዚህ ሰዎች በክርስቶስ ስም አይሁዳውያንን አሳደዷቸው፤ አሠቃዩዋቸውም። ከሩሲያ የዘረኝነት ጭፍጨፋ እስከናዚ እልቂት ተሠቃይተዋል። በመጠኑም ቢሆን አሜሪካና ጀርመን ውስጥ ዛሬም ከፀረ-ፅዮናውያን ማስፈራራት ይደርስባቸዋል። አብዛኛው የፅዮናዊነት ጥላቻ የሚመጣው ታዲያ የመስቀል አርማን በማንገብ ነው።

ብዙዎች አይሁዳውያንን በክርስቶስ ስም አሳደዋቸዋል፤ በድርጊታቸው ግን እናምንበታለን የሚሉትን ጌታ ክደውታል። የዛሬዎቹ አይሁዳውያን ለክርስቶስ ሞት ተጠያቂዎች አይደሉም። ኢየሱስ ከመያዙና ከመሰቀሉ በፊት፥ ስለ ዓለም ኃጢአት አልፎ መሰጠት የነበረበት መሆኑን እንዲህ በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ገልጦላቸዋል፦ "ለብዙዎች ኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" (ማቴ. 26፡28)። በተያዘ ጊዜ ደግሞ በፈቃዱ ራሱን የሰጠ መሆኑን እንዲህ በማለት ለጠላቶቹ ገለጠ፥ "ወይስ አባቴን እንድለምን፥ እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን?" (ማቴ. 26፡53)። ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ፈቃዱ ለሞት አልፎ ስለተሰጠ አይሁዳውያን ስለእርሱ ሞት ተጠያቂዎች አይደሉም።

ኢየሱስ የሞተው አይሁዳውያን ስለገደሉት ሳይሆን፥ ለኃጢአታችን ዕዳ የሚከፈል ዋጋ ስላስፈለገ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ ገና ወደ ፊት ሊሆን ያለውን ነገር በተመለከተ ጊዜ፥ በመጨረሻ ለኢየሱስ ሞት ተጠያቂ የሚሆነው ማን መሆኑን ተረድቶ፤ እኔንና እናንተንም የተመለከተ መሆኑን እንዲህ በማለት ገልጧል፦

> "በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፥ ሕማማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደተመታ በእግዚአብሔርም እንደተቀሰፈ፥ እንደተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለበደላችንም ደቀቀ፥ የድነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ" (ኢሳ. 53፡4-6)።

ስለ እኔና ስለ እናንተ ኃጢአት ልጁ እንዲሞት እግዚአብሔር ፈቅዷል። ልክ እንደ ማንኛውም ጲላጦስ ፊት ቆሞ ኢየሱስ እንዲሰቀል ይጠይቅ እንደ ነበረ አይሁዳዊ፥ እኛም ለኢየሱስ መሰቀል ተጠያቂዎች ነን።

ፀረ-ፅዮናዊነት ኢየሱስን በመግደላቸው እግዚአብሔር አይሁዳውያንን የሚቀጣበት መንገድ ካልሆነ፥ አይሁዳውያንን የመጥላቱ ምክንያት ወይም ምንጭ ምንድነው? ሐዋርያው ዮሐንስ የዘመናትን መጋረጃ ገልጦ፥ ከዓለም ታሪክ መድረክ በስተጀርባ በመካሄድ ላይ ያለውን ነገር ምስጢር ራእይ 12 ውስጥ በማስገንዘብ፥ ከላይ ለተጠቀሰው ጥያቄ መልስ ይሰጣል። ዛሬ ያለብን ችግር፥ እውነት፥ በምናየውና በምንመዝነው ነገር የሚለካ አለመሆኑን ለመገንዘብ እስኪሳነን ድረስ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ዓለማዊ አመለካከት የተጫነን መሆናችን ነው። ዓለማት ቁሳዊው ዓለም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መንፈሳዊ ኃይላት አሉባቸው። እነዚህ መንፈሳዊ ኃይላት፣ ፍጡራን አካላት የሆኑ መላእክት መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ በጉልህ ያስገነዝባል። መላእክት የሙታን መንፈስ ሳይሆኑ፣ ምድር ቅርፅ ከመያዟ በፊት በእግዚአብሔር የተፈጠሩና ሰብአዊ ተፈጥሮ የሌላቸው መንፈሳዊ አካላት ናቸው።

እነዚህ መንፈሳዊ አካላት፥ መላእክት እና አጋንንት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። መላእክት የሚባሉት ከተፈጠሩ በኋላ፥ ለእግዚአብሔር ታማኞች ሆነው የሚኖሩት ናቸው። አጋንንት ደግሞ ፍጹም ሆነው የተፈጠሩ፥ በኋላ ግን በፈጣሪያቸው ላይ ያመፁ መናፍስት ናቸው። ይህን በእግዚአብሔር ላይ የተደረገ ዓመፅ የመራውን ሌላ መልአክ ተከተሉ። ይህ የዓመፅ መሪ የሆነ መንፈሳዊ አካል ብዙ ስሞች አሉት፥"ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን፥ የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ" (ራእይ 12፡9)።

ሰይጣን ከወደቀበት ጊዜ አንሥቶ እግዚአብሔርንና ዕቅዶቹን ሁሉ ተቃውሟል። አዳምና ሔዋን ከልክሏን ፍሬ እንዲበሉ አስቷቸዋል (ዘፍጥ. 3፡1-7)። ኢዮብን (ኢዮብ 1፡6-12፤ 2፡1-7)፥ ሊቀ ካህኑን ኢያሱን (ዘካ. 3፡1-2) በእግዚአብሔር ፊት ከሷቸዋል።

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ዕቅዶችና ሕዝቦቹን በመቃወም በዘመናት ሁሉ በትጋት ሠርቷል። እግዚአብሔርን በመቃወሙ ረገድ የቱን ያህል የሚጥር መሆኑን ለማመልከት ሐዋርያው ዮሐንስ ሁለት ግልጥ ሁኔታዎች ላይ አትኩሯል። ይህን ለማመልከት ሲል ራእይ ምዕራፍ 12ትን "ፀሐይን ተጎናጽፋ ጨረቃ ከእግሮቿ በታች ያላት፥ በራሷም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች" (ቁ. 1) ብሎ ምስል በመሳል ይጀምራል። ዮሐንስ ይህን ምስል የወሰደው ዘፍጥረት 37 ውስጥ ከተጠቀሰውና "ፀሐይና ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋክብትም ሲሰግዱልኝ አየሁ" (ቁ. 9) ከሚለው የዮሴፍ ሕልም ነው። የዮሴፍ አባት እስራኤል፥ ለጥቆ ባለው ቁጥር ውስጥ ይህንኑ ቃል፥ እርሱ ፀሐይ፥ ሚስቱ ጨረቃ፥ አሥራ አንዱ የዮሴፍ ወንድሞች ደግሞ ከዋክብት እንደሆኑ

አድርጎ ተረዳ። ዮሐንስ ራእይ ውስጥ፥ ፀሐይን የተጎናጸፈችው ሴት፥ ጨረቃይቱና አሥራ ሁለቱ ከዋክብት የእስራኤል መንግሥትን ይወክላሉ።

ዮሐንስ፥ እስራኤል ወንድ ልጅ የምትወልድ መሆኗን በመግለጥ ራእዩን እንዲህ ይቀጥላል፥ "አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ፥ ወንድ ልጅ ወለደች" (ራእይ 12፥5)። ይህ ሕፃን ለእስራኤል ተስፋ የተገባለትና መሢሕ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ መሢሕ ዓለምን የሚመራ መሆኑንም እግዚአብሔር አስታወቋል። ሰይጣን ግን ይህን የእግዚአብሔር ዕቅድ ለማሰናከል ይሻል፥ "ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ" (ራእይ 12፥4)። የላከውን መሢሕ በማጥፋት የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለመቅጨት ሰይጣን ሞክሯል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ምድር ላይ በተመላለሰ ጊዜ በደረሰበት ጥላቻና ተቃውሞ ሁሉ የሰይጣን እጅ አለበት። በተወለደ ጊዜ፥ ቤተልሔም ውስጥ የነበሩና ዕድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ሁሉ ይገደሉ ዘንድ ታላቁ ሄሮድስ አዘዘ (ማቴ. 2፥7-8፥ 16-18)። እንደተጠመቀ ደግሞ፥ ሰይጣን ምድረ በዳ ውስጥ በሥጋ ምኞት፥ በዓይን አምሮትና በትዕቢት ሊፈትነው ሞከረ (ማቴ. 4፥1-11)። የመጣበትን ዓላማ ለማሳትም እጅግ ታማኝ በሆነው የኢየሱስ ደቀ መዝሙር በጴጥሮስ ተጠቀመ (ማቴ. 16፥21-23)። ኢየሱስን አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ ወደ ይሁዳ አሳብ ገባ (ዮሐ. 13፥21-30)። ይሰቀል ዘንድ እየጮኹ ይጠይቁ በነበሩት ሰዎች ጆሮ ሰይጣን ሹክ ይል እንደነበርም እርግጥ ነው።

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ልጅ በመግደል የፈጣሪን ዓላማ የቀለበሰ መስሎት ነበር። ኢየሱስ በሦስተኛው ቀን ከመቃብር በተነሣ ጊዜ ግን፥ ብስጭቱ እጅግ የመረረ ሆነ፥ "ልጇም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ" (ራእይ 12፥5)። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ቢነሣም ሰይጣን ዕቅዶቹን ለማሳካት ከመጣር አልተቆጠበም። አንደኛው ዕቅዱ ቢሰናከልበትም ወደ ሁለተኛው ተሸጋገረ። የእግዚአብሔርን መሢሕ ለማጥፋት ባይችልም፥ መሢሑ የሚገዛውን የአይሁድ ሕዝብ ለማጥፋት መሞከር ነበረበት።

ዛሬ፥ ሰይጣን እያሌ ፀረ-ፅዮናዊ ድርጊቶችን በማከናወን ላይ ነው። እግዚአብሔርን ይጠላል፥ በርሱ በተመረጡት ሕዝቦች ላይም ጥላቻን ይነዛል። ርኩሳን መናፍስት የዓለም ሕዝብን በአይሁዳውያን ላይ ለማስነሣት በመጣር ላይ ናቸው። በዙሪያችን በመከናወን ላይ ያለውን የክፉ መናፍስት አሠራር ልብ ልንልና ለአይሁዳውያን፥ እንዲሁም ለእስራኤል መንግሥት ልንጸልይላቸው ይገባል።

ሊሆን ያለ መከራ

ሐዋርያው ዮሐንስ በመሢሑ ላይ ሰይጣን ያደረሰውን ነገር ከገለጠ በኋላ፥ በእስራኤል መንግሥት ላይ ሊመጣ ያለውን የሰይጣን ተቃውሞ በዝርዝር አመልክቷል። ገለጣውን የሚጀምረው፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርገውን ጥበቃ በመግለጥ ነው፥ "ሴቲቱም ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቧት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሃ ሸሸች" (ራእይ 12፡6)። የዚህን የሦስት ዓመት ተኩል ክፍለ-ጊዜ ምንነት ምዕራፍ አምስት ውስጥ አጥንተናል። ይህ የሚያሳየው፥ በምድር ላይ ሊመጣ ያለውን ከሰባት ዓመቱ ውስጥ የመጨረሻዎቹን ሦስት ዓመት ተኩል ነው።

እስራኤላውያን በዚህ የፍጻሜ ዘመን የመሸሸጊያ ስፍራ ለምን እንደሚያስፈልጋቸው ዮሐንስ ይጠቅሳል። በሚካኤል በሚመራው የእግዚአብሔር ሠራዊትና፥ በሰይጣን ሠራዊት መካከል በሰማያት ስለሚካሄደው አስከፊ ጦርነትም ይገልጣል። ሰይጣን ለመጨረሻና ለዘላለም ከሰማይ ይወገዳል። ፍጻሜው መቃረቡን ሲረዳም፥ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ለማጥፋት ጥረቱን እጥፍ ያደርገዋል፥ "ዘንዶውም ወደ ምድር እንደተጣለ ባየ ጊዜ፥ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት" (ራእይ 12፡13)።

ዮሐንስ የሚገልጠው፥ አይሁዳውያንና የእስራኤል መንግሥት የሰይጣናዊው ተቃውሞና ጥቃት ልዩ ዒላማ የሚሆኑበትን የሦስት ዓመት ተኩሉን ክፍለ-ጊዜ ነው። ይህ ጥቃት ኢየሱስ መንግሥቱን በምድር ላይ ለመመሥረት በመምጣቱ ዋዜማ ይከናወናል። ወደፊት የሚሆነውን የዚህን የስደት ወቅት ሁኔታ ዮሐንስ በዝርዝር ገልጦታል። እርሱ ብቻ አይደለም ይህን የፍጻሜ ዘመን መገለጫ የሆነ ፀረ-ፅዮናዊነት እንቅስቃሴ የገለጠው።

ዳንኤልም እስራኤል በፍጻሜው ዘመን የሚገጥማትን መከራ አመልክቷል። በመጽሐፉ ምዕራፍ ሰባት ውስጥ፥ በእግዚአብሔር መንግሥት መምጫ ዋዜማ ላይ ምድርን ስለሚመራት አራተኛና የመጨረሻ መሪ ገልጧል። ያ መሪ ራሱን ከእግዚአብሔር ይልቅ ከፍ ከፍ ያደርጋል። የእስራኤል ሕዝብንም ለማጥፋት ይሞክራል፥ "በልዑሉም ላይ ቃልን ይናገራል፥ የልዑልንም ቅዱሳን ይሰባብራል፥ ዘመናትንና ሕግንም ይለውጥ ዘንድ ያስባል፤ እስከ ዘመንና ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም በእጁ ይሰጣሉ" (ዳን. 7፡25)። ዳንኤል ዘግየት ብሎ ይህ የፍጻሜ ዘመን መንፈሳዊ ውጊያና ስደት የሚካሄድበት መሆኑን ሲገልጥ እንዲህ ብሏል፡-

> "በዚያ ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል፤ ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ

ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል፤ በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል" (ዳን. 12፡1)።

በሐዋርያው ዮሐንስ የተጠቀሰው የመላእክት አለቃ ሚካኤል ራሱ ነው፥ መላእክቱን በመምራት በእስራኤል ላይ የሚነሣውን ሰይጣናዊ የመንፈስ ውጊያ የሚያዋጋው።

በዳንኤል ከተገለጡት አሠቃቂ ዝርዝሮች የላቀው፥ በፍጻሜው ዘመን እስራኤል የሚገጥማት ስደት ሳይሆን አይቀርም። በሂትለርና በግፈኛ አገዛዙ በአይሁዳውያን ላይ ግፍና ሥቃይ ደርሶባቸዋል። በፍጻሜው ዘመን የሚደርሰው ሁኔታ ግን ከዚያም የከፋ ይሆናል።

መሢሑ መንግሥቱን በምድር የመመሥረቻው ጊዜ ሲቃረብ፥ አይሁዳውያን ምሳሌ በማይገኝለት መከራ የሚሠቃዩበት ጊዜ የሚመጣባቸው መሆኑን ነቢዩ ኤርምያስ በጽሑፉ ገልጧል። በዚሁ ጽሑፉ ከምዕራፍ 30-33 ባለው ክፍል፥ ወደ ባቢሎን በምርኮ ለመወሰድ ለተቃረበ ሕዝብ ማጽናኛ የሚሆን ቃል አስፍሯል። ጽሑፉን የጀመረው፥ በመጨረሻ እግዚአብሔር አይሁዳውያንን ወደ ምድራቸው የሚመልሳቸው መሆኑን በማስታወቅ ነው። "እነሆ ሕዝቤን እስራኤልንና የይሁዳን ምርኮ የምመልስበት ዘመን ይመጣልና፥ ይላል እግዚአብሔር፤ ለአባቶቻቸውም ወደሰጣኋት ምድር እመልሳቸዋለሁ..." (ኤር. 30፡3)። የዚያ ዘመን ወጋገን ከመታየቱ በፊት ግን፥ በሕዝቡ ላይ የመከራ ጊዜ ይመጣል። "ወዮ ያ ቀን ታላቅ ነውና፥ እርሱንም የሚመስል የለምና፤ ያ የያዕቆብ መከራ ዘመን ነው፥ ነገር ግን ከእርሱ ይድናል" (ኤር. 30፡7)።

ከዳንኤልና ኤርምያስ ዘመን ስድስት ክፍለ-ዘመን ያህል ዘግይቶ፥ ኢየሱስ ይህንኑ መከራ ለደቀ መዛሙርቱ ገለጠላቸው። የፍጻሜው ዘመን ሁኔታዎችን እስከ ሰባት ዓመቱ አጋማሽ ማለት፥ "በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ" (ዳንኤል 9:27፥ ማቴ. 24፡15) እስከሚለው ድረስ ወስዷቸዋል። ድርጊቱ አይሁዳውያን ለሕይወታቸው ይሸሹ ዘንድ ምልክት ነው። "በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ያልሆነ፥ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና። እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ፥ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ" (ማቴ. 24፡21-22)። ይህ የሠቆቃ ጊዜ የሚያከትመው፥ ዓለም ካሸለበችበት ነቅታ፥ "የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል" (ማቴ. 24፡30) የሚለው ቃል መፈጸሙን ስትመለከት ነው። ይህ ያልተለመደ የስደት ጊዜ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ ነው የሚቆመው።

## ትንቢት ወይስ ጥላቻ?

ከላይ የተመለከትናቸው ነቢያት ሁሉ የገለጡት፥ እስራኤል ገና የሚጠብቃትን አሠቃቂ መከራ ነው። ይሁን እንጂ፥ እንዲህ ያለውን ነገር በምናውቅበት ጊዜ፥ ፀረ-ፅዮናዊነትን የምናስፋፋበት አደጋ አይኖር ይሆን? ማለት፥ የፍጻሜው ጊዜ እንዲመጣ በጣም ከመጓጓታችን የተነሣ፥ የእግዚአብሔርን ትንቢት ከማራመድ ጋር ሳይታወቀን ፀረ-ፅዮናዊነትን የማበረታታትና የማስፋፋት ተግባር እንፈጽም ይሆን?

ይህ ዝንባሌ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባይሆንም፥ ይኖር ይሆናል። ወደፊት የሚሆነውን ነገር እግዚአብሔር ነግሮን ይሆናል፤ የተነገሩት ነገሮች መቼ እንደሚሆኑ ግን አልገለጠልንም። በኢየሱስ ክርስቶስ የዳነ ሰው ዛሬ ሦስት እምነቶች ግድ ይሉታል። የመጀመሪያው፥ በዚህ ዘመን እግዚአብሔር የሰጠን ሥራ፥ በኢየሱስ ብቻ የሚገኘውን መልካሙን የዘላለም ሕይወት የምሥራች ለሌሎች መንገር ነው። እግዚአብሔር የጠራን ወራትንና ዘመናትን እንድንወስን ሳይሆን (ሐዋ. 1፡6-8)፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች እንሆን ዘንድ ነው። ሁለተኛው መታወቂያችን፥ አይሁዶችን ጨምሮ ለሌሎች ያለን ፍቅር መሆን አለበት (ዮሐ. 13፡34፤ 1ኛ ቆሮ. 13፡1-13፤ ገላ. 5፡22)። ሦስተኛ፥ የአብርሃም ዘር የሆኑ አይሁዳውያንን የሚረግሙትን ሁሉ፥ እግዚአብሔር የሚረግማቸው መሆኑን ማስታወስ አለብን (ዘፍጥ. 12፡3)። ፀረ-ፅዮናዊነትን የሚያበረታቱ፥ የሚያግዙ ወይም በድርጊት የሚሳተፉ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብን በማጥቃት ላይ ስለሆኑ፥ በርሱ የተረገሙ ይሆናሉ።

ኢየሱስ በይሁዳ መካዱን አስመልክቶ የተናገራቸው ቃላት፥ በአይሁዳውያን ላይ ቡጢያቸውን በቁጣ በሚያነሡ ሁሉ ላይ ይፈጸማሉ። ምንም እንኳን ይህ ነገር የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ አንድ አካል (የኢየሱስ ሞት እንዲሁ እንደሆነ ሁሉ) ቢሆን፥ እንዲህ ባለ ክፉ ድርጊት የሚሳተፉትን ሁሉ በደለኞች ያደርጋቸዋል፥ “የሰው ልጅስ ስለእርሱ እንደተጻፈ (ወደሞቱ) ይሄዳል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያስ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር” (ማር. 14፡21)። ፀረ-ፅዮናዊነት የእግዚአብሔርን ዕቅድ መፃረር ነው።

# > ክፍል ሁለት <

# መካከለኛው ምሥራቅ፡ የነዳጅ ዘይት፥ እስልምና እና አዲሱ ናቡከደነፆር

ፔንሲልቬንያ በተባለው የአሜሪካን ግዛት ገጠር ውስጥ ነው ያደግኩት። እዚያ ሳለሁ፥ ለጥቂት ጊዜ አንድ የከብት ማርቢያ ጣቢያ ውስጥ ሠርቻለሁ። የቀጠረኝ ገበሬ ወተቱን የሚሸጠው፥ የራሱ በሆነ መደብር ውስጥ ነበር። ወተቱን የምናዘጋጅ፥ ጠርሙስ ውስጥ የምንሞላና፥ ከማርቢያ ጣቢያው ወደ መሸጫ መደብሩ የምናጓጉዘው እኔና ሁለት የሥራ ባልደረቦቼ ነበርን። ዕድሜዬ አሥራ ስድስት ዓመት ሲሆን፥ ከሦስቱ ተቀጣሪ ተማሪዎች አንጋፋው እኔ ነበርኩ። ብዙ ሥራ ቢኖርብንም፥ ለጫወታ ጊዜ አላጣንም። የቆሻሻ ፍሳሽ መውረጃውን በመድኃኒት ማጽዳቱ፥ ማርቢያ ጣቢያ ውስጥ ከምናከናውነው የዘወትር ተግባራችን አንዱ ነበር። ቁሳቁሶቹንም እንዲሁ ቀላል አሲድነት ባለው ነገር እናጸዳለን። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኬሚስትሪ ያጠናን እንደመሆናችን መጠን፥ አሲድ፥ ከማይስማማው ነገር ጋር መቀላቀል የሌለበት መሆኑን ተገንዝ በናል። ቢሆንም፥ አሲድ ከማይስማማው ነገር ጋር ቢቀላቀል፥ የሚያስከትለውን ነገር ለማወቅ የነበረን ጉጉት አየለብንና ልንሞክረው ወሰንን። በዚሁ መሠረት አንድ የወተት ጠርሙስ ውስጥ እስከ ግማሹ ድረስ ፀረ-አሲድ የሆነ መድኃኒት ጨመርንበት። ከዚያም ጠርሙሱን ወለል ላይ አስቀመጥንና አሲድነት ያለውን ፈሳሽ አከልንበት።

ቅይጡ አሲድ እንደ መፍላት ብሎ በመጨረሻ ፈነዳ። ይህ ሲሆን በድንጋጤ ተንከባለልንና ከለላ ይዘን የተፈጠረው ነገር እስኪረጋጋ ድረስ ጠበቅን። ያኔ ነው፥ ተለዋዋጭ ባሕርይ ያላቸውን ንጥረ ነገሮች መቀላቀሉ እንዲህ ያለ ከባድ ፍንዳታ የሚፈጥር መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከትን።

## የመካከለኛው ምሥራቅ ተለዋዋጭ ሁኔታ

መካከለኛው ምሥራቅም፥ ልክ እኔና ጓደኞቼ ከብት ማርቢያው ጣቢያ ውስጥ እንደሠራነው የጠርሙስ ቦምብ፥ በመልክዓ-ምድርም ሆነ በብሔር ቅይጥነቱ ተለዋዋጭ ባሕርይ አለው። የዘረኝነት ብጥብጥና ሃይማኖታዊ ጥላቻ፥ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ እጅግ ገኗል። ዓረቦችና አይሁዶች አይዋደዱም። የዓረብ ሱኒ ሙስሊም የሚሰኙት ብዙሃንና፥ የፋርስ ሺያት ሙስሊም የሚባሉት አናሣ ቡድኖች ይበጣበጣሉ። ኩርድስ የሚባሉት ሕዝቦች የራሳቸው የሆነ ብሔራዊ ክልል ለመመሥረት ከቱርክ፥ ከሶርያ፥ ከኢራንና ከኢራቅ ጋር በየተራ በመዋጋት ላይ ናቸው። ዓረቦች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ስለ አንድነት ይናገራሉ፤ ይህን የተባበረ የዓረብ ሕዝብ ማን ይምራው? የሚለው ጥያቄ ሲነሣ ግን፥ በመልሱ አይስማሙም። እነዚህ ሁኔታዎች እያንዳንዳቸው ሌላ የመካከለኛው ምሥራቅ ግጭት ለማስነሣት ይችላሉ። ለዓለም አቀፉ ግጭት መፍትሔነት የተዘጋጀው መመሪያ፥ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ በሚፈጠሩ ሁኔታዎች ላይ ያተኩራል።

የመካከለኛው ምሥራቅ ሽብር አፈጣጠር

- -የእስራኤልን ምድር ሁለት እኩል ቦታ ለመክፈል ሞክሩና፥ ግማሹን "ለዓረቦች" ብላችሁ ለዩት። ግን ቆዩ ምንም አታድርጉበት።
- -ሺያት የተባሉ ሥር ነቀል ሙስሊሞችን እድገት በአንድ ወገንና፥ የአክራሪ አይሁዳውያንን ብሔረተኝነት በሌላ ወገን እዚህ ላይ ጨምሩበት።
- -የሳዳም ሁሴንን፥ የሙዓመር ጋዳፊንና የዓረብ ሽብርተኞችን አክሉበት
- -ከቀድሞው የሶቪየት ኅብረት ከተገነጠሉ አገሮች አንዱ የኑክሊየር መሣሪያ የማስፋፋቷን አደጋም ጨምሩበት።
- -እነዚህን ሁሉ በደንብ ይቀላቅሏቸውና ገንፍለው እስኪፈነዱ ተዉአቸው።

መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያሉት አያሌ ለውጦች፥ ከእግዚአብሔር ትንቢታዊ እንቅቅልሾች ጋር የሚስማሙት እንዴት ነው? በመከናወን ላይ ካሉት ነገሮች መካከል፥ እግዚአብሔር ለመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን የወደፊት ዕቅድ የሚጠቁሙ ምልክቶችን ለመለየት እንችላለን? ሩሲያ፥ ኢራቅ፥ ኢራን፥ ቱርክ ወይም ሊቢያ፥ እግዚአብሔር ትንቢታዊ ዕቅድ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎስ ምንድነው? እነዚህን ጥያቄዎች ነው፥ ቀጥሎ ባለው በዚህ የመጽሐፍ ክፍል የምንመረምራቸው።

በ1990ው ክረምትና በ1991ዱ ፀደይ ወቅት የዓለም ሕዝቦች ትኩረት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ዞሮ ነበር። ወቅቶቹ ትንቢት ሲፈጸም የምናይባቸው ጊዜያት መሰሉ። ይሁን እንጂ፥ የኅብረቱ ኃይል የሚባሉት አገሮች የጦር ኃይል የሳዳም ሁሴንን የጦር ኃይል ወዲያው ድል አደረገው። ሳዳም ሁሴን የሚያደርጉት የጠፋቻው መሰሉ፥ ብዙ የተነገረለት ሠራዊታቸውም ድል ሆነ። ታዲያ ይህ በሳዳም ሁሴን ላይ የተደረገ "የበረሃው ማዕበል ዘመቻ" የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት አካል ነበር ለማለት ይቻላልን?

ቀጥሎ ባለው የዚህ መጽሐፍ ክፍል፥ በአሁኑ ጊዜ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ በመከናወን ላይ ያሉ ነገሮችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት አንጻር በአዲስ መልክ እንመረምራቸዋለን። የመካከለኛው ምሥራቅ ካርታን እፊትዎ ይዘርጉ፥ መጽሐፍ ቅዱስዎንም ይግለጡና የእግዚአብሔርን ትንቢታዊ እንቅቅልሾች በተገቢ ስፍራቸው ስናስቀምጥ ይከታተሉን።

> ምዕራፍ ሰባት <

# ሩሲያ አንበሳው ጥርስ አልባ ሆኗል?

"በቀዝቃዛው ጦርነት" አስከፊ ቀናት ያደግኩ እንደ መሆኔ፥ ሶቪየት ኅብረትን አስባት የነበረው፥ አሜሪካንን በኑክሊየር መሣሪያ አማካይነት አመድ የማድረጊያ መላ እንደምትፈልግ ክፉ መንግሥት አድርጌ ነበር። ሶቪየት ኅብረት ስፑትኒክ የተባለውን መንኮራኩር ወደ ሕዋ ስትልክ የሰባት ዓመት ልጅ ነበርኩ። መምህራችን፥ ያን ግኝት የሰው ልጅ ጠፈርን በመመራመር ረገድ ያስገኘው ከፍተኛ ውጤት እንደ ነበር አድርገው አላደነቁትም ነበር። ይልቁንም የሰው ዘር አጥፊ የሆነ የኑክሊየር አደጋ ሰማይ ላይ ማንዣበቡን ነው የነገሩን። የሶቪየቶች ኩባ ውስጥ ሚሳይል መትከል በ1962 እአአ ውዝግብ ባስነሣ ጊዜ፥ ቤተሰቦቼ የጥቃት መከላከያ ምሽጎችን ለመመልከት በአቅራቢያችን ወደ ነበረች ከተማ ሄደው ነበር። ክፉዎቹ ኮሙኒስቶች በድንገት እንዳይመጡብን በትጋት መጠባበቅ ነበረብን።

እስከ 1980ዎቹ ድረስ አሜሪካን ከሶቪየት ኅብረት ጋር የሞት ሽረት ትንቅንቅ ታደርግ ነበር። በአሜሪካኑ ፕሬዝዳንት ሬጋን አስተዳደር ወቅት፥ ከኑክሊየር ጥቃት መከላከያ ለማዘጋጀት የኮከብ ጦርነቶች "ስታር ዋርስ" ለተሰኘ ዕቅድ ማከናወኛ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ተመድቦ ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ አንድ ነገር ተከሥተ። አሜሪካን የሶቪየትን ጥቃት ለመከላከል በመታጠቅ ላይ እያለች፥ የሶቪየት ኅብረት ፈራረሰች፥ እንዳልነበረች ሆነች። ዜና እረፍቷ ታኅሳስ 26 ቀን 1991 እአአ በዓለም ዜና ማሰራጫዎች ተገለጠ። አንድ ጋዜጣ የተገለጠው ዜና እንዲህ ይነበባል፡-

> "በሕልም ተስፋ ተፀንሶ፥ 'የጥቅምት አብዮት' በመባል በ1917ቱ ብጥብጥ የተወለደው ኅብረት፥ በታኅሳስ ወር ማብቂያ ላይ የመጨረሻ የጣር ትንፋሹን ተነፈሰ። የፖለቲካ ዘይቤውን ተገፈፈ፥ ተበታተነ፥ ከሰረ፥ ተራበ። በውድቀቱም እንኳን ያስደንቅ ነበር። ፍጻሜው፥ በጊዜው የኅብረቱ ፕሬዝዳንት የነበሩት ሚካኤል ጎርባቾቭ ሥልጣን መልቀቅ እና በ'ነጻ መንግሥታቱ የጋራ ብልጥግና' ውስጥ መካተት ሆነ"

## አንበሳው ዳግም ይመጣ ይሆን?

የሶቪየት ኅብረት መፈራረስ፥ ሩሲያ በዓለም ያላት ተጽዕኖ አበቃ ማለት ነውን? እንዴትም ብንመለከተው ይህ አላበቃም! የቀድሞዋ ሶቪየት ኅብረት የጦር መሣሪያዎችን፥ የመቀነሱ ዕቅድ ቢሳካ እንኳ፥ ያኔም ከማንኛውም በዓለም ካለ ባለኑክሊየር አገር ጋር ይወዳደራሉ። የባሕርና የምድር ጦሯ አሁንም ብርቱ ነው። የሩሲያ ሪፑብሊክ በአሮጌው የሶቪየት ኅብረት የበላይነት እንደነበራት ሁሉ፥ በአዲሱ የጋራ ብልጥግና ውስጥም የበላይነት ይኖራታል።

አሮጌው ኮሙኒስት የመንግሥት ሥርዓት ቢሞትም፥ ሥርዓቱ የነበረበት ምድር አለ። አገሪቱ (ሩሲያ) የተፈጥሮ ሀብት ክምችት፥ አንዳንድ አስፈሪና አውዳሚ መሣሪያዎችን የፈለሰፉና የፈበረኩ አያሌ ኢንጂነሮችና ሳይንቲስቶች ያሏት መሆኗን በኩራት ትገልጣለች። ደካማ የማጓጓዣና የማከፋፈያ አውታሮቿን ብትጠግንና፥ የፈራረሱ የአገልግሎት መዋቅሮቿን በአዲስ ሁኔታ ብትሠራቸው፥ የወደመ ኢኮኖሚዋን እንደገና ለመገንባት የሚያስችል ሀብት አላት።

## የኮሙኒስት ሥርዓት ማክተሙ ሠላምን ያስገኛልን?

ማርቪን ሴትሮን እና አውን ዴቪስ የተባሉ ሰዎች በ1991 እአአ ሲጽፉ እንዲህ ብለው ነበር፦

> ‹‹ዓለም ትመራበት የነበረ የመንግሥት መሠረት ስለተለወጠ፥ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ከነበሩት ዓመታት ይልቅ በ1990ዎቹ ዓመታት ሠላም የሰፈነባትና የበለጠገች ትሆናለች። በሚመጡት ዓመታት ለፖለቲካ ሥርዓትና ለወታደራዊ ፉክክር ሳይሆን፥ ለንግድና ለጋራ ጥቅም ለሚሠሩ አገሮች ደኅንነት በሚያመች መልኩ ትመራለች። ወታደራዊ ግጭቶች፥ የንግድ ግንኙነት ያላቸው አገሮች የጋራ ጥቅም ተፃራሪ ስለሆኑ አይታሰቡም››።

## ሌላው ጸሐፊ ደግሞ እንዲህ ብለው ነበር፦

> ‹‹በያዝነው ሺህኛ ዓመት መገባደጃ ላይ ባለንበት በአሁኑ ጊዜ፥ የቀኝና የግራ አምባገነን ፖለቲካዊ ሥርዓቶች የተጠሉ ሲሆኑ፥ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግን በመላው ዓለም የተሻለና አሸናፊ የፖለቲካ ዘይቤ ሆኖ አግኝተነዋል። ይህ እውነት አይለወጥም ብሎ ተስፋ ለማድረግ ይቻላል።››

መጽሐፍ ቅዱስ ግን፦ “ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ። ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው። ሕዝብ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና” (ማቴ. 24፡6-7) ይላል።

የአምባ ገነንና ጨቋኝ መንግሥታትን ፈጣን አወዳደቅ በ1990ዎቹ ዓመታት ተመልክተናል። በተለይ የኮሙኒስታዊው አገዛዝ መነሻ የሆነው የሶቪየት ኅብረት መፈራረስ ታላቅ ቁም ነገር ነበር። ይህ አምባገነን ሥርዓት ከጀመረበት ከ1917 አንሥቶ፥ ሥርዓቱን በዓለም ሁሉ ለማዳረስ በትጋት ይሠራ ነበር። በበለጠገችው አዲስ አገር ውስጥ ተንሰራፍቶ የነበረው ኮሙኒስታዊ ሥርዓት መንኮታኮት፥ ለመላው ዓለም የተላለፈ አስደንጋጭ መልእክት ነበረው። ታዲያ ይህን ተከትሎ ሠላም ይመጣ ይሆን?

በኮሙኒስታዊው ሥርዓት ትገዛ የነበረችው ዩጎዝላቪያ እንደ ምሳሌ የምትጠቀስ ከሆነ፥ ከላይ የተጠቀሰው ጥያቄ መልስ “አይመጣም” የሚል ይሆናል። ሶቭየት ኅብረትና አጋሮቿ በሆኑ አገሮች ውስጥ የነበረው ብርቱና ማዕከላዊ መንግሥት አንዱ ጥቅም፥ የጎሳና የሃይማኖት ግጭቶች እንዳይነሡ ለመቆጣጠር መቻሉ ነበር። መንግሥታቱ ችግሩን በልዩ ልዩ ዘዴ ለማብረድ ቢሞክሩም፥ ግጭቶቹ አሁንም አሉ፤ ጥላቻና ፍርሃት ታምቀው በሚፈነዱበት ሁኔታ ላይ ናቸው።

በኮሙኒስታዊው ሥርዓት መፈራረስ ዓለም በምትፈነጥዝበት ወቅት፥ ሌላ አደጋ ብቅ ማለት ጀምሯል። ይህ አደጋ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ያልታየ ብሔርተኝነት ነው። ወደኋላ መለስ ብለን ጥቂት ክንውኖችን ብናስታውስ፥ ያልተረጋጋ ብሔርተኝነት መኖሩን ይጠቁሙናል።

*ትውስታ ቁጥር 1፦* ጀርመን፤ ምዕራብና ምሥራቅ ጀርመን በ1990ው በጋ አንድ ሆኑ። 80 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት አዲስና የተባበረች አገር ወዲያውኑ ከአውሮፓ ብርቱ ኢኮኖሚ ያላት አገር ሆነች። አንድነቱ በሌላ አንጻር ወደ ጀርመን ብሔርተኝነትና ብጥብጥ ያመራ ጀመር። ከመጀመሪያው በናዚ አገዛዝ ዘመን ወዲህ ጀርመን በ1991 እአአ የላቀ የዘረኝነት ግጭት ተከሠተባት። የግጭቱ ቁጥር በ1992 እአአ ወደ 2,000 አደገ። በቅርቡ ከተሰጠው የሕዝብ ድምፅ ለመረዳት እንደተቻለው፥ ከጀርመን ሕዝብ ሁለት ሦስተኛው ለአይሁዳውያን ያላቸውን አመለካከት ለመግለጥ ፈቃደኞች አልነበሩም። እጅግ አስፈሪ የሆነው ነገር፥ ከ15-25 ዓመት ዕድሜ ባላቸው ወጣቶች ዘንድ “ለአዲሱ ናዚነት” ደጋፊዎች እያደገ መምጣቱ ነው።

*ትውስታ ቁጥር 2፦* ዩጎዝላቪያ፤ የኮሙኒስታዊው ሥርዓት መፈራረስ፥ ክሮትስ እና ሰርባውያን በተባሉ ወገኖች መካከል የሃይማኖት ግጭት እሣት ጫረ። ግጭቱን ለማብረድ፥ በ1991 እአአ ብቻ አሥራ አራት የተኩስ አቁም ስምምነቶች እየተደረጉ ተጥሰዋል። በግጭቱ ሳቢያ 5,000 ሰዎች ሲሞቱ፥ ቁጥራቸው ከ500,000 በላይ የሆኑ ሰዎች ለስደት ተዳርገዋል። ግጭቱን ለማስቆም ዓለም አቀም ያጣች እስኪመስል ድረስ፥ ጦርነቱ በ1992 እአአ ተባባሰ። የዩጎዝላቪያ ሕዝቦች በተመሰቃቀለ ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነው፥ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፥ የአውሮፓ የኢኮኖሚ ማኅበር ወይም ሌላ ውጫዊ ኃይል ሠላምን ያሰፍንላቸው ዘንድ ይጠባበቃሉ። አገሪቱ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው ግጭት፥ በክፍለ-ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ተቀስቅሶ እንደነበረው የጎሣ ጦርነት ቀጣፊ ሆነ።

*ትውስታ ቁጥር 3፦* አርሜኒያ እና አዘርባጃን፤ በክርስቲያን አርሜኒያውያንና በሙስሊም አዘርባጃውያን መካከል የነበረው የጎሣ ግጭት የተቀሰቀሰው በ1988 እአአ ነበር። ከዚያ ወዲህ በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ሞተዋል። ጸጥታውን ለማስከበር ሲል የሶቪየት መንግሥት ወታደሮችን ወደ ስፍራው ላከ። ይሁን እንጂ፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጠንካራውና ማዕከላዊው የሶቪየት ኅብረት መንግሥት በመፈራረሱ፥ ግጭቱ ተባባሰ። የአዘርባጃኑ ፕሬዝዳንት አገራቸው ከአርሜኒያ ጋር በጦርነት ላይ መሆኗን በማሳወቅ ችግሩን ገልጠዋል።

ሩሲያ ውስጥ የኮሙኒስት ሥርዓት ወድቋል፤ ይሁን እንጂ፥ በቦታው የተተካው የዲሞክራሲ ሥርዓት ሕዝቡን ለመመገብ ካልቻለ፥ የቀደመው ሥርዓት ዕጣ ይጠብቀዋል። በ1991 እአአ የኮሙኒስቱ ሥርዓት ክፉ ዕጣ ገጥሞት፥ ቦሪስ የልሲን የተባሉ ሰው ፕሬዝዳንታዊ ሥልጣኑን ሲይዙ፥ የደገፉቸው የሩሲያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፥ አሜሪካኖችም ናቸው። ያን ሁኔታ የተቃወሙ ሩሲያውያን ጥቂት ነበሩ። እነርሱ የሚጨነቁት ስለመንግሥታቸው ሳይሆን፥ በሰልፍ ጠብቀው ስለሚያገኙት ምግብ ዋጋ ነበር። በአዲሱ የዲሞክራሲ ሥርዓት ጊዜ የተፈጠረው ከፍተኛ የምግብ ዋጋ መናር፥ ከአሁኑ ሕዝባዊ ተቃውሞ አስነሥቷል። በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየጎዳናዎቹ እየወጡ፥ በስታሊን ዘመን ትመራ በነበረችው ሩሲያ የነበረው ዓይነት "መልካም ጊዜ" ዳግም ይመጣ ዘንድ በመጠየቅ ላይ ናቸው።

የኮሙኒዝም ሥርዓት ማብቃት ሠላምን አያመጣም፤ ምክንያቱም የዓለም ሰላም እውነተኛው ጠላት ሥርዓት ሳይሆን፥ ኃጢአት ነው። ዓለም ሠላምን ተርባለች፤ እውነተኛው ሠላም የሚኖረው ግን፥ የሠላሙ ልዑል ወደ ምድር በሚመጣበት ጊዜ ነው። የሶቪየት ኅብረት መፈራረስ ሠላምን

ለዓለም አያስገኝም። ወይም ዳቦ ለማግኘት ሞስኮ ከተማ ውስጥ የተሰለፉ ሰዎች ችግርን አያስወግድም። መሠረታዊዎቹ ችግሮች ስላልተለወጡ ዓለም መልፋቷን ትቀጥላለች።

ኪንግ እና ሰናይደር የተባሉ ሰዎች በአንድ ወቅት እንዲህ በማለት ጽፈው ነበር፦

"በዚህ ክፍለ-ዘመን መገባደጃ ወቅት ከየአቅጣጫው የሚመጡና ያልተለመዱ አያሌ ሁኔታዎች የሰውን ዘር ተጭነውታል። ይህን ለማስወገድ ዓለም ብርቱ አይደለችም። ምክንያቱም ባሕላዊ አሠራሮች፥ መንግሥታትና ተቋማት አሁን ባሉበት ሁኔታ ችግሩን መፍታቱ አይቻላቸውም። ይልቁንም እነዚህ ጥንታዊና አሁን ላለው ሁኔታ የማይስማሙ መዋቅሮች ራሳቸው ሞራላዊ ችግር ውስጥ ገብተዋል። ፋይዳ ያለው አሠራር መጥፋቱ፥ የባሕል ጉዳይ፥ የፖለቲካዊ ዘይቤ መበላሸት፥ ለምድሪቱ የሚሆን ራእይ አለመኖሩ እና አሁን ያለው ዲሞክራሲያዊ ውሱንነት ባጠቃላይ የማኅበረሰቡን ባዶነት ያረጋግጣሉ"።

ክርስቲያኖች በምድር ላይ ያሉት ጽድቅና ፍርድን በምድር እንዲያስፋፉ ነው። ጨውና ብርሃን በመሆን ይህን ጭለማና የተበላሸ ዓለም መለወጥ አለብን፤ እንችላለንም። በምድር እስካለን ድረስ የእግዚአብሔርን የወደፊት መንግሥት ሁኔታ በሕይወት ወይም በአኗኗራችን የመግለጥ ግዴታ አለብን። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ መንግሥቱን እስካልመሠረተ ድረስ፥ ዘላቂ ሠላም ሊኖር እንደማይችል እግዚአብሔር ገልጧል። ይሁን እንጂ፥ ክርስቲያኖች ይህን የእግዚአብሔር ቃል እንደ ምክንያት ቆጥረው ዛሬ ዓለምን ለመለወጥ መሞከራቸውን ሊያቋርጡ አይገባም። የዓለም ችግር መሠረታዊ ምክንያት ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ግን ይህን ሊለውጥ የሚችል መልእክት ሰጥቶናል።

## ሩሲያ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ውስጥ ተጠቅሳለችን?

የሶቪየት ኅብረትን ፈጣንና አስገራሚ አወዳደቅ የዓለም ሕዝብ የተመለከተው በመደነቅ ነው። አንዳንዶች የኅብረቱ መፈራረስ ምዕራባውያንን ትጥቅ ለማስፈታት ሲባል የተደረገ ማዘናጊያ ነው በማለት አሁንም በመጠራጠር ላይ ሲሆኑ፥ ብዙዎቹ ግን ሩሲያና ሌሎቹ ሪፑብሊኮች ውስጥ የተደረገው ለውጥ አሳማኝ ነው ይላሉ። ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት አንጻር ሲታይ ግን ይህ ምን ማለት ነው? የመጨረሻ ዘመኗን ሩሲያ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚተነብየው? ወይስ ስለ አገሪቱ የተጠቀሰ ትንቢት በጭራሽ የለም?

ብዙ ምሁራን፥ ሩሲያ የተጠቀሰችበት ነው ብለው የሚያምኑት ማዕከላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 38 እና 39 ናቸው። ሕዝቅኤል በእነዚህ ምዕራፎቹ ውስጥ የሚገልጠው፥ ጎግ በተባለ ሰው የሚመራ የተባበረ ኃይል እስራኤልን የሚወርራት መሆኑን ነው። ይህ አስገራሚ ስም ያለው ሰው ማን ነው? እስራኤልን ለመውረር ከእርሱ ጋር የሚተባበሩት አገሮችስ የትኞቹ ናቸው? አንዳንድ ሰዎች ሩሲያን ከዚህ ትንቢት አንጻር የሚመለከቷትስ ለምንድነው?

እግዚአብሔር ነው "በጎግ ላይና በማጎግ ምድር ላይ፥ በሞሳሕና በቶቤል ዋነኛ አለቃ ላይ" (ሕዝ. 38፡2) ትንቢት ይናገር ዘንድ ሕዝቅኤልን ያዘዘው። ንባቡ በመጀመሪያ ግልጥ ባይመስልም፥ ጥቅሱ ውስጥ ሩሲያ የተጠቀሰች መሆኗን አንዳንዶች አጢነዋል። አንደኛ፥ "አለቃ" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ አጠራሩ 'ሮሽ' ሲሆን፥ ትርጉሙም "ዋና" ማለት ነው። ይህ ዋና የተባለ ቃል በሰዋስው አሠራር እንደ ስም ወይም እንደ ቅጽል ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ "የዚህ ቤት ዋና ማነው?" ብንል፥ ቃሉን የተጠቀምንበት እንደ ስም ነው። "የቤተሰቡ ዋና ኃላፊ" ብንል ግን ቃሉ ያገለገለን እንደ ቅጽል ነው። ከላይ የተመለከትነው ጥቅስ፥ ይህን 'ሮሽ' የተባለ የዕብራይስጥ ቃል "ዋነኛ አለቃ" በማለት፥ "ዋነኛ" የሚለውን ቃል በቅጽል ነበር የተጠቀመበት። አንዳንዶች ግን 'ሮሽ' የሚለው ቃል እንደ ስም ማገልገል ያለበት መሆኑን ነው የሚያምኑት። በዚህ አሳብ ከተስማማን፥ ጎግ "የሮሽ ዋና ወይም አለቃ" ነው። ታዲያ ይህ "ሮሽ" የሚባለው ስፍራ የት ነው? ብዙዎች ሮሽ የሚለው መጠሪያ፥ በኋላ ሩሲያ ተብሎ ለተጠራው ስፍራ የተሰጠ ስም ነው ብለው ያምናሉ።

ሁለተኛ፤ አንዳንዶች ሩሲያ ሕዝቅኤል 38 ውስጥ ተጠቅሳለች የሚሉት፥ ነቢዩ ምንባቡ ውስጥ በጠቀሳቸው ሌሎች ስሞች ምክንያት መሆኑን ይገልጣሉ። "ሮሽ" የሚለው ቃል ሩሲያ ማለት ከሆነ፥ "ሞሳሕ" የሚለው ሞስኮ፥ "ቶቤል" የሚለው ደግሞ ቶቦልስክ (ሌላ የሩሲያ ከተማ) ሊሆኑ የማይችሉበት ምክንያት የለም። እነዚህ ከተሞች የሚገኙት ሩሲያ ውስጥ ስለሆነ፥ ሕዝቅኤል ውስጥ የተጠቀሱት ስሞች እነዚህ ዘመናዊ ከተሞች የሚጠሩባቸው ናቸው በማለት አንዳንዶች ያምናሉ።

ሦስተኛ፤ አንዳንዶች ሩሲያ ሕዝቅኤል 38 ውስጥ የተጠቀሰች መሆኗን የሚያምኑት፥ በዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ 38-39 ባለው ክፍል ውስጥ እስራኤልን ይወርራታል ተብሎ በተጠቀሰው መንግሥት መግለጫና በሩሲያ መካከል ባለው ተመሳሳይነት ምክንያት ነው። አንድ የማይበገር ኃይል ከተባባሪዎቹ ጋር በመሆን እስራኤልን ለመውረር በመዝመት ላይ

መሆኑን ነው ሕዝቅኤል የገለጠው። ሩሲያ ከቀድሞው የዋርሶ የጦር ቃል ኪዳን አገሮች ኅብረት የተውጣጣ ግዙፍ የጦር ኃይል አላት። ይህ ጦር "በሰሜን ዳርቻ" (ሕዝ. 38፡6)፥ የሚኖርና ከዚያ የሚመጣ መሆኑንም ሕዝቅኤል አመልክቷል። ለእስራኤል የሰሜን ዳርቻይቱ አገር ደግሞ ሩስያ ናት። እንዲህ ያሉ ተጣቃሽ ወይም ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው ሕዝቅኤል በጠቀሰው የንባብ ክፍል የሚተነብየው፥ የሚገልጠውም፤ ሩሲያ እስራኤልን የምትወራት መሆኑን ነው ብለው አንዳንዶች እንዲያምኑ ያደረጋቸው።

እንደ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 38-39 ያሉ ውስብስብ ምንባቦችን እንዴት ነው የምንመረምራቸው? የሕዝቅኤልን ትንቢት በመፍታት ጊዜ ቁልፉ መፍትሔ፥ በነቢዩ የተጠቀሱትን አገሮች ማንነት መረዳቱ ነው። እነዚህ አገሮች በሕዝቅኤል ዘመን የት ነበሩ? "ሮሽ" የሚለው ቃል የአገር ስም ነው? ወይስ ሕዝቅኤል ቃሉን እንደ ቅጽል ነው የተጠቀመበት? እሁን ያሉ ሁኔታዎችን ከመመርመራችን በፊት፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ቃል መፍታት ወይም መተርጎም አለብን።

ሕዝቅኤል በትንቢቱ የጠቀሳቸው አገሮች በርሱ ዘመን ነበሩ። እንደውም ሕዝቅኤል ከኖረበት ዘመን 900 ዓመት በፊት ብዙዎቹን አገሮች ሙሴ ለይቶ ጠቅሷቸዋል። ይህን ያደረገው፥ ሕዝቦች ከኖኅ ዘር የተወለዱበትን ሁኔታ ለእስራኤላውያን በገለጠ ጊዜ ነው። ሙሴ ዘፍጥረት 10፡2-5 ውስጥ የጠቀሰው ዝርዝር ሕዝቅኤል ከገለጠው ጋር ሲነጻጸር፥ ብዙ መመሳሰሎች ይታዩበታል። ሁለቱም የጋሜርን፥ የማጎግን፥ የቶቤልን፥ የሞሳሕንና የቴርጋማን ሕዝቦችን ጠቅሰዋል። ሮሽ የሚለው ስም ግን ዘፍጥረት ዝርዝር ውስጥ አልተጠቀሰም። ስለሆነም ሕዝቅኤል ይህን ስም የተጠቀመበት፥ ምናልባት ወራሪውን መሪ ለመግለጫ በቅጽልነት ሳይሆን አይቀርም። ይህ መሪ የሌሎቹ ወራሪ አገሮች "ዋነኛ አለቃ" ይሆናል።

በሙሴና በሕዝቅኤል የተጠቀሱ ሌሎች አገሮችን መመሳሰልና ልዩነት ለማጤን ብዙ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው። ጎሜር የሚለው ስም በአሦራውያን አጻጻፍ ጊሚራይ፥ በግሪክኛ ደግሞ ኪሜሮይ ተብሏል። በዚህ ስም ይጠሩ የነበሩ ሕዝቦች፥ ሲሜሪያውያን ተብለውም ነበር። ይኖሩ የነበረውም ትንሹ እስያ ውስጥ አርሜኒያ አጠገብ ነው። ማጎግ በጥቁርና ካስፒያን በተባሉት ባሕሮች መካከል የነበሩ የሲቲያን ሕዝቦች አባት ነው። እነዚህ ሕዝቦች ምሥራቅ ቱርክ፥ አርሜኒያ፥ አዘርባጃንና ጆርጂያ ተብለው በሚጠሩ አገሮችና ደቡብ ሩሲያ ጫፍ ውስጥ ይኖሩ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ሞሳህና ቶቤልን ሁልጊዜ እያዛመደ ነው የሚገልጣቸው። ሕዝቅኤል ከኖረበት ዘመን ቀደም ሲል አሦራውያን ታባል

የሚሉት ይህ ስፍራ፥ ሙስኩ ከሚሉት ቦታ ቀጥሎ መኖሩን ነበር የገለጡት። አንዳንድ ምሁራን፥ እነዚህ ስፍራዎች ዛሬ ቱርክ ተብሎ በሚጠራው አገር ምሥራቃዊ ክፍል ያሉ አካባቢዎች ናቸው ይላሉ። የሕዝቦቹ እንቅስቃሴም ከትንሹ ምሥራቃዊ እስያ ወደ ጥቁር ባሕር እንደ ነበር ነው የሚያስረዱት። ቴርጋማ ሕዝቅኤል ከጠቀሳቸው ወገኖች ውስጥ አሁን ያለ ቅሪት ነው። ቴርጋማ የጋሜር ልጅ መሆኑን ሙሴ ዘፍጥረት 10 ውስጥ ገልጧል። ሕዝቅኤል ከኖረበት ዘመን 700 ዓምታት ቀድሞ የተመዘገቡ ጥንታዊ ጽሑፎች፥ ታጋርማ በመባል የሚታወቅ ክፍለ አገርና ከተማ ዛሬ ምሥራቅ ቱርክ በሚባለው አካባቢ እንደነበር ይጠቅሳሉ።

ሕዝቅኤል፥ ምዕራፍ 38 ውስጥ የጠቀሳቸው አገሮች የት ነበሩ? አገሮቹ ዛሬ ሰሜናዊ ምሥራቃዊ ቱርክ፥ ሰሜናዊ ምዕራብ ኢራን፥ የቀድሞው የሶቪየት ሪፐብሊክ ክፍል የነበረችው አርሜኒያ እና አዘርባጃን ናቸው። ዛሬ ሩሲያ በመባል ከምትታወቀው አገር፥ በሕዝቅኤል በጠቀሰው ክልል ውስጥ የሚካተተው ቦታ ጥቂቱ ነው። በሕዝቅኤል መጽሐፍ ምዕራፍ 8 ውስጥ የተጠቀሰውን ትንቢት መተርጎም ያለብን፥ በነቢዩ የተጠቀሱትን ክልሎች ለይተን በማወቅ እንጂ፥ በትንቢቱ ከተጠቀሱ ስሞች ጋር የሚገጥሙ የመሰሉ ዘመናዊ ስሞችን በመፈለግ አይደለም። በእስራኤል ላይ የሚመጣ ወረራ ከቱርክ ግዛት፥ እንዲሁም በጥቁር ባሕርና በካስፒያን ባሕር መካከል ካለው ክልል የሚነሣ መሆኑን ሕዝቅኤል ተንብዮአል። አሁን የምትታወቀው ሩስያ ግን በሕዝቅኤል አልተጠቀሰችም።

በዚህ መልክዓ-ምድር ውስጥ የተካተቱት አገሮች እስራኤልን ለመውረር ከሌሎች ጋር እንደሚተባበሩ ሕዝቅኤል ገልጧል። ሶቪየት ኅብረት በጥቁር ባሕርና በካስፒያን ባሕር መካከል ያሉ አገሮችን የግዛቷ ክፍል አድርጋ ስለ ነበር፥ በእስራኤል ላይ በሚሰነዘረው ወረራ ተባባሪ ልትሆን ትችል ነበር። ከሶቪየት ኅብረት ተገንጥለው የጋራ ብልጥግና አገሮች በመባል አሁን የሚታወቁት አገሮችም፥ ከላይ በተጠቀሰው ክልል ውስጥ ስላሉ የወረራው ተባባሪ ይሆኑ ነበር። አሁንም ቢሆን፥ የጋራ ብልጥግናው አባል አገሮች ከአባልነቱ በማፈንገጥ በራሳቸው ውሳኔ የሚመሩ ይሆኑ ይሆናል።

የመጨረሻው መልስ ምንድነው ታዲያ? ሩሲያ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ውስጥ ተጠቅሳለችን? ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 38 ውስጥ በሰፈረው ቃል ግንዛቤ ላይ በመመሥረት፥ በአሁኑ ጊዜ የኔ መልስ በእርግጠኛነት የተጠቀሰች አይመስልም የሚል ነው። ሕዝቅኤል በዚህ ትንቢቱ ሩሲያን የሚጠቅስ አይመስልም። እስራኤልን ይወሯታል በማለት በጠቀሳቸው አካባቢያዊ ቦታዎች ውስጥም ሩሲያን አላስገባም። ሩሲያ

በሕዝቅኤል ትንቢት ውስጥ ስፍራ የሚኖራት፥ በጥቁር ባሕርና በካስፒያን ባሕር መካከል ያሉ አገሮችን እንደገና በተጽዕኖዋ ሥር ያዋለች እንደሆን ነው። በዚያ የዓለም ክፍል፥ ሁኔታዎች በፍጥነት በመለዋወጥ ላይ ናቸው፤ የየአገሮቹ ድንበር ከለላም አልተጠናቀቀም። ሕዝቅኤል፥ በእስራኤል ላይ የሚደረገው ወረራ ከየት እንደሚጀምር ይነግረናል እንጂ፥ የትኞቹ መንግሥታት አካባቢውን እንደሚቆጣጠሩና ጦርነቱንም ማን እንደሚጀምረው አይገልጥልንም።

ሩሲያ በፍጻሜው ዘመን በሚከናወኑ ነገሮች ውስጥ እጇን ታስገባ ይሆናል፤ ዋና ድርሻ ግን አይኖራትም። አገሪቱ ሕዝቅኤል 38-39 ባለው ክፍል ውስጥ ብትካተት እንኳ፥ በእግዚአብሔር አጠቃላይ ዕቅድ መሠረት በጦርነቱ ውስጥ የሚጨመረው፥ ከምድሪቱ ጥቂቱ ክፍል ብቻ ይሆናል። በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 11 ውስጥ ሕዝቅኤል 38-39 ባለው ክፍል የተገለጠውን ጦርነት ሁኔታ ይበልጥ በትኩረት እንመረምራለን፤ ጦርነቱ መቼ እንደሚደረግና የሚሳተፉበት እነማን እንደሆኑም ለማረጋገጥ እንሞክራለን። እስካሁን የመረመርነው፥ በዓመፁ ውስጥ የተካተቱትን አገሮች ዝርዝር በከፊል ብቻ ነው። በእስራኤል ላይ በሚሸረበው የወንጀል ሴራ የሚተባበሩ ሌሎች አገሮችም ገና አሉ።

> ምዕራፍ ስምንት <

# ነዳጅ ዘይት፥ የምዕራባዊው ሥልጣኔ መጠቂያ

ዓለም የነዳጅ ዘይት ጥገኛ ሆናለች። ዝቅተኛ ወጪ የሚደረግባቸው ነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዞች ሞተርን ያሽከረክራሉ፥ የሙቀት ምንጭም ይሆናሉ። የምዕራባዊው ሥልጣኔ መገለጫ ለሆኑ ተሽከርካሪዎችም ኃይል ናቸው። ከከርሠ-ምድር የተገኘ ይህ ሀብት የኅብረተሰብን ሕልውና ለውጧል። ይህ እንዲሆን ታዲያ ዋጋ ተከፍሎበታል። "የበረሃው ማዕበል" በመባል የሚታወቀው ጦርነት መንሥኤው የነዳጅ ዘይት ጉዳይ ነበር። የምጣኔ ሀብታችን አንቀሳቃሽ ኃይል ነዳጅ ዘይት ነው።

አንድ ሰው እንዲህ በማለት ጻፉ፡-

"የገንዘብ አስተዳዳር ወይም እንቅስቃሴ፥ ወደ ተገቢው እድገት ለማምራት ያስችላል የሚለው እምነት ሊወገድ ይገባል። በሌላ በኩል ግን፥ ነዳጅ ዘይት የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ኃይል ነው። ገንዘብ ያለው ድርሻ ነዳጅን መወከል ብቻ ይሆናል። አሁን ባለንበት የእድገት ደረጃ፥ በነዳጅ ኃይል እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ መፍጠር ያስፈልጋል የሚል ብርቱ ክርክር አለ።"

የነዳጅ ኃይል በ1990ዎቹ መገበያያ ገንዘብ ከሆነ፥ ነዳጅ፥ የገንዘቡን ደረጃ የሚወስን መመዘኛ፥ መካከለኛው ምሥራቅ ደግሞ የዚህ መመዘኛ ክምችት ነች። ዓለም ካላት የነዳጅ ሀብት ክምችት ግማሹ የሚገኘው በፋርስ ባሕረ-ሰላጤ አካባቢ አሸዋ ሥር ነው። አንድ አራተኛው ክምችት በሳውዲት ዓረብ፥ የቀረው አንድ አራተኛ ክምችት ደግሞ ኩዌትና ኢራቅ ከርሠ-ምድር ውስጥ ይገኛል። መካከለኛው ምሥራቅ በሁለት ነገሮች ይታወቃል- በነዳጅ ሀብት እና ባለመረጋጋት።

የምዕራቡ ሥልጣኔ የነዳጅ ኃይል ጥገኛ መሆን አሳዛኝ ክሥተት ግልጥ የሆነው በ1973 እአአ ነው። እስራኤል የ'ዮም ኩፐር' (አይሁዳውያን በጾምና በጸሎት የሚያከብሩት መንፈሳዊ በዓል)፥ ጦርነት በመባል በሚታወቀው ውጊያ ላይ በነበረች ጊዜ፥* የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት እርዳታ በማቅረብ ሊደግፉት ወስኖ ነበር። የሙስሊም አገሮች ይህን ተቃውመው የነዳጅ ምርታቸውን በመቀነስና በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ላይ የነዳጅ ሽያጭ ማዕቀብ በማድረግ የበቀል እርምጃ ወሰዱ። በአንድ ቀን የነዳጅ ዋጋ በአራት እጥፍ አሻቀበ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ አሜሪካውያን በነዳጅ ማደያ ጣቢያዎች ዙሪያ በመሰለፍ ረጅም ጊዜ

* ጥቅምት፥ 1973 እ.አ.አ.

ያሳልፉ ጀመር። ማዕቀቡ የኋላ ኋላ ቢቆምም እንኳ፥ የነዳጅ ዋጋ ማሻቀቡን ቀጥሎ ነበር። በ1970ዎቹ ዓመታት መጨረሻ፥ የነዳጅ ዋጋ በ1973 እአአ በፊት ከነበረው አሥር እጥፍ ሆነ።

## ከነዳጅ ዘይት ጥገኝነት ለመላቀቅ የተደረገው ሙከራ መክሸፍ

የነዳጅ ዋጋ በድንገት ማሻቀብ፥ አገሮች ወደ ነዳጅ ክምችት ፍለጋ እንዲያተኩሩ አደረጋቸው። በነዳጅ ፍጆታቸው የታወቁት የ1970ዎቹ ተሽከርካሪዎች ከአሜሪካን ጎዳናዎች እየጠፉ፥ በምትካቸው ነዳጅ ቆጣቢዎቹ ብቅ ማለት ጀመሩ። የነዳጅ ዋጋ ማሻቀብ፥ ራቅ ባሉ የዓለም ክፍሎች የነዳጅ ፍለጋ እንዲደረግ አስገደደ። በዚሁ መሠረት በ1975 እአአ "ከሰሜን ባሕር" ነዳጅ ዘይት ይመረት ጀመር። በ1977 እአአ አላስካ ከተባለው የአሜሪካን ምድር ራቅ ወዳሉት የአገሪቱ አካባቢ በቧንቧ ተላከ። በዚህም ሳቢያ ዩናይትድ ስቴትስና አውሮፓ ከመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት ጥገኝነት ይላቀቁ ጀመር።

ምዕራባውያን ያደረጉት ይህ ብቻ አይደለም፤ ከነዳጅ ፍለጋና ኃይል ቆጠባ በተጓዳኝ፥ ሌላ አማራጭ የኃይል ምንጭ ጨበጡ፤ በተለይም የኑክሊየር ኃይል። አውሮፓውያን በዝቅተኛ ወጪ የኑክሊየር ኃይል የማምረት ፕሮግራማቸውን ያፋጥኑት ጀመር። በዚሁ መሠረት በ1980 እአአ ዓለም ካላት የኑክሊየር ኃይል ማመንጫ ግማሹ በአውሮፓ ይገኝ ነበር። ዩናይትድ ስቴትስም ምንም እንኳን ከአካባቢው አየር ጥበቃ ቡድኖች የሚገጥማት ተቃውሞ ሥራውን ቢያጓትትባት፥ በኑክሊየር ኃይል መጠቀሚን በስፋት ገፋችበት። የኑክሊየር ኃይል ከውጭ ከሚመጣ የነዳጅ ጥገኛነት መላቀቂያ አንድ መፍትሔ በመሆኑ፥ አሁንም ብዙዎች ያመሰግኑታል።

ይሁን እንጂ፥ በ1980ዎቹ የተከሠቱ ሁለት ሁኔታዎች ምዕራቡ ዓለም ከውጭ ከሚመጣው የነዳጅ ዘይት ጥገኝነት ለመውጣት የሚያደርገውን ጥረት አሰናከሉት። የመጀመሪያው የነዳጅ ዘይት ፍለጋ ማደግ የዓለምን የነዳጅ አቅርቦት ከሚፈለገው በላይ አደረገውና፥ ፈጣን የነዳጅ ዋጋ ማሽቆልቆል ተፈጠረ። የነዳጅ ከሚፈለገው በላይ መመረት፥ የአምራቾቹን አገሮች ኅብረትም* አናጋው፤ ምዕራባውያን ወደ አገራቸው

* ኦፔክ የነዳጅ ላኪ አገሮች ድርጅት (O.P.E.C) ይህ ድርጅት የተመሠረተው እ.አ.አ. በ1960 ነው። በአሁኑ ጊዜ 11 አባል አገሮች ይገኙበታል። እነርሱም፤ ኢራን፥ ኢራቅ፥ ኳታር የተባበሩት አረብ ኢመሬት፥ ሳውዲ አረቢያ፥ ኩዌት፥ አልጀሪያ፥ ናይጀሪያ፥ ሊቢያ እና ቬንዙዌላ ናቸው። እነዚህ አገሮች በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያለውን 40%የነዳጅ ፍጆታ አቅራቢዎች ናቸው።

ከሚገባ ነዳጅ ጥገኛነት ለመላቀቅ የሚያደርጓቸውን ጥረቶችም አሰናከለ። ምዕራባውያኑ ኩባንያዎች ነዳጅ ዘይትን የሚተካ አማራጭ ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት አቋረጡ፤ የነዳጅ ዘይት ፍለጋም ተጓተተ። የነዳጅ ድፍድፍ ዋጋ በበርሜል ወደ 20 የአሜሪካን ዶላር ዝቅ አለ። ይህ ሁኔታ በአገር ውስጥ ኃይል ከማመንጨት ይልቅ፤ ከውጭ ማስገባቱ የተሻለ እንደሚሆን አረጋገጠ። በዚህም የተነሣ ምዕራቡ ዓለም ከውጭ በሚመጣ ነዳጅ ዘይት ላይ ጥገኛ የመሆኑ ነገር እንደገና ይጨምር ጀመር።

በ1980ዎቹ የተከሠተው ሌላ ችግር፥ የኑክሊየር ኃይል ለደኅንነት ያሠጋል፤ ማምረቱም ውድ ነው የሚለው ፍርሃት ከፍ ማለቱ ነበር። በመጋቢት ወር 1979 እአአ አሜሪካውያን የኑክሊየር ኃይልን አደገኛነት የተገነዘቡበት አንድ ሁኔታ ተፈጠረ። ፔንስልቫኒያ በተባለው ግዛት ውስጥ ከነበረ ቁጥር ሁለት የኑክሊየር ማመንጫ ያመለጠና ሬዲዮ አክቲቭ የተሰኘ መርዘኛ ንጥረ-ነገር በአካባቢው አየር ላይ ናኘ። የኑክሊየር ኃይል በሰው ወይም በመቆጣጠሪያ መሣሪያ ስሕተት ሊፈነዳና ጥፋት ለማድረስ የሚችል አሳሳቢ ነገር ሆነ።

ከሰባት ዓመት በኋላ በሶቪየት ኅብረት የነበረው የኑክሊየር ኃይል ማቢያ በድንገተኛ በተከናወነ ስሕተት ፈነዳ። ሚያዝያ 26 ቀን 1986 እአአ ሶቪየት ኅብረት ውስጥ የሚገኘው ቼርኖቤል የኑክሊየር ኃይል ማመንጫ ፍንዳታ ደረሰበት። በዚህ ጊዜ የኑክሊየር ብናኝ ወደ አየር ተነነና በመላው አውሮፓ ላይ ዘነበ። የሶቪየት ኅብረት መንግሥት ቼርኖቤል ውስጥና በአካባቢው የሚኖሩትን ሰዎች ወደ ሌላ ስፍራ አዛወራቸው፤ ድርጊቱ ግን ለብዙዎቹ በጣም የዘገየ ነበር። በመሆኑም፥ በኑክሊየሩ ጨረር ሳቢያ በሚፈጠር የካንሰር በሽታ የሞቱት ሰዎች ቁጥር፥ በአጠቃላይ ከአሥር ሺዎች በላይ እንደነበር ይገመታል። ይህ የቼርኖቤል ጥፋት፥ በኑክሊየር ኃይል ለመጠቀም በነበረው ተስፋ ላይ ጭለማ አጠላበት።

የነዳጅ መርከስና የኑክሊየር ጥፋት ምዕራባውያን ከውጭ ከሚያስመጡት የነዳጅ ዘይት ጥገኝነት ለመላቀቅ የሚያደርጉትን ጥረት አሰናከለው። ከቼርኖቤሉ ጥፋት አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በ1980 እአአ ነው፤ በአሜሪካ ምክር ቤት ተመሥርቶ የነበረው ሰው-ሠራሽ ነዳጅ ኮርፖሬሽን ተግባሩን ያቋረጠው። የነዳጅ ዘይት ዋጋ ማሽቆልቆል ነበር የኮርፖሬሽኑን ዕቅድ ማስፈጸሚያው ዋጋ ውድ ያደረገውና ያስቆመው።

## የበረሃው ማዕበል ዘመቻ

1990ዎቹ ዓመታት ሲገቡ፥ የምዕራቡ ዓለም ከውጭ የሚመጣ ነዳጅ ጥገኛ የመሆኑ ነገር እየጨመረ መጣ። ዩናይትድ ስቴትስ በአሁኑ ጊዜ

ለፍጆታዋ ከሚያስፈልጋት ነዳጅ አንድ አራተኛውን ያህል የምታገኘው ከመካከለኛው ምሥራቅ ነው። በመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ጥገኛ የመሆኑ ነገር አስተማማኝ አለመሆኑ ሳዳም ሁሴን በነሐሴ ወር 1990 እአአ ኩዌትን በወረሩ ጊዜ ታይቷል። እኚህ ሰው ከዓለም ነዳጅ ክምችት አሥራ ሁለት በመቶውን ከመቆጣጠር አልፈው፥ በሀያ አራት ሰዓት ውስጥ ሀያ አምስት በመቶውን ወደ መቆጣጠር ተሸጋገሩ። በጊዜው ይበልጥ አስፈርቶ የነበረው ነገር፥ ሰውዬው ኩዌትን በመውረር ብቻ ሳያበቁ፥ ሳውዲ ዓረቢያንም ይወራሉ የሚለው ሥጋት ነበር። ይህ ፍርሃት ነው የነዳጅ ዘይትን ዋጋ በ1990 እአአ ከአሥራ ስድስት የአሜሪካን ዶላር፥ ወደ አርባ ሁለት ዶላር እንዲመነጠቅ ያደረገው።

የተባበሩት የጦር ቃል ኪዳን አገሮች ጣልቃ ገብነት ሰውዲ ዓረቢያን ከወረራ ተከላከሉ ኩዌትንም ታደጋት። ከሁሉም ይልቅ የበረሃው ማዕበል ዘመቻ ያደረገው ታላቅ ነገር፥ ወደ ምዕራቡ ዓለም ይላክ የነበረው ነዳጅ እንዳይቋረጥ መከላከሉ ነበር። ይሁን እንጂ፥ ከውጭ የሚመጣ ነዳጅ ዘይት ጥገኞች መሆናችን የቱን ያህል ለጉዳት የሚያጋልጠን እንደሚሆን ከደረሰው ሁኔታ ተምረናል? መልሱ አልተማርንም ነው። ገና ጦርነቱ ሳያበቃ ነበር የነዳጅ ዘይት ዋጋ ቀድሞ ወደነበረበት ያሽቆለቆለው። ከኩዌት መወረር በኋላ ለጥቂት ወራት አንሰራርቶ የነበረው የነዳጅ ፍለጋ፥ የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዋጋ ሲወርድ፥ በፍጥነት ቀነሰ። ባጠቃላይ፥ ምዕራቡ ዓለም ጊዜያዊ ድንጋጤ የደረሰበት ቢሆንም፥ የፍርሃቱን ምክንያት ወዲያው ነው የረሳው።

ከበረሃው ማዕበል ዘመቻ በኋላ አሜሪካን ፈጣን የስሜት መለዋወጥ ታይቶባታል። ጦርነቱ እንዳበቃ የቃል ኪዳን አገሮች ኃይላት በድል ፈነጠዙ። የሳዳም ሁሴንን ሠራዊት ደምስሰን ኩዌትን ነጻ አወጣናት። የጦር መሣሪያዎቻችን ረቂቅነትና የበላይነት ከጠበቅነው በላይ አረካን። ከቬትናም ጦርነት ወዲህ አጥልቶብን የነበረው ሥጋት፥ በጥንቱና ባንዲራ በማወዛወዝ በሚገለጥ አርበኝነት ስሜት ተተካ አሉ።

የመጀመሪያው ድላችን ጥልቅ የሠላም ፍላጎትን ፈጠረ። ሳዳም ሁሴን አጣብቂኝ ውስጥ ስለገቡ በጥቂት ጊዜ ይወገዳሉ ብለን ነበር። በእስራኤልና በጎረቤቶችዋ መካከል ሠላም የመኖሩ ነገር እርግጠኛ ነው ባይባልም፥ ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ ሆነ። ምሥራቅ አውሮፓንና ሶቪየት ኅብረትን የለወጠው አዲስ የዓለም ሁኔታ፥ መካከለኛው ምሥራቅንም ይለውጠዋል የሚል ንግርት በ1991 እአአ በጋ ተፈጥሮ ነበር።

አለመታደል ሆነና ተስፋው ወዲያውኑ ወደ ተስፋ መቁረጥ ተለወጠ። ሳዳም ሁሴን የሚወገዱ ሰው አልሆኑም። የመካከለኛው ምሥራቅ

የሠላም ንግግር፥ የተለያዩ ቡድኖች አሠራርን በተመለከቱ ጥቃቅን ልዩነቶች ሳቢያ በፈጠሩት ጭቅጭቅ እጅግ ተጓተተ። የበረሃው ማዕበል ዘመቻ ኢኮኖሚውን ዋጋ ያስከፍለው ጀመር። በዚህ ሳቢያ አሜሪካን በገንዘብ ችግር ተጠፈረች። ለጦር ኃይሉ የሚደረገው ወጪ መቀነስና የአገሪቱ ኢኮኖሚ እያዘቀዘቀ መሄድ፥ ነጻውን ዓለም የመምራቱ ኃላፊነት የሚያስከፍለውን ከባድ ዋጋ ብዙ አሜሪካውያን እንዲገነዘቡ አደረጋቸው። ሳዳም ሁሴንን ቻል በማለት፥ አሜሪካ በራሷ ችግር ትጨነቅ ጀመር። ይሁን እንጂ፥ ከዚህ ሁሉ በኋላ አንዳች የተለወጠ ነገር ነበር?

አንድ ሰው እንዲህ ጻፈ፦

"የኃይል ምንጭ ፍላጎት ምን ተስፋ አለው? በአሁኑ ጊዜ ትርፍ የነዳጅ ኃይል ክምችት ቢኖርም፥ ይህ ሊታደስ የማይቻል ክምችት፥ በብዛትና በርካሽ ይቀርብ የነበረበት ረጅም ጊዜ ወደ ማክተሚያው በመቃረብ ላይ ነን።"

## ነዳጅ ዘይትና የመጨረሻዎቹ ጊዜያት

እግዚአብሔር ለመጨረሻዎቹ ጊዜያት ባለው ዕቅድ ውስጥ ነዳጅ ዘይት ይገባልን? የዚህ ጥያቄ መልስ ከሁለት አቅጣጫ ሊታይ ይገባል። የመጀመሪያው፥ በእግዚአብሔር ትንቢታዊ ዕቅድ ውስጥ ነዳጅ ዘይት መጠቀሱን መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ የሚነግረን ነገር መኖር አለመኖሩን መመርመር ነው። ሁለተኛ፥ ከነዳጅ ዘይት ጋር ሊዛመድ የሚችልና በተዘዋዋሪ ወይም በምሳሌ የተጠቀሰ አንዳች ነገር መኖሩን ልንመረምር ይገባል።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፥ ዘዳግም 33 ውስጥ ያለውንና "አሴር በልጆች የተባረከ ይሁን፥ በወንድሞቹ የተወደደ ይሁን፥ እግሩንም በዘይት ውስጥ ያጥልቅ" (ዘዳ. 33፡24) የሚለውን ቃል ይጠቅሱና፥ ከእስራኤል ምድር ነዳጅ ዘይት እንደሚወጣ የተነገረ ትንቢት አለ ይላሉ። በዚህ ትንቢታዊ ቃል ላይ በመመሥረት አንዳንድ ሰዎች ሰሜናዊ እስራኤል ውስጥ ነዳጅ ዘይት ለመፈለግም ሞክረዋል። ይሁን እንጂ፥ ዘዳግም 33 ውስጥ የተጠቀሰው ቃል የሚናገረው ስለ ነዳጅ ዘይት ነው ብለው ያመኑ ተሳስተዋል። በሙሴ የተተነበየው ዘይት የወይራ ዘይት እንጂ፥ ነዳጅ አልነበረም። እንደ ያዕቆብ ሁሉ፥ ሙሴም የአሴር እንጀራ ወፍራም እንደሚሆን፥ ወይም የተትረፈረፈ ምርት እንደሚኖረው ተናግሯል (ዘፍጥ. 49፡20ን ይመልከቱ)።

የመካከለኛው ምሥራቅን የነዳጅ ዘይት ምርት የሚመለከተው ቀጥተኛ ጥቅስ የሚገኘው፥ ዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ነው። ሙሴ ስለ

ባቢሎን ግንብ መገንባት በገለጠ ጊዜ፥ ሠሪዎቹ "ጡብም እንደድንጋይ . . . የምድርም ዝፍት እንደጭቃ. ." (ዘፍጥ. 11፡3) የተጠቀሙ መሆኑን አስረድቷል። የጥንታዊቱ ሜሶፖታሚያ ግንበኞች ቅጥራን ወይም ሬንጅ የመሰለ ወፍራም ነዳጅ ዝፍትን እንደ ሲሚንቶ ይጠቀሙ ነበር። ስለሆነም በጥንታዊው መካከለኛ ምሥራቅ የነዳጅ ዝፍት ወይም ድፍድፍ፥ ከነዳጅነቱ ይልቅ ለግንብ ሥራ ነበር ይበልጥ የሚያገለግለው።

ነዳጅ ዘይት በዘመን ፍጻሜ ዋዜማ ዋነኛ ሚና የሚኖረው መሆኑን የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት በግልጥ አልተናገረም። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ያለ አግባቡ እንዳንጠቀምበት ልንጠነቀቅ ይገባል። ይህ እንዳለ ሆኖ፥ ነዳጅ ዘይት በፍጻሜው ዘመን ዋነኛ ሚና የሚኖረው መሆኑን በተዘዋዋሪም ቢሆን የሚያመለክቱና፥ እኛም ይህን እንድናጤን የሚረዱን ምንባቦች ወይም ጥቅሶች ይኖራሉ? የነዳጅ ዘይትን ጠቃሚ ድርሻ የሚጠቁሙ የፍጻሜው ዘመን ሁኔታዎችን መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጥ መሆኑን አምናለሁ። ምክንያቱም አንደኛ፥ በፍጻሜው ዘመን ዋዜማ ላይ ባቢሎን ብርቱ እንደምትሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይተነብያል። በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 10 ውስጥ ይህን አሳብ እንመለከተዋለን። በአጭሩ ለመግለጥ ያህል ግን እውነተኛዋ የባቢሎን ከተማ እንደገና እንደምትሠራና በፍጻሜው ዘመን የምትጫወተው ከፍተኛ ሚና እንደሚኖር መጽሐፍ ቅዱስ ይተነብያል። የራእይ መጽሐፍ ከተማይቱ የአስደናቂ ብልጥግና ማዕከል እንደምትሆን ሲገልጥ፥ "የምድር ነጋዴዎች ከቅምጥልነትዋ ኃይል የተነሣ ባለጠጋዎች ሆኑ" (ራእይ 18፡3) ይላል። እነዚህ ነጋዴዎች ለከተማይቱ የሚሸጡትን የቅንጦት ቁሳቁስ ናሙናዎች በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 12-13 ባለው ምንባብ ውስጥ ዮሐንስ እንዲህ በማለት ገልጧቸዋል፥ "የመርከብም መሪ ሁሉ፥ በመርከብም ወደማናቸውም ስፍራ የሚሄድ ሁሉ፥ መርከበኞችም፥ ከባሕር የሚጠቀሙ ሁሉ" (ቁ. 17)፥ ስለ ከተማይቱ መውደቅ ያዝናሉ። የኀዘናቸው ምክንያት፥ ሰዎቹ ". . .የነገዱ፥ በእርስዋም ባለጠጋ የሆኑ" ስለነበሩ ነው። አሁን ግን፥ "ይህን የሚያህል ታላቅ ባለጠግነት በአንድ ሰዓት ጠፍቷልና" (ራእይ 18፡17-19)።

ደቡባዊ ኢራቅ ውስጥ ያለችው ባቢሎን፥ በመጨረሻው ዘመን ወደ ዓለም አቀፍ ተሰሚነትና ኃያልነት የምትደርስ መሆኗን መጽሐፍ ቅዱስ ይተነብያል። ከዓለም ዙሪያ የሚመጡ የቅንጦት ዕቃዎችን ለመግዛት በቂ ገንዘብ ይኖራታል። የምትፈልገውን ነገር ሁሉ የሚያቀርቡላት የዓለም ነጋዴዎች ሁሉ መልካም ገቢ ያገኛሉ። ይሁን እንጂ፥ የዮሐንስ ገለጣ ስለ አሁኒቱ ባቢሎን ካለን ግንዛቤ ጋር አይጣጣምም። ኢራቅ በሀያኛው ክፍለ ዘመን የፈራረሰች አይደለችምን? መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ውስጥ

ከተገለጠችበት ደረጃዋ ፍጹም በማትደርስበት ሁኔታስ አልተሸመደመደችም?

ኢራቅ ስለደረሰባት ጉዳት የነበረን ግምት የተሳሳተ ነው። የሳዳም ሁሴን ብዙ ሠራዊት በቃል ኪዳን ኃይላት ቢደመሰስም፥ ገና ብዙ አለ። ብዙውን የጦር መሣሪያ የማምረት ችሎታቸው ግን ወድሟል። ሳዳም ሁሴን ግን የተደበቁ የኑክሊየርና የኬሚካል መሣሪያዎቻቸውን ለመፈተሽ ከተሠማሩ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መርማሪዎች ጋር ድብብቆሽ በመጫወት ላይ ናቸው። መንግሥታቸው ይወድቃል ብለን ነበር፥ ተስፋ እንዳደረግነው አልሆነም። ይልቁንም የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ በሕዝብ ድምፅ መሠረት ሥልጣን ሲለቁ፥ ሳዳም ሁሴን ግን አሁንም በሥልጣናቸው ላይ ናቸው። ኢራቅ ትጎሳቆል እንጂ፥ አሁንም አለች።

ታዲያ ኢራቅ ቀድሞ ወደነበረችበት ቶሎ ትመለስ ይሆን? የአሜሪካን መንግሥት እያንዳንዱን የሳዳም ሁሴን እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ባይከታተል ኑሮ፥ ኢራቅ ቀድሞ ወደነበረችበት ትመለስ ነበር። ያም ቢሆን ታዲያ አሁንም ሳዳም ሁሴን ቢፈልጉ ኩዌትን እንደገና ወርረው ለመያዝ የሚያስችል ወታደራዊ ኃይል አላቸው። የአሜሪካን እርዳታ ባይደርስላት ኑሮ ሳውዲት ዓረቢያም ለሳዳም ወረራ ትጋለጥ ነበር። ሳዳም ሁሴን ወይም እርሳቸውን የሚተካ ሰው፥ ግማሹን የዓለም ነዳጅ ክምችት ለመቆጣጠር ቢችሉ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን ዓለም አቀፍ ሀብትና ኃይል ወዲያውኑ ይይዙ ነበር። ይህ የሚሆነው፥ የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይትን ለመቆጣጠር ሲቻል ብቻ ይመስላል። መጽሐፍ ቅዱስ ነዳጅ ዘይትን በግልጥ ባያመለክትም፥ ዛሬ በምናውቀው ላይ በመመሥረት፥ ባቢሎን የዓለምን ሀብትና ሥልጣን ለመጨበጫ በመሣሪያነት የምትጠቀምበት ይመስላል።

እግዚአብሔር የዓለምን ሀብቶች በመለኮታዊ ጥበቡ ፈጥሯል፤ ሉዓላዊ ዕቅዱን ለመፈጸም በታሪክ ውስጥ በመሥራት ላይ ነው። የፍጻሜው ጊዜ በመካከለኛው ምሥራቅ ሁኔታዎች ዙሪያ እንደሚሽከረከርም ተንብይዋል። ዓለም ጥገኛ የምትሆንበትን አንድ ሀብትም መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ አስቀምጣለች። ይህ በአጋጣሚ የሆነ ነውን? ይሆን ይሆናል። በሰው ልጅ ታሪክ፥ በተለይ በአሁኑ ጊዜ፥ ዓለም የነዳጅ ዘይት ጥገኛ መሆኗ ግን አጋጣሚ አይመስልም። የዘመኑ ፍጻሜ እየቀረበ እንደ መምጣቱ መጠን፥ በትንቢት የተጠቀሱ ነገሮች መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ሲፈጸሙ በመመልከት ላይ ነን። የነዳጅ ዘይት ፖለቲካዎች ከብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ጋር ይገጣጠማሉ።

> ምዕራፍ ዘጠኝ <

# እስልምናና የዓረቦች አንድነት አፈ ታሪክ

ሌላው የኢራቅ እምነት፥ "ዓረቦች በኦቶማን አገዛዝ ዘመን* ተሠቃይተዋል። ከዚያ ወዲህ ደግሞ በምዕራባውያን ቅኝ አገዛዝ አማካይነት መገፋት፥ መከፋፈልና ጭቆና ደርሶባቸዋል። ማንነታቸውን የማዛባት ሙከራም ተደርጎባቸዋል። ይህ ሁሉ ቢደርስባቸውም፥ የአንድነቱ መሠረት የሆኑት ሁኔታዎች ግን ብርቱና ደኅና ሆነው ኖረዋል። የዓረቡ ዓለም በመንግሥትነት ቢከፋፈልም፥ አንድ አገር ሆኖ ይኖራል። ከምድሪቱ በአጥቅ የምትለካው ብትሆንም እንኳ፥ በብሔርተኝነት፥ በተለይም የዓረቦች ብሔራዊ ጸጥታን በሚመለከት ትኩረት ልትታይ ይገባል። የዚህን ወይም የዚያኛውን የዓረብ አገር ጥቅምና መብት በምናስብበት ጊዜ ጠባብነትንና ራስ ወዳድነትን ማስወገድ ይኖርብናል። የዓረቦች ከፍተኛ ጥቅሞች፥ እንዲሁም ለዓረቦች ደኅንነት የሚበጁ የሩቅ ጊዜ ትልሞች፥ በአእምሯችን ሊኖሩና እርስ በርሳችን በምናደርገው ግንኙነት ውስጥም ዋናውን ስፍራ ሊይዙ ይገባል" የሚል ነው።

የኢራቁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፥ ታሪክ አዚዝ ይህን ብርቱ ማሳሰቢያ ለዓረቦች ኅብረትና ጸጥታ ጉባዔ ካቀረቡ ሁለት ሳምንት በኋላ ነው፥ የኢራቅ ታንኮችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች የኩዌትን ድንበር ጥሰው የገቡት። ነሐሴ 2 ቀን 1990 እአአ ኢራቅ ደካማ ጎረቤቷን መውረሯ፥ የዓረቦችን የአንድነት አፈ-ታሪክ ሐሰት አደረገው። ከዚያ በኋላ የተደረገው የእርስ በርስ መወጋገዝና ግጭት ዓረቦችን እርስ በርስ አቃቃራቸውና፥ "አረመኔ" ከሚሉት የምዕራቡ ዓለም ጋር በመተባበር ሙስሊም ወንድሞቻቸውን ይቃወሙ ጀመር። የዓረቦች አንድነት ምን ነካው?

---

* የኦቶማን ግዛት የተመሠረተው ኦስማን (ወይም ኦትማን) በተባለ ሰው አሁን ቱርክ በሚባለው ስፍራ በ1288 ዓ.ም. ሲሆን፥ አገዛዙ ያበቃውም በ1922 ዓ.ም. ነበር። ይህም በታሪክ ከሚታወቁት ግዛቶች ሁሉ ይበልጥ ሰፊና ረጅም ዕድሜ የነበረው ነው። ቀድሞ የሮም፥ የግሪክ፥ የባቢሎን፥ የፋርስ፥ እና የግብፅ ከነበሩ ግዛቶች ብዙዎቹን ያጠቃልል ነበር።

ደቡብ ምሥራቅ አውሮፓ ከ1345-1541 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በኦቶማን ቁጥጥር ስር ሆነ። ቀጥሎም ወደ ምሥራቅና ደቡብ በመስፋፋት ከ1512-1566 ዓ.ም. ሶርያ፥ ፍልስጥኤም፥ ግብፅ እና ዓረቢያን በግዛቱ ውስጥ አካተተ። ሱሌማን ቀዳማዊ፥ አርሚኒያ፥ ሜሶፖታሚያ፥ የመን፥ የፋርስ ባሕረ ሰላጤን፥ እንዲሁም አልጄሪያና ቱኒዝያን ጨምሮ አፍሪካን ወረረ።

በ1516 ዓ.ም. ኦቶማኖች በኢትዮጵያ ብቅ በማለት በመጀመሪያ አንዳንድ የኤርትራ ክልሎችን በቁጥጥራቸው ስር ከማድረጋቸውም በላይ ግራኝ መሐመድ ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ተባብረውታል።

## የዓረቦች አንድነት አፈ ታሪክ

አሜሪካ ስለ መካከለኛው ምሥራቅ ያላት ግንዛቤ፥ በአካባቢው ያሉ ሁኔታዎችን አጠቃላይና ተለዋዋጭ እንደሆኑ አድርጎ በመረዳት፥ በተሳሳተ ዜና፥ በጥላቻና በጥርጣሬ ላይ የተመሠረተ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት በተደረገ አንድ ጥናታዊ ፍተሻ ጊዜ፥ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ተሳታፊዎች ብዙዎቹ፥ የፋርስ ባሕረ-ሰላጤ የሚገኝበትን ስፍራ ለመግለጥ አልቻሉም። (የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት ስለ መልክዓ-ምድር ያለንን እውቀት እንድናዳብር ረድቶናል።) ከአሜሪካን ሕዝብ ከሞላ ጎደሉን ስለ መካከለኛው ምሥራቅ ሕዝቦች የሚያውቁትን እንዲገልጡልዎ ቢጠይቋቸው፥ እንዲህ የሚል መልስ ያገኛሉ። የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝቦች፥

- ዜግነታቸው ዓረብ፥
- ሃይማኖታቸው ሙስሊም፥
- በነዳጅ ዘይት ምክንያት ባለጠጎች የሆኑ፥
- ቴክኖሎጂያዊ እውቀታቸው ያልዳበረ፥
- አሜሪካንን እጅግ የሚጠሉ።

ከእነዚህ መልሶች የትኛውም ትክክል አይደለም። አሜሪካኖች ስለ መካከለኛው ምሥራቅ ያላቸው ግንዛቤ ባብዛኛው የተመሠረተው፥ "በአርእስተ ዜናዎች" እና በአገሪቱ ባለው የሲኒማ ኩባንያ በሚያመ ርታቸው ፊልሞች ላይ ነው። በመሆኑም፥ ብዙዎቹ አሜሪካኖች መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ስለሚኖሩ ሕዝቦች ያላቸው እውቀት መጠነኛና የተዛባ ነው።

## ሁሉም አይደሉም ዓረቦች

መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ያለ ሁሉ ዓረባዊ ነው ማለት አይደለም። ዓረባዊ የሚባለው ቋንቋው ዓረብኛ፥ ባሕሉም ዓረባዊ የሆነ ግለሰብ ነው። ቱርክ ሃይማኖቷ እስልምና ነው፥ የሕዝቦቿ ቋንቋ ግን ዓረብኛ ሳይሆን፥ ቱርክኛ ነው። ከኢራን ሕዝቦች ብዙዎቹ ዓረባውያን ሳይሆኑ ፋርሳውያን ናቸው። የሚናገሩትም በዓረብኛ ሳይሆን፥ በራሳቸው ማለት በፋርስኛ ቋንቋ ነው። ቱርክ፥ ሶርያ፥ ኢራቅ እና ኢራን ውስጥ የሚኖሩት ኩርዳውያን የሚናገሩት በኩርድ ቋንቋ ሲሆን፥ የራሳቸውን ነጻ መንግሥት ለመመሥረት ከእያንዳንዱ አገር ጋር በመዋጋት ላይ ናቸው።

ዓረቦች ናቸው በሚባሉት አገሮች ውስጥ እንኳን ብዙ ልዩነቶች አሉባቸው። የግብፅ ሕዝቦች በጥንታዊው ባሕልና ቅርሳቸው ይመካሉ። ስለዚህ ዓረባውያን ሳይሆኑ፥ ግብፃውያን ናቸው። ይህን መሰሉ የብሔርተኝነት ስሜት ነው ዮርዳኖሳውያን፥ ፍልስጥኤማውያን፥ ኩዌታውያን እና ሶርያውያን ዘንድም ያለው። እነዚህ ሕዝቦች ተመሳሳይ ቋንቋ ቢናገሩም፥ የሚለያዩዋቸው ልዩ ባሕላዊና ታሪካዊ ባሕሎች አሉ።

## ሁሉም አይደሉም ሙስሊሞች

ከመካከለኛው ምሥራቅ ነዋሪዎች ብዙዎቹ የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው። ይሁን እንጂ፥ በክፍለ-ዓለሙ የሃይማኖት ልዩነት መኖሩን ብዙ አሜሪካውያን አያውቁም። ለምሳሌ ብዙ ዓረቦች ክርስቲያኖች፥ በተለይም የካቶሊክና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ነን ይላሉ። ከግብፅ ሕዝብ አሥራ ሰባት በመቶዎቹ ክርስቲያኖች ነን ይላሉ። ሊባኖስ ውስጥ ደግሞ ይህ ቁጥር ወደ ሠላሳ በመቶ ከፍ ይላል። ከእስራኤል ይልቅ ብዙ ክርስቲያኖች የሚኖሩት ኢራቅና ኩዌት ውስጥ ነው።

እስላሞች ነን ባዮችም ቢሆኑ አንድ አይደሉም። የእስልምና እምነት አንድ ወጥ አይደለም። በውስጡ ሁለት ዋና ዋና ቅርንጫፎች አቆጥቁጠዋል። ሱኒ የሚባለው ክፍል ዋናው ሲሆን፥ ሱና የተሰኘው የነቢዩ መሐመድን መሠረታዊ አቅጣጫ እከተላለሁ ይላል። ወዲያው ነቢዩ መሐመድ እንደሞቱ ነው ተከታዮቻቸው የተከፋፈሉት። ሺያት የተባለው ቡድን መሐመድን ይከተሉ የነበሩ መሪዎችን አስወገዳቸው። በነዚህ መሪዎች ፋንታ ዓሊ የተባለውን የመሐመድ አማች እና የእርሱን ተወላጆች እንደ ትክክለኛዎቹ የመሐመድ ተከታዮች አድርጎ ተቀበለ። ሺያቶች በአብዛኛው የሚኖሩት ደቡባዊ ኢራቅ እና ኢራን ውስጥ ነው።

## ሁሉም አይደሉም ሀብታሞቹ

አሜሪካኖች ያላቸው የተለመደ ግንዛቤ፥ ዓረቦች ሁሉ ባለጠጋ ናቸው የሚለው ሳይሆን አይቀርም። መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ቁጥራቸው ከ170 ሚሊዮን የሚልቅ ዓረቦች ይኖራሉ። ከእነዚህ አሥር በመቶ የሚሆኑት ናቸው በምዕራባውያን መስፈርት እንደ ባለጠጋ በሚቆጠሩ አገሮች ውስጥ የሚኖሩት። ሌሎቹ ጥቂት ከሕዝብ ብዛት ጋር እየታገሉ አነስተኛ ሀብት ባላቸው አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። ብዙዎቹ ሙስሊሞች፥ ጎረቤቶቻቸው የሆኑ ሀብታም ዓረቦች በሚኖሩት ቅምጥል ኑሮና፥ በእነዚሁ አገሮች ለእነሱ ግድ የለሽ መሆን የሚከፉ ናቸው።

ለዚህ ነው ሳዳም ሁሴን የሰፊው ሕዝብ ታዳጊ በመምሰል ብቅ ባሉ ጊዜ፥ የብዙዎቹን ዓረቦች የልብ ትርታ የቀሰቀሱት። ይህንኑ በተመለከተ አንድ ጸሐፊ እንዲህ ብለዋል፦

"ከግብፁ የቀድሞ ፕሬዝዳንት፥ ከጋማል አብደል ናስር ወዲህ፥ አንድ ደፋር የዓረብ መሪ እምቢ ለምዕራባውያን በማለት ተነሥተው፥ ፍልስጥኤም፥ እስልምና፥ አንድነት፥ የዓረቦችን ነዳጅ ዘይት መጋራት፥ የሚሉ ማራኪ ንግግሮችን አደረጉ። ይህ ንግግር፥ ስንት ነገሮች መስተካከል እንደነበረባቸውና፥ ስንቶቹ በስሕተት እንደተበላሹ ዓረቦች እንዲያስታውሱ አደረጋቸው"

ፍልስጥኤማውያንና ዮርዳኖሳውያን የሳዳም ሁሴንን ንግግር በመደገፍ ሰልፍ ባደረጉ ጊዜ፥ አሜሪካውያን፥ "ይህን አምባገነን መሪ እንዴት ሰው ይከተለዋል?" ብለው በመገረም ራሳቸውን ነቀነቁ። ሳዳም ሁሴን እነዚህ ጭቁን ሕዝቦች ሊሰሙ የፈለጓቸውን ቃላት ሲናገሩ እኛ አላደመጥንም። ኩዌቶች ለዓረቦች የሰጧቸው፥ አነስተኛ የሥራ ዕድልና ጥቂት ገንዘብ ነው። ሳዳም ሁሴን ግን፥ ኩራትና ተስፋ ነው ለሰፊው የዓረብ ሕዝብ የሰጡት።

## ሁሉም አይደሉም የቴክኒዎሎጂ እውቀት ያላዳበሩት

የኢራቅ ጦር ሠራዊት በበረሃው ማዕበል ዘመቻ ወቅት በማያቋርጥ የቦምብ ውርጅብኝና የታንክ ድብደባ ተንኮታኮተ። የቃል ኪዳን አገሮች ሠራዊት በአየር ውጊያ ያገኘው የበላይነትና፥ የኢራቅን መከላከያ ጥሶ መግባት የፈጠረው እፎይታ፥ ጦርነቱ ያልተመጣጠነ ስለመሆኑ የነበረንን እምነት አረጋገጠልን። የጠለቀ እውቀት ያልነበራቸው የኢራቅ ወታደሮች፥ ረቂቁን የምዕራብ ጦር መሣሪያ ሊቋቋሙት አልቻሉም።

ከጦርነቱ በኋላ ነው የምዕራቡ ዓለም የኢራቅን ብቃት በጨረፍታ የተመለከተው። ጦርነቱ በጀመረ ጊዜ፥ የሳዳም ሁሴን የኒውክሊየር የጦር መሣሪያ ገና ከአምስት ዓመት በኋላ ለተግባር የሚበቃ መሆኑን ነበር ሊቃውንት የተነበዩት። ጦርነቱ ሲያበቃም፥ የቦምቡ ድብደባ ያደረሰውን ጉዳትና፥ የሳዳም ሁሴንን ምስጢራዊ ፋይል ለመመርመር እነዚሁ ሊቃውንት ወደ ስፍራው ሄዱ። የሳዳም ሁሴንን ምስጢር ፈልፍሎ ለማውጣት ገና ብዙ መሥራት ይኖርባቸዋል። እስካሁን ባገኙት መረጃ ላይ በመመሥረትም ኢራቅ የኑክሊየር የጦር መሣሪያ ለማምረት ተቃርባ እንደነበር የሚያስረዳ ምስጢር አግኝተዋል። አሁንም ቢሆን ብዙ የባዮሎጂካልና ኬሚካል መሣሪያዎችን አምርታለች። መርማሪዎቹ

በተጨማሪም ከባድና አውዳሚ ፈንጂዎችን በመቶ ማይሎች ወደሚቆጠር ርቀት የሚያወናጭፉ ታላላቅ መድፎችን ለመሥራት የሚያስችል ዕቅድና ቁሳቁሶችን አግኝተዋል። የኢራቅን ችሎታ ወይም ብቃት እንዴት ዝቅ አድርገን ተመልክተነው ነበር?

ምዕራቡ ዓለም የመካከለኛው ምሥራቅን የተማረ የሰው ኃይል ሁልጊዜ ዝቅ አድርጎ የሚመለከት ይመስላል። ሊባኖስ ውስጥ የሚታየውን የአክራሪዎች የአጥፍቶ መጥፋት ዜና ወይም ሳውዲት ዓረቢያ ውስጥ ያሉ ግመል ጋላቢ ዘላኖችን ዜና እናደምጥና፥ የዓረቦች ሁሉ ኑሮ እንዲያ ነው ብለን በሞኝነት እናምን ይሆናል። እስልምና ያለውን የረዢም ጊዜ ዘመን ባሕላዊና ሳይንሳዊ ቅርስ ብዙዎቻችን አንረዳም ወይም አናደንቅም።

አውሮፓውያን እየተፍገመገሙ ጭለማው ዘመን ብለው ይጠሩት ወደነበረ ዘመን ያመሩ በነበረ ጊዜ፥ የዓረብ ምሁራን በግሪካውያንና በሮማውያን የተጀመረውን የሳይንሳዊ አቅጣጫ ጉዞ ገፍተውበት ነበር። አንድ ጸሐፊ እንዳሉት ዓረቦች፥ "ጥንታዊውን የግሪካውያን የእውቀት ቅርስ መጠበቅ፥ ማጥናት፥ ማሻሻልና ወደ ዓረብኛ መተርጎም ብቻ ሳይሆን፥ ከራሳቸውም አዲስና ጠቃሚ ግኝቶችን አክለውበታል።" ኮለምበስ የተባለው የዓለም አሳሽ ከኖረበት ዘመን 600 ዓመት ቀድሞ ነው፥ አንድ የዓረብ ምሁራን ቡድን ምድር ክብ መሆኗን የገለጠውና ዙሪያ መጠንዋንም ያሰላው። የምድር ወገብ አካባቢ ስሌታቸው መጠኑን በ1370 ኪሎ ሜትር ያህል ያሳነሰ ቢሆንም፥ ግኝታቸው ታላቅ ነበር።

ብዙዎቹ የዓረብ አገሮች ሦስተኛው ዓለም ውስጥ እንዳሉ ሌሎች አገሮች ናቸው። ብዙው ሕዝባቸው የዳበረ ቴክኖሎጂያዊ እውቀት የለውም። እያንዳንዱ አገር ግን ሕዝቡን ወደ ዘመናዊነት በመለወጡ ተግባር የሚረዱ ብዙ ምሁራንንና ሳይንቲስቶችን አፍርቷል።

## ሁሉም አይደሉም አሜሪካንን የሚጠሏት

መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚከናወኑ ሦስት ነገሮች ማለት አፈና፥ አጥፍቶ የመጥፋት አደጋ እና የአይሮፕላን ጠለፋ፥ በአሜሪካውያን ላይ ሥነ-ልቦናዊ ፍርሃት አሳድረውባቸዋል። የአሜሪካዊው ኢራን ውስጥ ካለው የአሜሪካን ኤምባሲ መታፈን፥ ሊባኖስ ውስጥ የተፈጸመው ተመሳሳይ ሁኔታ እና፥ ሽብርተኞች አሜሪካውያንን በማፈንና በማሠር የሚፈጽሙት ተግባር፥ ለአሜሪካውያን ቅዠት ሆኖባቸዋል። አፈናው በሌሎች አገሮች ዜጎች ላይ የሚፈጸም ቢሆንም፥ የጥላቻውና የቁጣው ዋና ተጠቂ የሆነችው አሜሪካን ትመስላለች።

ይህን የመሰለው የዓረቦች ማስፈራራት ቢኖርም ታዲያ፥ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ መገኘቷ ሥር የሰደደ እንዲሆን አሜሪካ በብርቱ ሠርታለች። በ1982 እአአ የአሜሪካ ሠራዊት ከየአገሮቹ ከተውጣጣው ዓለም አቀፍ ሠላም አስከባሪዎች ኃይል ጋር በመሆን ሊባኖስ ውስጥ የነበረውን የእርስ በርስ ጦርነት ለማስቆም ወደዚያው አመራ። ጥቅምት 23 ቀን 1983 እአአ አንድ የአጥፍቶ ጠፊ ቡድን አባል፥ ቤይሩት አይሮፕላን ማረፊያ አጠገብ ወደነበረው የአሜሪካን የባሕር ኃይል ሠራዊት ክልል ገብቶ፥ ሕንጻውን በፈንጂ ሲያወድም ድርጊቱ ቁጣና ቅሬታን ፈጠረ። በአደጋው 241 የባሕር ኃይል አባላት ሞቱ። ድርጊቱ ሊባኖስ ውስጥ በአሜሪካን ይረዳ የነበረውን የመልሶ ማቋቋም ሥራ ተስፋ አጨለመው። ዓመት ባልሞላው ጊዜ ደግሞ ቤይሩት አቅራቢያ ያለው የአሜሪካን ኤምባሲ የቦምብ አደጋ ደረሰበትና 14 ሰዎች ተገደሉ። አሜሪካን እንደገና የሽብር ፈጣሪዎች ዋና ዒላማ ሆነች።

በአሜሪካን ላይ የተሰነዘረው ሦስተኛ ጥቃት የደረሰው በ1985 እአአ ነበር። ከአቴንስ ወደ ሮም ይበር የነበረውን የትራንስ ወርልድ አየር መንገድ፥ ሺያት የተሰኙት የእስልምና እምነት ተከታይ አሸባሪዎች ጠልፈው አንዱን አሜሪካዊ ሲገድሉ፥ ሠላሳ ዘጠኙን በመያዣነት ለአሥራ ስድስት ቀናት አቆዩዋቸው። ከአራት ወራት በኋላ አቺሌ ላውሮ የተሰኘውን የኢጣሊያን መርከብ ይዘው አንድ አሜሪካዊ ከገደሉና ሌሎቹንም ካስፈራሩ በኋላ እጃቸውን ለግብፅ ባለሥልጣኖች ሰጡ።

*አሜሪካውያን በማንኛው የመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ደኅንነታቸው የተጠበቀ ነውን?*

*ይህ አፈናና፥ ግድያ እንዲሁም የቦምብ አደጋ እና የአይሮፕላን ጠለፋ፥ ብዙ አሜሪካውያንን ያስጨንቃቸዋል። መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ አሜሪካውያንን ይጠላቸዋልን? በቴሌቪዥን የቀረቡ ዘገባዎች በተመልካቹ ዘንድ እንዲህ ያለውን እምነት ያሳድራሉ። ይሁን እንጂ፥ ዘገባዎቹ ትክክለኛውን ምስል አይሰጡም። እርግጥ ነው፥ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ያሉ ብዙ ቡድኖች አሜሪካን ለእስራኤል ድጋፍ መስጠቷና የቆመችለት ፋይዳ ያስቆጣቸዋል። የብዙዎቹ ቁጣ ግን አሜሪካንን እንጂ፥ አሜሪካውያንን እንደ መጥላት ተደርጎ አልተተረጎመም።*

*የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት አሜሪካንን በተመለከተ ያሉ የተለያዩ ስሜቶች እንዲገለጡ አደረገ። የተናደዱ ሰልፈኞች ዮርዳኖስና ኢራቅ ውስጥ የአሜሪካንን ባንዲራ አቃጠሉ። የሳውዲ ዜጎች፥ ሶርያውያንና ግብፃውያን ግን አሜሪካንን እንደ ቃል ኪዳን ወዳጅ ቆጠሯት። በኩዌት*

ከተማ ኩዌታውያን በከተማቸው መሀል ያልፍ ለነበረ የአሜሪካን ሠራዊት አድናቆታቸውን ለመግለጥ በየጎዳናዎቹ ተሠለፉ። አሜሪካን በባሕረ-ሰላጤው ጦርነት ወቅት መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ አዳዲስ ወዳጆች አፍርታለች።

## ዓረቦች በዘመኑ ፍጻሜ

ዓረቦች አንድ የሚሆኑበት ጊዜ ይመጣ ይሆን? የዓረቦች አንድነት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ጋር የሚገናኘውስ እንዴት ነው? በሚቀጥሉት ምዕራፎች አንዳንድ አገሮችን ጠለቅ ባለ ሁኔታ በጥናት እንፈትሻቸዋለን። አሁን ግን መሠረታዊ የሆኑ አንዳንድ ገለጣዎች ልናደርግ እንችላለን። አንደኛ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በፍጻሜው ዘመን ትንቢቱ አንድን የዓረብ መንግሥት በተናጠል አያመለክተንም። እስልምና በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ሥር አይጠቃለልም። ሙስሊሞች ለእስላማዊው አንድነት አፍአዊ ድጋፍ መስጠታቸውን ይቀጥላሉ፤ አንድነቱ ግን አይፈጠርም።

ነቢዩ ዳንኤል ትንቢታዊ መጋረጃውን ገልጦ፥ የግብፃውያንንና የዮርዳኖሳውያንን የወደፊት ሁኔታ ያስገነዝባል። በትንቢቱ ምዕራፍ 11 ውስጥ፥ አሕዛብ ነገሥታትንና መንግሥታትን አመልክቷል። እነዚህ ነገሥታትና መንግሥታት በታሪክ ሂደት በዳንኤል ሕዝቦች (እስራኤላውያን) ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው። ምንም እንኳን ዳንኤል ትንቢቱን ሲዘግብ የገለጣቸው ነገሮች ሁሉ ገና ወደፊት እንደሚከናወኑ አድርጎ ቢሆን፥ ብዙዎቹ በመፈጸም ላይ ናቸው። ከቁጥር 36 ጀምሮ ግን፥ ገና የሚፈጸሙ ሁኔታዎችን ይጠቁማል። ወደፊት የሚመጣውን የከፋት አለቃ እንዲህ ይገልጠዋል፥ "ንጉሡም እንደፈቃዱ ያደርጋል፤ ራሱንም ከፍ ከፍ ያደርጋል፥ በአማልክት ሁሉ ላይ ራሱን ታላቅ ያደርጋል፥ በአማልክትም አምላክ ላይ በትዕቢት ይናገራል" (ዳን. 11፡36)። ዳንኤል በተለይ የሚያተኩረው፥ ይህ ክፉ መሪ ምድርን በሞላ ድል ለማድረግና የእስራኤልን መንግሥትም ለማውደም በሚሞክርበት በመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመት ተኩል ላይ ነው። ቁጥር 41 ውስጥ፥ "መልካሚቱ ምድር" የሚላትን እስራኤልን ይህ ንጉሥ እንደሚወራት ዳንኤል ገልጧል።

ይህ ክፉ መሪ፥ በፍጻሜው ዘመን ብዙ አገሮችን ይወርራል፤ "ወደ አገሮቹ ይገባል፥ ይጎርፍማል፥ ያልፍማል" (ዳን. 11፡40)። ይሁን እንጂ፥ ሁሉም አገሮች አይደሉም የዚህ አረመኔ ገዢ መዓት የሚደርስባቸው። እንዲህ ይላል ዳንኤል፥ "ብዙ አገሮችም ይወድቃሉ፤ ነገር ግን ኤዶምያስና ሞዓብ ከአሞንም ልጆች የበለጡት ከእጁ ይድናሉ" (11፡41)። እነዚህ ሦስት አገሮች የተመዘገቡት፥ ከደቡብ ወደ ሰሜን

በቅደም ተከተል ነው። ከስምጥ ሸለቆ፣ ከሙት ባሕርና ከዮርዳኖስ ሸለቆ በስተ ምሥራቅ ይገኛሉ። ይህን ምድር ዛሬ የምናውቀው በዮርዳኖስነት ነው። የዮርዳኖስ ዋና ከተማ አማን፥ አሞን የሚለውን ስም ይዟል።

በዚህ ቃል መሠረት፥ ዮርዳኖስ ከዚህ አረመኔ መሪ ወረራ ታመልጣለች። የዚህች አገር ሕዝቦች በሽብሩ ወቅት አንጻራዊ ሠላም የሚኖራቸው መሆኑን እንጂ፥ አገሪቱ የማትወረርበትን ምክንያት ዳንኤል አልገለጠም። አይሁዳውያን ከወራሪው ለማምለጥ፥ ወደ ተራራዎች እንደሚሸሹ አንዳንድ ትንቢታዊ ምንባቦች ይጠቁማሉ። አንዳንዶቹ የሚሸሹት፥ ምናልባት ወደ ዮርዳኖስ ተራራዎች ይሆናል።

ዮርዳኖስ ታመልጣለች፤ ግብፅ ግን የዕጣው ተቋዳሽ ትሆናለች። ዳንኤል፥ አረመኔው ወራሪ ብዙ አገሮችን በወረራ የሚይዝ መሆኑን ከገለጠ በኋላ፥ እንዲህ በማለት አስፈሪ ማስጠንቀቂያ ያክልበታል፥ "የግብፅም ምድር አታመልጥም። በወርቅና በብርም መዝገብ ላይ፥ በከበረችም በግብፅ ዕቃ ሁሉ ላይ ይሠለጥናል" (ዳን. 11፡42-43)። ይህ የመጨረሻ የዓለም መሪ፥ ግብፅንና በዙሪያዋ ያሉ አገሮችን በመውረር ይዘርፋቸዋል። ወረራው የሚከናወነው፥ በመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመት ተኩል ፍጻሜ ወቅት መሆን አለበት፤ ምክንያቱም፥ "ከምሥራቅና ከሰሜን ግን ወሬ ያውከዋል" (11፡44)፥ እናም ከግብፅ እንዲወጣ ያስገድደዋል። ይህ ሰው ከግብፅ ወጥቶ አዳዲስ ጠላቶቹን ካጠቃ በኋላ "ወደፍጻሜው ግን ይመጣል" (11፡45) ወደተባለለት ወደ እስራኤል ይሄዳል።

በዳንኤል ትንቢት ቅደም ተከተል መሠረት፥ የጥፋት ልጅ "ከምሥራቅና ከሰሜን በሚመጣ ወሬ ሳቢያ" ግብፅን ይለቃል። የወሬዎቹን ምንነት ዳንኤል ባይገልጥም፥ አንዱ ወሬ የባቢሎን እንደገና መገንባት ሊሆን ይችላል። እንደገና የተሠራችው ባቢሎን፥ በመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት ኃያል ትሆንና በአረመኔው መሪ ላይ ተጽዕኖ ታሳድርበታለች። ሐዋርያው ዮሐንስ ይህን ተጽዕኖ የሚገልጠው፥ ጋለሞታይቱ ሴት (የባቢሎን ከተማ)፥ አውሬውን (የመጨረሻው ዘመን ገዥ)፥ የምትጋልበው መሆኑን በማመልከት ነው። ባቢሎን የዓለም ገዥ በሚሆነው ሰው ላይ ተጽዕኖ የምታሳድርበትን ሁኔታ ወይም ምክንያት ባይገልጥም፣ ሊሆን የሚችለው ግልጥ ነገር ግን፥ በመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት አማካይነት ነው። አንድ ሰው የኢራቅን፥ የኩዌትንና የሳውዲት ዓረቢያን የነዳጅ ሀብት ለመቆጣጠር ከቻለ፣ በምዕራቡ ዓለም ላይ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ነዳጅ ዘይትን በመቆጣጠሩ ሳቢያ፥ ምዕራቡን ዓለም እንዳሻው ይቆጣጠራል ለማለት ይቻላል።

የጨካኞቹ ገዥዎች ግብፅንና በአካባቢዋ ያሉ ሙስሊም መንግሥታትን መውረር፥ ከባቢሎኑ ገዢ የፖለቲካ አጀፋን ያስነሣል። የባቢሎኑ መሪ፥ ምናልባትም አፔክ የተባለው የነዳጅ አምራች አገሮች ማኅበር፥ በ1973 እአአ እንዳደረገው የነዳጅ ማዕቀብ ያደርግ ይሆናል። አጸፋው ምንም ይሁን ምን፥ አረመኔውን መሪ ያስጨንቀውና ሠራዊቱን ከግብፅ በማውጣት፥ ሥቃይ ወደሚያደርስበት ወደሌላ አዲስ ስፍራ ያዛውራል፦ "ብዙ ሰዎችንም ይገድል ዘንድና ፈጽሞ ያጠፋ ዘንድ በታላቅ ቁጣ ይወጣል" (ዳን. 11፡44)።

ሐዋርያው ዮሐንስ፥ ይህ መሪ ወደ ባቢሎን ከተቃረበ በኋላ የሚሆነውን ታሪክ በመቀጠል እንዲህ ይላል፥ "ያየሀቸውም አሥር ቀንዶችና አውሬው ጋለሞታይቱን ይጣላሉ፤ ባዶዋንና ራቁቷንም ያደርጓታል፥ ሥጋዋንም ይበላሉ፤ በእሳትም ያቃጥሏታል" (ራእይ 17፡16)። ባቢሎን ትጠፋለች። ዮሐንስ ይህን የባቢሎንን ጥፋት፥ በሰባት ዓመቱ የፍዳ ዘመን ፍጻሜ ላይ የሚሆን እንደሆነ በመግለጥ ረገድ ከዳንኤል ጋር ይስማማል። እንዲሁም ይህ ክፉ መሪ ወደ እስራኤል ማለትም በመጨረሻ ወደሚሸነፍበት ስፍራ ይመጣል። ይህ የሚከናወነው ክርስቶስ በሚመለስበት ወቅት ሲሆን፥ አሳቡም ከዳንኤል ጋር የሚስማማ ማስገንዘቢያ አለው።

ጥረቶች ሁሉ ቢደረጉም፥ መካከለኛው ምሥራቅ ሁከትና ሽብር እንደሰፈነበት ይቆያል። ዮርዳኖስ በምሥራቅና በምዕራብ መካከል መዋዠቋን ትቀጥላለች። ይህ ሁኔታዋም ከግጭቱ ውጭ እንድትቆይ ይረዳታል። ግብፅን፥ ከምዕራብ የሚመጣው መሪ ስትራቴጂያዊ አቀማመጧንና የቅርስ ብልጥግናዋን በተገነዘበ ጊዜ፥ ነጻነቷን ያሳጣታል። ያን ጊዜ፥ "ከምሥራቅና ከሰሜን" የሚመጡ መንግሥታት የግብፅን ውድቀት በመቃወም ሊረዷት የሚነሡ መሆኑ ስለሚታወቅ፥ የሙስሊሞች ኅብረትን የሚመስል ነገር በጊዜው በተግባር ላይ የሚገኝ መሆኑ ግልጥ ነው። እነዚህ የግብፅ ረዳቶች፥ ባቢሎንና የአካባቢው ነዳጅ አምራች አገሮች ይሆናሉ። የእነርሱ ተቃውሞ፥ የፍጻሜው ዘመን ገዥ የሚሆነውን ሰው ያስፈራውና፥ በነዚህ የመጨረሻ ጠላቶቹ ላይ ሠራዊቱን እንዲልክ ያስገድደዋል። ይህን የዓረቦች ዓመፅ ከደመሰሰ በኋላ ነው፥ አይሁዳውያንን ለመጠራረግ ወደ እስራኤል የሚያመራው። ያኔ ብቻ ነው መሢሑ ወደ ምድር የሚመለሰው።

> ምዕራፍ አሥር <

# ሳዳም ሁሴንና የባቢሎን መግነን

ለስምንት ወራት ያህል የዓለም ሕዝብ ዓይኖች ፋርስ ባሕረ-ሰላጤ አካባቢ በሚከናወኑ ነገሮች ላይ አትኩረው ነበር። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ከሥራ ወደቤታቸው እንደተመለሱ የጦርነት ዜናን በቴሌቪዥኖቻቸው ይከታተሉ ነበር። ለአጭር ጊዜ በዚህ ሁኔታ ትኩረታችን ተሰቦ ነበር፤ ነገር ግን ማኅበረሰባችን እንዳለው እንደማንኛውም ሌላ ነገር ጦርነቱ ያሳሰበን ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው።

ከዚያ በኋላ መድፎች ጸጥ አሉ፤ የጦርነቱ ማብቃትም ይፋ ሆነና የዓለም ሕዝብ ትኩረቱን ወደሌላ አገሮችና ግጭቶች አዞረ። ስለሆነም በሌሎች አገሮች የሚከናወኑ ሁኔታዎች ከባግዳድ ይልቅ የዕለታዊ አበይት ርዕስ ዜናዎች ሆኑ። ለመካከለኛው ምሥራቅ አዲስ የሰላም ዕቅድ ቀረበ፤ አዲሱ የዓለም ሥርዓትም የበላይነትን ያዘ።

ይሁን እንጂ ዓለም ጥቂት እፎይታ ባገኘበት ጊዜ ብዙ ሰዎች ፋርስ ባሕረ-ሰላጤ ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮችን በቅርብ በመመርመር፥ ሁኔታዎቹን እግዚአብሔር ለአሁኒቱ ዓለም ባለው የእንቆቅልሽ ዕቅድ ውስጥ ሊያስማሟቸው ይሞክራሉ። ጦርነቱ ያስገኘው ጠቀሜታ ምንድነው? ሳዳም ሁሴን አሁንም ኢራቅን በመቆጣጠር ላይ ናቸው። የተባበሩት ኃይላትን ያቀናጁት የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆርጅ ቡሽ ከሥልጣን ሲወርዱ እሳቸው ግን በስፍራቸው ላይ ናቸው። ሳዳም ሁሴን በሥልጣን ላይ ለመቆየት መቻል ወይም አለመቻላቸው ገና አልለየለትም። ብዙዎች እኚህ ሰው በአጭር ጊዜ ይወገዳሉ የሚል ተስፋ የነበራቸው ቢሆንም እኚህ ሰው እስካሁን በስልጣን አሉ። ሰውዬው ፖለቲካዊ ለውጥ ለማድረግ በመሞከር ላይ ያሉም ይመስላሉ። የጥላቻ መንፈስ የሞላባቸው እኚህ ሰው የተሻሉ ሆነው ለመቅረብ ራሳቸውን ለጊዜው ሸሽገው ነበር። ከኩርዳውያን ተቃዋሚዎቻቸው ጋርም ሰላም ለመመሥረት ይሻሉ፤ ኩዌትን የወረሩ እኚህ አምባገነን ሰው ከዓረባውያን ወንድሞቻቸው ጋር የቅርብ ግንኙነትን በመፈለግ ላይ ናቸው። ራሳቸውን እንደናቡከደነፆር (ጥንታዊ የባቢሎን ንጉሥ) የቆጠሩት ሳዳም ዛሬ ለሕዝባቸው ስለሚበጅ ዲሞክራሲ በመምከር ላይ ናቸው።

የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት እንዳበቃ ሎስአንጀለስ (አሜሪካ) ውስጥ የሚታተም አንድ ጋዜጣ በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ሊቃውንት የሆኑ ስምንት ሰዎችን ሳዳም ሁሴን በፖለቲካ ሥልጣን ለመቆየት ስለሚኖራቸው ዕድል በተመለከተ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ጠይቋቸው ነበር። ብዙዎቹ ሳዳም ሁሴን ረጅም ፖለቲካዊ ዕድሜ አይኖራቸውም ሲሉ፥ ራሚ ካውሪ

የተባሉ፥ ደራሲና የፖለቲካ አምድ አዘጋጅ ፍልስጥኤማዊ ግን የሳዳም ሁሴንን በሥልጣን ላይ መቆየት አስመልክተው ቀጥሎ ያለውን ለየት ያለ አስተያየት ሰጡ።

> “ሳዳም ሁሴን ምንም እንኳን ወታደራዊ ብልሀታቸው ዝቅተኛ ቢሆን፥ በሥልጣን የሚቆዩ ይመስላሉ. . .። በገሐድ ከሚታየው የጠላት የበላይነት አንጻር ያለውን የዓረቦችና የእስላሞች አይበገሬነት፥ እንዲሁም የድፍረት መንፈስ በግልጥ ተናገሩት፥ በግብርም ገለጡት። ይህ መንፈስ የተፈጠረው፦ (1ኛ) ዓረቦች ሰው-ሠራሽ በሆነውና ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በተጀመረው አካባቢያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ሥርዓት የተፈጠረው ቅያሜ፥ (2ኛ) የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ዓለም ባጠቃላይ የጸጥታው ምክር ቤት ውሣኔን በመተግበር ጊዜ የሚያሳዩት አድልዎ፥ (3ኛ) ምዕራባውያን ቅኝና የእጅ አዙር ቅኝ ገዢዎች የእነሱን ጥቅምና የሩቅ ዓላማ እንጂ፥ የአካባቢውን ዓረባዊ ሙስሊሞች ለማይጠቅም ዓላማ ወታደሮቻቸውን ወደመካከለኛው ምሥራቅ መላካቸው እና (4ኛ) እስራኤል ጎረቤቶቿ ከሆኑት ዓረቦች ይልቅ ብርቱ መሆን አለባት የሚለው የአሜሪካ ግትር አቋም እጅግ ቅር ባሰኛቸው ዓረቦች ዘንድ ስፍራ አግኝቷል።”

መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የተገኘው ድል አስደሳች ቢሆንም፥ ድሉ በዚያ አካባቢ ባለው ሁኔታ ላይ ያስከተለው ለውጥ ግን ጥቂት መሆኑን የዓለም ሕዝቦች አልተገነዘቡም። የትኛውም የመካከለኛው ምሥራቅ አገር መሪውን አልለወጠም። ሳውዲት ዓረብና ኩዌት የሚተዳደሩት አሁንም ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የመመሥረት ፍላጎት በሌላቸው ንጉሣዊያን ቤተሰቦች ነው። ሶሪያና ኢራቅ ደግሞ ጊዜው ሲያመች የግዛት ድንበሮቻቸውን የማስፋፋት ምኞት ባላቸው የባዝ ፓርቲ አምባገነኖች ነው የሚተዳደሩት። ምዕራቡ ዓለም እጅጉን የነዳጅ ዘይት ጥገኛ ነው። ዓለም ከሚያስፈልጋት ነዳጅ ግማሹ የሚገኘው ደግሞ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ነው። በአሁኑ ጊዜ በዓለም ውስጥ አንፃራዊ ሰላም አለ። ይሁን እንጂ ይህ ሰላም ዘላቂ ነው፥ ወይስ ቀጣዩ ማዕበል እስኪመጣ ድረስ የሚቆይ የእረፍት ጊዜ?

## ነቢያትና ንግረኞች

የመካከለኛው ምሥራቅ ችግር በ1970ዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢቶች ለመረዳት የነበረው ልዩ ትኩረትና ፍላጎት እንደገና እንዲያንሰራራ አድርጓል። ትንቢትን አስመልክተው የሚታተሙ መጻሕፍት ኒው ዮርክ ታይምስ በተባለው መጽሔት ላይ የላቀ ሽያጭ

ያላቸው መጻሕፍት የሚለውን ስፍራ ሲይዙ፥ በክርስቲያን መጻሕፍት ሽያጭም አቻ የለሽ ሆነው ነበር። ብዙዎቹ መጻሕፍት መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮችን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት አንጻር መርምረዋል። የኔ ድርሰት የሆነውና "የባቢሎን ትንሣኤ" በሚል ርዕስ የሚታተመው መጽሐፍም ማንም ባልገመተው ሁኔታ ሽያጫቸው ከፍ ካሉት መጻሕፍት አንዱ ነበር።

አንድ ጓደኛዬ ሁልጊዜ፥ "ብርሃን ጥቃቅን ነፍሳትን" ይስባቸዋል የሚል አባባል አለው። ብዙ መጻሕፍት በአሁኑ ጊዜ የሚከናወኑ ነገሮችን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት አንጻር ሲተረጕሙ፥ ሌሎቹ ደግሞ ትንቢቶችን አሁን ካሉ ሁኔታዎች ጋር እንዲስማሙ እያደረጉ ሊያነቧቸው ሞክረዋል። ይህ የአተረጓጎም ልዩነት ረቀቅ ያለ ቢሆንም፥ ልዩነቱን መረዳቱ በጣም ጠቃሚ ነው። የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ብርቱ አማኝ እንደመሆኔ፥ እግዚአብሔር ለዚህ ባቢሎንና እስራኤል ላሉበት ዓለም አንድ ዕቅድ ያለው መሆኑን ተረድቻለሁ። የትንቢቶቹ ፍጻሜ በተቃረበ መጠንም፥ በዓለማችን የሚከናወኑ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ከተገለጡ ሁኔታዎች ጋር እጅግ ተመሳሳይ እየሆኑ እንደሚመጡ አምናለሁ። ይሁን እንጂ ለማንኛውም ንጽጽር መነሻ ሊሆን የሚገባው መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ የወቅቱ ሁኔታዎች አይደሉም።

የፋርስ ባሕረ-ሰላጤ ጦርነት በተከሰተ ጊዜ፥ የአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን አስደናቂ "ትንበያዎች" ስሕተት መሆናቸው ተረጋገጠ። የበረሃው ማዕበል ዘመቻ የአርማጌዶን ውጊያ አልነበረም፥ ሳዳም ሁሴንም ሐሰተኛው ክርስቶስ አይደሉም፤ እንዲሁም ጦርነቱን ከፍጻሜ ያደርስ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ አልተመለሰም። ስከድ ሚሳይልና ተመሪ የሌዘር ቦምብ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ውስጥ ተገልጧል ያሉ ሰዎች፥ ፋርስ ባሕረ-ሰላጤ ውስጥ የተደረገው ጦርነት ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 13 እና ትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ 50-51 ውስጥ ባሉት ክፍሎች የተገለጠው የፍጻሜ ዘመን ጦርነት አለመሆኑን ተገነዘቡ። መጽሐፍ ቅዱስ ነበር የተሳሳተው? አይደለም። ችግሩ የእነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በተሣሣተ መንገድ መረዳታቸው ነበር። የወቅቱን ሁኔታ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ከመመርመር ይልቅ፥ ሁኔታዎቹን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉ አድርገው ተመለከቷቸው።

የበረሃው ማዕበል ዘመቻ ቢያበቃም፥ የሚያዘናጉ ጥርጣሬዎች ግን አሉ። ጦርነቱ የአርማጌዶን ውጊያ ባይሆንም መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ በቅርቡ በተከናወኑ ነገሮችና በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢቶች መካከል ያለው ተመሳሳይነት ችላ የሚባል አይደለም። እነዚህ መመሳሰሎች የታሪክ

አጋጣሚዎች ወይስ ቀድሞ ስለዓለም ወደተወሰነው ፍጻሜ የሚያፋጥኑ ሁኔታዎች ናቸው? የእግዚአብሔር ቃል ስለባቢሎንና በታሪክ መድረክ ስለሚኖራት የመጨረሻ ዘመን ሚና ብዙ ይናገራል። በመሆኑም ወደፊት በዓለም ስለሚሆነው ነገር ለማወቅ የሚፈልግ ሰው የወቅቱን ሁኔታዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትንቢት ሊያጠና ይገባል። ምክንያቱም ሁለቱ ነገሮች በመቀራረብ ላይ ናቸው።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊቱ ባቢሎን እንዴት ትገለጥ ይሆን?

ባቢሎን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ የጎላ ስፍራ አላት። በእግዚአብሔር ላይ የሚነሣ ሰብአዊ ኩራትና ዓመፅ ተምሳሌትም ናት። ባቢሎን የሚለውን ስም ያገኘችው ባብ (በር) እና ኤል (አምላክ) ከሚሉ ጥምር ቃላት ማለት ባቤል ከሚለው የእብራይስጥ ቃል ነው። ባቤል ሰው ራሱ ወደ እግዚአብሔር ለመግቢያ የሠራት በር ናት። ሰዎች ከእግዚአብሔር ዓላማ ውጭ በራሳቸው ጥረት ወደ እግዚአብሔር ለመድረሻ ተስፋ ያደረጉባትም ነበረች (ዘፍጥ. 11)።

ባቢሎን ያላትን ባህርይ እንደያዘች ነው በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምትጠቀሰው። እግዚአብሔር ላይ ያላት ጥላቻ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው፥ ወታደሮቿ ኢየሩሳሌምን ባጠፉና ምድራዊውን የእግዚአብሔር መንግሥት ባፈራረሱ ጊዜ ነበር (586 ዓ.ዓ.)። ከዳዊት ቤት የሆነውን ንጉሥ ከዙፋኑ አውርደው በሰንሰለት በማሠር ወሰዱት። የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ አቃጥለው የይሁዳን ሕዝብ በምርኮ ወሰዱ። ዳንኤል ባቢሎንን "በአሕዛብ ዘመን" ማለት አሕዛብ ኃይሎች የእግዚአብሔር ሕዝብ ገዥዎች በሚሆኑበት ጊዜ የምትገኝ "የወርቅ ራስ" ይላታል።

ይሁን እንጂ፣ የባቢሎንን ድል የተነበየው እግዚአብሔር ራሱ ፍጻሜዋን እስከፊ መፈራረስ እንደሚያደርገውም ተስፋ ሰጥቷል። ነቢዩ ኢሳይያስ ውድቀቷን ሲገልጥ እንዲህ ብሏል፥ "እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ባፈረሰ ጊዜ እንደነበረው፥ የመንግሥታት ክብር የከላዳውያንም ትዕቢት ጌጥ ባቢሎን እንዲሁ ትሆናለች" (ኢሳ. 13፡19)። እጅግ ከፍ ከፍ ያለችው ከተማ ትንኮታኮታለች። የባቢሎን ውድቀት ከእስራኤል ትንሣኤ ጋር ባንድ ወቅት የሚከናወን መሆኑን ሲገልጥም እንዲህ ብሏል፥ "እግዚአብሔርም ያዕቆብን ይምረዋል፥ እስራኤልንም ደግሞ ይመርጠዋል፥ በአገራቸውም ያኖራቸዋል" (14፡1)። እነዚህ የኢሳይያስ ትንቢቶች ገና አልተፈጸሙም።

ኢሳይያስ ባቢሎን ላይ ከተነበየ ከመቶ ዓመት በኋላ፣ ነቢዩ ኤርምያስም እንዲህ በማለት ተመሳሳይ ትንቢት ተናግሯል፥ "ሰዶምንና

ገሞራን በአጠገባቸውም የነበሩትን ከተሞች እግዚአብሔር እንደገለበጣቸው፥ ይላል እግዚአብሔር፥ እንዲሁ ሰው በዚያ አይቀመጥም፥ የሰው ልጅ አይኖርባትም” (ኤር. 50፡40)። እግዚአብሔር ከባቢሎን ጥፋት በኋላ ሕዝቡን ወደ ምድራቸው የሚመልስ መሆኑንም ነቢዩ እንዲህ በማለት ገልጧል፥ “በዚያ ወራትም፥ በዚያም ጊዜ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ የእስራኤል ልጆችና የይሁዳ ልጆች በአንድነት ሆነው ይመጣሉ። እያለቀሱም መንገዳቸውን ይሄዳሉ፥ አምላካቸውንም እግዚአብሔርን ይፈልጋሉ። ፊታቸውንም ወደዚያ አቅንተው፥ ኑ ከቶ በማይረሣ በዘላለም ቃል ኪዳን ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ፥ ብለው ስለጽዮን መንገድ ይጠይቃሉ” (50፡4-5)።

አንዳንድ ምሁራን የባቢሎን ቂሮስ በተባለ የፋርስ ንጉሥ እና በሜዶ-ፋርስ እጅ መውደቅ የኢሳይያስንና የኤርምያስን ትንቢት ፈጽመውታል ይላሉ። ይሁን እንጂ፥ እነዚህ ነቢያት ከተናገሯቸው ትንቢቶች ብዙዎቹ ያኔ አልተፈጸሙም። ከተማይቱ ቶሎ አልወደመችም፥ ቤቶችም አልተቃጠሉም። በነዋሪዎቿ ላይ የከፋ እልቂት አልደረሰም። የኢሳይያስንና የኤርምያስን ገለጣ በትክክለኛ ግንዛቤ ከተረዳነው፥ የቂሮስ ከተማይቱን መያዝ ትንቢታቸውን አልፈጸመውም። ታዲያ ይህ የጥፋት ትንቢት ከዚህ ቀደም ያልተፈጸመ ከሆነ፥ መቼ ነው ባቢሎን የምትጠፋው?

## የራእይዋ ባቢሎን

ሐዋርያው ዮሐንስ ያልተፈጸመ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶችን ራእይ መጽሐፍ ውስጥ ጠቅለል አድርጎ አቅርቧል። ሐዋርያው፥ ባቢሎንን እግዚአብሔር ቃል ውስጥ በማስገባት አገሪቱ በታሪክና በትንቢት ውስጥ ያሏትን ሚናዎች ከሁለት ምዕራፎች በላይ በሆነ ክፍል በአንድ ላይ ገልጧቸዋል። ራእይ ከምዕራፍ 17-18 ያለው ክፍል በዓለም ታሪክ ውስጥ የባቢሎንን ፍጻሜ ያመለክተናል። እስቲ በዮሐንስ ራእይ የተዘረዘሩትን ትንቢቶች አካሄድ እንመልከት።

በራእይ ምዕራፍ 17 እና 18 መካከል ያለውን ግንኙነት መገንዘቡ፥ ምዕራፎቹ ውስጥ ባቢሎንን ለይቶ ለማወቅ ይረዳል። ብዙ ሰዎች እንደተረዱት ራእይ ምዕራፍ 17 እና 18 የተለያዩ ባቢሎኖችን ለየብቻ ይገልጣሉን? ይህን ጥያቄ በአዎንታ የሚመልሱ ሰዎች ራእይ 17 የሚገልጠው ሃይማኖታዊዋን ባቢሎንን ሲሆን፥ ምዕራፍ 18 ደግሞ ኢኮኖሚያዊቱን ባቢሎንን ማለት የፍጻሜ ዘመኑን የዓለም መሪ መዲና ነው ብለው ያምናሉ። ሌላው መረዳት ደግሞ ምዕራፎቹ ስለ አንዲት ባቢሎን ይገልጣሉን? ለዚህ ምላሽ አዎን ኢራቅ ውስጥ እንደገና ስለምትሠራው ባቢሎን የሚያመለክት ነው የሚል መረዳት ነው።

ሐዋርያው ዮሐንስ ሁለቱም ምዕራፎች ውስጥ የጠቀሳቸውን ባቢሎኖች የገለጣቸው፥ በአእምሮው ውስጥ የነበረችው አንዲት ባቢሎን መሆኗን በሚያስገነዝብ ተመሳሳይ መንገድ ነው። ለምሳሌ�:-

## ባቢሎን

*ስሟ አንድ ነው።*

- "ታላቂቱ ባቢሎን" (ራእይ 17፡5)
- "ታላቂቱ ባቢሎን" (ራእይ 18፡2)

*መለያዋ አንድ ነው።*

- "ያየሃት ሴት . . . ታላቂቱ ከተማ ናት" (17፡18)
- "ብርቱይቱ ከተማ ባቢሎን ወዮልሽ" (18፡10)

*ልብሷ አንድ ነው።*

- "ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጎናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቁዎችም ተሸልማ ነበር" (17፡4)
- "በቀጭን ተልባ እግርና በቀይ ሐምራዊ ልብስ ለተጎናጸፈች፥ በወርቅና በከበረ ድንጋይም በዕንቁም ለተሸለመች ለታላቂቱ ከተማ ወዮላት" (18፡16)

*ሁለቱም ጽዋ ይዘዋል።*

- "በእጅዋም የሚያስጸይፍ ነገር የዝሙትም ርኩሰት የሞላበትን የወርቅ ጽዋ ያዘች" (17፡4)
- "በቀላቀለችው ጽዋ ሁለት እጥፍ አድርጋችሁ ቀላቅሉባት" (18፡6)

*ከነገሥታት ጋር የሚኖራት ግንኙነት ተመሳሳይ ነው።*

- "የምድርም ነገሥታት ከርስዋ ጋር ሴሰኑ" (17፡2)
- "የምድር ነገሥታት ከርስዋ ጋር ሴሰኑ" (18፡3)

*ከመንግሥታት ጋር ያላት ግንኙነት ተመሳሳይ ነው።*

- "በምድር የሚኖሩ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ ሰከሩ" 17፡2)
- "አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቁጣ ወይን ጠጅ የተነሣ ወድቀዋል" (18፡3)

*ከአማኞች ጋር የሚኖራት ግንኙነት ተመሳሳይ ነው።*

- ♦ "ሴቲቱም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት" (17፡6)
- ♦ "በእርስዋም ውስጥ የነቢያትና የቅዱሳን ደም በምድርም የታረዱ ሁሉ ደም ተገኝባት" (18፡24)።

*የማጥፊያው መሣሪያ ተመሳሳይ ነው።*

- ♦ "ባድዋንና ራቁትዋንም ያደርጓታል...በእሳትም ያቃጥሉአታል" (17፡16)።
- ♦ "በእሳትም ትቃጠላለች" (18፡8)

*የጥፋቱ ምንጭ አንድ ነው።*

- ♦ "እግዚአብሔር አሳቡን እንዲያደርጉ...በልባቸው አግብቶአልና" (17፡17)
- ♦ "እግዚአብሔር አመጻዋን አሰበ... የሚፈርድባት እግዚአብሔር ብርቱ ነውና" (18፡5፥ 8)

ሁለቱም ምዕራፎች ውስጥ የተጠቀሰችው ባቢሎን ዝርዝር መመሳሰል ያስደንቃል። እያንዳንዱ ምዕራፍ ባቢሎን የተባለች ከተማን ይጠቅሳል። ሁለቱም ምዕራፎች ባቢሎንን የሚገልጧት ሀብቷንና ክፉ ቅርሷን ለይስሙላ የምታሳይ ከተማ እንደሆነች አድርገው ነው። ይህች ከተማ፥ የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ፍርድ እስክትቀበል ድረስ ከሌሎች መንግሥታት ጋር የምታደርገውን ሕገ ወጥ ግንኙነት ሁለቱም ምዕራፎች ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ። ዮሐንስ የሚገልጠው ስለሁለት ሳይሆን ስለአንዲት ከተማ ነው። በአእምሮው ያለችው አንዲት ባቢሎን ስትሆን፥ በዘመናት ሁሉ ራሷን በእብሪት ስታሰግግ የኖረችውም እሷው ናት።

ራእይ ምዕራፍ 17 እና 18ን ዮሐንስ ሲያቀርብ የምዕራፎቹን ስምምነት በሚያጎላና ሰፋ ባለ አቀራረብ ነው። ሁለቱን ምዕራፎች ያስገባቸው፥ ምዕራፍ 16፡19 ውስጥ እግዚአብሔር "በታላቂቱ ባቢሎን" ላይ ያወጀባትን የጥፋት ፍርድ በዝርዝር ለመግለጥ ነው፥ "ታላቂቱም ባቢሎን የብርቱ ቁጣው ወይን ጠጅ የሞላበትን ጽዋ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች"። ይህን ነው ራእይ 17 እና 18 የሚያብራሩት።

ዮሐንስ ስለባቢሎን ውድቀት ከሰማይ የተሰጣትን ፍርድ ራእይ ምዕራፍ 19፡1-3 ባለው ክፍል ውስጥ እንዲህ እያለ በአጭሩ ይገልጠዋል፥

"ሃሌሉያ" ይላሉ የሰማይ አእላፋት፥ ምክንያቱም "በዝሙትዋ ምድርን ያጠፋችይቱን ታላቂቱን ጋለሞታ ስለፈረደባት" (19፡2)። ዮሐንስ ምዕራፍ 17 ውስጥ ደግሞ ባቢሎንን ጋለሞታ ብሎ ገልጧታል። ደግመውም፡- "ሃሌሉያ ጢስዋ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይወጣል" ብሏል (19፡3)። "እስከ ዘላለም" የሚወጣው "ጭስ"፥ ምዕራፍ 18 ውስጥ የተገለጠችውን የተቃጠለችውን የባቢሎን ምስል ያመለክታል።

የምዕራፍ 16 እና 19 ጠቀሜታ የባቢሎንን ውድቀት ለማስተዋወቅና ታሪኩን ጠቅለል ማድረግ ነው። በዚህ ክፍል መሠረት በዮሐንስ አእምሮ ያለችው አንዲት ባቢሎን ስትሆን፥ እርሷንም ምዕራፍ 17 እና 18 ውስጥ በዝርዝር ገልጧታል። ባቢሎን ገናና ትሆናለች፥ እንደገናም ትወድቃለች።

## ጋለሞታይቱ ባቢሎን

ዮሐንስ ራእይ 17 ውስጥ ባቢሎን ላይ የተነገረውን ትንቢት የጀመረው ቀይ አውሬ ላይ የተቀመጠችን ጋለሞታ በመግለጥ ነው። ለዚህ ታላቅ ጽሑፍ ዮሐንስ በቃላት የሚሣል ምሥሉን በመጀመሪያዎቹ ስድስት ቁጥሮች ገልጦታል። ከዚያ በኋላ ነው ቀጥሎ ባሉት አሥራ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ የተጠቀሱትን ራእዮች ይገልጥ ዘንድ እግዚአብሔር አንድ መልአክ የሚልከው። ራእይ 17 ውስጥ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ዓላማ፥ ባቢሎን የምትጠፋበትን ምክንያት ለሐዋርያው ዮሐንስ መግለጥ ነው። ምዕራፍ 18 ደግሞ የባቢሎን ጥፋት በሚኖረው ውጤት ላይ ያተኩራል። እግዚአብሔር ባቢሎንን ለይቶ ለማወቂያ የሚረዱ አራት ቁልፍ የትርጉም መፍቻዎች በዚህ ሁለት ምዕራፎች ሰጥቶናል። ስለባቢሎን የሰጠን ትርጉም ወይም ፍቺ ራእይ 17፡1 ውስጥ የሚገኘው ሲሆን እርሱም፥ "በብዙ ውኃዎች ላይ የተቀመጠችው ታላቂቱ ጋለሞታ" ይላል። ባቢሎንን እንደጋለሞታ የሚገልጠው ቃል፥ ብዙዎች ባቢሎንን እንደ ሐሰተኛ የሃይማኖት ሥርዓት አድርገው እንዲረዱ ምክንያት ሆኗቸዋል። እግዚአብሔር ግን የባቢሎንን ሃይማኖታዊ ሁኔታ በመመልከት አይደለም ባቢሎንን እንደጋለሞታ ሴት የገለጣት። ጋለሞታ ያላት ለኢኮኖሚ ብልጥግና ስትል የምታሳየውን ከመልካም ሥነምግባር የወጣ ምግባሯን አጉልቶ ለማሳየት ነው።

ራእይ 17 ውስጥ የተገለጠችው ክፉ ሴት፥ በብዙ ሁኔታዋ ትንቢተ ዘካርያስ ምዕራፍ 5 ውስጥ ከተጠቀሰችውና "ክፋት ከተሰኘችው ሴት ጋር ትመሳሰላለች። ዘካርያስ በኢፍ መስፈሪያው ውስጥ እግዚአዘብሔር "ክፋት" ብሎ የሰየማትን ሴት ተመለከተ (ዘካ. 5፡7-8)። ክፋት ሁሉ የሞላባት ነበረች። ዘካርያስ ከእርሱ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ፥ የኢፍ

መስፈሪያውን ሁለት መላእክት "በሰናኦር (ባቢሎን) ምድር፤ ቤት ይሠሩለት ዘንድ ይወስዱታል፤ በተዘጋጀም ጊዜ በዚያ በስፍራው ይኖራል አሉኝ" (ዘካ. 5፡11) ብሎ እንደነገረው ገልጧል። ክፋት በክፉ ሴት ተመስሎ አንድ ቀን ባቢሎን ውስጥ ይኖራል። ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 17 ውስጥ የጠቀሳት ጋለሞታ የዘካርያስ ትንቢት ፍጻሜ ትሆን ይሆን?

## ይህ ለኔ ምስጢር ነው

ሌላው የእግዚአብሔር የትርጉም መፍቻ ቁልፍ፥ በጋለሞታይቱ ግንባር ላይ የተጻፈው ስም ነው፥ "ታላቂቱ ባቢሎን" ይልና "ምስጢር የሆነ ስም" "የጋለሞታዎችና የምድር ርኩሰት እናት" (ራእይ 17፡5) በማለት ሌሎች ስሞችንም ያክልበታል። የእነዚህ ስሞች ትርጉም ምንድነው?

ለጥያቄው መልስ ከመስጠታችን በፊት ሁለት ችግሮች መፍትሔ ሊያገኙ ይገባል። አንደኛ፥ ሴቲቱ "ምስጢር" የተባለችው በምን ሁኔታ ነው? ዮሐንስ ሊነግረን የፈለገው፥ ሴቲቱ ግንባር ላይ የተጻፈው ቃል፥ "ምስጢር የሆንሽው ታላቂቱ ባቢሎን" የሚል ነው፤ ወይም "ታላቂቱ ባቢሎን" ተብሎ የተጻፈው ቃል ምስጢር ነው ለማለት ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው አማራጭ ከጽሑፉ አገባብ ጋር ይስማማል። ዮሐንስ መጽሐፉ ውስጥ ሌላ ስፍራ ሴቲቱን ሲጠቅሳት፥ "ታላቂቱ ባቢሎን" በማለት እንጂ "ምስጢር የሆነችው ታላቂቱ ባቢሎን" ብሎ አይደለም (ራእይ 16፡19 እና 18፡2ትን ይመልከቱ)።

መፍትሔ የሚሻው ሁለተኛ ችግር፥ የምስጢሩ ትክክለኛ ምንነት ነው። "ታላቂቱ ባቢሎን" የሚለው ስም ምስጢር የሆነው እንዴት ነው? አንዳንድ ሰዎች "ምስጢር" የሚለውን ቃል በመጠቀም፥ ባቢሎን የተምሳሌትነት ፍች እንዲኖራት ነው እግዚአብሔር የፈለገው ይላሉ። አዲስ ኪዳን ውስጥ ግን ምስጢር የሚለው ቃል የእውነትን ዓይነት ወይም ባህርይ ሳይሆን የሚያሳየው ተረድተውት ባልነበረ እውነትን መገኘትን ላይ የሚያተኩር ነው።

እግዚአብሔር ባቢሎንን ምስጢር ሲላት፥ በ"ጡብና ስሚንቶ" የተሠራች ከተማ እንጂ፥ የጥፋት ረቂቅ ኃይል ሥርዓት ናት ማለቱ አይደለም። ምስጢር ያላት፥ ይህን ለባቢሎን የተነገረ እውነት ቀደም ሲል ያልገለጠ መሆኑን ለማመልከት ነው። የእግዚአብሔር መልአክ ባቢሎን አውሬውን የምትጋልብ የመሆኗን ምስጢር ለዮሐንስ ከገለጠለት በኋላ፥ "የምትደነቅ ስለምንድር ነው? የሴቲቱን ምስጢርና የሚሸከማትን፥ . . . የአውሬውን ምስጢር እኔ እነግርሃለሁ" (17፡7) ይለዋል።

ለዮሐንስ የተገለጠለት ሁለቱ የዓለም ኃያላን (ጋለሞታይቱና የምትጋልበው አውሬ) በፍጻሜው ዘመን በሰላም አብረው የሚኖሩ የመሆኑን ምስጢር ነው። አራተኛው የዓለም ኃያል መሪ (አውሬው)፥ የሚነግና የኢየሱስ መንግሥት በምድር ላይ በመመሥረቻው ዋዜማ ዓለምን የሚገዛ መሆኑን ነቢዩ ዳንኤል ተንብይዋል (ዳን. 2፡40-45፤ 7፡23-27፤ 9፡26-27)። ሌሎች የብሉይ ኪዳን ነቢያት ግን፥ ባቢሎን በእግዚአብሔር ትንቢታዊ ዕቅድ መሠረት በኃያልነት ብቅ የምትል መሆኗን ነው የተነበዩት (ኢሳ. 13-14፤ ኤር. 50-51፤ ዘካ. 5፡5-11)። ነገር ግን ሁለቱ ኃያላን በአንድ ወቅት ሊኖሩና እግዚአብሔር ለዓለም ባለው ዕቅድ ውስጥ ስፍራ ሊኖራቸው የሚችለው እንዴት ነው? የዚህ ጥያቄ ምስጢር ነበር ለዮሐንስ የተገለጠለት።

ሴቲቱም. . .

እግዚአብሔር የሰጠው ሦስተኛ የትርጉም መፍቻ እግዚአብሔር ባቢሎንን የሚገልጥበት መለያ ስለሆነ ከሁሉ የላቀ ሳይሆን አይቀርም። ባቢሎን ስለተባለችው ጋለሞታ ብዙዎች የራሳቸውን ትርጉም ሰጥተዋል። ይሁን እንጂ ማንኛውም መለያ ወይም መግለጫ መጀመር የሚኖርበት እግዚአብሔር ራእይ 17፡18 ውስጥ ከገለጠው መለያ ነው። ምንባቡ ውስጥ መልአኩ ያቀረበው፥ እግዚአብሔር ስለጋለሞታይቱ የገለጠውን ነው። "ያየሃትም ሴት፥ በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት" ብሏል። እግዚአብሔር ስለጋለሞታይቱ የሰጠው ፍች ጠቃሚ የሚሆንበት ምክንያት፥ ራእይ 17 ውስጥ የተጠቀሰች ባቢሎንን እንደክርስትና ሃይማኖት መሪ ወይም እንዳች ምሥጢራዊ ሥርዓት ሳይሆን፥ እንደአንዲት ከተማ ስለሚገልጣት ነው። ባቢሎን ዓለም አቀፍ ጠቀሜታ ያላት ከተማ መሆን አለባት። ምክንያቱም እግዚአብሔር "በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ" ብሎ ያውጅላታል። በዚህች የፍጻሜ ዘመን ባቢሎን ምንነት ላይ ምንም ታከለበት ምን፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሚገልጣት እንደ አንድ ከተማ ነው።

ሰባቱ ተራራዎችስ ምንድናቸው?

ዮሐንስ "የአውሬውን ውበት" ሲገልጥ፥ ሴቲቱ የምትቀመጥበት አውሬ ሰባት ራስ አለው ይለናል። የእግዚአብሔር መልአክ ይህን ጉዳይ ለዮሐንስ የገለጠለት እንዲህ በማለት ነው፥ "ጥበብ ያለው አእምሮ በዚህ ነው። ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች ናቸው፤ ሰባት ነገሥታት ደግሞ ናቸው። አምስቱ ወድቀዋል፥ አንዱም አለ፥

የቀረውም ገና አልመጣም፤ ሲመጣም ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል” (ራእይ 17፡9-10)።

ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች ምንድናቸው? ብዙዎች በተለምዶ ሰባቱ ተራራዎች የሚለው ቃል፥ በዮሐንስ ዘመን፥ ባለ ሰባት ተራራይቱ ከተማ በመባል የምትታወቀውን የሮም ከተማ ነው ይላሉ። እንደእነሱ አባባል ሴቲቱ የምትቀመጠው ሰባት ተራራዎች ላይ ከሆነ፥ ከተማይቱ ሮም መሆን አለባት እንጂ፥ ባቢሎን አይደለችም። ይህ የእግዚአብሔር ትርጉም ነውን?

በሰባቱ ተራራዎች መጠቀስ ምክንያት ጋለሞታይቱን ሴት ከሮም ከተማ ጋር ማገናኘት ከባድ ስሕተት ነው። የመጀመሪያው ስሕተት በሴቲቱና በተራራዎቹ መካከል ግንኙነት አለ የሚለው ነው። ሰባቱ ራሶች ከአውሬው እንጂ ከሴቲቱ ጋር የተያያዙ አይደሉም፤ ሰባቱ ተራራዎችም የአውሬው አካላት ናቸው። ዮሐንስ በሴቲቱና በአውሬው መካከል ልዩነት እንዳለ ያሳያል። መልአኩም እንዲህ ብሎ ነው የገለጠው፥ “የሴቲቱን ምስጢርና የሚሸከማትን፥ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉትን የአውሬውን ምስጢር እኔ እነግርሃለሁ” (17፡7)። ሰባቱ ተራራዎች ስለሮም የሚገለጡ ከሆነ እንግዲህ፥ ዮሐንስ የሚናገረው፥ የፍጻሜው ዘመን የዓለም መሪ የግዛት ማዕከል፥ ሮም ትሆናለች ብሎ ነው ሊባል ይሆናል። ጋለሞታይቱ ሴት የአውሬው አካል ክፍል ስላልሆነች፥ ሰባቱ ተራራዎች እርሷ የምትገኝበትን የሚያመለክቱ አይደሉም።

አንዳንዶች አሁንም ዮሐንስ “ሴቲቱ የምትቀመጥባቸው ሰባት ተራራዎች” ብሎ ስለተናገረ ጋለሞታይቱ ከሮም ጋር መሆን አለባት ይላሉ። የጋለሞታይቱ በሰባቱ ተራራዎች ላይ መቀመጥ የሚያመለክተው አድራሻዋን ሳይሆን፥ ገዢነቷን ነው። ራእይ 17፡1 ውስጥ እንደተገለጠው ሴቲቱ፥ “በብዙ ውኃዎች” ላይ ትቀመጣለች። ራእይ 17፡15 ውስጥ መልአኩ ውኃዎቹን ሲተረጉም፥ “ወገኖችና ብዙ ሰዎች፥ አሕዛብም ቋንቋዎችም ናቸው” ይላል። ውኃዎች ላይ መቀመጧ የሚያመለክተው፥ የዓለም ሕዝቦችን የመቆጣጠር ሥልጣኗን ነው። ዮሐንስ ሴቲቱ “በቀይ አውሬ ላይ መቀመጧን በተጨማሪ ይገልጣል (17፡3)። ሴቲቱ የምትቀመጠው በአውሬው ሁለንተና ላይ እንጂ፥ ራሶቹ ላይ ብቻ አይደለም። ይህም የሚያመለክተው ሥፍራን ሳይሆን የመቆጣጠር ጉዳይ ነው። የጋለሞታይቱ መቀመጥ ምዕራፉ ውስጥ ሁለት ጊዜ ገዢነቷን በግልጥ የሚያመለክት ከሆነ፥ ሁኔታው ለሦስተኛ ጊዜ ቢደገም ታዲያ ለዚያው ጉዳይ የተለየ ትርጉም መስጠቱ ተስማሚ ይሆናል? የጋለሞታይቱ “መቀመጥ” በሰባቱ ተራራዎች ላይ ያላትን ገዢነት ያመለክታል ማለቱ፥

አድራሻዋን ነው የሚገልጠው ከሚለው ትርጉም እጅግ የላቀ ተስማሚነት አለው።

ሰባቱ ተራራዎች የሚለው ቃል የሮም ከተማ ማለት ነው ብንል እንኳን፥ ትርጉሙ ከተማይቱ ናት ጋለሞታይቱ ማለት አይደለም። ሰባቱ ተራራዎች የሚያመለክቱት የሮም ከተማን ሳይሆን፥ ሌላ መሆኑን ለማመን የሚያስችል ማስረጃ አለ። የተራራዎቹ ተምሳሌታዊነት ገለጣ፥ ሐዋርያው ዮሐንስ ከአይሁድ የወረሰውን ዘይቤ የሚከተል ነው። "የራእይ መጽሐፍ በቋንቋውና በምስል ገለጣው ከማንኛውም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ይልቅ በእጅጉ አይሁዳዊ ነው። መጽሐፉ የሚጠቀመው ጳውሎስ የተጠቀመበትን ቋንቋ ሳይሆን፥ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ማለት ኢሳይያስ፥ ሕዝቅኤልና ዳንኤል የተጠቀሙበትን ቋንቋ ነው።"

አዲስ ኪዳን ውስጥ ተራራ የመንግሥት ወይም የብሔራዊ ኃይል ተምሳሌት ሆኖ ነው ያገለገለው። ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሏል፥ "በዘመኑ ፍጻሜ የእግዚአብሔር ቤት ተራራ፥ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል፥ ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል፥ አሕዛብም ሁሉ ወደእርሱ ይሰበሰባሉ" (ኢሳ. 2፡2)። ኤርምያስ 51፡25 ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር ለባቢሎን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ እንዲህ ብሏል፥ "አንተ ምድርን ሁሉ የምታጠፋ አጥፊ ተራራ ሆይ፥ እነሆ እኔ በአንተ ላይ ነኝ፤ ይላል እግዚአብሔር፤ እጄንም እዘረጋለሁ፥ ከድንጋዮችም ላይ አንከባልልሃለሁ፥ የተቃጠለም ተራራ አደርግሃለሁ"።

ነቢዩ ዳንኤል እንዲህ የገለጠውን ራእይ ተመለከተ፥ "ምስሉን የመታ ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሆነ፥ ምድርንም ፈጽሞ ሞላ" (ዳን. 2፡35)። ተራራው የምን ተምሳሌት ነው? "በእነዚያ ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ የዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል። ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል። እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች፥ ታጠፋቸውማለች ለዘላለምም ትቆማለች" (ዳን. 2፡44)።

ብሉይ ኪዳን ተራራን እንደተምሳሌት የሚጠቀምበት አንድን መንግሥት ለመግለጥ ነው። ራእይ 17 ውስጥ የተጠቀሱትን ሰባት ተራራዎች የሰባት መንግሥታት ተምሳሌት ናቸው ለማለት የሚያስችል ሌላ ምክንያትም አለ። ሰባቱን ተራራዎች እንደ የሰባት የመንግሥታት ተምሳሌቶች ናቸው፥ የአውሬው ሰባት ራሶችም የሚያመለክቱት የተራራዎቹና የነገሥታት ተምሳሌትን ነው።

ሰባቱ ተራራዎች ሮምን የሚገልጡ ከሆነ ግን፥ ራእዩ ውስጥ የተጠቀሱትን ሰባት ነገሥታት መለየቱ አስቸጋሪ ይሆናል። የሮም ሰባት ነገሥታት እነማን ናቸው? ብዙዎቹ ሰባቱ ነገሥታት ከአውግስጦስ ቄሳር

እስከ ቲቶ ያሉት የሮም አገዛዝ ነገሥታት ናቸው ለማለት ይሞክራሉ። ሰባቱን ተራራዎች በእነዚህ ነገሥታት ቁጥር ለማስተካከል ቢሞከር፥ ኔሮና ቨስፓሲያን በተባሉት ነገሥታት መካከል የነበሩት ሌሎች ሦስት የሮም ነገሥታት መዘለል አለባቸው። ይህ ጥሩ አተረጓጎም አይደለም። ይህን አተረጓጎም ጥሩ የሚያደርገው በመሀከል የነበሩን ነገሥታትን ማለትም ጋለባ፥ ኦቶ እና ቪቴሊየስን ቸል ማለቱ ነው። እነዚህ መሪዎች ታዋቂ መሪዎች ባይሆኑም በነገሥታትነት የሚታወቁና በቀድሞ የታሪክ ጸሐፊዎች የተዘገቡ ናቸው። በዮሐንስ ራእይ የተገለጡት ሰባት ነገሥታት ከሮም ታሪክ ጋር አይስማሙም።

መልአኩ የእግዚአብሔርን ራእይ ለዮሐንስ ሲገልጥለት፥ የአውሬው እያንዳንዱ ራስ አንድ ተራራ እና አንድ ንጉሥ የሚወክሉ መሆናቸውን አስገንዝቦታል። ይህ ገለጣ የሚመስል ሊሆን የሚችለው "ተራራ" የሚለው ቃል መንግሥትን የሚያመለክት ምሳሌ ሲሆን ብቻ ነው። ራሶቹ ሰባት መንግሥታትና እነርሱን የሚገዙ ሰባት ነገሥታት ናቸው። በተለምዶ አንድን መሪ ከሚመራው መንግሥት ጋር የምናዛምድበት አገላለጥም አለ። ለምሳሌ የአሜሪካንና የሩሲያን መንግሥትን ለመግለጽ "የፕሬዚዳንት ክሊንተን አስተዳደር" ወይም "የፕሬዚዳንት የልሲን" አስተዳደር እንደማለት ነው።

ነቢዩ ዳንኤል ይህን አገላለጥ በሚገባ ተጠቅሞበታል። ዳንኤል 2 ውስጥ ነቢዩ ናቡከደነፆር በሕልሙ ስላየውና ከተለያዩ ብረቶች ስለተሠራው ምስል ፍች በተናገረ ጊዜ፥ "አንተ [ንጉሥ ናቡከደነፆር] የወርቁ ራስ ነህ። ከአንተም በኋላ ከአንተ የሚያንስ ሌላ መንግሥት ይነሣል" (ዳን. 2፡38-39) ብሏል። ወርቅ የሆነው የምስሉ ራስ ንጉሥ መሆኑን ነቢዩ ጽፏል። የምስሉ ሁለተኛ አካል ግን ሌላ መንግሥትን የሚያመለክት ነበር። ዳንኤል የተመለከተው፥ እፊቱ በነበረው ንጉሥ ውስጥ ሰውኛ ተምሳሌት የተላበሰውን የባቢሎንን መንግሥት መሆኑ ግልጥ ነው። በመሆኑም የታሪኩን አካሄድ ሳይጠብቅ ትኩረቱን ከንጉሡ ወደመንግሥቱ ሊያዞር ይችል ነበር። ሐዋርያው ዮሐንስ ሰባቱን መንግሥታትና ሰባቱን ነገሥታት የተመለከታቸው በተመሳሳይ አኳኋን ነው። መልአኩ ራእይ 17፡9-10 ውስጥ ባለው ክፍል የገለጣቸው "ተራራዎች" እና "ነገሥታት" የሚያመለክቱት፥ ምናልባት ሰባት መንግሥታትንና ነገሥታቶቻቸውን እንጂ፥ የሮም ከተማን አይደለም።

## በመቃረብ ላይ ያለው ምን ይሆን?

እግዚአብሔር ራእይ ምዕራፍ 17 እና 18 ውስጥ በፍጻሜው ዘመን ስለሚነሣውና ባቢሎን ስለሚባለው ኃይል ጠቃሚ መግለጫ ሰጥቷል።

ባቢሎን የሚለው ቃል በጥሬ ትርጉሙ ሲታይ ዓለምን የምትገዛ ከተማ ማለት ነው። ባቢሎን ለቁሳዊ ቅንጦት ስትል በሥነ-ምግባራዊ ፋይዳዋ በምታመነዝር ጋለሞታ ተመስላለች። እግዚአብሔር ባቢሎንን ምስጢር ይላታል፤ ምክንያቱም ከፍጻሜው ጊዜ የዓለም ገዢ ጋር የሚኖራትን ግንኙነት ቀደም ብሎ አልገለጠም ነበር። ባቢሎን በአብዛኛው የዓለም ክፍል ላይ የቁጥጥር ሚና የምታደርግ ይመስላል።

ራእይ 17 ውስጥ እግዚአብሔር የሚገልጣቸው አራት የትንቢት መፍቻዎች ወደዓለም የሚገቡትን ረቂቅ የሃይማኖት ሥርዓቶች ቁልፎች አይከፍቱልንም። በዚያ ፈንታ ከጡብና ስሚንቶ በተሠራችው፥ እንዲሁም በኃይልና በቅንጦት በሰከረችው ባቢሎን ላይ የሚነገረውን ትንቢት በር ነው የሚከፍቱልን። በዚህ ምዕራፍ የተገለጠችው ባቢሎን በመልክዓ-ምድርም ሆነ በፖለቲካ ገናና ትሆናለች።

ዮሐንስ “ታላቂቱ ባቢሎን፥ የምድር ጋለሞታዎችና ርኩሳን እናት” የተባለችውን ጋለሞታ ነው የሚገልጠው። እግዚአብሔርም ራእይ 17፡18 ውስጥ “ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት” በማለት የጋለሞታይቱን ማንነት ይተረጉማል። የዮሐንስ ባቢሎን፥ ደቡብ ኢራቅ ውስጥ የምትገኝና በፍጻሜው ዘመን የምትኖር አንዲት ከተማ ናት። ለምንድነው ባቢሎን “የአመንዝራዎች ሁሉ እናት” የተባለችው? እግዚአብሔር የሚሰጠው ስያሜ አስጸያፊውን የባቢሎን ታሪክ በአጭሩ ይገልጠዋል። እግዚአብሔር መለስ ብሎ የባቤልን ግንብ በማየት፥ ከጥፋት ውኃ በኋላ ባቢሎን የዓመፅ መፈልፈያ ስፍራ መሆኗን ይመለከታል። ይህች የጥፋት ከተማ በእግዚአብሔር ሳይሆን በራሷ መንገድ ወደሰማይ ለመድረስ ዓመፅንና ያልተሳካ ሙከራዎችን አድርጋለች።

ባቢሎን በፍጻሜው ዘመን ዓለምን እንደገና የምትቆጣጠር መሆኗን ዮሐንስ በአስደናቂ ሁኔታ ይተነብያል። የምትቆጣጠረው ኢኮኖሚውን ነው። ከተማይቱ ለማመን የሚያዳግት ብልጥግና እንደሚኖራት ሲገልጥ፥ “የምድርም ነጋዴዎች ከቅምጥሊቱ ኃይል የተነሣ ባለጠጋዎች ሆኑ” (ራእይ 18፡3)። “አውሬው” የሚል ስም የተሰጠውን የፍጻሜው ዘመን የዓለም ገዢም ትቆጣጠረዋለች! “ከምድር ነገሥታት” (18፡9) ጋርም ሕገ-ወጥ ንግድ ታካሂዳለች። ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተሰሚና ኃያል ወደመሆኑ ከፍታ ትወጣለች።

ይሁን እንጂ፥ በገሃድ የምናውቃት ባቢሎን እነዚህን ትንቢቶች የምትፈጽመው እንዴት ነው? ባቢሎን የምትገኘው ኢራቅ ውስጥ አይደለምን? የኢራቅ ክብርና ኃይልስ በበረሃው ማዕበል ዘመቻ ጊዜ ለመልካም ዓላማ ሲባል አልተደመሰሰምን? መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትንቢት

ተዓማኒ አድርገው ከተቀበሉት፥ ምንም የበረሃው ማዕበል ዘመቻ ቢካሄድባት፥ ባቢሎን በዓለም ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ትይዛለች ብለው እርግጠኛ ይሁኑ። ነገር ግን ይህ እንዴት ነው የሚሆነው?

*መጀመሪያ* በባሕረ-ሰላጤው ጦርነት ወቅት የባቢሎን ከተማ በቦምብ አልተደበደበችም ወይም አልተደመሰሰችም። በሳዳም ሁሴን የተጀመረው ባቢሎንን መልሶ የመገንባት ዕቅድም አልተቋረጠም። ጦርነቱ ከቆመ ወዲህ እንደውም ባቢሎን ውስጥ የሚከናወነው ግንባታ ቀጥሏል። በመስከረም ወር 1992 እአአ አራተኛውን የባቢሎን በዓል ለማክበር ኢራቅ የጥሪ መልእክት አሠራጭታለች። ከመላው ዓለም የሚመጡ እንግዶች ሳዳም ሁሴን የሚገነቧት ባቢሎንን እንዲመለከቱ እንደገና ተጠርተዋል።

> ኢራቅ ያቀደችውን አዲስ ቁፋሮ ስታካሂድ፥ ጎብኚዎች ቆመው ይመለከቱባቸው ዘንድ ሦስት ትልልቅ የመመልከቻ ሠገነቶች በመሠራት ላይ ናቸው። ሠገነቶቹ የሚሠሩት የናቡከደነፆር ባቢሎን ከነበረችበት ግንብ በስተውጭ ነው። "ይህ ሥራ ፕሬዚዳንቱ በግል ያዘዙት ነው" ብለዋል የኢራቅ ጥንታዊ ቅርሶች ጉዳይ ዳይሬክተር የሆኑት ሞዋያድ ሰይድ።

አንድ ሰው ባንድ ወቅት ባቢሎን ዋና ከተማችን ትሆናለች ባለ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች ይፈጸማሉ። ከተማይቱ ሙሉ በሙሉ እንደገና በመታደስ መገንባት አያስፈልጋትም። ባቢሎን እንደምትኖር፥ የመካከለኛው ምሥራቅ ግዛት ዋና ከተማ እንደምትሆንና እጅግ ግዙፍ የሆነ ብልጥግናና ንግድ መነኻሪያ እንደምትሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጣል።

ሳዳም ሁሴን ባቢሎን ዋና ከተማዬ ናት ብለው አላወጁም። ነገር ግን እሳቸውም ሆኑ ወደፊት የሚነሣ ሌላ መሪ አወጀው፥ ብቻ በማንኛውም አኳኋን ባቢሎን መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ እንደገና የአንድ ግዛት ዋና ከተማ ትሆናለች።

ሁለተኛ ኢራቅ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ አሁንም በወታደራዊ አቅሟ ኃያል ናት። "ለስድስት ወራት ያህል ሳዑዲት ዓረቢያ ምድረበዳ ውስጥ አሜሪካን የጦር ኃይሏን ስታከማች ከዚህ የአሜሪካን ወታደራዊ ኃይል ጋር ሲነጻጸር የኢራቅ የጦር ኃይል ደካማ ይመስል ይሆናል። ከጎረቤቶቿ ጋር ሲተያይ ግን እጅግ የላቀና ግዙፍ ነው"። አሜሪካን ወደፊት የባሕረ-ሰላጤው መንግሥታትን የመከላከል አቅም ባይኖራት ወይም ፍቃደኛ ባትሆን ኢራቅ ኩዌትን ለመውረርና ሳዑዲት ዓረብን ለማስፈራራት አሁንም ወታደራዊ ኃይል አላት። ሳዳም ሁሴንን ከወራሪነት ድርጊታቸው ለመግታት ወይም እሳቸውን የሚተካን የወደፊት መሪ ለመከላከል፥ በቂ ወታደራዊ ኃይል ወደመካከለኛው ምሥራቅ

ለማስገባት የሚችል ከአሜሪካ በቀር ሌላ የዓለም ኃያል መንግሥት የለም። ሳዳም ሁሴን ዓለም ካላት ነዳጅ ዘይት ከግማሽ በላይ የሚገኝበትን አካባቢ ቢቆጣጠሩ ሰውዬው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የማዕቀብ ውሳኔዎችን ለማስሻር፥ ባላቸው ዕቅድ መሠረት ምዕራቡን ዓለም ለማሳመን የሚያስችል የገንዘብም ሆነ የተጽዕኖ አቅም ይኖራቸው ነበር። ዓለምም የነዳጅ እደላው እንዳይቋረጥ በመሥጋት የሰላም ስምምነት ያደርግ ነበር።

ከነሐሴ 1990 እአአ ቀደም ሲል ከኢራቅ ይመጣ የነበረውን አስፈሪ ነገር የዓለም ሕዝቦች ችላ አሉ። ሳዳም ሁሴን ግን በሳምንታት ውስጥ ነው ዓለም ለጥቃት የተጋለጠች መሆኗን በድርጊታቸው ያሳዩት። ከጦርነቱ በኋላም ቢሆን ብዙ የዓለም መንግሥታት አስፈሪው ነገር ያበቃለት መሰላቸው። ይህ ግን ሙሉ በሙሉ እውን አልነበረም። በታህሣስ ወር 1993 እአአ ሳዳም ሁሴን የምዕራቡን የቃል ኪዳን ኃይል ተገዳደሩት። በጊዜው አንድ የኢራቅ ባለሥልጣን እንዲህ ብለው ነበር፥ "የጦርነት ማቆም ስምምነቱን ተቀብለናል፤ እጃችንን ሰጥተናል ብለን ግን ለማንም አልፈረምንም ... ጦርነቱ እንዳበቃ የተቀበልነውን ግዴታ፥ ከአንድ ዓመት በኋላ እምቢ አልን። ከዚያ አንድ ዓመት ወዲህ የተቀበልነውን፥ አሁን እምቢ እንላለን፥ አሁን የምንቀበለውንም ከአንድ ዓመት በኋላ እምቢ እንላለን።" ባቢሎን በዓለም ፍጻሜ መቃረቢያ ላይ ዋና የኢኮኖሚ ኃይል እንደምትሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጣል። ኢራቅም ለፈጣን እድገት አሁንም እጅግ ምቹ ሁኔታ አላት።

> ምዕራፍ አሥራ አንድ <

# ቱርክ፥ ኢራን እና የእስላማዊው ኅብረት በእስራኤል ላይ ማበር

በ1979 እአአ ኢራን ውስጥ ይከናወን የነበረው የአክራሪነት እንቅስቃሴ ለአሜሪካኖች የሚያስገርምና የሚያናውጥ ዜና ነበር። የኢራን ሺያት አክራሪዎች ሃይማኖታዊ መሪ የነበሩት አያቶላ ሩሆላህ ሆሚኒ ለአሥራ አምስት ዓመታት በስደት ከቆዩ በኋላ ወደ አገራቸው ተመለሱ። እኚህ ሰው፥ የኢራኑን ሻህ ከዙፋናቸው አስወግደው፥ ኢራንን ወደ እስላማዊት ሪፑብሊክነት ለመለወጥ ይታገሉ ጀመር።

አሜሪካን የእስልምናና የኢራን ሕዝብ ጠላት ሆና ተቆጠረች። ጥቅምት 4 ቀን 1979 እአአ ኢራን ውስጥ ለተቃውሞ የወጣ ሕዝብ የአሜሪካንን ኤምባሲ ከቦ እዚያ የነበሩ ሠራተኞችን አሠራቸው። አክራሪ እስላሞች በኢራን ጎዳናዎች እየተዟዟሩ "ሞት ለአሜሪካን!" ሲሉ፥ የአሜሪካንን ባንዲራ ሲያቃጥሉና ዜጎቿን ሲያሥሩ፥ አሜሪካን ለ443 ቀናት ግራ በመጋባትና በዝምታ ተመለከተች። ሁኔታው እስከዛሬ አገሪቱ ስለ መካከለኛው ምሥራቅ ባላት ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ስሜት አሜሪካ ውስጥ ፈጠረ።

## ሳዳም፥ ሳዳም፥ የኛ ጀግና ናቸው

የባሕረ-ሰላጤው የ1979 እአአ ችግር ለ1991 እአአ ጦርነት ምክንያት የሚሆን ዘር በውስጡ ነበረው። አያቶላ ሆሚኒ ወደ ኢራን በተመለሱ በአምስት ወሩ፥ ሳዳም ሁሴን ኢራቅ ውስጥ ከፍተኛውን ሥልጣን ያዙ። አንድ የሃይማኖት መሪና ሌላ አብዮተኛ አብረዋቸው ነበሩ። ሁለቱም ሥር የሰደደ ተልእኮና ግብ ነበራቸው! የመካከለኛው ምሥራቅን መልክ መለወጥ። የአሜሪካን ታጋቾች ኢራን ውስጥ በመሠቃየት ላይ ባሉበት መስከረም 22 ቀን 1980 እአአ የሳዳም ሁሴን ታንኮች ወደ ኢራን ድንበር ተጠጉና፥ በኢራቅና በኢራን መካከል የተካሄደውን የስምንት ዓመት ጦርነት ጀመሩ።

ሳዳም ሁሴን ብዙውን ወታደራዊ እርዳታና ሥልጠና ከሶቪየት ኅብረት ሲያገኙ፥ አሜሪካን ደግሞ ቀደም ሲል የኢራንን ሠራዊት በአሜሪካ ሠራሽ የጦር መሣሪያዎች አስታጥቃለች። ይሁን እንጂ፥ የሆሚኒ ወደ ሥልጣን መውጣት፥ አሜሪካን ከኢራን ጋር የነበራትን ግንኙነት ለወጠው። ምንም እንኳን አሜሪካን ሁለቱ አገሮች ጦርነት በሚያደርጉ ጊዜ ገለልተኛ ነኝ ብትልም፥ ተቃዋሚ ሠልፈኞች ዜጎቿን ካገቱባት ወዲህ፥

አሜሪካን ውስጥ የነበሩት የኢራን ሀብቶች እንዳይንቀሳቀሱ አግዳ ነበር። ማንኛውም ወታደራዊ መሣሪያ ወይም መለዋወጫ ወደ ኢራን እንዳይጓጓዝ ከለከለች። የውጭ ፖሊሲዋ አያቶላ ሆሚኒንና ኢራንን ከመጥላት አኳያ የተቀረፀ ሆነ።

የሳዳም ሁሴን ጦር በመጀመሪያ ድል ያገኘ ቢመስልም፥ በኋላ ግን ይበታተንና ያፈገፍግ ጀመር። የኢራን ወታደሮች የኢራቅን ጦር አጥቅተው ከተያዘው ግዛታቸው አስወጡት። በ1980ዎቹ አጋማሽ ላይ ድሉ ወደ ኢራን ማድላቱ ግልጥ ሆነ። የኢራቅ ድል መሆን ገሀድ እየሆነ በመጣ ጊዜ፥ አሜሪካንና ሌሎች ምዕራባውያን አገሮች ሳዳም ሁሴንን በመርዳት፥ ኢራቅ ይደርስባት የነበረውን ጥፋት አገዱት። ብዙ አገሮች ዘመናዊ ጦር መሣሪያዎችንና ጠቃሚ መረጃዎችን ለኢራቅ ለመስጠት ተባበሩ።

እነዚህ አገሮች ኢራቅንና ሳዳም ሁሴንን የረዱቸው ለምንድነው? የሰውዬውን አሸባሪነትና የሰብአዊ መብት ረገጣ ታሪክ አልዘነጉትም። ሳዳም ሁሴን ሥልጣን በያዙ በጥቂት ቀናት ውስጥ ነው ሀያ አንድ ተቃዋሚዎቻቸውን ያሠሩና የረሸኗቸው። በኩርዳውያን ላይ የሚያካሄዱትን የሽብር አገዛዝ ገፍተውበታል። "አሜሪካውያንና ምዕራባውያን፥ ኢራቅን ለመርዳት የሚያሳዩት ዝንባሌ፥ ባዝ የተባለው የአገሪቱ ፓርቲ ኩርዳውያንን እንዲጨፈጭፍ ምቹ ሁኔታ ፈጠረለት።" የሳዳም ሁሴንን ጭካኔና አደገኛነት የተረዳ ሰው አልነበረምን?

ሌሎቹ የዓለም መንግሥታት የሳዳም ሁሴንን ድርጊት ችላ ቢሉትም፥ እስራኤል ግን አላለችም። የሰውዬውን እኩይ ዕቅድ በመረዳቷ ነው፥ የሚደርስባትን ዓለም አቀፍ ውግዘት በመቋቋም፥ በሰኔ ወር 1981 እአአ ባግዳድ አቅራቢያ የነበረውን የኑክሊየር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ በቦምብ የደበደበችው። ይህ ብቻም አይደል፥ ብረት ለበሶችንና ሌሎች ወታደራዊ መሣሪያዎችን ለኢራናውያን አቀብላለች። ይህ ግን የአገሪቱ መሪ ሆሚኒም ሆኑ፥ አክራሪ እሳላሞች በአደባባይ ያመኑት ጉዳይ አይደለም። ሳዳም ሁሴን ለወታደራዊ የበላይነት ካላቸው ምኞት ሳቢያ የሚመጣባቸውን አደጋ እስራኤላውያን ተገንዘቡና፥ ሊገቷቸው ፈለጉ።

የተከናወኑ ነገሮችን ዞር ብሎ መመልከቱ መልካም ግንዛቤን ያስገኛል። በዚሁ መሠረት የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት የሳዳም ሁሴንን አነሣሥ ጥርት ባለ ሁኔታ እንድናጤን ይረዳናል። ይሁን እንጂ፥ የሳዳም ሁሴን ዓላማዎች ሊገለጡ ይችሉ የነበሩት ሰውዬው ኩዌትን ከወረሩ በኋላ ነበር? ምርጥ የዓለም የመረጃ ተቋማት ሳዳም ሁሴን እጅግ ኃያል እንዲሆኑ በዝምታ በተመለከቷቸው ጊዜ ይከተል የነበረውን አደጋ አላጤኑትም ነበር? ለምን ነበር ምዕራባውያን ትኩረታቸውን በኢራን ጉዳይ ላይ አድርገው፥

ለምዕራቡ ዓለም አደገኛ የሆነችውን አገር ችላ ያሏት? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሆኑ ሁለት ምክንያቶች አሉ።

መጀመሪያ፥ የኢራን በአክራሪ እስላማውያን እጅ መውደቅ ለምዕራቡ ዓለም ድንገተኛ ነገር ሆነበት። የሆሚኒ በፍጥነት ወደ ሥልጣን መውጣትና የአክራሪ ሙስሊሞችን ድጋፍ ማግኘትም በምዕራቡ ዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ ፍርሃትና ግራ መጋባትን ፈጠረ። በቬትናም ጦርነት ምክንያት የተፈጠረው ሥነ-ልቦናዊ ችግር በሕዝቦቿ ላይ ስለአጠላ፥ ኢራን ለአሜሪካን ዜጎች ችግርን ልትፈጥር በምትችልባቸው ጉዳዮች ላይ አንዳች እርምጃ ለመውሰድ አሜሪካን ኃይል ያጣች መሰለች። የአሜሪካን ትኩረት ያደላው በሳዳም ሁሴን ላይ ሳይሆን፥ በሆሚኒና በአክራሪ እስላማውያን እንቅስቃሴ ላይ ነበር።

ሁለተኛ፥ አሜሪካን መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚገኙትንና የምዕራቡ ዓለም ወዳጅ የሆኑትን አገሮች ከጥቃት ለመከላከል የነበራት ፍላጎት ኢራንን እንደ ጠላት እንድታያት አደረጋት። የኢራን መሪ የነበሩት የሆሚኒ ዕቅድ፥ ፀረ-ምዕራቡ ዓለም የሆነውን አዲስ ሃይማኖታዊ አክራሪነት በመላው የሙስሊም ዓለም ማሰራጨት ነበር። ቢሳካላቸው ኖሮ፥ ፋርስ ባሕረ-ሰላጤ አካባቢ ያለውንና ዓለም ካላት የነዳጅ ሀብት ግማሹ የተከ ማቸበትን የባሕር ዳርቻ በመያዝ፥ ዛቻቸውን ዓለም አቀፋዊ ይዘት እንደሚኖረው ማድርግ ነበር ዓላማቸው። የምዕራቡ ዓለም ሥልጣኔ ኢራናውያን አክራሪዎች የሚይዙት ሁለተኛ ታጋች ይሆን ነበር? ይህ አደጋ ያሠጋቸው በተለይ ኩዌትና ሳውዲት ዓረቢያ ነበሩ። ምንም እንኳን መከታው ከሳዳም ሁሴንና ከኢራቅ ሠራዊት ቢሆን፥ አሜሪካን እነዚህን አገሮች ከሆሚኒ አደጋ መከላከል ነበረባት።

## ኢራን፥ የደከመች ግን ያልወደቀች አገር

በኢራንና በኢራቅ መካከል ለስምንት ዓመት የተካሄደው ጦርነት በ1988ቱ በጋ አበቃ። ባገኙት ድል የተበረታቱት የኢራቅ ወታደሮች፥ በኢራናውያን ይዞታ ላይ ባደረሷቸው ሦስት ጥቃቶች በመጀመሪያው ፋኦ የተባለችውን ባሕረ-ገብ ምድር ያዙ። ጦርነቱና ቀደም ሲል የተደረገው ሃይማኖታዊ የማጥራት እርምጃም የኢራንን ኢኮኖሚ አደቀቀው። የገንዘብ ዋጋ ግሽበትና የሥራ እጦ ብዛት ኢኮኖሚውን ሲያናጋው፥ የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች ደግሞ እንደ ችግር ፈጣሪ እየተመከኛኙ እርስ በርሳቸው ይወቃቀሱ ጀመር።

ሆሚኒ በተባበሩት መንግሥታት አማካይነት የቀረበውን የተኩስ አቁም ስምምነት ለመቀበል ተስማምተው ነበር። ውሳኔው የአክራሪ እስልምና አብዮት መሐንዲስ ለነበረችው አገር መራራ ሽንፈት ሆነ። ሆሚኒ

እራሳቸው የተኩስ አቁም ስምምነቱን ስለ መቀበል አስመልክተው ሲናገሩ፥ "ከመርዝ የከፋና ገዳይ ውሳኔ ነው" ብለዋል። ቢሆንም ስምምነቱን ከመቀበል ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም።

ኢራን በሼሁ አመራር ሥር ትተዳደር በነበረ ጊዜ የነበራት ገናናነት በሆሚኒ ዘመን አልነበረም። የዘጠኝ ዓመቱ እስላማዊ አክራሪነት አመራርና የስምንት ዓመቱ ጦርነት አፈራረሳት። አንዳንዶች እንደገመቱት፥ ኢራን ከነዳጅ ሽያጭ ታገኝ የነበረውን 23 ቢሊዮን ዶላር በጦርነቱ ሳቢያ አጥታለች። በተጨማሪም ለጦር መሣሪያ መግዣ 24 ቢሊዮን ዶላር እንድታወጣ ጦርነቱ አስገድዷታል። ከኢራቅ ጋር በተደረገው ጦርነትም በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢራናውያን ሞተዋል። በአሥር ሺሆች የሚቆጠሩት ደግሞ "ከሀዲዎችን ማስወገድ" በሚለው የአክራሪ እስላማውያን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ዘመቻ ተገድለዋል።

ኢራን ጦርነቱን የፈጸመችው ተጎሳቁላ፥ ተጎድታና ሌሎች አገሮች አግልለዋት ነው። ኢኮኖሚዋ ወድሞ፥ ጦር ኃይሏ ፈራርሶ ለማንሠራራት የነበራት ተስፋም ጨልሞ ነበር። እስላማዊው አብዮትም አልተሳካም። ከሆሚኒ ሞት በኋላ፥ ምዕራባውያን አገሮች ኢራን ከመከራዋ ስለተማረች፥ ከሠለጠኑት የዓለም ሕዝቦች ጋር ቀስ በቀስ ትቀላቀላለች በማለት ተስፋ አድርገው ነበር። እነዚህ ሕዝቦች አሁንም በመጠባበቅ ላይ ናቸው። ኢራን መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ እንደገና የምትጫወተው ሚና ይኖር ይሆን?

ከባሕረ-ሰላጤው ጦርነት ወዲህ፥ ኢራን የምታካሄደው የጦር ኃይል ግንባታ፥ ጎረቤቶቿ የሆኑ ዓረቦችንም ሆነ ምዕራባውያንን የሚያሳስብ ሆኗል። አገሪቱ የጦር መሣሪያ ለመግዣ በዓመት ሁለት ቢሊዮን ዶላር ታወጣለች። መሣሪያዎቹን የምትገዛው በዋናነት ከቻይናና ከሩሲያ ነው። ሲ.አይ.ኤ የተባለው የአሜሪካን የስለላ ድርጅት እንዳረጋገጠው፥ ኒውክሊየራዊ፥ ኬሚካላዊና ባዮሎጂካላዊ የጦር መሣሪያዎችንም በማምረት ላይ ናት። ሩቅ ተምዘግዛጊ ሚሳይሎችና ባሕር-ሰርጓጅ መርከቦችንም ትሠራለች። እስላማዊ አክራሪነትን ለማስፋፋት ያላት ቁርጠኛ ዓላማም ያለገደብ በመስፋፋት ላይ ነው። የአገሪቱ የመጨረሻ ግብ፥ ባጠቃላይ መካከለኛው ምሥራቅን ፀረ-ምዕራባዊ ዓለም የሆነ አክራሪ እስላማዊ ግዛት ማድረግ ነው። ምዕራቡ ዓለም ሳዳም ሁሴንን ለማስወገድ ሲል የሠራው አንድ ስሕተት፥ ኢራን ጦሯን አደራጅታ ጠብ አጫሪነቷን እንድትቀጥልበት ማድረጉ ነበር።

## ቱርክ "ምዕራባዊቱ" እስላማዊ መንግሥት

ቱርክ ከጥንት ጀምራ ምዕራቡንና ምሥራቁን ዓለም እንደድልድይ በማገናኘት አገልግላለች። ሐዋርያው ጳውሎስ ያደገው፥

የደቡባዊው ቱርክ ክፍል በሆነችው የጠርሴስ ከተማ ውስጥ ነበር። ዛሬ ምዕራብ ቱርክ እየተባለ በሚጠራው ክፍል አብያተ ክርስቲያን ተክሏል። እግዚአብሔር ለአገልግሎት ጠርቶት ወደ አውሮፓ ምድር እስከገባ ድረስ አገልግሎቱ ያተኮረው፥ ቱርክ ወይም ትንሹ እስያ ውስጥ ነበር። ቱርክ ዛሬ የምዕራቡና የምሥራቁ የሆኑ ጥንታዊና ዘመናዊ እንዲሁም መንፈሳዊና ዓለማዊ ነገሮች ተቀይጠው የሚታዩባት ምድር ናት።

ከኔቶ ቃል ኪዳን አገሮች የደቡባዊው ምሥራቅ ክፍለ-ጦር ማረፊያም ናት። በዚህ ሁኔታዋ ከሙኒዝምን በመከላከሉ ረገድ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ትከሻ ለትከሻ ተያይዛ በመከላከያው ግንባር መሥመር ላይ ትገኛለች። ይሁን እንጂ፥ የጋራ ገበያው አባል ወይም የአውሮፓ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አካል እንድትሆን የአውሮፓ መንግሥታት አልፈቀዱላትም። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ሳቢያ አገሪቱ በአንድ እግሯ ምዕራቡ፥ በሌላው ምሥራቁ ዓለም ውስጥ በመቆም፥ በተለያዩ ሁለት ሕዝቦች መካከል ሚዛናዊነቷን ጠብቃ ለመኖር ትጥራለች።

ጥንታዊው የኦቶማን መንግሥት፥ ኢስታንቡል እተባለችው መናገሻ ከተማው ውስጥ ሆኖ መካከለኛው ምሥራቅንና የአውሮፓን አንዳንድ ክፍሎች ለ600 ዓመታት ገዝቷል። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ግን ይህ የኦቶማን ገናና መንግሥት "የአውሮፓው ገመምተኛ" ሆኖ ነበር። ብልሹነትና መገለል በምድሪቱ ተንሰራፋ። በዚህ ምክንያት በሀያኛው መቶ ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ "ወጣት ቱርካውያን" የተሰኘ ቡድን ተነሥቶ የመንግሥት ለውጥ እንዲሆን አስገደደ። የቡድኑ አባላት በኦቶማን መንግሥት ውስጥ የተሻለ ለውጥ ቢያመጡም፥ አገሪቱን አንደኛው ዓለም ጦርነት ውስጥ በማስገባት ከጀርመን፥ አውስትርያና ሀንጋሪ ጎን እንድትሰለፍ አድርገዋታል።

ጀርመን በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ይዋጓት በነበሩ መንግሥታት ድል በመነሣቷ፥ የኦቶማንን ገናና መንግሥት ፍጻሜን አስከተለ። ይህን በጀርመን የሚመራ ኃይል ድል ያደረጉ ወገኖች የኦቶማን መንግሥትን ቀሪ ግዛቶች ወሰዱ። ቱርክ እራሷ በ1923 እአአ የቱርክ ሪፑብሊክ መንግሥት እስኪመሠረት ድረስ ሠላም አልነበራትም። ሙስጠፋ ከማል አታቱክ የተባሉ መሪዋ ነበሩ የሪፑብሊካዊ መንግሥቱን ሥር ነቀል ለውጥ ያመጡት። ምንም እንኳን የሕዝቧ 98 በመቶው ሙስሊም ቢሆን፥ አገሪቱን ዘመናዊ በማድረጉ ረገድ መሪዋ የእርዳታ ፊታቸውን ያዞሩት ወደ ምዕራቡ ዓለም ነበር። አዲሱ የቱርክ ሕገ መንግሥት እስልምና የመንግሥቱ ሃይማኖት መሆኑን አላወጀም። ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ነጻነት በአገሪቱ መኖሩ፥ ቱርክን ከአውሮፖ ጋር በቅርብ በማስተሳሰር በምዕራባዊው ዲሞክራሲ የምትመራ አድርጓታል።

ቱርክ ለወደፊቱም ከምዕራቡ ጋር መተባበር ብትፈልግም፥ የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት የፈጠረው ስውር ሥጋት አለባት። ኢራቅ ኩዌትን ከወረረች በኋላ፥ የቀድሞው የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ቡሽ የቱርኩን ፕሬዚዳንት ቱርጋት ኦዛልን በስልክ አነጋግረዋቸው ነበር። ፕሬዚዳንት ቡሽ ያሰቡት፥ ኢራቅ ወደ ውጭ የምትልከውን የነዳጅ መጠን በመቀነስ በአገሪቱ ላይ ጫና ለመፍጠር ነው። ኢራቅ ለገበያ ከምታቀርበው ነዳጅ አብዛኛው በቱርክ ምድር ላይ በሚያልፈው ቧንቧ በኩል ነበር የሚላከው። ይህን መሥመር ቱርክ አቋረጠችው። በዚህ ምክንያት ቱርክ የሚደርስባት ኢኮኖሚያዊ ችግር ግን ከባድ ነበር። የነዳጅ ቧንቧውን በመዝጋቷ ከቀረጥ ታገኝ የነበረውን በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ አጣች።

የአገሪቱ መሪ ሙስጠፋ ከማል የቱርክ ሪፑብሊክን ሲመሠርቱ፥ በምዕራቡና በምሥራቁ ዓለም መካከል በመልካም ለመመላለስ ወስነው ነበር። ከቱርክ የውጭ ፖሊሲዎች አንዱና ዋናው ነገር፥ በዓረባዊ ወይም በእስላማዊ ግጭቶች ውስጥ አለመግባት ነበር። የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ኦዛል የኢራቅ ነዳጅ መተላለፊያ የሆነውን ቧንቧ ሲዘጉ፥ እንዲሁም የምዕራቡ ጦር ኃይል አይሮፕላኖች ቱርክ ውስጥ እንዲያርፉና እንዲነሡ ሲወስኑ ግን ከምዕራቡ ዓለም ጋር በመተባበር ፀረ-ኢራቅ አቋም መያዛቸው ነበር።

የፕሬዚዳንቱ ውሳኔ፥ የምዕራቡ የጦር ቃል ኪዳን ኃይል ከኢራቅ ጋር ለሚያደርገው ጦርነት ቢረዳውም፥ የሚያስከፍለው ፖለቲካዊ ዋጋ ግን ግዙፍ ነው። በዚሁ መሠረት፥ የአገሪቱ ፕሬዚዳንት የነበራቸው ተወዳጅነት እያዘቀጠ መጣ። አገሪቱ እነርሱ "አረመኔዎች" ከሚሏቸው ኃይሎች ጋር በመተባበር፥ እስላማዊ ወንድሞቿን ለመውጋት በመወሰኗ እስላሞች በምሬት ተቃወሚት። ከኢራቅ ታገኝ የነበረው የነዳጅ ቀረጥ በመቋረጡ ምክንያት ኢኮኖሚዋ ተጎዳ። ከአሜሪካና ከምዕራባውያን አገሮች የሚመጣላት እርዳታም ችግሯን ሊቀርፈው አልቻለም። በኢኮኖሚ ችግር ቱርክ እንዲህ ስትሠቃይ ምዕራባውያን የቃል ኪዳን አገሮች ያደረጉላት ነገር ቢኖር፥ መጠነኛ የእርዳታ ጥገናና የቃላት ማበረታቻ ብቻ ነበር።

የባሕረ-ሰላጤው ግጭት ካበቃ በኋላ እንኳን የቱርክ ችግር በማሻቀብ ላይ ነው። ከ400,000 በላይ የሆኑ ኩርዳውያን ዓማፂዎች ዓመፃቸው በሳዳም ሁሴን በተደመሰሰባቸው ጊዜ፥ መኖሪያ ቀበሌያቸው ከሆነው ሰሜን ኢራቅ ሸሹ። ከነዚህ ውስጥ በሺህ የሚቆጠሩት ወደ ቱርክ ግዛት ነበር የገቡት። አገሪቱ በራሷ ግዛት የነበሩ ኩርዳውያን በሚፈጥሩባት ችግር ተወጥራ ነበር። ኩርዳውያን የራሳቸው ነጻ መንግሥት ለመመሥረት በነበራቸው ጥያቄ ሳቢያ፥ የቱርክ መንግሥትና ኩርዶች ሲዋጉ ኖረዋል። ቱርክ ለቃል ኪዳን ጦር ኃይል ድጋፍ መስጠቷ፥ አገሪቱ ከኩርዶች ጋር የነበራትን ጸብ አባባሰው።

ሌላው የዓለም ክፍል በጨቋኝ ገዢዎቹ ላይ ባገኘው ድል ሲደሰት፥ ቱርክ ግን ችግር ውስጥ ነበረች። በከባዱ የምጣኔ ሀብት ችግር ላይ በሙስሊም ወንድሞቻቸው ላይ በሚደረገው ጦርነት ውስጥ ተሳታፊ የመሆኑ ጸጸት ተዳምሮ መንግሥቱን አናወጠው። የአገሪቱ ፕሬዚዳንት የምዕራቡ ዓለም ደጋፊ በመሆናቸው ምክንያት በሕዝቡ ዘንድ የነበራቸውን አመኔታ ከምን ጊዜውም ይልቅ ዝቅ አደረገው። አገሪቱ በደጋፊዎቿ የመከዳቷ ስሜት ከፍ ያለባት፥ ኩርዶች በችግሯ ላይ በተጨመሩባት ጊዜ፥ ትጠብቀው የነበረ የኢኮኖሚ እርዳታ ስለቀረባት ነው። ቱርክ የምዕራቡን ዓለም ለመርዳት የተቻላትን ሁሉ ብታደርግም፥ ምዕራቡ ዓለም የሰጣት አጸፋ ግን ችግሯን ማባባስ ነበር።

> “የቱርክ የኢኮኖሚ ሁኔታ ከጦርነቱ በፊት ከነበረው ይልቅ ተባባሰ። ከነዳጅ የምታገኘው ቀረጥ መቅረቱ፥ የቱሪዝም ገቢዋ ማሽቆልቆሉ፥ ባሕረ-ሰላጤው አገሮች ውስጥ ከሚሠሩ ዜጎቿ የሚላከው ገንዘብ መቋረጡ እና የውጭ ገበያዋ መቀነሱ ያስከተለባት ችግር ከባድ ነበር። የቱርክና የኢራቅ የጋራ ሀብት የሆነው የነዳጅ ዘይት ማስተላለፊያ ቧንቧ በመዘጋቱ ምክንያት ቱርክ ከቀረጥ ታገኝ የነበረውና ያጣችው ገንዘብ ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ይገመታል። ኢራቅ ነዳጅ ዘይት ወደ ውጭ እንዳትልክ የተጣለባት ማዕቀብ እስካልተነሣ ድረስ ከቀረጥ የሚገኘው ገቢ መጠን ቀድሞ ወደ ነበረበት ሊመለስ አይችልም።”

ቱርክ ለእርዳታ ወደ ምዕራባውያን አገሮች ብትመለከትም ምዕራባውያን ተገቢውን ምላሽ አልሰጧትም ነበር። ከምዕራባውያን ጋር ያላትን ግንኙነት እንደጠበቀች ለእርዳታ ወደ ሌሎችም መመልከት ነበረባት። የምትፈልገው እርዳታም ከቀድሞው የሶቪየት ኅብረት አባል አገሮች፥ ከምሥራቅ አውሮፓና ከኢራን ነበር የሚመጣላት። በምሥራቁና በምዕራቡ ዓለም መካከል የተፈጠረው ውጥረት በ1989 እአአ እንዳበቃ፥ ቱርክ ለንግድ ግንኙነት ምሥረታ ብዙ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችንና ሶቪየት ኅብረትን ጠየቀች። ከሶቪየት ኅብረት መፈራረስ በኋላ የንግድ ግንኙነቱ ሂደት ተፋጥኗል። ቱርክ በአሁኑ ጊዜ የጥቁር ባሕር ምጣኔ ሀብት ልማት ክልል ለመመሥረት በትጋት በመሥራት ላይ ናት። ይህ ዘጠኝ አባላት ያሉት የጥቁር ባሕር አዋሳኝ አገሮች “የምጣኔ ሀብት ገበያ” ቱርክን፥ ቡልጋሪያን፥ ሩማኒያን እና የቀድሞይቱ የሶቪየት ኅብረት መንግሥት አባላት የነበሩትን (አርሜኒያን፥ አዘርባጃንን፥ ጆርጂያን፥ ሞልዳቪያን፥ ሩሲያን እና ዩክሬይን) ያካትታል። “የምዕራቡ በር የተዘጋባቸው ቱርኮች የሰሜን አገሮችን በመቃኘት ላይ ናቸው።”

አገሪቱ ወደ ሰሜን ብቻ ሳይሆን፥ ወደ ምሥራቅም ትመለከት ይሆናል። የቀድሞው ሶቪየት ኅብረት አካል የነበሩ አምስት የመካከለኛው

እስያ አገሮች ከቱርክ ጋር የሚያገናኟቸው ብዙ የጋራ ነገሮች አሉ። አምስቱ አገሮች (ካዛክስታን፥ ኪርጊስታን፥ ታጂክስታን፥ ቱርክሜኒስታን እና ኡዝቤክስታን) በጋራ ከ50 ሚሊዮን የላቁ ሙስሊሞች አሏቸው። ብዙዎቹ የጋራ ታሪክ ሲኖራቸው፥ ቋንቋቸው ቅይጥ ቱርክኛ ነው። በእነዚህ በቅርቡ ነጻ የወጡ የሶቪየት ኅብረት አገሮች ላይ የላቀ ተጽዕኖ ለማሳደር ቱርክና ኢራን በመፎካከር ላይ ናቸው።

ቱርክ እግሯቿን በ‘‘ባስፓራስ’’ [Bosporus] እና ‘‘በዳአርዶኔልስ’’ [Dardenelles] በማድረግ ቆይታለች። አንድ እግሯን በምዕራብ ዳርቻ ዲሞክራሲ ባለበት፥ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በተለያዩበት፥ የኔቶ የጦር ቃል ኪዳን አባል በሆነችበት እና የአውሮፓ ምጣኔ ሀብት ማኅበር አባል የመሆን ፍላጎቷ በሰፈነበት የምዕራቡ ዓለም አቅጣጫ ተክላለች። በሌላው እግሯ ደግሞ፥ በሰተምሥራቅ ከሌሎች የሙስሊም አገሮች ጋር በምጣኔ ሀብትና በሃይማኖት ወደተሳሰረችበት፥ በኩርዶች ምክንያት ተመሳሳይ ችግር ወዳለባቸው፥ ከሷ ጋር ባሕላዊ ትስስር ወዳላቸው የቀድሞ የመካከለኛው እስያ አገሮች አቅጣጫ ቆማለች። እንዲህ በማድረግ እስከ ዛሬ በምሥራቁና በምዕራቡ ዓለም መካከል በሚዛናዊነት ለመቆም ችላለች። ወደፊትም እንዲሁ ለመቀጠል ትችል ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስስ ቱርክና ኢራን ወደፊት በዓለም ታሪክ ውስጥ ስለሚኖራቸው ሚና የሚጠቁመው ነገር አለ? የዚህ ጥያቄ መልስ ትንቢተ ሕዝቅኤል ውስጥ ይገኛል።

## እስልምና በእስራኤል ላይ የሚሰነዝረው ጥቃት

በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ሰባት ውስጥ፥ እስራኤል መንግሥታት በሚፈጥሩት አንድ ኅብረት የምትወረር መሆኗን አስመልክቶ በሕዝቅኤል የተገለጠን አስደናቂ ትንቢት መርምረናል። የነቢዩን ትንቢት በትኩረት ለመመርመር ይቻለን ዘንድ ወደ ሕዝቅኤል 38-39 መለስ ብለን የመመልከቻችን ጊዜ አሁን ነው። ነቢዩ የሚያስተምረን ምንድነው? አሁን ካለው የመካከለኛው ምሥራቅ ሁኔታ ጋርስ እንዴት ይዛመዳል?

ሕዝቅኤል ትንቢቱን የሚጀምረው፥ በፍጻሜው ዘመን ሠራዊት ግንባታ ውስጥ የሚሳተፉት እነማን መሆናቸውን ለአንባቢዎቹ በመግለጥ ነው። ሕዝቅኤል 38፥2-3፥6 ውስጥ ጎግ የተባለ ሰው ይገለጣል። ጎግ ማለት፥ ማጎግን፥ ሞሳህን፥ ቶቤልን፥ ጋሜርንና ቴጋርማን ጨምሮ የመንግሥታቱን ኅብረት የሚመራ ሰው ነው። እነዚህ መንግሥታት በሕዝቅኤል ዘመን የት ነበሩ? አገሮቹ ዛሬ ሰሜናዊና ምሥራቃዊ ቱርክ በሆነው አካባቢ፥ ሰሜናዊ ምዕራብ ኢራቅ፥ እንዲሁም የቀድሞው ሶቪየት ሪፐብሊክ አካል በነበሩት ጆርጂያ፥ አርሜንያ እና አዘርባጃን ባሉበት

ወጣገባና ለም አካባቢ ነበሩ። በሕዝቅኤል ከተገለጡት አገሮች ብዙዎቹ ዛሬ የቱርክ ምድር ሆነዋል።

በፍጻሜው ዘመን ወረራ ወቅት የሚነሡት መሪዎች የሚኖሩት፥ ከቱርክ አንሥቶ በጥቁር ባሕርና ካስፒያን ባሕር መካከል እስካለው ምድር በተዘረጋው አገር የሚኖሩ ናቸው። ሕዝቅኤል ከእነዚህ ወራሪዎች ጋር የሚተባበሩ ሌሎች አገሮችን ስምም እንደሚከተለው ይገልጣል፥ “ፋርስንና ኢትዮጵያን ፉጥንም ከእነርሱ ጋር . . . አወጣለሁ” (ሕዝ. 38፡5)። የመጀመሪያው “ፋርስ..” ነው። ጥንታዊቱ ፋርስ የዘመናዊቱ ኢራን እቻ ናት። ኢራናውያን ዛሬ የሚናገሩት ቋንቋ አሁንም ፋርስኛ ወይም የፋርስ ቋንቋ ይባላል። በሕዝቅኤል ገለጣ መሠረት እንግዲህ፥ ኢራን እስራኤልን ከሚወርሩ አገሮች ጋር ትተባበራለች።

ከእስራኤል ወራሪዎች ጋርም የምትተባበረው ሌላ አገር ኩሽ ወይም ኢትዮጵያ ናት። በሕዝቅኤል ዘመን ኩሽ ተብሎ የሚጠራው፥ ግብፅ ውስጥ ካለውና አስዋን ከሚባለው ስፍራ ጀምሮ ያለው አገር ነበር። ሕዝቅኤል ቀደም ሲል እግዚአብሔር፥ “የግብፅንም ምድር ከሚግዶል [ሰሜናዊ ግብፅ] ጀምሮ እስከ ሴዌኔና [ደቡባዊ ግብፅ] እስከ ኢትዮጵያ ዳርቻ ድረስ ውድማና ባድማ አደርጋለሁ” (ሕዝ. 29፡10) ማለቱን ተንብዮ ነበር። ኩሽ የተባለው አገር፥ ከደቡብ ግብፅ ጀምሮ አሁን ሱዳንና ኢትዮጵያ የምንላቸውን አገሮች ይጨምር ነበር።

ወረራው ኅብረት ውስጥ የምትጨመረው ሌላ አገር ፉጥ ናት። ፉጥ የሚባለው አገር ከግብፅ በስተምዕራብ ይገኝ ነበር። ጥንታዊቱ ፉጥ የዛሬይቱ ሊቢያ ናት። ብዙ ሰዎች ሕዝቅኤል 38-39 ውስጥ የተጠቀሰውን የወራሪ አገሮች እንግዳ መሰል ስብጥር ሲመለከቱ ይገረማሉ። ከእስራኤል ግንዛቤ አንጻር ሲታይ ግን፥ ለወረራው የሚተባበሩ አገሮች የእግዚአብሔርን ምርጥ ሕዝቦች ከየአቅጣጫው ለመውረር ሲተባበሩ አሁን ከሚታሰበው ይበዛሉ። የኅብረቱ መሪ የሚሆነው ሰው ከሰሜን ሆኖ፥ በጥቁር ባሕርና በካስፒያን ባሕሮች ዙሪያ ያሉ አገሮችን ያስተባብራል። እነዚህ አገሮች ቱርክና ከቀድሞዎቹ የሶቪየት ኅብረት አገሮች አንዳንዶቹ ናቸው። የዚህ የሰሜን ኅብረት መሪ ከምሥራቅ፥ ከደቡብ እና ከምዕራብ ሌሎች አገሮችንም ማለት ኢራንን፥ ሱዳንንና ሊቢያን ያስተባብራል። ይህን በማድረግ የኅብረቱን ኃይል መርቶ እስራኤልን ይወርራል።

የዚህ በእስራኤል ላይ የሚነሣ ኅብረት መፈጠር ጉዳይ የማይሆን መስሎ ለብዙ መቶ ዓመታት ቆይቷል። ከዚህ አንጻር የሕዝቅኤልን መልእክት ቁም ነገር ለመረዳት የፈለጉ ሰዎች በኅብረቱ ለሚሣተፉ አገሮች ሌላ መለያ በመስጠት ትንቢቱን ተዓማኒ ለማድረግ ሞክረዋል። አንዳንዶች

ሕዝቅኤል ከጠቀሰውና ሞሳሕ ከሚለው ስም ጋር የሚመሳሰል ስም ያላቸው ከተማዎች ፈልገዋል፥ (ለምሳሌ ሞሳሕ፥ ሞስኮ እንደማለት)። ሌሎቹ በሕዝቅኤል የተጠቀሱ ሕዝቦችን እንቅስቃሴ ፈትሸዋል፥ (ለምሳሌ ጋሜር፥ የጀርመን ጎሳዎች እንደማለት)። እነዚህ ሰዎች የሕዝቅኤልን ትንቢት ለመረዳት ያላቸው ፍላጎት የሚደነቅ ቢሆንም፤ የተከተሉት ዘዴ የተሟላ አይደለም።

የእግዚአብሔርን ቃል ለመፍታት የተሻለው አማራጭ፥ ቃላቱ ራሳቸው የሚናገሩትን እንዲሉ መፍቀድ ነው። እግዚአብሔር ፍጻሜን ከጅማሬው የሚያውቅ ስለሆነ፥ አገሮቹ ወይም ሕዝቦቹ ባይኖሩ እንኳን ስም ሊሰጣቸው ይችል ነበር። ለምሳሌ አይሁዳውያንን ከባቢሎን ምርኮ ነጻ የሚያወጣቸውን ሰው፥ የቂሮስን ስም ለኢሳይያስ ነግሮታል። ይህ ሰው የተወለደው ኢሳይያስ ስሙን የጠቀሰው ከመቶ ዓመት በኋላ ነበር (ኢሳ. 45፡1)። በሕዝቅኤል የተጠቀሱት አገሮች እርሱ በነበረበት ዘመን ይታወቁ ነበር። እነዚህ አገሮች እስራኤልን ለመውጋት የሚተባበሩ መሆናቸውን እግዚአብሔር ተናግሯል። ይሁን እንጂ፥ እንዲህ የተለያዩ ወገኖችን ሊያስተባብራቸው የሚችል ነገር ምን ሊሆን ይችላል? እስልምና፥ ነው መልሱ።

## እስልምናን ማሠራጨት

የሶቪየት ኅብረት መፈራረስ ከአክራሪ እስላማዊ እንቅስቃሴ ማቆጥቆጥ ጋር ገጠመ። የቀድሞይቱ የሶቪየት ኅብረት አባላት በነበሩ ስድስት አገሮች ውስጥ 50 ሚሊዮን ሙስሊሞች ይኖራሉ። ቱርክና ኢራን የሶቪየት ኅብረትን የበላይነት ተጽዕኖ ስፍራ ለመተካት ከሳውዲት ዓረቢያ ጋር የጥድፊያ ዝግጅት በማድረግ ላይ ናቸው።

አንድ ጸሐፊ እንዳሉት፥

> “ቱርክ፥ ኢራንና ሳውዲት ዓረቢያ በአካባቢው ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር እርስ በርሳቸው የሚፎካከሩ አገሮች ናቸው። እነዚህ አገሮች በገበያ፥ በወርቅ፥ በጥጥና በተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋ ይፎካከራሉ። ከ74 ዓመቱ አምባገነን አገዛዝ በቅርቡ ነጻ የወጡ 50 ሚሊዮን ሙስሊሞችን አእምሮና ልብ ለመማረክም ይፎካከራሉ። ውድድሩ የሚካሄድበት ሁኔታ ለአካባቢው፥ ምናልባትም ለመላው ዓለም ታላቅ ሁኔታ ያስከትል ይሆናል።”

የቀድሞይቱ ሶቪየት ኅብረት ግዛት በነበሩ አገሮች ውስጥ በአሁኑ ጊዜ በመከናወን ላይ ካሉ ነገሮች አንጻር ሲታይ፥ የሕዝቅኤል ትንቢት አዲስ ተዛማጅነት አለው። አንድ ሃይማኖት ያላቸው የሰሜን ሕዝቦች፥ ቃል ኪዳን የማድረጋቸው ነገር በጣም የሚቻል ሲሆን፥ የቃል ኪዳኑ መሪዎችም ቱርክና ኢራን ይሆናሉ። ሁለቱም አገሮች የአካባቢውን

በኢኮኖሚና በሃይማኖት መተሳሰር ይበልጥ ለማጎልበት ታላቅ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው። ለወታደራዊ ግንኙነትም በመመሥረት ላይ ናቸው። ኢራን ኑክሊየራዊ የጦር መሣሪያ ከካዛኪስታን ሪፑብሊክ ለመግዛት በሶቪየት ኅብረት መፈራረስ ጊዜ የተፈጠረውን ዝብርቅርቅ ሁኔታ የተጠቀመችበት መሆኑን አንድ በዓረብኛ ቋንቋ የታተመ ሪፖርት አጋልጧል። መቀራረቡ እየጠነከረ ሲሄድ፥ የላቁ የሃይማኖታዊ፥ ምጣኔ ሀብታዊና ወታደራዊ ትሥሥሮች ይመሠረታሉ።

የሰሜንና የምሥራቁ ኅብረት የመጀመሪያ ምልክቶች ቱርክና ኢራን ውስጥ በመታየት ላይ ናቸው። በሕዝቅኤል የተጠቀሱት ሌሎች ተባባሪዎችስ የታሉ? ሊቢያና ሱዳን እንዴት ነው እዚህ ስሌት ውስጥ የሚገቡት? በቅርቡ ሱዳን ውስጥ የተደረጉት ለውጦች ለሙስሊሙ ዓለም አሳሳቢ ሆነዋል። ኢራን ሱዳን ውስጥ የምታሳድረው ተጽዕኖ በአሳሳቢ ፍጥነት በማደግ ላይ ነው። በ1991 እአአ መገባደጃ የኢራኑ ፕሬዚዳንት፥ ሀሼሚ ራፍሳንጃኒ አንድ የመልእክተኞች ቡድን በመምራት ወደሱዳን ሄደው ነበር። ቡድኑ ውስጥ የኢራን የስለላ ድርጅት የአብዮታዊ ዘቦች ኃላፊ ነበሩበት። የሱዳንን የጦር ኃይል አባላት ያሠለጥኑ ዘንድ ኢራን 2,000 የአብዮታዊው ዘብ አባላትን ወደዚያው ልካለች። በተጨማሪም 17 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ወታደራዊ ጦር መሣሪያ ለሱዳን ልካለች።

አሚር ታሄሪ የተባሉ ጸሐፊ ሲዘግቡ፥ “ኢራን በአካባቢው አዲስ ወዳጆችን ትፈልጋለች፤ ሱዳን አንዷ ትሆን ይሆናል” ብለዋል። ሊቢያ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ያላት ሚና አልተለወጠም። የአገሪቱ መሪም ሙአመር ጋዳፊ እስራኤልን ይቃወማሉ፤ አይሁዳውያንን ለማጥፋትም የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። ሊቢያ ሽብር ፈጣሪዎችን የማደራጀትና በ1990 እአአ ስኮትላንድ ሎከርቢ አየር ላይ የበረራ ቁጥሩ 007 የሆነ የፓን አም አይሮፕላንን በቦምብ ማፈንዳትን የመሳሰሉ የሽብር ድርጊቶችን የመርዳት ታሪክ አላት። እስራኤልን ለማጥቃት ከተደራጀ የሙስሊም ቡድን አባላት ጋር ተባብራ የምታደርገውንም ለመገመት ይቻላል። የቀድሞው የሶቪየት ኅብረት አባላት ከነበሩ ሪፐብሊኮች ጋር ግንኙነት ለመመሥረት በመሞከር መልእክተኞችን ወደዚያው ልካ ነበር።

ቱርክ፥ ኢራን፥ ሙስሊማዊ ሪፐብሊኮች፥ ሱዳንና ሊቢያ፥ ከእስልምና ታሪካቸው በቀር እምብዛም የጋራ የሆነ ነገር የሌላቸው ናቸው። ሕዝቅኤል ግን እነዚህ አገሮች እስራኤልን በማጥቃቱ አድማ ውስጥ እንደሚኖሩበት ያመለክታል። ለብዙ ዓመታት ይህ ቃል ኪዳን የማይቻል ይመስል ነበር፤ አሁን ግን መሠረት በመጣል ላይ ነው። ይሁን እንጂ፥ በቃል ኪዳን የሚተሣሰሩት አገሮች ጦርነቱን የሚጀምሩት መቼ ነው?

## ጊዜው

ሕዝቅኤል፥ እስራኤልን የሚወሯት እነማን መሆናቸውን ካስገነዘበ በኋላ፥ በትንቢቱ ምዕራፍ 38፡8 ውስጥ እንዲህ በማለት የወረራውን ጊዜ ይገልጣል፥ “ከብዙ ዘመንም በኋላ ትፈለጋለህ፤ በኋለኛውም ዘመን፥ የዘላለም ባድማ በነበሩ፥ በእስራኤል ተራሮች ላይ፥ ከብዙ ሕዝብ ውስጥ ወደተሰበሰበች፥ ከሰይፍ ወደተመለሰች ምድር ትገባለህ።” እነዚህ መንግሥታት እስራኤልን የሚወርሯት፥ አይሁዳውያን ተመልሰው ምድራቸው ላይ መኖር ከጀመሩ በኋላ ሊሆን ይችላል። ከሕዝቅኤል ግንዛቤ አንጻር፥ ይህ ወረራ እስራኤላውያን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ539 ዓ.ዓ. ከባቢሎን ምርኮ ወደ ምድራቸው ከተመለሱ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ሊሆን ይችል ነበር። ይሁን እንጂ፥ ከምርኮው ከተመለሱ ከ539 ወዲህ በሮማውያን ከምድራቸው እንዲወጡ እስከተደረጉ ድረስ ምንም ወረራ አልደረሰባቸውም። ስለዚህ ትንቢቱ ገና የሚፈጸም ነው።

ጦርነቱ የሚደረግበትን ጊዜ ለመገንዘብ ይረዳን ዘንድ ሕዝቅኤል ሌሎች ዝርዝሮችን ይጨምራል። እስራኤላውያን ወደ ምድራቸው መመለስ ብቻ ሳይሆን፥ በሠላም መኖርም አለባቸው። “እርስዋም ከሕዝብ ውስጥ ወጥታለች፥ ሁሉም ሳይፈሩ ይቀመጡባታል” (ሕዝ. 38፡8)። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ለወራሪዎቹ እንዲህ ይላቸዋል። “በዚያ ቀን ሕዝቤ እስራኤል ሳይፈራ በተቀመጠ ጊዜ አንተ አታውቀውምን?” (ሕዝ. 38፡14)።

እስራኤላውያን ምድራቸው ላይ መኖር ብቻ ሳይሆን፥ ኑሯቸውም የሠላም ይሆናል። ሕዝቅኤል ወራሪዎች፥ የተዘናጋች እስራኤልን ለመውረር የሚያወጡትን አረመኔያዊ ዕቅድ እንዲህ በማለት ይገልጣል፥ “ቅጥር ወደሌላቸው፥ መንደሮች እወጣለሁ፤ ተዘልለው ወደሚኖሩ፥ ሁላቸው ሳይፈሩ ያለ ቅጥርና ያለ መወርወሪያ፥ ያለ መዝጊያም ወደሚቀመጡ እገባለሁ” (38፡11)። ቅጥሮች በብሉይ ኪዳን ዘመን ከጠላት ለመከላከያነት ያገለግሉ ነበር። ወረራው የሚከነወነው፥ እስራኤል የተጠበቀችና የሚያስፈራት ነገር የሌለ በሚመስላት ጊዜ ነው በማለት ሕዝቅኤል ይገልጣል። ይህ ዘመነኛይቱን እስራኤል የሚያመለክት አይደለም። ምክንያቱም ከ1948 እአአ ወዲህ እስራኤል ጸጥታዋ ተሚልቶ፥ የመከላከያ ኃይሏንም አዘናግታ አታውቅም። ባለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት እስራኤል ውስጥ ጦርነት የቆመበት እንጂ፥ ሠላም የሰፈነበት ጊዜ አልነበረም።

መቼ ነው እስራኤል ሠላም የሚኖራት? ሁለት የሠላም ጊዜያት እንደሚኖሯት ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጠው። የመጀመሪያው በጣም

አጭር የሠላም ጊዜ፥ ወደፊት የሚነሣው የዓለም ገዥ ለመካከለኛው ምሥራቅ ችግር ‘‘መፍትሔ’’ ሲያገኝለትና ለእስራኤልም ሠላም ሲያመጣላት ነው። በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 4 ውስጥ እንደተገለጠው፥ ይህ አንጻራዊ የሠላም ጊዜ የሦስት ዓመት ተኩል ዕድሜ ብቻ ነው የሚኖረው። በዚህ ጊዜ እስራኤል ሠላም ይሰማታል። ሁለተኛው የሠላም ጊዜ የሚሆነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሠላም መንግሥቱን ምድር ላይ ለመመሥረት ሲመጣ ነው። ያን ጊዜ፥ ‘‘በአሕዛብ መካከል ይፈርዳል፥ በብዙ አሕዛብም ላይ ይበይናል፥ ሰይፋቸውም ማረሻ፥ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ፤ ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፥ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም’’ (ኢሳ. 2፡4)።

የትኛውን የሠላም ጊዜ ነው ሕዝቅኤል የሚገልጠው? ሁለቱም የሠላም ጊዜዎች የሚያበቁት፥ እስራኤል ላይ በሚደረገው ወረራ ቢሆንም፥ የሕዝቅኤል 38-39 ግልጥ ማስገንዘቢያዎች የሚያስረዱት ግን፥ በወረራ የሚተጓጎለውን የመጀመሪያ የሠላም ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ክብሩን ለእስራኤል ለመግለጥ ሲል ወረራውን ይፈቅዳል። ‘‘ከእንግዲህ ወዲያ የእስራኤል ቤት እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው እንደሆንሁ ያውቃሉ’’ (39፡22)። ወረራው የእስራኤል ሕዝብን ከመንፈሳዊ ዝለታቸው ለማንቃትና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ለማድረግ ያገለግላል። በመሆኑም ወረራው የሚከናወነው፥ ከመጨረሻው መንፈሳዊ መታደሳቸው በፊት ነው። መሢሑ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ በሚኖረው ሁለተኛ የሠላም ወቅት እስራኤል በመንፈሳዊ ሕይወቷ ንቁ ትሆናለች (ኢሳ. 59፡21፤ ኤር. 31፡31-34)። ስለዚህ ጦርነቱ የሚከናወነው፥ እስራኤል በመንፈሳዊ ሕይወቷ በደነዘዘችበት የመጀመሪያው የሠላም ጊዜ መሆን አለበት።

ሕዝቅኤል ወረራው የሚካሄድበትን ጊዜ አስመልክቶ ሁለተኛ ፍንጭ ይሰጣል። ወረራው የሚደረገው፥ እስራኤላውያን ወደ ምድራቸው ከተመለሱ በኋላ ቢሆንም፥ ሕዝቡ ባጠቃላይ ከወረራው በፊት ይመለሳሉ ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ስለ ጦርነቱና ስለሚያስከትለው ጥፋት ከተናገረ በኋላ፥ ለሕዝቡ እንዲህ ይላል፥ ‘‘አሁን የያዕቆብን ምርኮ እመልሳለሁ፥ ለእስራኤልም ቤት ሁሉ እራራለሁ፤ ስለ ቅዱስ ስሜም እቀናለሁ’’ (ሕዝ. 39፡25)። የወረራው አንድ ውጤት፥ አይሁዳውያንን ለመጨረሻ ጊዜ ወደ እስራኤል ምድር መመለስ ይሆናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በሚመለስበት ወቅት፥ አይሁዳውያን ሁሉ ወደ ምድራቸው የሚከማቹ መሆናቸው ስለሚታወቅ (ማቴ. 24፡31)፥ ጦርነቱ መሆን ያለበት ይህ በኢየሱስ ምጽአት ጊዜ የሚደረገው፥ የአይሁዳውያን መመለስ ከመከናወኑ በፊት ነው።

ትንቢተ ሕዝቅኤል ከምዕራፍ 38-39 ባለው ክፍል የተገለጠው ወረራ የሚከናወነው፥ እስራኤላውያን ወደ ምድራቸው በሠላም ተመልሰው በሚኖሩበት ጊዜ ነው። ይሁን እንጂ፥ ይህ የሠላም ጊዜ እግዚአብሔር ለእስራኤል ተስፋ የሰጣት የመጨረሻ ሠላም አይደለም። በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን በአጠቃላይ አይደሉም ወደ ምድራቸው የሚመለሱት፤ የተመለሱትም ቢሆኑ ጌታን በትክክል አያውቁትም። እግዚአብሔር ከጦርነቱ በኋላ ስለሚሆነው ነገር ተስፋ ሲሰጥ እንዲህ ብሏል፥ "ፊቴንም ከእነርሱ ከእንግዲህ ወዲህ አልሸሽግም፤ መንፈሴን በእስራኤል ቤት ላይ አፍስሻለሁና" (ሕዝ. 39፥29)። ጦርነቱ መደረግ ያለበት፥ በመጨረሻው ሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት። በዚህ ጊዜ፥ እስራኤል የደኅንነቷን ጉዳይ የዓለምን ሠላም ለማስከበር ኃይል ላለው የዓለም መሪ በእምነት ታስረክባለች።

ይህ ዕለት ቅርብ ነው? አናውቀውም። ከዚያ ቀጥሎ እግዚአብሔር በጊዜ ሰሌዳው የያዘው ነገር ቤተ ክርስቲያኑን ከዓለም ማውጣት ነው።

እግዚአብሔር ባለንበት ዘመን* በቤተ ክርስቲያን አማካይነት በምድር ላይ በመሥራት ላይ ነው። የብሉይ ኪዳን ትንቢታዊ ፕሮግራም ግን በእስራኤል ሕዝብ ላይ ያተኩራል። የፍጻሜው ዘመን ነገሮች በምድር ላይ መከናወን ከመጀመራቸው በፊት እንደሚመጣና አማኞችን እንደሚወስዳቸው ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን ተስፋ ሰጥቷል (1ኛ ተሰ. 4፥13-5፥11፤ ራእይ 3፥10)። ቤተ ክርስቲያን ከምድር ከተወሰደች በኋላ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን ትንቢታዊ ፕሮግራም ይቀጥላል።

ወደፊት የሚነሣው የዓለም መሪ ከእስራኤል ጋር አንድ ስምምነት እስኪፈራረም ድረስ፥ የእግዚአብሔር ትንቢታዊ ሰዓት መሥራት አይጀምርም። ከስምምነቱ መፈራረም በኋላ፥ በፍጻሜው ሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ፥ በአንድ ወቅት፥ በሕዝቅኤል የተገለጠው ጦርነት ይጀምራል። ይህ እንዲህ ቢሆንም፥ የምናያቸው የዓለም ሁኔታዎች የጊዜውን መቃረብ ይጠቁማሉ። አሁን በዓለም መድረክ ላይ የሚታዩት ሁኔታዎች በነቢያት ከተነገሩት ትንቢቶች ጋር ይመሳሰላሉ። ቱርክ፥ ኢራን እና ከቀድሞው የሶቪየት ኅብረት ግዛት የወጡት እስላማዊ ሪፑብሊኮች ኢኮኖሚያዊ፥ ወታደራዊና ሃይማኖታዊ ትሥሥር በመመሥረት ላይ ናቸው። ሱዳንና ሊቢያም ከእነዚህ አገሮች ጋር ኅብረት ለመፍጠር የቅርብ ግንኙነት በማድረግ ላይ ናቸው። እስራኤል ሠላሟ ተከብሮ ዓለም አቀፍ እውቅና ባለው ድንበሯ ውስጥ እንድትኖር ለማድረግ የተጀመረውን ሁለ ገብ የመካከለኛው ምሥራቅ የሠላም ሂደት ለማጠናቀቅ፥ የዓለም

* በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ያለውን የጊዜ ማውጫ ይመልከቱ።

መንግሥታት በጉጉት በመሥራት ላይ ናቸው። የዓለም ሁኔታዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት ውስጥ የተጠቀሱ ነገሮችን ምስል ማሳየት ሲጀምሩ፥ የፍጻሜው ጅማሬ ቅርብ ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ።

እግዚአብሔር እና ጎግ

ሕዝቅኤል እስራኤልን የሚወርሯት እነማን መሆናቸውንና የወረራውን ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ ወራሪዎቹ ከወረራቸው የሚታቀቡበትን ሁኔታም ይገልጣል። በጎግ የሚመሩት መንግሥታት ሠራዊት እስራኤልን ለመውረር ጉዞ ሲጀምር፥ የእስራኤል የወደፊት ዕጣ አጠያያቂ ይሆናል። እስራኤል ድንገት ይደረስባታል። ወራሪዎቿ ከየአቅጣጫው ጥቃት ይሰነዝሩባታል። በሚገባ የሚቀናጀው የወራሪዎቹ ዕቅድ እስራኤልንም ሆነ ሊከላከልላት ቃል ገብቶ የነበረውን የዓለም መሪ ያስደነግጣቸዋል። እንዴት ነው ወረራው ሊቆም የሚችለው?

ሕዝቅኤል 38፡19-22 ውስጥ እግዚአብሔር ጦርነቱ የሚቆምበትን ሁኔታ ገልጧል። ጠላቶቿን ሊያጠፉና እስራኤልን ለመታደግ በቀጥታ ጣልቃ ይገባል። ወራሪዎች ወደ እስራኤል እንደተጠጉ፥ እግዚአብሔር በአካባቢው ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ያስነሣል፥ "በቅንዓቴና በመዓቴ እሳት ተናግሬአለሁ። በእርግጥ በዚያ ቀን በእስራኤል ምድር ጽኑ መናወጥ ይሆናል። . . . ተራሮችም ይገለባበጣሉ፥ ገደላገደሎችም ይወድቃሉ፥ ቅጥርም ሁሉ ወደ ምድር ይወድቃሉ" (38፡19-20)። ወራሪዎቹ ሠራዊቶች ጥቂት ድል እንዳገኙ፥ ታላቅ የምድር መናወጥ ተነሥቶ ድልድዮችንና ሕንጻዎችን ስለሚያፈራርሳቸው ከወረራቸው ይታቀባሉ። ተራሮችና ኮረብታዎች እየተናዱ ጎዳናዎችን ይዘጋሉ፤ ለአደጋው የሚጋለጡ ሰዎችንም በቁማቸው ይቀብሯቸዋል።

የምድር መናወጡ፥ የወራሪዎቹን የመጀመሪያ ዕቅድ ያቋርጥና ታላቅ የግንኙነት ችግር ይፈጥርባቸዋል። የሠራዊቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ስለሚበታተኑ ማዕከላዊ እዝና ቁጥጥር ይጠፋል። ከተለያዩ አገሮች የተውጣጣው ሠራዊት ፍጹም ግራ ይጋባል። አንዳንዶቹ ወራሪዎች ቱርክኛ፥ ሌሎቹ በፋርስ ቋንቋ፥ የቀሩት ደግሞ ዓረብኛ የሚናገሩ ይሆናሉ። ከግራ መጋባትና ከድንጋጤ የተነሣ የወራሪው ሠራዊት አባላት በስሕተት እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ። "በተራሮችም ሁሉ በእርሱ ላይ ሰይፍን እጠራለሁ፥ የሰውም ሁሉ ሰይፍ በወንድሙ ላይ ይሆናል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር" (ሕዝ. 38፡21)። ብዙ ወራሪዎች ከወዳጅ በሚተኮስ ጥይት ይሞታሉ።

የጦርነቱ ሁለት ውጤቶች "ቸነፈርና ደም" ናቸው (38፡22)። በድንጋጤ አንዱ በሌላው ላይ እየተኮሰ ከወራሪዎች ብዙዎቹ ይቆስላሉ፥

ብዙዎችም ይሞታሉ። ሠራዊቱ የሕክምና እርዳታና ሌላ አቅርቦት እንዳያገኝ የምድር ነውጡ ያግዳል። ሙታን የሚቀብራቸው፥ ቁስለኞች ለሕክምና የሚያነሣቸው አያገኙም። የምግብና የውኃ አቅርቦት ስለሚያልቅ፥ ወታደሮች የሚያገኙትን ነገር ሁሉ ለመመገብ ይገደዳሉ። ሁኔታዎቹ ለተላላፊ በሽታዎች መነሣት ምቹ ይሆናሉ። ኮሌራ፥ ተቅማጥና ከንጽሕና ጉድለት ሳቢያ የሚመጡ በሽታዎች ይስፋፋሉ። ብዙዎች በጦርነቱ ከደረሰባቸው ቁስል ወይም በዚያ ሳቢያ በሚመጣ ሕመም ይሞታሉ።

እግዚአብሔር በወራሪው ሠራዊት ላይ የሚያደርሰውን እልቂት “በተፈጥሯዊ” ጥፋት ጀምሮ በዚያው ይጨርሰዋል። የእግዚአብሔር ፍርድ መጀመሩን ያመለከተው የምድር ነውጥ መነሻ ብቻ ነው፥ “በቸነፈርና በደም እፈርድበታለሁ፤ ዶፍም፥ የበረዶም ድንጋይ፥ እሳትና ድኝም በእርሱና በጭፍሮቹ ከእርሱም ጋር ባሉ በብዙ ሕዝብ ላይ አዘንባለሁ” (38፡22)። በወራሪዎቹ ላይ የሚደርሱት ሦስት መቅሠፍቶች ከሰማይ የሚወርዱ ናቸው። ኃይለኛ ዝናብ ወታደሮቹ እርዳታ እንዳይደርስላቸው ያግዳል፥ የመሬት ናዳና ጎርፍ ብዙዎቹን ይገድላል። የውኃ የማጥፋት ኃይል አስፈሪ ነው፤ ያን ኃይል ነው እግዚአብሔር በወራሪዎቹ ላይ የሚያመጣባቸው።

ከእግዚአብሔር የመጨረሻ መቅሠፍቶች ሁለተኛው በረዶ ነው። በረዶን እንደመግደያ መሣሪያ አናስበውም። ነገር ግን ከሰማይ የሚወርድ ታላቅ የበረዶ ዝናብ ጥፋት ሊያደርስ ይችላል። በብሉይ ኪዳን ዘመን በተካሄደ አንድ ጦርነት፥ የእስራኤልን ጠላቶች ለማጥፋት እግዚአብሔር በሰይፍና በበረዶ ድንጋይ ተጠቅሟል፥ “ከእስራኤልም ልጆች ፊት እየሸሹ በቤትሆሮን ቁልቁለት ሲወርዱ፥ ወደ ዓዜቃ እስኪደርሱ ድረስ እግዚአብሔር ከሰማይ ታላላቅ የበረዶ ድንጋይ አወረደባቸውና ሞቱ። የእስራኤል ልጆች በሰይፍ ከገደሏቸው ይልቅ፥ በበረዶ ድንጋይ የሞቱት በለጡ” (ኢያሱ 10፡11)። ወራሪዎቹ ምንም መከለያ ወይም መጠለያ ስለማያገኙ ለበረዶው ጥቃት ይጋለጣሉ።

ከሰማይ የሚወርደው ሌላ የእግዚአብሔር አደጋ “እሳትና ድኝ” ነው። ይህን መዓት ሕዝቅኤል ባያብራራውም፥ ቃሉ እግዚአብሔር በሰዶምና ገሞራ ላይ ወዳወረደው ፍርድ ይወስደናል፥ “እግዚአብሔርም በሰዶምና በገሞራ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳትና ዲን አዘነበ” (ዘፍጥ. 19፡24)። ሰዶምን ያወደማት እሳት እስራኤልን በሚወር ሠራዊት ላይ እንደገና ይዘንባል። አንዳንዶች “እሳትና ድኝ” ከእሳተ ገሞራ ፍንዳታ በኋላ የሚኖረውን ሁኔታ የሚገልጥ ይመስላቸዋል። ይህ በእርግጥ ሊሆን ይችላል። ብዙው የሰሜናዊ እስራኤል ክፍል በእሳተ ገሞራዊ ቋጥኝ


ተሸፍኗል። ይህ ሁኔታ ምድሪቱ ባንድ ወቅት "የእሳት ድኝ" ሸፍኗት እንደነበር የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው። ግዙፎቹ እሳተ ገሞራዊ የጎላን ተራራዎች እንደ ዝምተኛ ምስክሮች ቆመው የርዳኖስ ሸለቆ ውስጥ የሚከናወኑትን ከርሠ-ምድራዊ እንቅስቃሴዎች ይመለከታሉ።

የጎግ ወራሪ ሠራዊት በእግዚአብሔር ኃያል ክንድ ፊት ምንም አይደለም። እስራኤል ከወረራው ትተርፋለች። ይሁን እንጂ፥ የእስራኤል ሠራዊት ድሉ የኔ ነው ሊል አይችልም። የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በዚያን ጊዜ የሚሆኑ ነገሮችን "የእግዚአብሔር ድርጊት" ይሏቸዋል፤ ተስማሚ ስያሜ ነው። የወራሪውን ሠራዊት ውጊያ ለመግታት እግዚአብሔር የምድር መናወጥን፥ ኃይለኛ ዝናብ፥ የበረዶ ድንጋይ እንዲሁም እሳትና ድኝ ይልካል። ወራሪዎቹ ወታደሮች በፍርሃትና ግራ በመጋባት እርስ በርሳቸው ይታኮሳሉ። ከመድኃኒት ችግርና ሌላ አቅርቦት እንዲሁም ከንጽሕና ጉድለት ጋር ተዳምረው ወረርሽኝ ያስነሣሉ። በዚያን ጊዜ "እኔም እግዚአብሔር እንደሆንሁ ያውቃሉ" (ሕዝ. 38፡23)።

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር በዚህ እስላማዊ ኅብረት ላይ የሚያደርሰው ጥፋት መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ አስደናቂ ውጤት ያመጣል። ሕዝቦቿ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ታዳጊነት ሲረዱ፥ እስራኤል ብሔራዊና መንፈሳዊ መነቃቃት ታደርጋለች። የዓለም መሪ የሆነው ሰው የደኅንነት ዋስትና ሊሰጣት አልቻለም። እግዚአብሔር ግን ጣልቃ ሊገባ የቻለ ብርቱ አምላክ ነው። ጦርነቱ ካበቃ በኋላ፥ እስራኤል ቤተ መቅደስ ውስጥ ለሚቀመጠው የዓለም መሪ ምስል አልሰግድም ትላለች። ይህን የቀድሞ አጋሯን አልከተልም የምትልበትን ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ አይገልጥም። ምናልባት እግዚአብሔር የጦርነቱን አስደናቂ ፍጻሜ ተጠቅሞ የሕዝቡን ዓይኖች ከፍቶ ይሆናል።

ቱርክ፥ ኢራንና የቀድሞው ሶቪየት ኅብረት ክፍል የነበሩ እስላማዊ ሪፑብሊኮች የራሳቸውን አዲስ የዓለም ሥርዓት በማበጃጀት ላይ ናቸው። ሊቢያ እና ሱዳንም ከዚህ የእስላማዊ አገሮች ቡድን ጋር የቅርብ ትሥሥር ለመፍጠር ይፈልጋሉ። ግንኙነቱ ወደፊት ምንም ዓይነት መልክና መለዋወጥ ቢኖረው፥ አገሮቹ አንድ ቀን የእስራኤልን ምድር ለማጥፋት ወደሚነሣሡበት ጦርነት ይመራቸዋል።



# > ክፍል ሦስት <
# አውሮፓ፡ ወታደራዊ ኃይልና አዲሱ የዓለም ሥርዓት

በ1992 እአአ ክረምት የተካሄደው የኦሎምፒክ ውድድር አውሮፓን የሚያጥለቀልቀውን አስደናቂ ለውጥ አጉልቶታል። ይህም በዩጎዝላቪያ መከፋፈል ነበር። የዩጎዝላቪያው ቡድን በ1988 እአአ በተወዳደረ ጊዜ፥ እንደ አንድ አገር ነበር የቀረበው። በ1992 እአአ ግን ከዚህ አገር የተገነጠሉት ክሮሺያና ስሎቪኒያ የየራሳቸውን የአትሌቲክስ ቡድን ላኩ። በ1936 እአአ ኢስቶኒያ፥ ላቲቪያና ሉቱዋኒያ ለየግላቸው ቡድንን በኦሎምፒክ ውድድር ላይ አቅርበው፥ ከ1936-1988 በነበረው ጊዜ ግን እንደ አንድ ቡድን በሶቪየት ሕብረት ሥር ተሰልፈው ነበር። በ1992 እአአ ደግሞ እንደገና ተከፋፍለው ቀረቡ። የሶቪየት ኅብረት በ1992 እአአ ፈርሶ የነበረበት ወቅት ቢሆንም፥ አንድ ቡድን ተወዳድሮ ነበር። ቡድኑ "የተባበረው ቡድን" በሚባል ስያሜ ሲወዳደር፥ ያለ ሰንደቅ ዓላማ ወይም ብሔራዊ መዝሙር ነበር። ሆኖም፥ ልብሳቸው ላይ የሚነበበው "የተባበሩት ሶቪየት ሶሻሊስት ሪፐብሊክ" የሚል ጽሑፍ ነበር። የምሥራቅና የምዕራብ ጀርመን የኦሎምፒክ ቡድኖች የሁለት መሆናቸው ቀርቶ የአንድ አገር ሆኑ። እነዚህ ሁሉ ምድርን የከፋፈሉ ሁኔታዎች የተከናወኑት ከአራት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ነው።

አንድ ሰው ጀርመን እንደገና አንድ ትሆናለች፥ ሶቪየት ኅብረት በሠላም ትበታተናለች፥ የዋርሶ ኃይል ይፈርሳል፥ ብሎ በ1980ዎቹ ቢናገር ኑሮ ይቀለድበት ነበር። በምዕራብና ምሥራቅ አውሮፓ መካከል ያለውን የልዩነት ርቀት ያህል ቋሚ የመሰለ ነገር አልነበረም። የሁለቱ ወገን ወታደሮች በሽቦና በፈንጂ በብዙ ርቀት ከታጠሩ ድንበሮቻቸው ባሻገር፥ በተያዩ ቁጥር፥ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጠባሳ ሲያመረቅዝባቸው ነበር የቆየው። ይሁን እንጂ፥ ሁሉም ነገር በአጭር ጊዜና በሚያስገርም አኳኋን ተለወጠ።

አውሮፓ ውስጥ የተካሄዱት ለውጦች ምን ያህል ጠቃሚ ናቸው? በዓለም ያለውን የኃይል ሚዛንና ተጽዕኖ ለመረዳት የሚጠቅም ነገር አላቸው። አሜሪካንና ጃፓን ዓለም አቀፋዊ የበላይነትን ለመያዝ በውድድር ላይ ያሉ ይመስላሉ። ሁለቱም በአዲሲቱ አውሮፓ ገለል ይደረጉ ይሆናል።

"በክፍለ-ዘመኑ መጨረሻ ገደማ የአውሮፓው ኅብረት 520 ሚሊዮን ሕዝብ ያሏቸው ሀያ ሦስት መንግሥታትን የሚይዝ ይሆናል። የነበራቸው አጠቃላይ ምርት 5 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይደርሳል። ከዚህ ጋር ሲነጻጸር፥ የአሜሪካን አጠቃላይ ምርት 4 ትሪሊዮን ዶላር፥ የጃፓን ደግሞ 2 ትሪሊዮን ዶላር ይሆናል። የሁለቱ አገሮች ሕዝብ ድምር ከ375 ሚሊዮን በታች ነው።"

አውሮፓ በፖለቲካና በኢኮኖሚ አጠቃላይ ለውጥ በምታደርግበት ጊዜ፥ የፖለቲካ ሰዎችና ኢኮኖሚስቶች ደግሞ፥ የወደፊት ውጤቱን ለመለየት የራሳቸውን ይህ ይሆንን የሚል ትንታኔ ያደርጉ ነበር። አውሮፓ እንደተባበረ አዲስና ግዙፍ የዓለም ሥርዓት ሆና ትወጣለች? ወይስ ሂደቱ ግጭትና ብጥብጥን ያስከትል ይሆን? ስለ ወደፊቷ አውሮፓ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠን ፍንጭ አለን? በእርግጥ ስለ ወደፊቱ አውሮፓና ስለቀረው ዓለም ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጠው ነገር አለ። እስቲ የአውሮፓን የወደፊት ዕጣ በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል የሚገልጠውን እንፈትሽ።

> ምዕራፍ አሥራ ሁለት <

# የአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ ኮሚሽንና የአውሮፓ ኅብረት

“ከአትላንቲክ እስከ ኡራል ተራራዎች” የሚዘልቀው የአውሮፓ ኅብረት። ሚካኤል ጎርባቾቭ በ1989 እአአ ፓሪስ ውስጥ በሰጡት አንድ ቃለ መጠይቅ ይህን አንቀጽ በተናገሩ ጊዜ፥ ከሠላሳ ዓመታት በፊት በቻርልስ ደጎል የተባሉትን ቃላት ነበር ያስተጋቡት። ምሁራን፥ የአካባቢው መሪዎችና ወታደሮች ይህን የተባበረች አውሮፓ ህልም ለምዕተ ዓመታት አልመዋል። እንደ ናፖሊዮንና አዶልፍ ሂትለር ያሉት መሪዎች ዕቅዳቸውን ወደ ተግባር በመተርጎም፥ አውሮፓን አጥፊ ጦርነት ውስጥ ከተዋት ነበር። የአውሮፓ ኅብረት ፕሬዚዳንት የነበሩት ጃክ ድሎርስ ደግሞ፥ በጸጥታና በማይታይ አኳኋን በመሥራት ያለ ምንም ጦርነት ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ጥረዋል። የእነዚህ ሰዎች ዘዴዎች ይለያዩ እንጂ፥ ግባቸው ያው የተባበረች አውሮፓን መመሥረት ነበር።

ብዙ ልዩነቶች ያሉባት የአውሮፓ አህጉር አንድ ልትሆን ትችላለች? እንዴት ነው የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ የሆኑ፥ የተለያዩ የሃይማኖት መሠረቶችና፥ መንግሥታዊ መዋቅር ያሏቸው አገሮች አንድ ቡድን ወደ መሆን የሚደርሱት? መሰናክሎቹ ብዙ ናቸው፤ ያንኑ ያህል ጠቀሜታዎችም አሉ። አውሮፓ የሚኖራት የመጀመሪያ ጥቅም ኢኮኖሚያዊ ነው። አንድ ጸሐፊ፥ “አንዳንድ ጸሐፊዎች እንዳስገነዘቡት የኅብረቱ ዋነኛና አንድ ምክንያት፥ አውሮፓ ኢኮኖሚያዊና ቴክኒዎሎጂያዊ አሠራሯን ለማሻሻል ዋና ዋና እንቅስቃሴዎችን ካልጀመረች፥ ከአሜሪካ ብቻ ሳይሆን ከጃፓንም በጣም ወደ ኋላ የመቅረት ዕጣ ይጠብቃታል።” ብለው ነበር።

1202 በአጭሩ ሲገለጥ፥ አውሮፓ በዓለም አቀፋዊ ኢኮኖሚ ተወዳዳሪ ለመሆን መተባበር አለባት። ልክ ዛሬ ከታላላቅ የግብርና ተቋማት ጋር እንደሚወዳደሩ አነስተኛ ገበሬዎች ሁሉ፥ የተወሰነ ገበያ ያላቸው ትንንሽ አገሮች መተባበር አለባቸው። ያለዚያ ምርታቸውን በቁጠባዊ ዘዴ በሚያመርቱ ታላላቅ አገሮች ይዋጣሉ። የአውሮፓ አገሮች ከእንግዲህ የተለያየ የምርት ደረጃ፥ የተለያየ የገንዘብ ፖሊሲ ወይም የተለያየ የትርፍ፥ የወጪና የገቢ ሕግ ሊኖራቸው አይገባም። ለሁሉም አገሮች ደረጃዎችንና ፖሊሲዎችን የሚያወጣ ማዕከላዊ የሥልጣን አካል መኖር አለበት።

የተባበሩት የአውሮፓ አገሮች

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በአውሮፓ አንድ ዓይነት ኅብረት ለመፍጠር ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል። “የአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ ትብብር ድርጅትን” ለመመሥረት በ1948 እአአ አሥራ ሰባት የአውሮፓ አገሮች ተባብረው ነበር። ይህ ድርጅት ማርሻል ፕላን በመባል ከሚታወቀው የአሜሪካን የእርዳታ ፕሮግራም የሚገኘውን የእርዳታ ሥርጭት ያስተባበረ ነው። ይሁን እንጂ፥ ድርጅቱ ውሳኔውን ለማስፈጸም ሥልጣን አልነበረውም። የማርሻል ፕላን ዕቅድ ሲያበቃ፥ የድርጅቱ አስፈላጊነትም አበቃ።

በ1958 እአአ ስድስት አገሮች፥ ማለት ቤልጂግ፥ ፈረንሳይ፥ ኢጣሊያ፥ ሉክሰንበርግ፥ ኔዘርላንድና ምዕራብ ጀርመን “የአውሮፓ ማኅበርን” መሠረቱ። የዚህ ማኅበር ግብ፥ የአውሮፓን ኢኮኖሚ አንድ ማድረግ ነበር። በዚሁ መሠረት አገሮቹ ቤልጅግ፥ ብራሰልስ ከተማ ውስጥ ፓርላማና ፍርድ ቤት በመመሥረት፥ በኅብረታቸው ሥር ሦስት የተለያዩ ቡድኖችን አቋቋሙ። አንደኛው፥ “የአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ ማኅበር”፥ ብዙውን ጊዜ “የጋራ ገበያ” በመባል የሚታወቀው ነው። በሁለተኛ ደረጃ የጋራ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነደፉ፤ በመጨረሻም የሸቀጥ ትርፍን አስቀሩ። “የአውሮፓ የከሰልና የብረት ማኅበር” በኅብረቱ አገሮች የሚገኙ የከሰልና የብረት እንዱስትሪዎችን ፖሊሲዎችና አሠራሮችን ለማስተባበር ሞከሩ። “የአውሮፓ የአውቶሚክ ኃይል ማኅበር” ደግሞ አውቶሚክ ኃይልን ለማስፋፋትና ለሠላም ዓላማ ለማዋል ፈለገ።

1203 ድርጅቱ በአባላት ብዛት ቢያድግም፥ የአንድነቱ ሂደት ግን ቢሮክራሲያዊ የጭቅጭቅ አረንቋ ውስጥ ዘቅጧል። በ1980ዎቹ ዓመታት የግዙፉ “የአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ ማኅበር” ግብ ከሸፈ። አባላቱም ተስፋ ከመቁረጥና የጭቅጭቅ ቡድን ከመሆን የሚርቁ አልመሰሉም። ይሁን እንጂ፥ የአሜሪካና የጃፓን የኢኮኖሚ እድገት በአውሮፓ አገሮች ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ እያደገ በመምጣት፥ የብሔራዊ ጥቅም ተከላካይነታቸውን በመተው ለአንድነታቸው እንዲጥሩ አደረጋቸው። ከመተባበር ወይም በቴክኒዎሎጂ ኃያላን በሆኑ አገሮች ከመጥፋት አንዱን መምረጥ ነበረባቸው።

“የአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ ኮሚሽን” በ1986 እአአ በፖለቲካ የተባበረችው አውሮፓን ግብ በግልጥ አወጣ። በአህጉሪቱ ለዓመታት ሰፍኖ የቆየው ግጭትና ውድድር ሲታሰብ እድገቱ ታላቅ ነበር። በ1992 እአአ አገሮቹ የምርታቸውን ደረጃ ባስተባበሩና የሸቀጥ ትርፍን ባስወገዱ ጊዜ ነው የመጀመሪያውን እንቅፋት ያስወገዱት። እነዚህ እርምጃዎች ግን ጅማሬዎች

ብቻ ናቸው። ለሁሉም አገሮች ከሚሆን አንድ የገንዘብ ፖሊሲ ጋር የአውሮፓን ማዕከላዊ ባንክ አቋቁሟል። በአዳዲስ የባቡር ሀዲዶችና በመኪና መንገዶች የመገናኘቱ ሂደት የዚህ ሰፊ ኅብረት አባላት የሆኑ አገሮችን አንድነት ያጠናክረዋል፤ በአገሮች መካከል በሚደረገው ጉዞ ላይ የተጣለው ቁጥጥርም ይላላል። ከቀረጥ እስከ ማጓጓዣ ባለው እንቅስቃሴ አውሮፓ እንደተባበረ ማኅበረሰብ ትሠራለች።

በ1980ዎቹ ፍጻሜና በ1990ዎቹ መጀመሪያ አውሮፓን የናጧት አስደናቂ ነገሮች ወደ አንድነት የምታደርገውን ጉዞ አፋጠኑት። የሶቪየት ኅብረትና የዋርሶ ኃይል መፈራረስ አውሮፓን ከቀዝቃዛው ጦርነት ግንባር ወደ ኋላ መለሳት። በምሥራቅና ምዕራብ አውሮፓ ድንበር ላይ የነበረው የሽቦ አጥር በመፈራረሱ፥ በታሪክ ጠላቶች የነበሩ አገሮች ወዳጆች በመሆን ላይ ናቸው።

የቀድሞይቱ ሶቪየት ኅብረት ክፍሎች የነበሩና፥ ካፒታሊዝምን ለማፈራረስ ያልሙ የነበሩ አገሮች፥ ዛሬ መዋዕለ ንዋይ በመሻት ወኪሎቻቸውን ወደ ምዕራብ በመላክ ላይ ናቸው። ሶቪየት ኅብረት ጠንካራ ከሆነው ከኮሚኒስት አመራር የካፒታሊዝም አመራርን በመጠኑ ወደሚቀበል አስተዳደር ተለውጣለች። አውሮፓ ከጦር መጣሪያ ጥቃት ፍርሃት ነጻ ስለሆነች፥ ስለ ሠላማዊት አህጉር ለማለም ትችላለች። ይህ ህልም በዚህ ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ገደማ የማይታሰብ ነበር።

የግዴታ ጋብቻ

የአውሮፓ ኅብረት አዋቃሪዎች በቅርብ ዓመታት አንድ አስደናቂ እድገት አድርገዋል። ይሁን እንጂ፥ ለተባበሩት የአውሮፓ አገሮች ኅብረት አሁንም የሚቀረው ነገር ስላለ፥ ሙሉ የሆነ ነገርን ለመጻፍ የሚችል ሰው የለም። ብዙዎች ኅብረቱን በፍቅር እንደተጀመረ ሳይሆን፥ በግዴታ የተጀመረ ጋብቻን የሚመስል ታሪክ እንዳለው አድርገው ነው የሚያዩት። የፈገግታዋ ጭምብል ቢገለጥ፥ አውሮፓን የተጋፈጧት ብዙ ችግሮች ይታያሉ።

ሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ብዙዎቹ የአውሮፓ አገሮችን "ጀርመን ከሁሉም በላይ" የሚለውን መፈክር እንዲፈሩ አድርገዋቸዋል። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ፥ ድል አድራጊዎቹ የቃል ኪዳን አገሮች ጀርመንን ሁለት ላይ በመክፈል ይዘዋት ነበር። የአውሮፓው አሸባሪ ድል ሆነ። 1980 እአአ በጀመረ ጊዜ፥ ክፍለ-ዘመኑ ሳያበቃ ሁለቱ ጀርመኖች ይዋሐዳሉ ብሎ ማንም ከልቡ ያመነ አልነበረም። የበርሊን ግንብ መገርሰስ

ግን፥ ሁለቱን አገሮች ለያይቶ ያቆየው የኮሙኒስት ግዛት መፈራረስ ምሳሌ ሆኖ ነበር።

ጀርመን በአንድ ሌሊት የአውሮፓ ኃያል አገር ሆነች። አውሮፓ ውስጥ ብዙ ጦርና ብርቱ ኢኮኖሚ ያላቸው ሰማኒያ ሚሊዮን ጀርመናውያን፥ በቀረው የአህጉሪቱ ክፍል ላይ የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ ተባበሩ። አንድ ጸሐፊ እንዳሉት፥ "ብዙዎቹ የጀርመን ጎረቤት አገሮች፥ በተለይም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በናዚ ወረራና ጭካኔ የተሠቃዩት ውሕደቱን ፈሩት።" በመርህ ደረጃ የአውሮፓ ኅብረት መልካም ነው። ነገር ግን፥ በአህጉሪቱ ከሚገኙት አገሮች የትኛውም ቢሆን በጀርመን የበላይነት አንድ የምትሆነው አውሮፓ አባል ለመሆን አይሻም።

የናዚ ጀርመን አሳፋሪ ገጽታ የአውሮፓ መጥፎ ትዝታ እንደሆነ አለ። በጀርመን ወጣቶች መካከል የተፈጠረው አዲስ የናዚ ንቅናቄም በአገሪቱ ለሚኖሩ ብዙ የውጭ ሰዎች ችግር ሆኖባቸዋል። የአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት መገታትና፥ ሁለቱን ጀርመኖች በማዋሐድ ጊዜ የወጣው ወጪ ያስከተለው ችግር፥ የወጣት ጀርመናውያንን ቁጣ አባባሰው። ጀርመን ውስጥ የዘረኝነት ግጭት ከጊዜ ወደጊዜ በማደግ ላይ ነው። ብዙዎቹ ግጭቶች የሚመነጩት "ከራሰ ልጩ" [skin head/ስኪን ሄድ] ናዚዎች ነው። በ1992 እአአ ብቻ 2,000 ያህል የተለያዩ ጥቃቶች በናዚዎቹ ተፈጽመዋል። "ጀርመን ከራሷ የብሔርተኝነት ጥቅም ይልቅ፥ የአውሮፓን ጥቅም ታስቀድማለች ተብላ ትታመናለችን? "ጀርመን፥ ከውሕደቱ ጊዜ ወዲህ አዲስ ኃያል መንግሥት አለዚያም ቢያንስ የአውሮፓ እድገትና ዲሞክራሲያዊ ተሐድሶ አንቀሳቃሽ ትሆናለች ተብላ ብትጠበቅም፥ ዛሬ በራሷ የማንነት ችግር በመወጠሯ፥ የተጠበቀችውን ለመሆን አልቻለችም።"

የጀርመን ውሕደትና ብሔርተኝነት ብዙዎቹን አውሮፓውያን አስፈርቷቸዋል። ይሁን እንጂ፥ ከብሔርተኝነት ጋር የምትታገለው ጀርመን ብቻ አይደለችም። የሶቪየት ኅብረት ግዛት መበታተን የብሔርተኝነት ስደድ እሳትን ወደ ብዙዎቹ የአውሮፓ ክፍሎች አዛምቷል። ዩጎዝላቪያ ውስጥ ክሮትሳውያን እና ሴርቢያውያን የተባሉ ሕዝቦች እርስ በእርሳቸው ሲጨፋጨፉ ነበር። በቀድሞው ሶቪየት ኅብረት ሪፑብሊክ ደቡባዊ ክፍል አርመናውያንና አዘርባጃውያን ይጠቃቃሉ። የባስክ ተገንጣዮች ስፔይን ውስጥ፥ የአየርላንድ ጦር አባላት ደግሞ ብሪታኒያ ውስጥ በምብ ይቀብራሉ።

አውሮፓ የበቀለችው በብሔርተኝነት አፈር ላይ ነው። ብዙዎቹ የአውሮፓ ማኅበረሰቦች የተመሠረቱት በአንድ ቋንቋ ወይም ሃይማኖት

በተባበሩ ዘሮችና ኮንፌዴሬሽን ነው። እነዚህ ተናጠል ቡድኖች ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ቅርሳቸውን በሰፊ ማኅበረሰብነት ሊተኩት ይችላሉ? የተባበረች አውሮፓን ለመፍጠር ለሚደረግ ሙከራ ሁሉ ብሔርተኝነት ስፍራ ይለቅ ይሆን?

የተባበረች አውሮፓ ፍርሃቶች ጀርመንና በማንሠራራት ላይ ያለው ብሔረተኝነት ብቻ አይደሉም። የዛሬዎቹ ዋና መሰናክሎች፥ በአሁኑ ኅብረት ወይም ድርጅት ውስጥ ያልተካተቱት ብዙ መንግሥታት ሊሆኑ ይችላሉ። የአውሮፓን የወደፊት ገጽታ ለመቅረፅ የሚሹ ኃያላን ቡድኖች፥ የአውሮፓ ኢኮኖሚ ኮሚሽን እና ኔቶ ናቸው። የኮሚሽኑ አባላት አሥራ ሁለት አገሮች ሲሆኑ፥ የኔቶ ተባባሪዎች ደግሞ አሥራ ስድስት የአውሮፓ አገሮች ናቸው። ብዙዎቹ የአውሮፓ አገሮች የእነዚህ ሁለት ድርጅቶች አባላት አይደሉም። እውነተኛው አውሮፓዊ ኅብረት ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ ግን፥ መላይቱን አውሮፓ የሚወክል መሆን አለበት።

አውሮፓ ለአንድ አህጉር ውሕደት የሚበጅ ምሥጢር በመፈለግ ላይ ናት። ለኀምሳ ዓመታት ያህል የተደረገው ጥረት መጠነኛ ውጤት አስገኝቷል፤ በሚመጡት ጥቂት ዓመታትም ጥሩ እድገት የሚገኝበት ሁኔታ አለ። ከዚህ የሚገኘው ጥቅም እጅግ ብዙ ቢሆንም፥ እንቅፋቶቹ ግን አያሌ ናቸው። አውሮፓን ወደ ፖለቲካዊ ኅብረት ለማድረስ ብርቱ አመራር ያሻል። የአህጉሪቱን ዋና ዋና አገሮች አንድ የሚያደርግ ድርጅት መፈጠር አለበት። እንዲህ ያለ አንድነት ይፈጠር ይሆን?

*ዳንኤል የገለጣቸው "የአሕዛብ ዘመናት"*

ነብዩ ዳንኤል በባቢሎን አደባባይ የእግዚአብሔር አፈ ጉባኤ ነበር። ኢየሩሳሌም ውስጥ ከነበሩ የነገሥታትና የመሣፍንት ዘር ከሆኑት ከአንዱ ቤተሰብ የተወለደ ሲሆን፥ በ605 ዓመተ ዓለም እንደ ንጉሣዊ ቤተሰብ በምርኮ ተወሰደ። እዚያም በናቡከደነፆር መንግሥት ውስጥ በፍጥነት ወደ ታላቅ ባለሥልጣንነት አደገ። ዳንኤልን የምናስታውሰው ግን በመንግሥት ውስጥ ከነበረው አገልግሎቱ ይልቅ፥ በነቢይነቱ ነው። ስለ ወደፊቱ ያያቸው የተሸፈኑና ግር የሚያሰኙት ራእዮቹ ብዙ አንባቢዎችን ግራ ያጋባሉ። የዳንኤልን ሕልሞች ልንረዳቸው እንችላለን?

የዳንኤል ትንቢቶች ይበልጥ ግልጥ የሚሆኑልን፥ የመጽሐፉን አደረጃጀት ስንገነዘብ ነው። የመጀመሪያ ምዕራፉን የጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን፥ ምዕራፉም እንደ መጽሐፉ መግቢያ ያገለግላል። ዳንኤል ወደ ባቢሎን እንዴት እንደሄደና የእግዚአብሔርን በረከት ያገኘበትን ምክንያት የምንረዳው በዚሁ ምዕራፍ ነው። ከሁለተኛው ምዕራፍ ጀምሮ ግን ዳንኤል

ቋንቋዎችንና ጉዳዮችን ይለውጣቸዋል። ምዕራፍ 2፡4 ላይ ጽሑፉን ከዕብራይስጥ ወደ ሶርያ ቋንቋ (አራማይክ) እንዲህ በማለት ይለውጠዋል ("ከለዳውያኑም ንጉሡን በሶርያ ቋንቋ")። ቋንቋዎቹ ተመሳሳይ ናቸው፤ በአንባቢዎቹ ላይ የሚያሳድረው ግንዛቤ ግን፥ ጽሑፉን ልክ ከእንግሊዝኛ ወደ ፈረንሳይኛ የለወጠው ያህል ነው። ከምዕራፍ 2-7 ያለውን ክፍል በሶርያ ቋንቋ ከጻፈ በኋላ፥ ምዕራፍ ስምንትን ሲጀምር እንደገና ወደ ዕብራይስጥ ይመልሳል።

ቋንቋውን የሚቀያይረው ለምንድነው? ዳንኤል ከምዕራፍ 2-7 በጻፈው ክፍል የመዘገበው፥ ለሕዝቦቹ ሁሉ የሚጠቅሙ ሁኔታዎችን ስለሆነ፥ በጊዜው በነበረ የመገበያያ ቋንቋ አሰፈረው። ከምዕራፍ 8 ጀምሮ ግን እስራኤላውያንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ስላተኮረ፥ በዕብራይስጥኛ ወደመጻፉ ተመለሰ። ከምዕራፍ 2-7 ባለው ክፍል ከ"አሕዛብ ዘመን" ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል።

ናቡከደነፆርና ባቢሎናውያን የይሁዳን መንግሥት እንዲያጠፉና አይሁዳውያንን በምርኮ እንዲወስዱ እግዚአብሔር ፈቀደ። እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የነበረው የሁልጊዜ ዓላማ፥ ይመጣ በነበረው መሲሕ አማካይነት መንግሥቱን በምድር ላይ መመሥረት ነበር። ነገር ግን ሕዝቦቹ አንታዘዝም በማለታቸው፥ ለበደልና ለምርኮ በመዳረግ ቀጣቸው። ምንም እንኳን በሥቃይ ውስጥ ቢሆኑ፥ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን እንደሚቆጣጠርና ለዓለም ያለውን ዕቅድ በማከናወን ላይ መሆኑን ለአይሁዳውያን ለማሳወቅ ነበር ዳንኤል የጻፈው። የእግዚአብሔር መንግሥት ገና ትመጣለች፤ አይሁዳውያንም አንድ ቀን ወደ እስራኤል ምድር ይሰበሰባሉ።

ዳንኤል በመጽሐፉ አንድ ክፍል በአረማይክ የጻፈው፥ የእግዚአብሔር መንግሥት ገና የሚመጣ መሆኑን ለአይሁዳውያን (ለሌሎች ቃሉን ለሚያነቡም ጭምር)፥ ለመግለጥ ነበር። ምዕራፍ ሁለት ውስጥ እንደምንመለከተው፥ ዳንኤል ለንጉሥ ናቡከደነፆር ሕልሙን በፈታበት ጊዜ የንጉሡን መንግሥታዊ ሐውልት ያፈራረሰውን ድንጋይ ትርጉም ገልጧል። "በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፤ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል" (ዳን. 2፡44)። ዓለም ውስጥ የሚርመሰመሱትን አራዊት ለማጥፋት "የሰው ልጅ የሚመስል" የሚመጣ መሆኑን ዳንኤል ምዕራፍ 7 ውስጥ ተመልክቷል። "ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው" (ዳን. 7፡14)።

ዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ከምዕራፍ 2-7 ባለው ክፍል የይሁዳ መንግሥት ከፈራረሰበትና በመጨረሻም የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር እስከሚመሠረትበት ጊዜ ድረስ የሚሆነውን ነገር ነብዩ ይገልጣል። ይህ በተለምዶ፥ "የአሕዛብ ዘመን"፥ ማለት የአሕዛብ ኃያላን አይሁዳውያንን የሚገዙበትና የእስራኤልን ምድርና ኢየሩሳሌምን የሚቆጣጠሩበት ጊዜ ነው። ዳንኤል እግዚአብሔር፥ "ለአሕዛብ ዘመን" ያለውን ሉዓላዊ ዕቅድ ለመከታተል ይረዳው ዘንድ ሦስት ተመሳሳይ ምዕራፎችን በመጠቀም መልእክቱን ይቋጫል። ቅንብሩ (ጽሑፉ)፥ የታወቀውን ዕብራይስጥኛ የአጻጻፍ ዘዴ ተከትሎ የመጀመሪያና ስድስተኛውን፥ ሁለተኛና አምስተኛውን፥ እንዲሁም ሦስተኛና አራተኛውን ክፍል በማዛመድ ነው የቀረበው። መዋቅሩን እንደሚከተለው ለመግለጥ ይቻላል።

ምዕራፍ 2. እግዚአብሔር ለአሕዛብ ዘመን የነደፈው ዕቅድ "የአሕዛብ ዘመን"

ምዕራፍ 3. በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚደርስ ስደትና የእግዚአብሔር ጥበቃ ።

ምዕራፍ 4. እግዚአብሔር አሁንም ልዑል መሆኑን ለአሕዛብ መሪዎች ያሳያቸዋል።

ምዕራፍ 5. እግዚአብሔር አሁንም ልዑል መሆኑን ለአሕዛብ መሪዎች ያሳያቸዋል።

ምዕራፍ 6. በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚደርስ ስደትና የእግዚአብሔር ጥበቃ።

ምዕራፍ 7. እግዚአብሔር ለአሕዛብ ታሪክ የነደፈው ዕቅድ "የአሕዛብ ዘመን"

## አራቱ መንግሥታት

ነቢዩ በመጽሐፉ ከምዕራፍ 2-7 ባሉት የመጀመሪያና የመጨረሻ ክፍሎች የሚያስገነዝበው፥ ከናቡከደነፆር ጊዜ አንሥቶ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያዘጋጃት መንግሥት እስክትመጣ ድረስ እስራኤልን ስለሚመሯት የአሕዛብ ኃይሎች ነው። ምዕራፍ ሁለት መንግሥታቱን የግዙፉ ምስል አራት ክፍሎች አድርጎ ነው የሚያቀርባቸው። ምዕራፍ 7 ግን መንግሥቱን ከባሕር የሚወጡ አራት አራዊት አድርጎ ይገልጣቸዋል። በማንኛውም ደረጃ ቢሆን፥ እነዚህን ራእዮች በእርግጠኝነት ልንፈታቸው እንችላለን? ወይስ ራእዮቹ ልንረዳቸው የማይቻሉን ናቸው?

በዳንኤል አገላለጥ መሠረት እነዚህን ራእዮች ለመፍታት መቻል ይኖርብናል። ዳንኤል በአንድ ድንጋይ የደቀቀውን ምስል ከገለጠ በኋላ፥ ራእዩን እንዲህ በማለት ይገልጠዋል፦ "ሕልሙ ይህ ነው፥ አሁንም ፍቺውን በንጉሡ ፊት እንናገራለን" (ዳን. 2፡36)። ምዕራፍ 7 ውስጥ እንደምንመለከተው ግን አንድ መልአክ መጥቶ እስኪፈታለት ድረስ ሕልሙ ዳንኤልን ግራ ያጋባዋል፥ "እርሱም ነገረኝ፥ የነገሩንም ፍቺ አስታወቀኝ" (ዳን. 7፡16)።

ከብዙ ብረት የተሠሩ ሐውልቶች ወይም ከመጽሐፍ ገጾች የሚዘሉ የሚመስሉ አራዊት ምስልን በአሠቃቂ ታሪኮች ውስጥ ስናነብ ይሰገጥጠናል። ዳንኤል እንቅልፍ የሚነሣ ምግብ በልቶ ከተኛ በኋላ የመዘገበው ሕልም በዘመን ሁሉ ቅዱሳንን ወይም አማኞችን ግራ ያጋባቸዋል ብለን እናስብ ይሆናል። ነገር ግን ራእዮቹ ያልተለመዱ ቢመስሉም፥ ከግንዛቤ የራቁ አይደሉም። ከእያንዳንዱ ራእይ በኋላ የተለያዩ ክፍሎችን እግዚአብሔር ራሱ ተርጉሟቸዋል። እናም ቃሉን በምንመረምርበት ጊዜ የእርሱ ትርጉሞች ፍጹም ግንዛቤ ይሰጣሉ።

ዳንኤል 2 ውስጥ የተገለጠውና ናቡከደነፆር በሕልሙ ያየው ባለ አራት ክፍል ምስል ምንድነው? የምስሉን ክፍሎች ዳንኤል ለንጉሡ በዝርዝር ገልጦለታል። የወርቁ ራስ፥ ራሱን ናቡከደነፆርን የሚወክል ነበር። "አንተ የወርቁ ራስ ነህ" (ዳን. 2፡38)። የአሕዛብ ዘመን የጀመረው ናቡከደነፆር አይሁዳውያንን በወረረ፥ ድል ባደረገና ከእስራኤል ምድር ሕዝቡን በምርኮ በወሰደ ጊዜ ነው። ናቡከደነፆር፥ እስራኤልን ያጠፋት አገር መሪ እንደመሆኑ፥ በአሕዛብ መንግሥታት ቅደም ተከተል ዋናውን ስፍራ ይዟል።

ዳንኤል የወርቁን ራስ ምሥጢር ከፈታ በኋላ፥ የራእዩ ሁለተኛ ክፍል ወደሆኑት የብር ደረትና እጆች ነው የተሻገረው። ለምንድነው ምስሉ ወይም ሐውልቱ ረከስ ወዳለው ማለት ወደ ብርነት የተሸጋገረው? "ከአንተም በኋላ ከአንተ የሚያንስ ሌላ መንግሥት ይነሣል" የሚለውን ለማመልከት ነው። ናቡከደነፆር የነገሠበት የባቢሎን ግዛት በሌላ ንጉሣዊ አገዛዝ ይተካ ነበር። የትኛው መንግሥት ነው በታሪክ ውስጥ ባቢሎንን የተካው? ዳንኤል ባቢሎን ስትወድቅ ያየ ስለሆነ ለጥያቄው መልስ አለው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ጥቅምት 12 ቀን በ539 ባቢሎን በሚዶናዊው ቂሮስ እጅ ወደቀች (ዳን. 5፡30-31)። ይህን ሁለተኛ መንግሥት ዳንኤል "የሜዶንና የፋርስ ነገሥታት" (ዳን. 8፡20) ይለዋል።

ዳንኤል የመጀመሪያዎቹን ሁለት ክፍሎች ምዕራፍ ሁለት ውስጥ ከገለጠ በኋላ፥ የራእዩን ሦስተኛ ክፍል አስከትሏል። የምስሉ "ሆዱና

ወገቡም ናስ" (ዳን. 2፡32) ነበር። ዳንኤል ናስ ስለሆነው ሆድ የሰጠው ገለጣ በጣም አጭርና "ሌላ ሦስተኛ የናስ መንግሥት ይነሣል" (ዳን. 2፡39) የሚል ነው። የሜዶንና የፋርስ ግዛት በድል አድራጊው ግሪካዊ በታላቁ እስክንድር መያዟን በዓለም ታሪክ ንባባችን የእሩቅ የትውስታ ማህደር ትዝ ይለናል። የግሪክ ግዛት የምስሉ ሦስተኛ ክፍል ሊሆን ይችል ነበር? ዳንኤል ምዕራፍ 8 ውስጥ ከሜዶንና ፋርስ ቀጥሎ የሚነሣውን መንግሥት በገለጠ ጊዜ ቅደም ተከተሉን አረጋግጧል። (በምዕራፍ 8 ውስጥ እንደተገለጠው የሜዶንና ፋርስን መንግሥት የሚደመስሰው "አውራው ፍየል") የ"ግሪክ" (8፡21) መንግሥት ነው ይላል። ባቢሎን፥ ሜዶንና ፋርስ እንዲሁም ግሪክ "በአሕዛብ ዘመን" የመጀመሪያዎቹ ሦስት መንግሥታት መሆናቸውን ዳንኤል ገልጧል። እነዚህ ሦስት መንግሥታት መካከለኛው ምሥራቅን በመያዝ የእስራኤልን ምድር አስተዳድረዋል። ዳንኤል በመጨረሻ የሚገልጠው የራእዩን አራተኛ ክፍል "የብረት እግሮችን" ነው። እዚህም ላይ የሚያስረዳው፥ በምስሉ ላይ ያለው አዲስ ብረት፥ አንድን መንግሥት የሚወክል መሆኑን ነው። "አራተኛውም መንግሥት ሁሉን እንደሚቀጠቅጥና እንደሚያደቅቅ ብረት ይበረታል" (2፡40)። ዳንኤል ይህን አራተኛ መንግሥት መጽሐፉ ውስጥ ባይገልጥም፥ ግሪክን ያሸነፈ፥ መካከለኛው ምሥራቅን ድል ያደረገና የእስራኤልን ምድር የያዘው የሮም መንግሥት ነበር። ይሁን እንጂ፥ ይህ አራተኛው መንግሥት መሆኑን በትክክል ለማወቅ እንችላለን?

ዳንኤል ራእይ ውስጥ የታየው አራተኛ መንግሥት፥ የሮም መንግሥት ነው ለማለት የሚያስችሉን ሁለት ማረጋገጫዎች አሉ። በመጀመሪያ በድንጋይ የተመሰለው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደመጣና "ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ" (2፡34) እንደታየ ዳንኤል ገልጧል። ይህ አራተኛ መንግሥት የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ምድር በሚመጣበት ጊዜ እስራኤልን በማስተዳደር ላይ የሚገኝ ነው። ኢየሱስ ወደ እስራኤል በመጣና "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" (ማቴ. 4፡17) ባለበት ጊዜ እስራኤልን ያስተዳድር የነበረው የሮም መንግሥት ነበር።

ሁለተኛ፥ የዳንኤልን ራእይ በተመለከተ የራሱን ትርጉም የሰጠና ጆሴፈስ የተባለ አይሁዳዊ የታሪክ ሰው ያኖረው ምስክርነት አለን። ጆሴፈስ ኢየሱስ በምድር ከኖረበት ጊዜ ለጥቆ የኖረ ከመሆኑም ሌላ፥ ክፉ ዕጣ የገጠመውና በሮም መንግሥት ላይ በተነሣው ዓመፅ የተሳተፈ ነበር። በኋላም ለሮም መንግሥት እጁን በመስጠት የሮም ንጉሠ ነገሥት ከሆነው ጄኔራል ቬስፓሲያን ጋር ወዳጅነት መሠረተ። ይህ ሰው ስለ አይሁዳውያን ታሪክና ጦርነቶች አንድ ዘገባ ጽፎ ነበር። የጽሑፉ ዕቅድ አንድ ክፍል፥

ሮማውያንና አይሁዳውያን ምንም እንኳን በቅርቡ ቢዋጉ፥ ብዙ የሚመሳሰሉበት ነገር መኖሩን ለማሳየት ነበር። በሮማውያንና በአይሁዳውያን መካከል የነበረውን የቅርብ ግንኙነት ያመጡትን እያንዳንዳቸውን ሁኔታዎች ለመግለጥ ብዙ ጥረት አድርጓል። ከዚህም ሌላ አይሁዳውያንን በሮማውያን ላይ ያስነሡዋቸውን ማናቸውንም ሁነቶች በማቃለል ወይም በማሳነስ ለመግለጥ ሞክሯል።

ጆሴፈስ ዳንኤል ምዕራፍ 2 ውስጥ ናቡከደነፆር ስለአየው ምስል ያቀረበው ማብራሪያ ያስደንቃል። የወርቁ ራስ የሚወክለው፥ "አንተን (ናቡከደነፆርን) እና ከአንተ በፊት የነበሩትን የባቢሎን ነገሥታት" ነው በማለት ገልጧል። የሜዶንና ፋርስ መንግሥትን እንደ ሁለተኛው መንግሥት ባይጠቅስም "ሁለቱ ክንዶች የሚያመለክቱት መንግሥትህ በሁለት ነገሥታት ይጠፋል" ብሎ በጻፈ ጊዜ፥ ይህን ሁለት ክፍል የሆነ መንግሥት በግልጥ በአእምሮው በመያዝ ነበር። ግሪክን በስም አልጠቀሰም፤ ነገር ግን ይህ በመደብ የተወከለ ሦስተኛ መንግሥት "ከምዕራብ" እንደሚመጣ በጥንቃቄ ገልጧል። ጆሴፈስ የምስሉ አራተኛ ክፍል የሮም መንግሥት ነው ብሎ በግልጥ ባያመለክትም፥ አራተኛውን መንግሥት ስለሚያጠፋው ድንጋይ የተረዳውን በማድበስበስ ለመግለጥ በሞከረ ጊዜ እንዲህ ብሏል፦ "ዳንኤል የድንጋዩን ትርጉምም ለንጉሡ ገልጧል፤ ይሁን እንጂ፥ እኔ የገለጥኩት ያለፈና የአሁን ጊዜ ነገሮችን ስለሆነ የወደፊት ነገሮችን ከዚህ ጋር ማዛመድ ተገቢ አይመስለኝም"። ሮም የጊዜው ኃያል መንግሥት ነበረች። ጆሴፈስ ግን የመጨረሻው መሢሐዊ የእግዚአብሔር መንግሥት ሮምን ያጠፋል በማለት ወዳጆቹን ለማስቀየም አልፈለገም።

ዳንኤል ምዕራፍ 2 ውስጥ ነቢዩ አራት መንግሥታትን ነው የሚገልጠው። እነዚህ መንግሥታት እስራኤላውያን በምርኮ ከሚወሰዱበት ጊዜ አንሥቶ የመሢሑ መንግሥት እስኪመጣ ድረስ ያለውን ከፍተ ጊዜ የሚሞሉ ናቸው። አራቱ፥ ማለት ባቢሎን፥ ሜዶንና ፋርስ፥ ግሪክ እና ሮም፥ ከዳንኤል ጊዜ ጀምሮ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ያለውን ጊዜ በማይቋረጥ ተከታታይነት ይይዛሉ።

ዳንኤል ምዕራፍ 7 ውስጥ አራቱን መንግሥታት ከባሕር እንደሚወጡ አራዊት ነው የገለጣቸው። ገለጣው የሚለያይ ቢሆንም፥ መንግሥታቱ እነዚያው ናቸው። የመጀመሪያው አውሬ የንሥር ክንፍ ያለው አንበሳ ቅርፅ ነው። ይህ የሁለት አራዊት ቅርፅ ያለው ምስል፥ የመጀመሪያውን መንግሥት ገናናነት ያመለክታል። በጥንት ዘመንም ቢሆን አንበሳ እንደ "አራዊት ንጉሥ" ይከበር ነበር። ንስር ደግሞ የአየር ላይ ጌታ የሚል ክብር ተሰጥቶታል። አውሬይቱ "ክንፎቿ ከእርሷ እስኪነቀሉ

ድረስ" (ዳን. 7፥14) በከፍተኛ ሁኔታ እንደገዛች ዳንኤል በጽሑፉ አመልክቷል። ይህ ገለጣ፥ ነቢዩ፥ ዳንኤል ምዕራፍ 4-5 ባለው ክፍል ስለናቡከደነፆርና ስለባቢሎን መዋረድ የመዘገበውን ነው የሚያስገነዝብ።

ነቢዩ የገለጣት ሁለተኛ አውሬ ድብ የምትመስልና "በአንድ ወገንም ቆመች" (7፥5) የተባለችው ናት። ይህች ገዳዳ ድብ የሜዶንና ፋርስ ሁለት ግማሽ መንግሥት ምሳሌ ናት። የፋርሳውያን ክፍል የሆነው የመንግሥቱ ግማሽ ይበልጥ የጸና ነው። ድቢቱ "ሦስት የጎድን አጥንቶች በአፍዋ ውስጥ በጥርሷ መካከል ነበሩ"። ይህ የሚያመለክተው፥ የሜዶንና ፋርስ መንግሥት ሊዲያን፥ ባቢሎንንና ግብፅን ድል የሚያደርግ መሆኑን ነው።

ከባሕር የወጣችውና ዳንኤል ያያት ሦስተኛ አውሬ "ነብር የምትመስል" (7፥6) ነበረች። ፈጣኗ ነብር በታላቁ እስክንድር ይመራ የነበረውና ዓለምን ያጥለቀለቀው የግሪክ መንግሥት ዓይነተኛ መግለጫ ናት። የነብሪቱ "አራት ራሶች" የታላቁ እስክንድርን መንግሥት የመጨረሻ ቅርፅ ይገልጣሉ። ከእርሱ ሞት በኋላ ግዛቱ ለአራት ጄኔራሎቹ ተከፋፈለ።

ዳንኤል አራተኛዋን አውሬ ሊገልጥ አልቻለም። ይህች የዳንኤል አውሬ በእርሱ አተያይ "ታላላቅ የብረት ጥርሶች" እና "አሥር ቀንዶች" የነበሯት ስለመሆኑ ከመናገር በቀር በዝርዝር አልተገለጠችም (7፥7)። ዳንኤል "ብረት" የሚለውን መግለጫ መጠቀሙ፥ አራተኛይቱን አውሬ ምዕራፍ 2 ውስጥ ከተጠቀሰው ምስል አራተኛ ክፍል ጋር ያገናኛታል። በመሆኑም አውሬይቱ የሮምን መንግሥት ትወክላለች።

## የሮም መንግሥት በተቃውሞ ይነሣል

ክርስቶስ መንግሥቱን በምድር ላይ ለመመሥረት በሚመጣ ጊዜ፥ የሮም መንግሥት አምባገነን ሆኖ የሚያገኘው መሆኑን ዳንኤል በሚያስገርም አኳኋን ተንብይዋል። እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደተናገረው ክርስቶስ የአይሁዳውያን መሲሕ ሆኖ በመጣ ጊዜ፥ የሮም መንግሥት የእስራኤልን ምድር ይዞ ነበር። ያኔ ግን አንድ አሳዛኝ ስሕተት የተፈጸመ ይመስላል። ኢየሱስ መንግሥቱን በመምራት ፋንታ ተሰቀለ። በሃይማኖት መሪዎች አማካይነት የተነሣሡት ዓመፀኞች "አስወግደው፥ አስወግደው፥ ስቀለው! ... ከቄሳር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም" እያሉ ጮሁ (ዮሐ. 19፥15)።

እግዚአብሔር ተሳስቶ ነበርን? የመንግሥቱ ዕቅድስ ያልተስተካከለ ነበር? መልሱ አልነበረም ነው። እንደውም መሲሑ

የሚገደል መሆኑን ዳንኤል ተንብዮ ነበር። ምዕራፍ 9 ውስጥ የእግዚአብሔርን ትንቢታዊ ክንውኖች የጊዜ ሰሌዳ ነቢዩ ተናግሯል። መጀመሪያ የተነበየው፥ "ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሢሑ ድረስ" (ዳን. 9፥25) የሚለውን ነው። ትንቢቱ ኢየሱስ እንደ እስራኤል መሢሕ ወደ ኢየሩሳሌም የገባበቱን ("የሆሣዕና") ዕለት ነው ያመለከተው።

በትንቢት የተነገረው ነገር ከመከናወኑ 600 ዓመታት ያህል ቀድሞ ነው ዳንኤል መሢሑ የሚደርስበትን ነገር እንዲህ በማለት የተነበየው:- "ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሢሕ ይገደላል፥ በእርሱም ዘንድ ምንም የለም" (9፥26)። የኢየሱስ ሞት ድንገተኛ አልነበረም። መሢሑ እንደሚሞት እግዚአብሔር ተናግሮ ነበር። ነገር ግን ለምን ሞተ? ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ በማለት ለጥያቄው መልስ ይሰጣል:-

> "እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለበደላችንም ደቀቀ፥ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፥ ከእኛ እያንዳንዱ ወደገዛ መንገዱ አዘነበለ፥ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ" (ኢሳ. 53፥5-6)። መሢሑ የሞተው የከፋታችን ምትክ በመሆን ነው። የኃጢአታችንን ቅጣት ለመክፈል ወደ መስቀል ሄደ። መጀመሪያ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ፥ ለእስራኤል መንግሥትን ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔር የዓለምን መድረክ አዘጋጅቶ ነበር። እስራኤል እውነተኛ ንስሐ ብትገባና መሢሕዋን ብትቀበል ኑሮ፥ እግዚአብሔር ዕቅዱን ይተገብር ነበር። እስራኤል ግን መሢሕዋን አልተቀበለችም። ይህን እምቢታዋን መሢሑ ለዓለም ኃጢአት እንዲሞት በማድረግ ከቀድሞው ለሰፋ ዕቅዱ ማከናወኛነት ተጠቀመበት። ይሁን እንጂ፥ ይህ ሁሉ ነገር ከሮማውያን መንግሥት ጋር ምን ግንኙነት አለው?

ዳላስ ሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት ውስጥ በመምህርነት አገለግል በነበረ ጊዜ፥ ወደ ክፍል ከመግባቴ በፊት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ሁሉ በጥንቃቄ አዘጋጅ ነበር። አንዳንዴ ግን የማስተማር ዕቅዴ ይቋረጣል። ወደማስተምርበት ስፍራ ከመሄዴ በፊት ኃይለኛ በረዶ ይጥላል፥ መንገዴ በተሽከርካሪዎች ይጨናነቃል፥ እነዚህና ሌሎችም እክሎች የዕለቱን ፕሮግራሜን ለሚቀጥለው የትምህርት ክፍለ-ጊዜ እንዳስተላልፍ ያስገድዱኛል። ያ ክፍለ-ጊዜ ሲመጣ ግን ትምህርቴን የምቀጥለው ካቆምኩበት እንጂ ወደኋላ ተመልሼ አይደለም።

የታቀደ ነገር በጊዜው ካልተከናወነ፥ ለሌላ ጊዜ ይተላለፋል። ይህ ብዙ ጊዜ የሚሆን ነገር ነው። እግዚአብሔርም መንግሥቱን በምድር ላይ መመሥረትን በተመለከተ ያደረገው ይህንኑ ነው። ኢየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ምድር ይመጣል። ያኔ ነው በእግዚአብሔር ተስፋ የተገባው መንግሥት የሚመሠረተው። ኢየሱስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ የእስራኤልን ምድር የሚቆጣጠረው የአሕዛብ ኃይል፥ ጌታ መጀመሪያ በመጣ ጊዜ ምድሪቱን ይቆጣጠር የነበረው ያው ኃይል ይሆናል። የሮም መንግሥት እንደገና ይነሣል ማለት ነው።

አዲስ የሮማውያን መንግሥት እስራኤልን የሚቆጣጠራት መሆኑን እንዴት እናውቃለን? ሦስት ማረጋገጫዎች ቀጥሎ ካሉ መደ ምደሚያዎች ላይ እንድደርስ አድርገውኛል። ስለሚነሣው የሮማውያን መንግሥት፥ ዳንኤል ምዕራፍ 2 እና 7 ውስጥ የተናገረው ትንቢት፥ ክርስቶስ መጀመሪያ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ አላበቃም። ዳንኤል የገለጠው መንግሥት በዚህ ዘመን ያለውን የቤተ ክርስቲያን ጊዜ አይደለም። ምክንያቱም "መንግሥትም ግዛትም፥ ከሰማይም ሁሉ በታች ያሉ የመንግሥታት ታላቅነት ለልዑሉ ቅዱሳን ሕዝብ ይሰጣል" (7፡27) በተባለለት ዘመን አይደለም ያለነው። በዳንኤል የተነገረው መሢሐዊ መንግሥት ገና ወደፊት ነው የሚመጣው። ዳንኤል እንደሚለው ያ የእግዚአብሔር መንግሥት በሚመጣበት ጊዜ የምትደመሰሰው አገር ሮም ናት።

በመጨረሻው ዘመን አዲስ የሮም መንግሥት የሚነሣበት ሁለተኛ ምክንያት ዳንኤል 9 ውስጥ ይገኛል። ቀደም ሲል እንደተገለጠው፥ በዚህ ምዕራፍ ዳንኤል ለእስራኤል አስደናቂ የጊዜ ሰሌዳ ያቀርባል። በመጀመሪያ የተነበየው፥ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ኢየሩሳሌም እንደገና በመገንባቷና በመሢሑ መገለጥ መካከል ያለውን ጊዜ ነው። ይሁን እንጂ፥ በ483ቱ የመጀመሪያ የእስራኤል የትንቢት ዓመታት ታሪክና፥ በመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት ታሪኳ መካከል ክፍተትን ትቷል። ዳንኤል ምዕራፍ 9 ውስጥ በሚገለጠው የክፍተት ጊዜ ሦስት ሁነቶች ይከናወናሉ። መጀመሪያ መሢሑ ተገደለ። ይህ በኢየሱስ መሰቀል ተከናውኗል። ሁለተኛው የኢየሩሳሌም መፍረስ ነው። "የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ"። ቬስፓሲያን እና ቲቶ በተባሉ የጦር አለቆች የተመራው የሮማውያን ጦር በ70 እአአ ኢየሩሳሌምን አጥፍቷታል። ዳንኤል ከዚህ በኋላ የተነበየው፥ በአይሁዳውያን ላይ ስለሚመጣው የመከራ ጊዜ ነው። "እስከ መጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል፤ ጥፋትም ተቀጥሮአል"።

ዳንኤል በእግዚአብሔር ትንቢታዊ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ያለውን ክፍተት ካመለከተ በኋላ፥ የእግዚአብሔር ዕቅድ ቀዜማ የሚሆንበትን

ትክክለኛ ጊዜ ይገልጣል። እስራኤል የሚመሠረተውን መንግሥቷን የምትጠብቅባቸው የመጨረሻ ሰባት ዓመታት የሚጀምሩት፥ "እርሱም ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ 'ሱባዔ' ያደርጋል" (9፡27) በተባለበት ጊዜ ነው። የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት የሚጀምሩት አንድ ሰው ከእስራኤል መንግሥት ጋር አንድ ውል ሲያደርግ ነው። ይሁን እንጂ ዳንኤል "እርሱም" የሚለው ያ ሰው ማነው? ሰውዬው፥ ዳንኤል "የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ" በሚለው፥ ቀደም ባለው አንቀጽ ውስጥ የተጠቀሰው ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን የሚያጠፋው ነው። ዳንኤል 9፡27 ውስጥ "እርሱም" የተባለው ይህ ሰው ከእስራኤል ጋር ስምምነት የሚያደርገው የወደፊት መሪ ነው። ስለዚህ ሰው ዳንኤል የሰጠው ብቸኛ መለያ፥ ይህ መሪ በ70 እአአ ኢየሩሳሌምን ካጠፋው ሕዝብ ወገን መሆኑ ነው። ኢየሩሳሌም የጠፋችው በሮም መንግሥት ሠራዊት መሆኑን ስለምናውቅ፥ በመጀመሪያ እስራኤልን ከሌላ ኃይል የሚከላከላት፥ በኋላም የሚያሳድዳት የመጨረሻ ዘመን መሪ ማን መሆኑን የሚጠቁመን አንድ እርግጠኛ ፍንጭ አለ። ያ መሪ የሚመጣው ከሮማውያን መንግሥት ነው። ዳንኤል 9፡26-27 ውስጥ ያለው ገለጣ፥ ዳንኤል 2 እና 7 ውስጥ ካለው ጋር በትክክል ይስማማል።

አዲስ የሮማውያን መንግሥት መነሣቱን የሚያመለክተው ሦስተኛ ማስረጃችን የሚገኘው መጽሐፈ ራእይ ውስጥ ነው። ዮሐንስ የራእይን መጽሐፍ የጻፈው ከክርስቶስ ልደት በኋላ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ነበር። እግዚአብሔር ነው መጻፍ ያለበትን ነገር እንዲህ በማለት በአጭሩ ያዘዘው፦ "እንግዲህ ያየኸውን፥ አሁንም ያለውን፥ ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ" (ራእይ 1፡19)። ዮሐንስ በግርማ ስለታየው የእግዚአብሔር ልጅ፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተመለከተውን በዚሁ ምዕራፍ ቀደም ባለው ክፍል ገልጦታል። ምዕራፍ 2 እና 3 ውስጥ በጊዜው ለነበሩት ሰባት አብያተ ክርስቲያን የሚላኩ ሰባት ደብዳቤዎችን ነው የጻፈው። እነዚያ አብያተ ክርስቲያን ባለፉት 2,000 ዓመታት የነበሩ አብያተ ክርስቲያን የታዩባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ነበሩባቸው።

ከምዕራፍ 4 አንሥቶ ግን ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ በማለት አዲስ ክፍል ይጀምራል፦ "እንደመለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ" (ራእይ 4፡1)። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ከዚህ በኋላ ዮሐንስ ስለ ዘላለም መጻፍ እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ መጽሐፉ ውስጥ አይጠቀስም። በዚያ ፋንታ ዮሐንስ የሚጽፈው፦ "ከእስራኤል ልጆች ነገድ" ስለሚታተሙት ሰዎች (7፡4)፥ ኢየሩሳሌም ውስጥ ስለሚያገለግሉት "ሁለት ምስክሮች" (ራእይ 11)፥ "ፀሐይን ተጎናጽፋ

ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት ሴት" ስለተባለላት ሴት (12፡1)፥ (ይህ ዘፍጥረት ምዕራፍ 37 ውስጥ ስለ እስራኤል ሕዝብ የተወሳ ምስል ነው) ይሆናል። ከራእይ ምዕራፍ 4-19 ባለው ክፍል ዮሐንስ የሚሰጠው ገለጣ፥ በነቢዩ በዳንኤል ስለተገለጠው የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት ፍዳ ነው።

ራእይ 13 ውስጥ ዮሐንስ የሚገልጠው፥ ስለ መጨረሻው ዘመን ክፉ የምድር ገዥ ነው። "አውሬ ከባሕር ሲወጣ" (13፡1) ይለዋል። ዳንኤልም ገዢውን ምዕራፍ 7 ውስጥ የገለጠው ልክ እንዲሁ ነው። ዮሐንስ የገለጠውን ይህን የመጨረሻ ግዛት ስንመለከት፥ ትንቢቱ የሚያስረዳው፥ ዳንኤል በመጽሐፉ ምዕራፍ 7 ውስጥ በአራተኛይቱ አውሬ የመሰለው ግዛት መሆኑ ግልጥ ይሆንልናል። ዮሐንስ አውሬይቱን "አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሯት" (ራእይ 13፡1) በማለት የገለጠ ሲሆን፥ ዳንኤል የአውሬይቱን ቀንዶች ሲተረጉም ደግሞ፥ "አሥሩም ቀንዶች . . . አሥር ነገሥታት ናቸው" ብሏል (ዳን. 7፡7፥ 24)። ዮሐንስም ለተመለከታቸው አሥር ቀንዶች ራእይ 17 ውስጥ ይህንኑ የመሰለ ትርጉም ነው የሚሰጣቸው:- "ያየሃቸው አሥር ቀንዶች. . . አሥር ነገሥታት ናቸው" (17፡12)።

ዳንኤል የተመለከታት አራተኛ አውሬ የእስራኤልን ሕዝብ ለምን ያህል ጊዜ እንደምታሳድደው ሲገልጥ:- "ቅዱሳን. . . እስከ ዘመን እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም በእጁ ይሰጣሉ" ይላል። ይህ "አንድ ዓመት፥ ሁለት ዓመት እና መንፈቅ ወይም ግማሽ ዓመት" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ዳንኤል በራእዩ ያየው አራተኛ መንግሥት፥ እስራኤልን ለሦስት ዓመት ተኩል ያሳድዳታል። ይህ ጊዜ ዳንኤል 9፡27 ውስጥ "የሚመጣውም አለቃ" የተባለው ሰው እስራኤልን ከሚያሳድድበት የጊዜ ርዝመት ጋር አንድ ነው። ዮሐንስ የመጨረሻውን ዘመን ክፉ መንግሥት ሲገልጠው:- "በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው" (ራእይ 13፡5) ብሏል። አርባ ሁለት ወራት ሦስት ዓመት ተኩል ማለት ነው።

ዳንኤልና ዮሐንስ የሚገልጡት አንድ መንግሥት ነው። ከባሕር የሚወጣው ባለ አሥር ቀንድ አውሬ፥ የአሥር መንግሥታትን ኮንፌዴሬሽን የሚወክል መሆኑን ሁለቱም ይገልጣሉ። ይህ መንግሥት፥ እስራኤልን ለሦስት ዓመት ተኩል የሚያሳድዳት መሆኑን ሁለቱም ተንብየዋል። ዳንኤል ያየው አራተኛ መንግሥት፥ የሮም መንግሥት መሆኑን ቀደም ሲል ተረድተናል። ዮሐንስ የሚገልጠው ወደፊት የሚከናወኑ ነገሮችን ስለሆነ፥ የሮም መንግሥት፥ ዋነኛው ወታደራዊ ኃይል በመሆን በመጨረሻው ዘመን እንደገና በአካባቢው ብቅ የሚል መሆኑን ነበር የተነበየው።

## ኢ.ኢ.ሲ. ማለትም የአውሮፓ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ውስጥ ተጠቅሷል?

ኢ.ኢ.ሲ. በዳንኤል ራእይ የተገለጠው የአሥሩ መንግሥታት ኮንፌዴሬሽን ይሆን ይሆን? አሁን ባለበት ሁኔታው አይደለም። አሁን ኢ.ኢ.ሲ. የተባለውን ድርጅት የመሠረቱት 12 አገሮች ሲሆኑ፥ ሌሎች ብዙዎችም ለአባልነት አመልክተዋል። በመጨረሻው ዘመን አምባገነን ሰው የሚመራ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ተንብይዋል። ይህ መንግሥት የሚተባበሩትን አሥር አገሮች የሚያቅፍ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ እንዲህ ያለ ትብብር የለም።

ባለፉት አሥር ዓመታት አውሮፓ በአስደናቂ አኳኋን ተለውጣለች። የብረት መጋረጃ የተሰኘው ከለላ ተወግዷል። ሁለቱ ጀርመኖች ሲዋሀዱ፥ አንድ አገር የነበረችው ዩጎዝላቪያ ተከፋፍላለች። አህጉሪቱ በታላቅ ፖለቲካዊ ነውጥ ውስጥ ናት። በመሆኑም መጨረሻዋ ምን እንደሚሆን ከእግዚአብሔር በቀር የሚያውቅ የለም።

በመጨረሻው ዘመን አንድ ሚና ስለሚኖረው የአውሮፓ ኃይል እግዚአብሔር ሦስት ማረጋገጫዎችን ይሰጣል። አንደኛ፥ ያ መንግሥት በዓለም የበላይነት ያለው ወታደራዊ ኃይል ይሆናል። የቀረው የዓለም ሕዝብ የመጨረሻውን ዘመን ገዢ እና የእርሱ ግዛት የሆነውን የአውሮፓ መንግሥት ተመልክቶ "እርሱንስ ማን ሊወጋ ይችላል?" (ራእይ 13፡4) ይላል። በአሁኑ ጊዜ አሜሪካን ናት በምድር ላይ እንደ ዋና ወታደራዊ ኃይል የምትቆጠረው። የኋላ ኋላ ግን ስፍራዋን ለዚህ አውሮፓዊ ኃይል ትለቃለች።

ሁለተኛ፥ ይህ የአውሮፓ መንግሥት በወታደራዊ ኃይልና በኢኮኖሚ ብርቱ ቢሆንም፥ ኅብረቱ ግን ጠንካራ አይደለም። የመጨረሻው የአውሮፓ ኃይል ያኔም ቢሆን፥ ሁልጊዜ አውሮፓን ሲከፋፍላት በኖረው ብሔርተኝነት የተናጋ ይሆናል። የቋንቋ ልዩነት፥ የቆየው የፖለቲካ፥ የሃይማኖት እና በሕዝቦች መካከል የነበረ ጠላትነት መንግሥቱን ለመምራት አስቸጋሪ ነገሮች ይሆናሉ። የዚህ ግዙፍ ወታደራዊ ኃይል ደካማ ብልት፥ መለያየቱ ነው። ለዚህ ነው ዳንኤል ይህን የመጨረሻ መንግሥት የብረትና የሸክላ ቅልቅል የሚለው። እንደ ብረት የጠነከረ ወታደራዊ ኃይል ቢኖረውም፥ ዳንኤል ቀጥሎ እንደገለጠው፥ በሸክላ የተወከለው ብሔርተኝነት ያዳክመዋል። "ብረት ከሸክላው ጋር ተደባልቆ እንዳየህ እንዲሁ ከሰው ዘር ጋር ይደባለቃሉ፤ ነገር ግን ብረት ከሸክላ ጋር እንደማይጣበቅ እንዲሁ እርስ በርሳቸው አይጣበቁም" (ዳን. 2፡43)።

ሦስተኛ፥ ያ መንግሥት በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ የሚታመን በመሆኑ ይሰናከላል። የሚያንሠራራው የሮም መንግሥት፥ ባቢሎንን ማዕከሉ ባደረገና መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ በሚነግ ኃይል የበላይነት ሥር እንደሚሆን ሐዋርያው ጳውሎስ ገልጧል። ራእይ ምዕራፍ 17 ውስጥ ዮሐንስ ይህን መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚነግ ኃይል (በአመንዝራይቱ ሴት የተመሰለው)፥ ባንሰራራው የሮም መንግሥት (እንደ አውሬ የተገለጠው) ላይ እንደሚጋልብ በምሥል መልክ ያስገነዝባል። ራእይ ምዕራፍ 17 ውስጥ እንደተገለጠው፥ ባቢሎን በአውሬው፥ በራሶች እና ብዙ ውኃዎች ላይ ትቀመጣለች። በእነዚህ ነገሮች ላይ መቀመጧ፥ እነሱን መቆጣጠሯን የሚያመለክት መሆኑን ዮሐንስ ገልጧል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ሲታይ ባቢሎን ይህን የአውሮፓ መንግሥት ጨምሮ “በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ” ናት (17፡18)።

እንዴት ነው አውሮፓ ታላቅ ወታደራዊ ኃይል እያላት፥ ከመካከለኛው ምሥራቅ በሚነግ አንድ ሰው የምትመራው? ዮሐንስ ይህን የመጨረሻ ዘመን ኃያል ማንም በወታደራዊ ኃይል እንደማይረታው ቀደም ብሎ ስለገለጠ (13፡4)፥ ከባቢሎን የሚነግ መሪ አውሮፓን ድል ያደርጋታል ሊል አይችልም። ባቢሎን አውሮፓን የምትጋልብበትን ሁኔታም አልገለጠም። ሊሆን የሚችለው አንድ መንገድ፥ በነዳጅ ዘይት አማካይነት የሚመጣ የኢኮኖሚ ጫና ነው። መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ አንድ ሰው ወደ ምዕራቡ ዓለም የሚሄደውን የነዳጅ መጠን ቢወስነው፥ በዚህ የመጨረሻው አውሮፓዊ ኃይል ላይ ከባድ የቁጥጥር ተጽዕኖ ሊያደርግበት ይችላል።

የአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ ኮሚሽን ዛሬ በምናየው መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ውስጥ አልተጠቀሰም። የኮሚሽኑ ግቦች ግን፥ አውሮፓን ማዕከሉ የሚያደርገውን የመጨረሻ ዘመን ገዥ አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሰው ትንቢት ጋር ይገጣጠማል። የተባበረችው አውሮፓ፥ ማለት የዓለም ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ኃይል ድንገት ብቅ ይላል። የሚጎድለው ነገር፥ በዓለም ያሉትን የተለያዩ ቡድኖች ማዋሐድና አንድ የማድረጉ ብቃት ይሆናል። ያ ሰው በመምጣት ላይ ነው።

> ምዕራፍ አሥራ ሦስት <

# የሰላም ሰው/የሥልጣን ሰው

ሰነዱ ላይ ያረፉት ፊርማዎች የቼኮዝላቫኪያን ዕድል ዘጉት። ኔቪል ቻምበርሌይን የተባሉት የብሪታኒያ ጠቅላይ ሚኒስትር፥ ሂትለር ታላቂቱን ጀርመን ለመመሥረት ያለውን ፍላጎት ለማርካት ሲሉ፥ የቼኮዝላቫኪያን ብዙ መሬትና ከኢንዱስትሪዎቿ አብዛኛዎቹን በፊርማቸው በማረጋገጥ ሰጥተውት ነበር። እኚህ ሰው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ባደረጉት ንግግር የተፈራረሙት ውል፥ "ለጊዜያችን ሠላም" ያመጣል አሉ። ነገር ግን ከአሥራ አንድ ወራት በኋላ ሂትለር ውሉን በማፍረስ ፖላንድን ወረረ። በዚህ ሳቢያ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ስለተቀሰቀሰ፥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኀፍረት ሥልጣናቸውን ለቀቁ። "ማንኛውንም ዋጋ በመክፈል ሠላም" ለማምጣት ያደረጉት ጥረት አውሮፓን ጦርነት ውስጥ ዘፈቃት።

ዛሬ ሠላም የማይኖረን ለምንድነው?

ዓለም ሠላምን ትናፍቃለች፥ እኛም ያንኑ ጦርነትና ብጥብጥን የምንደጋግም እንመስላለን። ለምንድነው ዓለም እፎይ የማትለው? የጦርነት ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም፥ ዛሬ ላሉት ችግሮች አምስት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። መጀመሪያ የምጣኔ ሀብት አለመመጣጠን፥ በደሀና በሀብታም መንግሥታት መካከል ግጭትን ያመጣሉ። ለምጣኔ ሀብት አስቸጋሪ የሆኑ ወቅቶች በሀብታም አገሮች መካከል እንኳን ሳይቀር ዓለም አቀፋዊ ግጭት ይፈጥራሉ። አሜሪካን ከ1991-1992 እአአ የነበረው የምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆል ከፕሬዚዳንታዊው ምርጫ ጋር ተዳምሮ ብዙ ተጽዕኖ በማስከተሉ፥ "አሜሪካን ትቅደም" የሚል የንግድ ፖሊሲ እንድትነድፍ አስገደዳት። ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ችግሮች ፈረንሳይ፥ ጀርመን፥ ታላቋ ብሪታኒያና በሌሎች የብድር ጫናና የኑሮ ማሽቆልቆል በገጠማቸው አገሮች ውስጥ ብጥብጥን አስነሥተዋል።

ለብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ግጭት ሁለተኛው ምክንያት፥ ማኅበራዊ፥ ባሕላዊ ወይም የዘረኝነት አለመቻቻል ነው። ከባቢሎን ግንብ ወዲህ የሰው ልጅ በተለያዩ ብሔረሰቦች ተከፋፍሏል። እነዚህ የተለያዩ ብሔረሰቦች "የተለዩ" በመሆን ጠባብነትን፥ ወገናዊነትንና ጥላቻን ለሚያሳዩዋቸው አጸፋውን መልሰውላቸዋል። አሜሪካን እንኳን በዚህ ችግር ተወጥራለች። በብሔረሰቦችና ዘሮች መካከል ያለው ፍርሃትና አለመተማመን በሚያሳስብ ሁኔታ በማደግ ላይ ነው።

ለዓለም አቀፋዊ ብጥብጥ ሦስተኛው ምክንያት፥ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ጥላቻ ነው። በሁለቱ ክፍሎች መካከል ያለው ችግር በሃይማኖት

ሥር የሰደደ ባይሆን ኑሮ፥ በዓረቦችና በእስራኤላውያን መካከል ያለው ግጭት ገና ድሮ መፍትሔ ያገኝ ነበር። ኢየሩሳሌም ለሁለቱም ወገኖች የተቀደሰች ከተማ ናት። በመሆኑም የትኛውም ወገን ቢሆን ቅድስቲቱን ከተማ የራሱ እንዲያደርግ በማይፈቅድ ሰላም አይስማማም። ሰሜን አየርላንድ፥ ሕንድ፥ ሱዳን፥ ዩጎዝላቪያ ወይም አርሜኒያና አዘርባጃን ውስጥ ያሉት ግጭቶች መሠረታቸው የሃይማኖት ልዩነት ነው።

በዓለም ላለው ግጭት አራተኛው ምክንያት፥ የመንፈሳዊነትና ሥነ-ምግባር ፋይዳዎች (Values) መዝቀጥ ነው። በአደንዛዥ ዕፅ እና በመጠጥ ሳቢያ የሚደርሰው ጥፋት፥ ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፥ በቴሌቪዥንና በሲኒማ የሚታየው የጥፋት ፊልም፥ በጋራ አንድ ነገር አላቸው። ይኸውም የተለመደውን ትክክለኛና ስሕተትን የመለያ መስፈርት መጣሳቸው ነው። ይሁን እንጂ፥ ከማንኛውም የሥነ-ምግባር ክልል ለመውጣት የሚጠየቅ ፍጹም ነጻነት፥ ኃጢአት ከሚያስከትለው ጣጣ ሰውን ነጻ አያደርገውም። በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች አስደናቂ እድገት፥ የኤይድስ መስፋፋት፥ የፈረሱ ትዳሮች፥ የግብረ-ሥጋ ወንጀል እና ሰው መግደል፥ የምናደርገው ነገር በሚያስከትለው ውጤት መሠረት በማንኛውም ሁኔታ ከቅጣት የማናመልጥ መሆናችንን በአስደናቂ ሁኔታ ያስገነዝቡናል።

ለብሔራዊና ዓለም አቀፋዊው ግጭት አምስተኛው ምክንያት፥ የብርቱ መሪዎች መታጣት ነው። በባሕረ-ሰላጤው ጦርነት የመሪነት ችሎታ በስተቀር የተቀረው ዓለም የመሪነት ብቃት እያሽቆለቆለ መምጣቱን ያመለክታል። ዛሬ መሪዎች ለሕይወት ችግሮች መፍትሔ እናመጣለን ብለው ተስፋ ይሰጡ ይሆናል። ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ግን፥ የሕዝቡ አስተያየት የሚነፍስበትን አቅጣጫ ለመረዳት የሕዝብ አስተያየት በማንበብ ነው። ዓለም፥ ሚካኤል ጎርባቾቭን አድንቋቸዋል፤ የአብዛኛው ሩሲያዊ ችግር ግን፥ ከእርሳቸው የፖለቲካ መርህ፥ ማለት ፔሬስትሮይካ ይልቅ ዳቦ ነበር። ጎርባቾቭ ከሥልጣን መወገድ ነበረባቸው። ዓለም ለግል ጥቅም የሠሩትን መሪዎች ከሸለመችና ትክክለኛውን ነገር በማድረጋቸው ደግሞ ከቀጣቻቸው፥ በደካማ መሪዎች ሳቢያ የተረገመች ትሆናለች።

ዓለም አሁን የምትፈልገው ነገር

የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት እንዳበቃ፥ ዓለም ፕሬዚዳንት ቡሽ የነደፉትን አዲስ የዓለም ሥርዓት ዕቅድ የጨበጠች መስላ ነበር። ቡሽ በዓይነ ሕሊና የታያቸው፥ ሕዝቦች በመካከላቸው የሚፈጠሩ ችግሮችን ያለ ጦርነትና ደም መፋሰስ የሚፈቱበት ጊዜ ይመጣል የሚል ነበር። ይህ ጊዜ መንግሥታት ለሁሉም ጥቅም በጋራ የሚሠሩበት ወቅት ይሆናል ተብሎ

ነበር። እነዚህ ታላቅና ከፍተኛ ዓላማዎች ቢሆኑም፥ በዓለም ምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆል፥ እንዲሁም እያደገ በመጣው ብሔርተኝነትና ጥቅምን የመከላከል አዝማሚያ ሟሸሹ። ድንበርና ጦርነት አልባ የሆነ ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰብ በመመሥረቱ ጉዳይ ሁሉም ተስማምቷል። ነገር ግን ክሮሾችና ሰርቦች፥ አርሜኒያውያንና አዘርባጃውያን፥ የአየርላንድ ፕሮቴስታንቶችና ካቶሊኮች፥ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ብሔረሰቦችና የሃይማኖት ክፍሎች ዓለም አቀፋዊውን ጥቅም እራሳቸውን ከመጠበቅ ሊያስቀድሙ አልፈለጉም።

ለዚህ ዓለም ሠላም ለማምጣት የሚያስፈልገው ምንድነው? ችግሮቹ ለአካባቢው ሠላምና መረጋጋት ለማምጣት ስንል የዘረጋናቸው ሥርዓቶች ሁሉ የማይችሏቸውና እጅግ የገዘፉ ናቸው? ከኀምሳ ሦስት አገሮች የተውጣጣውና የተለያዩ ባሕሎችን፥ አይዲዮሎጂዎችንና ሞያዎችን የሚወክል አንድ ቡድን ተመሥርቶ ነበር። ቡድኑ የሮም ክለብ የሚባል ሲሆን፥ ዓለማችን በገጠሟት ችግሮች ላይ ለመወያየት ተሰበሰበ። ቡድኑ ያወጣውና ቀጥሎ የሰፈረው የጊዜው የዓለማችን ችግሮች የማጠቃለያ ትንታኔ፥ የማስጠንቀቂያ ድምፀት አለው:-

"የሰው ልጅ በታሪኩ ውስጥ ፈጽሞ እንዲህ ያሉ አስፈሪ ነገሮችና አደጋዎች አልገጠሙትም። ሰው ሳይዘጋጅ ጊዜና ርቀት ወደተወገደበት ምድር ተገፍቶ፥ ባልተገናኙ ነገሮች ሳቢያ በተነሣው ዓውሎ ንፋስ ውስጥ ገብቷል። የዓውሎ ንፋሱ ምክንያትና ውጤቱ ሊወጡት የማይቻል ግራ መጋባት ውስጥ የሚከት ነው።"

## ለችግሩ መፍትሔ ልናገኝለት እንችላለን?

ዓለም፥ ምግባረ ብልሹነት አረንቋ ውስጥ በመዝቀጥ ላይ ሳለች፥ ከባቢያዊ ጥፋት፥ የዘረኝነት ውጥረት እና ብርቱ የዓለም መሪ የመመኘቱ ጉዳይ እያደገ ይመጣል። ብዙ አምባገነን መሪዎች የተነሡት፥ ሠላምና መረጋጋት በጠፋበት ጊዜ መሆኑን ታሪክ ያረጋግጣል። ናፖሊዮን የፈረንሳይን በትረ መንግሥት የጨበጠው፥ በፈረንሳይ አብዮት መክሸፍ ምክንያት በተፈጠረው ግራ መጋባት ጊዜ ነው።

ጀርመን በታላቅ የምጣኔ ሀብት ውድቀትና ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በጠላቶቿ ከደረሰባት ውርደት ያድነኛል ብላ ነበር ሂትለርን ወደ ሥልጣን ማማ ያወጣችው። ሌኒንና ስታሊን እንደ ብረት በጠነከረ ክንዳቸው ሩሲያን ለመያዝ የቻሉት፥ የተጨቆኑ ሕዝቦችን ተስፋ መቁረጥ ለራሳቸው መጠቀሚያ በማድረግና የምጣኔ ሀብት መረጋጋትና ዋስትና እንደሚያሰፍኑ ተስፋ በመስጠት ነበር። የምጣኔ ሀብት ችግሮችና የፖለቲካ

ብጥብጦች፥ ተከታዮቻቸውን የሚያሳምኑና አገራቸውን ከመፈራረስ እናድናለን የሚሉ መሪዎችን ያበቅላሉ።

እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ለዓለም ባለው ዕቅድ ትልቅ ሚና ስለሚጫወተው ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጣል። ያ ሰው "የሚመጣውም አለቃ" (ዳን. 9፡26-27)፥ "የዓመፅ ሰው" (2ኛ ተሰ. 2፡3)፥ "የክርስቶስ ተቃዋሚ" (1ኛ ዮሐ. 2፡18)፥ "ዘንዶውም" (ራእይ 13፡2) የሚሉትን ጨምሮ፥ በብዙ ስሞች የሚጠራ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ዓለምን እንደ ማዕበል የሚያጥለቀልቃትንና በመጨረሻ በእግዚአብሔር ላይ የሚነሣውን ዓመፅ የሚመራውን የዚህን ሰው ምስል ውስብስብ አድርጎ ነው የሚገልጠው።

## ታይም የተባለው እውቅ መጽሔት፥ "የዓመቱ ሰው" ብሎ የሚመርጠው ግለሰብ

መጽሔቱ የዓመቱ ሰው ብሎ ለሚመርጠው ሰው መለያ የሚያወጣው መስፈርት ፍጹም ተስማሚ ይመስላል። ለታላቅነት የሚታጭ መሪ ካለ፥ ያ ሰው ለምርጫው የተገባ ይሆናል። ይህ ሰው መጀመሪያ በሕዝብ ዘንድ እውቅና የሚያገኘው፥ አውሮፓን ለማዋሀድና ለማረጋጋት ጥረት በሚጀምርበት ጊዜ ይሆናል። ኢ.ኢ.ሲ.ንና ኔቶ የተባሉት የጦር ባለ ቃል ኪዳን አገሮች ድርጅቶችን የሚተካው፥ የእርሱ የአውሮፓ ኮንፌዴሬሽን ታላቅ የፖለቲካ ክንውን ይሆናል። የአሜሪካን ምጣኔ ሀብት በፍጥነት በሚወድቅበት ጊዜ፥ ዓለምን የመምራቱን ስፍራ የሚወስደው ይህ የአውሮፓ ኮንፌዴሬሽን ይሆናል።

አስቸጋሪ ጊዜዎች ብርቱ መሪ ይሻሉ፤ በዚሁ መሠረት ብጥብጥን አስወግዶ ሥርዓት ለማስፈን ብርቱ መሪ ያስፈልጋል። ይህ መሪ ስለ ኢኮኖሚያዊ ኅብረት የሚያቀርበውን አሳብ በመጀመሪያ ብዙ አገሮችና ቡድኖች ይቃወሙ ነበር። አንዳንዶች እንደውም ይህን አንድነት በወታደራዊ ኃይል ጭምር ለመቃወም ያስፈራራሉ፤ በኋላ ግን ሳይወዱ ይስማማሉ። ሦስት መንግሥታት ግን ግዴታውን ላለመቀበል ስለሚወስኑ፥ በተባበረው የኔቶ ወታደራዊ ኃይል ይመታሉ።

ታይም የተባለው መጽሔት ይህን ሰው የዓመቱ ሰው ብሎ የሚመርጠው፥ አውሮፓን አንድ ስለሚያደርግ ብቻ አይደለም። መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ሠላምን ለማስፈን፥ እንዲሁም እስራኤልና ጎረቤቶቿ የሆኑት ዓረቦች ችግራቸውን በሠላም ይፈቱ ዘንድ ለመጫን የሚያደርገው ጥረት፥ ሊፈጠር የሚችለውን አስከፊ ችግር ያስወግዳል። እግዚአብሔር በእርሱ ደስ የሚሰኝ ይመስል የሚያደርገው ነገር ሁሉ

ይከናወንለታል።

ሰውዬው የዓመቱ ሰው ተብሎ በታይም መጽሔት ሲመረጥ በእርግጥ የሚገባው ይሆናል። ትናንሽ ጌቶችና እርስ በእርሳቸው የሚዋጉ ፖለቲከኞች መርገም ባለባት ዓለም ላይ ይህ መሪ በግርማና በክብር ብቅ ይላል። የሚያስበው ለመላው ዓለም ሲሆን፥ ውሳኔዎቹም ስልታዊ ይሆናሉ። በኃይሉና በማሳመን ጥበቡ ዓለም ሁሉ ይደነቃል። ታዲያ ይህ ታላቅ መሪ ማን ይሆን?

ታይም የተሰኘው እውቅ መጽሔት ይህን ሰው የዓመቱ ሰው ብሎ ገና በስሙ አልገለጠውም። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን ከ2,000 ዓመታት በፊት "የዓመፅ ሰው" በማለት ገልጦታል። ዛሬ ብዙ ሰዎች "የክርስቶስ ተቃዋሚ" እያሉ ይጠሩት ይሆናል። የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዘመን ዕቅድ ቀርቦ ከሆነ፥ ይህ ሰው በአሁኑ ጊዜ በሕይወት ያለ ባለሥልጣን ይሆን ይሆናል። ከእስራኤል መንግሥት ጋር የሰባት ዓመቱን ውል እስኪፈራረም ድረስ ትክክለኛ ማንነቱ አይገለጥም። ነገር ግን ምንም እንኳን የሰውዬውን ሰብዓዊ ማንነት ባናውቅ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ባሕርይውንና ምግባሩን በተመለከተ ብዙ የሚለው አለ። እስቲ እግዚአብሔር ይህን የመጨረሻ ዘመን አምባገነን እንዴት እንደሚገልጠው በአጭሩ እንመልከት።

## የኖቤል የሠላም ተሸላሚ ይሆናል?

እንደተጋባዥ ተናጋሪና ደራሲነቴ ብዙ ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ እየተዘዋወርኩ ንግግር እንዳደርግ እጋበዛለሁ። በዚህ ጉዞዬ፥ በፊት ያላየኋቸው ሰዎች፥ "በጣም ወጣት ነህ፤ በዕድሜህ ጠና ያለ ሰው አድርጌ ነበር የምገምትህ" እንደሚሉኝ እጠብቅ ነበር። ቀድሞ ያላዩኝ ሰዎች እንደሚገምቱት ሸበቶ ምሁር አይደለሁም። በግምታችን ከነበረው ለየት ያለ ሰው ስናይ ሁላችንም እንደነቃለን። ወደፊት የሚመጣውን የክርስቶስ ተቃዋሚ በተመለከተም ይህ ሁኔታ ይገጥመን ይሆናል።

በመጨረሻው ዘመን የሚነሣው አምባገነን መሪ ምን ይመስላል ብለው ይገምታሉ? አንዳንዶች ሥጋ የለበሰ ሰይጣን፥ ማለት ክፉ ስብእናው ቀንድና ጅራት ያበቀለ ነው ይላሉ። ሌሎቹ እንደ ዘመናዊ አዶልፍ ሂትለር፤ የሚቃወሙትን ሁሉ የሚደመስስና የሚያጠፋ፥ እንዲሁም አክራሪ ሰይጣናዊ እምነት ያለው እንደሚሆን ይገምታሉ። የቀሩት ደግሞ ክፉ ተናጋሪ፥ ራሱን እጅግ የሚወድ፥ ያለኀፍረት ራሱን የሚያሞግስ፥ በጣም አሳሳችና ድል የሚሳካለት ይሆናል ይላሉ። በሰባተኛው ዓመት መጨረሻ ገደማ እነዚህ ባሕርያት ሁሉ ይገለጣሉ። ነገር ግን ከእነዚህ ግምቶች የትኛውም ቢሆን፥ ዓለም የክርስቶስን ተቃዋሚ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያይ የሚኖረውን ግንዛቤ አያመለክቱም።

ሰይጣን የጭለማው ዓለም ገዥ ነው ቢባልም፥ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን እንዲህ በማለት አስጠንቅቋቸዋል፦ “ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣል” (2ኛ ቆሮ. 11፡14)። ይህን መለየት የሚሳናቸው ሰዎች በሰይጣን ውጫዊ ገጽታ ይታለላሉ። ነገሩ ሁሉ ካለፈባቸው በኋላ ነው “አንተ ለካ ሰይጣን ነህ! እኔ የጠበቅኩህ በሌላ ገጽታና ባሕርይ ትመጣለህ ብዬ ነበር” የሚሉት። ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ፥ በሰይጣን የሚረዳና የሚመራ ይሆናል። ሰይጣን ለዚህ የጥፋት መልእክተኛው ተስማሚ ማስመሰያ ይሰጠዋል። ምን ይሆን የክርስቶስ ተቃዋሚ የመጀመሪያ ማስመሰያ?

ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ በግልጥ የሚለይበት ፍንጭ ዳንኤል መጽሐፍ ምዕራፍ 9 ውስጥ ተጠቅሷል። “ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባዔ ያደርጋል” (9፡27)፤ የተባለው እስኪፈጸም ድረስ፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ ማንነትን ዓለም አያውቅም። ሰውዬው ለሠላም በሚሠራበት ወቅት ነው ዓለም ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚ ጥቂት ፍንጭ የሚያገኘው። እንዲህ ያለውን ስምምነት ያደርግ ዘንድ ያለ ምንም ጥርጥር ቀደም ብሎ ሥልጣን ኮርቻ ላይ መውጣት አለበት። ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለም በግልጥ የሚታወቅበት ጊዜም ይህ ነው።

የክርስቶስ ተቃዋሚ ከእስራኤል ጋር የሚፈራረመው ይህ “ቃል ኪዳን” ምንድነው? ቃል ኪዳኑን ዳንኤል ባይገልጠውም፤ ለሰባት ዓመት የሚቆይ መሆኑን ግን አመልክቷል። በዚህ የሠላም ጊዜ አጋማሽ ላይ እስራኤል ሠላምና ዋስትና ያገኘች ይመስላታል። ስለዚህ፥ ቃል ኪዳኑ ለእስራኤል ብሔራዊ ጸጥታ ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት። ቃል ኪዳኑ፥ እስራኤል ጎረቤቶቿ ከሆኑት ዓረቦች ጋር በሠላም እንድትኖር የሚያደርጋት ይመስላል። የቃል ኪዳኑ አንድ ውጤት፥ እስራኤል ቤተ መቅደሷን ኢየሩሳሌም ውስጥ እንድትሠራ የሚፈቀድላት መሆኑ ነው። የቀድሞ የአሜሪካን ታላላቅ ባለሥልጣናት፥ ማለት ኪሲንጀር፥ ካርተር፥ ሬጋን፥ ቡሽ እና ሌሎችም የዓለም መሪዎች የተሳናቸውን፥ ይህ የዓለም መሪ ያከናውናል። የሠላም ሰው በመባልም ይታወቃል!

ዓለምን ለብዙ ሥቃይና ጥፋት የሚዳርጋት ይህ ሰው፥ የዓለም የሠላም መሪ መምሰሉ ምንኛ ምጸት ነው? በዓለም እጅግ አስቸጋሪ የሆነውን ጠብ በሠላም በመፍታቱ፥ ለኖቤል የሠላም ሽልማት ይታጫል። ዓለም ፍጹም አምባገነን መሪ በምትጠብቅበት ጊዜ ነው ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ የሠላም ተስፋ የሚሰጥና ታማኝ መሪ ሆኖ ብቅ የሚለው።

የፖለቲካ ስልት ጠቢብ ይሆናል

የክርስቶስ ተቃዋሚ ብቅ የሚለው የሠላም ምልክት የሆነውን የወይራ ቅጠል ይዞ ነው። በሠላም ቅጠሉ ውስጥ ግን ሰይፍ ተሸሽጓል። በሌሎች አገሮች ላይ የሚቀዳጀው ድል፥ ከእስራኤል ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን በአጭር ጊዜ ውስጥ ይሽፍነዋል። ዳንኤል መጽሐፍ ምዕራፍ 11 ውስጥ ነቢዩ የክርስቶስ ተቃዋሚን ድብቅ ዓላማ ለማስገንዘብ ሲል የተሸፈነውን ማስመሰያ ቀዷል። ያ ሰው የሚሠራቸው ነገሮች ሁሉ የሚመነጩት ከትዕቢቱና ለሥልጣን ካለው ጥም ነው። መጀመሪያ ትሁት ቢመስልም፥ የድርጊቶቹ ሁሉ የመጨረሻ ዓላማ ግን ራሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ነው። "የአባቶቹንም አማልክት፥ የሴቶቹንም ምኞት (በሴቶች የሚመለክ አምላክ) አይመለከትም፤ ራሱንም ከሁሉ በላይ ታላቅ ያደርጋልና" (11፡37)። የክርስቶስ ተቃዋሚ "እኔ" የሚል ስሜት የተጠናወተው ትውልድ ውጤት ይሆናል።

ትዕቢቱ የሚመሳሰለው፥ ለፍጹም ሥልጣን ካለው ፍላጎት ጋር ነው። ማናቸውንም አማልክት ከማምለክ ይልቅ "የአምባዎቹን አምላክ ያከብራል፤ አባቶቹም ያላወቁትን አምላክ በወርቅና በብር በዕንቁና በከበረ ነገር ያከብራል" (11፡38)። ገንዘቡን ለጦር መሣሪያ መግዣ ያውላል። ብርታቱ በእግዚአብሔር ላይ ባለው እምነት ሳይሆን፥ በጦር ኃይሉ ነው።

የዚህ ሰው እምነት በቦምቦችና በጥይቶች ላይ እንደሚሆን በዓለም የሚከናወኑ ነገሮች ወደፊት ይጠቁማሉ። በሰባቱ ዓመታት ውስጥ የክርስቶስ ተቃዋሚ በሚሆነው ሰው ላይ በተከታታይ የሚነሡ ተቃውሞዎችን ዳንኤል ገልጧል። ይሁን እንጂ፥ እነዚህ ኅብረት የሚፈጥሩ ሌሎች ወገኖች የመጨረሻውን ዘመን መሪ በብርታት አይተካከሉትም። ይህንኑም ዳንኤል እንዲህ በማለት ገልጦታል፦ "ወደ ብዙ አገሮችም ይገባል፥ ይጎርፍማል፥ ያልፍማል። ወደ መልካሚቱም ምድር (ዳንኤል ለእስራኤል የሰጣት ስም) ይገባል። ብዙ አገሮችም ይወድቃሉ . . .። እጁን በአገሮች ላይ ይዘረጋል" (11፡40-42)።

የክርስቶስ ተቃዋሚ በወታደራዊ ኃይልና ገናናነት የሚታመን እንደሚሆን ሐዋርያው ዮሐንስም ገልጧል። የሰባት ዓመቱን የፍዳ ዘመን የሚጀምሩ ሁኔታዎችንም ምዕራፍ ስድስት ውስጥ አስገንዝቧል። ያ ዘመን የሚጀምረው፥ ዓለምን ድል የማድረግ ዓላማ ባለው ጋላቢ እንደሚሆን ዮሐንስ ሲገልጥ እንዲህ ብሏል፦ "አየሁም፥ እነሆም አምባላይ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ቀስት ነበረው፥ አክሊልም ተሰጠው፤ ድልም እየነሣ ወጣ፥ ድል ለመንሣት" (ራእይ 6፡2)። ጋላቢው የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። ዓለምን የመግዛት ፕሮግራሙ የሚጀምረውም በፍዳው

ዘመን መግቢያ ላይ ነው። የሠላም ሰው መስሎ ነው ብቅ የሚለው፤ ፍላጎቱ ግን ዓለምን መግዛት ይሆናል።

## ሰይጣናዊ አስመሳይነት

አንድ ሌላ ነገር ካላጤንን በስተቀር፥ ስለክርስቶስ ተቃዋሚ የምናቀርበው ትንታኔ የተሟላ አይሆንም። ይህ ሰው የሚመጣው፥ የሠላም ሰው መስሎና በትዕቢት፥ እንዲሁም በሥልጣን ጥማት ተነሣስቶ ሊሆን ይችላል። የሚያገኘው ድል ሁሉ የሚከናወንለት፥ በአብዛኛው ከጀርባው ባሉት መናፍስት አሠራር ነው። በመጨረሻም ሰይጣን እንደፈለገው የሚያደርገው ይሆናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ተቃዋሚን ሰግጣጭ ገጽታ እንደሚከተለው ገልጦታል፦ "ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉ በምልክቶች፥ በሐሰተኞች ድንቆችም፥ በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደሰይጣን አሠራር ነው" (2ኛ ተሰ. 2፥9-10)። የክርስቶስ ተቃዋሚ መገለጥ በክርስቶስም ሆነ በሐዋርያት ዘመን ባልታየ ተአምራት የታጀበ ይሆናል።

የሰይጣን ኃይል ውሱን ነው። ሁሉን የሚያውቅ ወይም በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ለመገኘት የሚችልና ሙሉ ኃይል ያለው አይደለም። ቢሆንም፥ ሙታን ከሆኑ ፍጡራን እጅግ የላቀ ኃይል ይኖረዋል። ሰይጣን የክርስቶስን ተቃዋሚ ተዓማኒነት ከፍ ለማድረግ ሲል፥ ተአምር የሚመስል ኃይልን በመስጠት ይተጋል። ይህ የመጨረሻው ዘመን ኃያል ሰው፥ "ሰዎች ካላቸው ብርታት እጅግ የላቀ ኃይል" ያለው ይመስላል።

የክርስቶስ ተቃዋሚ ሆኖ የሚነሣውን ሰው ተዓማኒ ለማድረግ በምን ዓይነት ተአምራት ነው ሰይጣን የሚጠቀመው? ይህን ጉዳይ ጳውሎስ በግልጥ አይናገረው እንጂ፥ ተአምራቱ ብዙና የተለያዩ እንደሚሆኑ ጠቁሟል። የክርስቶስ ተቃዋሚ የክርስቶስን ሰብእናና አገልግሎት ለማስመሰል በሚያደርገው ጥረት፥ አንዳንድ ተአምራቱ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ካደረጋቸው ተአምራት ጋር በቅርብ የሚመሳሰሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ዓለማችን የእግዚአብሔር ቃልን እውነት ትቶታል። የምንኖረው መንፈሳዊ ባዶነት በሰፈነበትና "የማየውና በሕይወቴ የሚያጋጥመኝ ነገር ከሆነ አምናለሁ" በሚል ማኅበረሰብ ውስጥ ነው። ያም ሆኖ ማኅበረሰቡ ወይም ዓለም ያን መንፈሳዊ ባዶነት የሚሞላለት አንድ ነገር ወይም ሰው ይፈልጋል። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርገው የሚቻለው ነገር ነው። ሰዎች እውነትን ባለመቀበላቸው፥ በውሸት ለተሸፈነ የሰው ልምምድ

ወይም የኑሮ ዘይቤ ትምህርት የተጋለጡ ናቸው። የአጋንንትን በመንፈስ መኖር ስላልተቀበሉ የዚህ ዓለም ገዢ የሆነው ሰይጣን በሚሠራቸው "ተአምራት" ይደነቃሉ። ተአምራቱም የሚታዩ ይሆናሉ፤ የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚሆነው ሰው ኃይል ምንጭ ግን ስውር ይሆናል።

በመጨረሻ ሠላም?

ዓለም ከእግዚአብሔር ያልሆነ ሠላም በጽኑ በመፈለግ ላይ ናት። ሰዎች፥ ኃላፊነትን ሳይሆን ጥቅሞችን ብቻ የምንሻ ፍጡራን ነን። ኃጢአታችንን እንድናምን ሳይጠይቀን ተስፋ የሚሰጠንን መሪ እንጠብቃለን። የአኗኗር ዘይቤያችንን የማይነካ፥ ግን ፍላጎታችንን የሚያረካ አዲስ የዓለም ሥርዓት እንፈልጋለን። በአጭሩ፥ የምንሻውም፥ ሥጋዊ የሆነና እግዚአብሔር የሌለበትን የሺህ ዓመት መንግሥት የሚመሠርትልንን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው።

ይህን መሰሉ መሪ በመምጣት ላይ ሊሆን ይችላል። አንድ ቀን ለዓለም ጸሎት መልስ ይሆንና፥ በደዌ ለተጎሳቆለችው ዓለም ሠላምና ብልጥግና ሊያመጣ ብቅ ይላል። በእርግጥ የማይቻል ነገር እንደሚያደርግ ከቃሉ ይልቅ ድርጊቶቹ ይገልጣሉ። "በዓይኖቼ ባላይ ኑሮ አላምንም ነበር" የሚለው ቃል በዓለም ሁሉ ያሉ ተከታዮቹ እንደ ጸሎት የሚደግሙት ይሆናል። በጦርነት ለተጎሳቆለችው ዓለምም ሠላምን በኃይል ያሰፍናል።

ሰዎች የዚህን ሐሰተኛ የዓለም መሪ ሌሎች ድርጊቶች ማየቱ እስኪሳናቸው ድረስ፥ በተአምራቱ አድናቆት ይደነዝዛሉ። የሚያመጣው የዓለም ሠላም እጅግ በናረ የመከላከያ ወጪ ልዋጭ የሚገኝ ይሆናል። ከሁሉ የሚያስቀድመው ወታደራዊ ኃይሉን ነው። ከሐር የተሠራ ጓንት ያጠለቀ ይመስል ይሆናል፤ ጓንቱ የሸፈነው ግን ተቃዋሚዎቹን ሁሉ የሚያደቅ የብረት መዳፍን ነው። የዓለም ሕዝቦች አጠቃላይ ሁኔታውን ከተገነዘቡ በኋላ ከድንዛዜያቸው ይነቁ ይሆናል፤ ያ ግን ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ እንደሚባለው ይሆናል። ሕዝቦች አለማክበሩ የሚያስከትለውን ስለሚያውቁ፥ ያን ክፉ የዓለም መሪ ያከብሩታል፦ "አውሬውን ማን ይመስለዋል፥ እርሱንስ ማን ሊዋጋ ይችላል?" (ራእይ 13፡4)። በመጨረሻም "የሠላሙ ሰው"፥ "የዓመፅ ሰው" ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ በጊዜው በሕይወት ለሚኖሩ ብዙ ሰዎች ይህ ግንዛቤ በጣም የዘገየና ፋይዳ የለሽ ይሆንባቸዋል።

> ምዕራፍ አሥራ አራት <

# የአውሬው ውበት

በ1960ዎቹ ዓመታት ለአሜሪካን ሕፃናት የሚነገር አንድ ተረት ነበር። ተረቱ የሚገልጠው፥ ስለ አንድ በድንገት ባለጠጋ ስለሆነ ቤተሰብ ነው። የሀብቱ ምንጭ ቤተሰቡ በአጋጣሚ ያገኘው ነዳጅ ዘይት ነበር። የዓለም የነዳጅ ፍላጎት መናጢ ቤተሰቦችን በድንገት ባለጠጋዎች የማድረግ ኃይል አለው።

ከላይ የተጠቀሰው ተረት እውነትነት የሌለው ይሆን ይሆናል፤ ነገር ግን ባለፈው ክፍለ ዘመን የነበረውን የፐርሺያ ባሕረ-ሰላጤ አካባቢ ምስል በትክክል ያንጸባርቃል። የነዳጅ ዘይት በአካባቢው መገኘት፥ በዘላንነት ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን ወደ ብልጥግና ሲያሸጋግር፥ የመካከለኛው ምሥራቅን ገጽታም ለውጦታል። በ1900 እእአ አብዱል አዚዝ ኢብን ሳውድ የተባለ ሰው፥ እዚያው ዓረብ ባሕረ-ሰላጤ ውስጥ ዋሕቢ የተባለ ጎሣውን በመምራት ሌሎቹን ጎሣዎች ተዋግቶ ድል አደረጋቸው። በ1926 ዓ.ም እራሱን ንጉሥ ብሎ ሰየመና በ1932 እእአ ደግሞ ግዛቱን ሳውዲት ዓረብ ብሎ ጠራት። በጊዜው ከዚህ ሰው ግዛት አብዛኛው አሸዋማና ድንጋይማ ነበር። በየትኛውም የመንግሥታት ስብሰባ ላይ ሳውዲት ዓረቢያ እንዲህ የበለጠገች አገር ትሆናለች ብሎ ድምፅ የሚሰጥ ሰው አይኖርም ነበር።

በ1935 እእአ ግን ለአል ሳውዲ ቤተሰብና ምድረ በዳ ለሆነች ግዛቱ ሁሉም ነገር ተለወጠ። በዚያ ዓመት የአሜሪካን የከርሠ- ምድር ተመራማሪዎች ሳውዲት ዓረቢያ ውስጥ ግዙፍ የነዳጅ ክምችት አገኙ። የነዳጅ ክምችቱ በዓመታት ውስጥ ከፍ እያለ መጣ። ዛሬ አገሪቱ እንዳላት የተረጋገጠው የነዳጅ ዘይት ክምችት ከ250 ቢሊዮን በርሜል በላይ ነው። ዓለም እንዳላት ከተረጋገጠው የነዳጅ ዘይት ክምችት አንድ አራተኛው የሚገኘው በዚህች አገር ውስጥ ነው።

ሳውዲት ዓረቢያ ምንም እንኳን ሰፊ የነዳጅ ሀብት ያላት አገር ብትሆን፥ ከድህነት ወደ ብልጥግና በድንገት በመሸጋገር ረገድ ከባሕረ-ሰላጤው አገሮች ብቸኛይቱ አይደለችም። ነዳጅ ዘይት የተገኘው ከሳውዲት ዓረቢያ በፊት ኢራንና ኢራቅ ውስጥ ነው። እንግሊዞች ናቸው የኢራንን የነዳጅ ክምችት መጀመሪያ በ1908 እእአ ያወጡት። ሀያ ዓመታት ባልሞላ ጊዜ ደግሞ ኢራቅ ውስጥ ነዳጅ ዘይት አገኙ። ልክ ሳውዲት ዓረቢያ ውስጥ ነዳጅ ዘይት በተገኘ ማግሥት፥ ኩዌት በተባለች ትንሽ አገር ውስጥ ግዙፍ የነዳጅ ዘይት ክምችት ተገኘ። ዓለም እንዳላት ከተረጋገጠው የነዳጅ ዘይት ግማሹ የሚገኘው ሳውዲት ዓረቢያ፥ ኢራቅና ኩዌት ውስጥ ነው።

## ለፋኖሴ ነዳጅ ዘይት ስጡኝ

ዓለም በነዳጅ ዘይት ፍላጎት አባዜ ተይዛለች። ለዓለም ዘይት አቅራቢ ብቸኛ ድርጅት ደግሞ ኦፔክ [OPEC]* ነው። በ2000 እአአ ዓለም ካስፈለጋት ኃይል አብዛኛውን የተካው ነዳጅ ዘይት ነበር፤ ኦፔክም የገበያ ድርሻውን አስፍቷል። አንድ ጥናት እንዳረጋገጠው፥ ኦፔክ የሚያቀርበውን ነዳጅ ዓለም ለመግዛት ያለው ፍላጎት፥ በ1986 እአአ ከነበረው በቀን ከ15 ሚሊዮን በርሜል፥ ከሦስት ዓመት በኋላ ወደ 20 ሚሊዮን በርሜል ከፍ አድርጎታል።

በ2000 እአአ ይህ ቁጥር ወደ 25 ሚሊዮን በቀን አሻቅቧል። በዓለም ደረጃ ትልቋ የነዳጅ ዘይት ተጠቃሚ አገር አሜሪካን ስትሆን፥ የራሷ የነዳጅ ክምችት እያሽቆለቆለ በመሄድ ላይ ነው። አገሪቱ ግን የራሷን ነዳጅ ፍለጋ ከመቀጠል ይልቅ፥ ፍላጎቷን ለማሟላት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ይበልጥ በማዘንበል ላይ ናት።

ነገር ግን፥ ምንም እንኳን ዓለም የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ጥገኝነቷ እያደገ ቢሄድ፥ የነዳጅ ዘይት ዋጋ በሚመጣው አሥር ዓመት ውስጥ እንደሚያሽቆለቁል ነው ብዙዎች የሚተነብዩት። የዚህ ተስፈኛ ትንቢት ምክንያቶች፥ በኦፔክ አገሮች መካከል የሚኖረው ውድድርና ኦፔክ የነዳጅ ምርቱን ለመቆጣጠር ያለመቻሉ ናቸው። አንድ ጥናት እንዳረጋገጠው፥ ኦፔክ የነዳጅ ምርቱ በየገበያው በተትረፈረፈ ጊዜ፥ ዋጋውን እንደ ነበረ ለማቆየት ይቻለው ዘንድ ምርቱን ለመቀነስ የሚችል አይደለም። ወደፊትም የተሻለ ነገር አይኖረውም። ወደፊት ብዙና ርካሽ የነዳጅ ዘይት እንደምናገኝ ዋስትና ይኖረን ይሆን?

## የሳዳም ድንገተኛ ነገር

ዓለም ለጊዜው ብዙ ነዳጅ ዘይት አላት። ችግሩ ካለው የነዳጅ ክምችት ከግማሽ በላይ የሚሆነው የፖለቲካ መረጋጋት በሌለበት የዓለም ክፍል አሸዋ ሥር መሆኑ ነው። መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚገኘውን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ አለመረጋጋት ያላጤኑ ትንበያዎች ወይም ዕቅዶች እንደማይፈፀሙ የታወቀ ነው። በ1970ዎቹ መጨረሻ፥ የኢራኑ ሻህ

---

* ይህ ድርጅት የተመሠረተው እአአ በ1960 ነው። በአሁኑ ጊዜ 11 አባል አገሮች ይገኙበታል። እነርሱም፤ ኢራን፥ ኢራቅ፥ ኳታር የተባበሩት አረብ ኢመሬት፥ ሳውዲ አረቢያ፥ ኩዌት፥ አልጀሪያ፥ ናይጀሪያ፥ ሊቢያ እና ቬንዙዌላ ናቸው። እነዚህ አገሮች በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያለውን 40% የነዳጅ ፍጆታ አቅራቢዎች ናቸው።

በአያቶላህ ሆሜኒና ሃይማኖት አክራሪ በሆኑ ተከታዮቹ አማካይነት ይገለበጣል ብሎ የገመተ አልነበረም። በ1990 እአአ ሳዳም ሁሴን ኩዌትን ይወራሉ ብሎ ያመነ ሰው አልነበረም። ሁለቱም ሁኔታዎች ግን ተከናውነዋል፤ ለምዕራቡ ዓለም የሚደረገውን የነዳጅ አቅርቦት ሊያስተጓጉሉም ችለው ነበር።

ሳዳም ሁሴን ኩዌት ላይ የሰነዘሩት ወረራ በተለይ ከፈጣንነቱና፥ በዓለም የነዳጅ አቅርቦት ላይ ካደረሰው ጉዳት አንጻር ሲታይ አሳሳቢ ነበር። ሳዳም ሁሴን የነዳጅ ዘይት ክምችታቸውን በአንዴ በእጥፍ በማሳደግ በቁጥጥራቸው ሥር ያለውን የዓለም የነዳጅ መጠን እስከ 25 በመቶ ከፍ አደረጉት። ይበልጥ አስጨናቂ የነበረው ነገር ግን፥ ጦራቸውን ወደ ሳውዲት ዓረቢያ ለመላክ ዓቅደዋል የሚለው ዜና ነበር። እኚህ ሰው፥ ከዓለም የነዳጅ አቅርቦት ግማሹን ሊቆጣጠሩ ነው በሚል ፍርሃት የነዳጅ ዋጋ ወደ ላይ አሻቀበ። ይህ ሁኔታ ነበር የአሜሪካኑ መሪ፥ ፕሬዚዳንት ቡሽ የበረሃው ጋሻ የተባለውን ወታደራዊ ኃይል ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እንዲያዘምቱ ያስገደዳቸው።

ሳዳም ሁሴን ዕቅዱ አልተሳካላቸውም እንጂ፥ ለዓለም ከሚቀርበው የነዳጅ ዘይት ብዙውን በአንድ ሰው ቁጥጥር ሥር ወደ ማድረጉ አደገኛ ሁኔታ ተቃርበው ነበር። ይህ ሁኔታ ራሱን ከነዳጅ ዘይት ለማላቀቅ በማይችለው ዓለም ዘንድ አስፈሪ ጥያቄን ያስነሣል። ኢራቅ፥ ኩዌትና ሳውዲት ዓረቢያ በአንድ ሰው የሚመሩ ቢሆኑስ ኑሮ? ሳዳም ሁሴን ኩዌት ላይ ባይገቱና፥ የአሜሪካን ጦር ሳይቀድማቸው ወደ ሳውዲት ዓረቢያ ቢያመሩስ ኑሮ?

የተባበሩት አገሮች የቃል ኪዳን ጦር፥ ሳዳም ሁሴንን በመግታት ከኩዌት ቢያስወጣቸውም፥ አሁንም ኢራቅን በመምራት ላይ ናቸው። አሜሪካን ከምታደርገው ቁርጠኛ መከላከል ብትዳከም፥ የኢራቅ ወታደሮች እንደገና በማንኛውም ሁኔታ በአረብ አገሮች ድንበር አካባቢ ይከማቻሉ። ሳዳም ሁሴን ወይም እሳቸውን የሚተካ መሪ፥ በስተደቡብ ባሉት በጎረቤቶቻቸው ላይ እንደገና ከመነሣት ምን ያግዳቸዋል? መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ያሉት የቆዩ ቂሞች በቶሎ አይረሱም፤ ሳዳም ሁሴንም ኩዌትንና ሳውዲ ዓረቢያን በሚመሩ ቤተሰቦች ላይ ቂም አላቸው። አሜሪካን የዓረብ አገሮችን ልትረዳቸው የማትችል ወይም የማትፈቅድ ብትሆን፥ የኢራቅ ወታደሮች ድንበሩን ሊያልፉ ይችላሉ።

መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚገኘው የነዳጅ ሀብት በአንድ ሰው ቁጥጥር ሥር መሆኑ፥ የዓለምን ምጣኔ ሀብት ያናጋዋል። ይህ ቢሆን ሁለት ነገሮች ወዲያውኑ ይከሠታሉ። አንደኛ፥ ነዳጁን የሚቆጣጠረው ሰው

ምርቱን ይቀንስና፥ የነዳጅን ዋጋ ከፍ ያደርገዋል፥ እናም ትርፉን ያግበሰብሳል። ሁለተኛ፥ በነዳጅ ዘይት በአያሌው የሚጠቀሙ አገሮች፥ በዚህ ጨካኝ የመካከለኛው ምሥራቅ ገዥ አጣብቂኝ ውስጥ የመግባት የምጣኔ ሀብት ጫና ይሰማቸዋል። ይህ ሰው በዚህ አኳኋን በኢንዱስትሪ የበለጠጉ አገሮችን በቁጥጥሩ ሥር ያደርጋቸውና እንቅስቃሴና ፖለቲካቸውን ይቆጣጠራል። በተለይ አውሮፓ፥ ከመካከለኛው ምሥራቅ የሚመጣው ነዳጅ በእጅጉ ተጠቃሚ እንደ መሆኗ በጣም ትጎዳለች።

## ውቢት በአውሬው ስትጋልብ

ሐዋርያው ዮሐንስ ራእይ 17-18 ባለው ክፍል ውስጥ የሚገልጠው በትክክል ይህንኑ ምሥል ነው። ይህ ብቻም አይደል፥ በፍጻሜው ዘመን በክርስቶስ ተቃዋሚና በጊዜው በሚኖረው የባቢሎን መሪ መካከል ስለሚኖረው ውስብስብ ግንኙነትም ገልጧል። ነቢዩ ዳንኤል የተጠቀመበትን ቋንቋ በመውሰድም የክርስቶስን ተቃዋሚና ግዛቱን "አውሬው" ይለዋል። ይህ አውሬ፥ ዮሐንስ ራእይ 13፥4 ውስጥ "አውሬውን ማን ይመስለዋል? እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል?" በማለት በመጨረሻው ዘመን አገሮችን ሁሉ በወታደራዊ ኃይል የሚገዛ መሆኑን የገለጠው ነው።

ራእይ 17 ውስጥ ግን አንድ ነገር በጣም ስሕተት ሆኖ ይታያል። ይኸውም አውሬው ወታደራዊ ባለሥልጣን ሊሆን ይችላል፥ ነገር ግን "በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ" (17፥3) የተባለላት አንድ ሴት በአውሬው ላይ ተጽዕኖ የምታደርግበት ይመስላል። እዚያው ምዕራፍ ውስጥ መልአኩ ለዮሐንስ እንዲህ ብሎታል፦ "የምትደነቅ ስለምንድነው? የሴቲቱን ምሥጢርና የሚሸከማትን ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉትን የአውሬ ምሥጢር እነግርሃለሁ" (17፥7)። ዮሐንስ የተመለከተው ራእይ የሚያስረዳው፥ ሴቲቱ በአንዳች ሁኔታ የመጨረሻውን ዘመን የዓለም ገዥ የምትጋልበው ወይም የምትቆጣጠረው መሆኑን ነው። ይህ ግን እንዴት ሊሆን ይችላል?

ይህች ሴት ባቢሎን የምትባል መሆኗን ምዕራፍ 10 ውስጥ ዳሰስናል። ሴቲቱ በትክክል የባቢሎን ከተማ እንደምትሆን እግዚአብሔር አመልክቷል። ይህች ከአሁኒቱ የባግዳድ ከተማ ኀምሳ ማይልስ ርቃ የምትገኝ ከተማ፥ በፕሬዚዳንት ሳዳም ሁሴን አማካይነት በመገንባት ላይ ናት። የባቢሎኑ መሪ በሰባት ዓመታት አገዛዙ መጨረሻ ላይ፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚሆነውን ሰው በአንዳች ሁኔታ ይቆጣጠረዋል።

ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ከባቢሎን ጋር በሚኖረው ግንኙነት ደስተኛ ባይሆንም፥ ለተወሰነ ጊዜ ግንኙነቱን ይቀጥላል። በመጨረሻ ግን፥

የጎን ውጋት የሆነባትን ይህን ሰው ለማጥፋት "ዳግማዊ የበረሃው ማዕበል ዘመቻ" የተሰኘ ዘመቻ ያደርጋል። "ያየሃቸውም አሥር ቀንዶችና አውሬው ጋለሞታይቱን ይጣላሉ፤ ባዶዋንና ራቁትዋንም ያደርጓታል። ሥጋዋንም ይበላሉ በእሳትም ያቃጥሉአታል" (17፡16)። የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚሆነው ሰው ግዙፍ የጦር ኃይሉን በመጠቀም፥ ችግር የሚፈጥርበትን መንግሥት ያጠፋዋል።

የምታንሠራራው የባቢሎን ከተማ በምን ሁኔታ የክርስቶስን ተቃዋሚና ግዛቱን ለመቆጣጠር እንደምትችል መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ አያመለክትም። ዮሐንስ ግን፥ ባቢሎን በክርስቶስ ተቃዋሚ ላይ ተጽዕኖ የምታደርግበት፥ በንግድና በኢኮኖሚ መስክ እንደሚሆን በጽሑፉ ገልጧል። ባቢሎን በምትወድቅበት ጊዜ የንግድና የልውውጥ ሸርኮቿ የሚያዝኑ ስለመሆናቸው እንደሚከተለው ተገልጧል፦ "የመርከባቸውን ጭነት ከእንግዲህ ወዲህ የሚገዛ የለምና የምድር ነጋዴዎች ያለቅሱላታል ያዝኑላትማል" (18፡11)። የመርከብ ካፒቴኖች ሳይቀሩ ባለጠጋ ላደረገቻቸው ከተማ እንዲህ የሚሉ መሆናቸው እንደሚከተለው ተገልጧል፦ "የመርከባቸውን ጭነት ከእንግዲህ ወዲህ የሚገዛ የለምና፥ የምድር ነጋዴዎች ያለቅሱላታል ያዝኑላትማል" (18፡19)።

ባቢሎን የክርስቶስ ተቃዋሚ በሆነው ሰውና በግዛቱ ላይ ምጣኔ ሀብታዊ ተጽዕኖ ታደርጋለች። ይህ ምጣኔ ሀብታዊ ቁጥጥር ስለሚያካትታቸው ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጠው ዝርዝር ባይኖርም፥ ነዳጅ ዘይት ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለ። አንድ ሰው መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ያለውን የነዳጅ ሀብት በመቆጣጠር እና፥ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘቡን ለባቢሎን ከተማ መገንቢያ ያውላል፥ ብሎ መገመቱ ከሳዳም ሁሴን ወረራ ወዲህ፥ አያዳግትም። ይህ መሪ፥ ነዳጅ ሀብቱን በቁጥጥሩ ሥር ከማድረጉ የተነሣ፥ በዓለም ውስጥ የበላይነት ሚና ይኖረዋል። አዲሲቱን ባቢሎን ማዕከሉ ያደርጋታል፤ ግዛቱም "በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ" (17፡18) ትሆናለች።

የክርስቶስ ተቃዋሚ ብርቱ የዓለም ወታደራዊ ኃይል ቢሆንም፥ ድካምና ውሱንነትም ይታይበታል። አንደኛው አስከፊ ድክመቱ፥ የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት ጥገኛ መሆኑ ነው። በዓለም ብርቱ የሆነ የጦር ኃይል ቢኖረውም፥ የጦር ኃይሉ ይንቀሳቀስ ዘንድ ነዳጅ ዘይት ያስፈልገዋል። በመሆኑም እርሱ በማይቆጣጠረው የኃይል ምንጭ ችግር ሳቢያ እክል ይገጥመዋል።

የክርስቶስ ተቃዋሚ አውሮፓ ውስጥ በሚነሣበት ጊዜ፥ አንድ ሌላ መሪ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ያለውን የነዳጅ ዘይት ክምችት

ይቆጣጠራል። ይህ መሪ የነዳጅ ዘይትን ዋጋ ሽቅብ ያንረዋል። በዚህም ሳቢያ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ያግበሰብሳል። ከሚያገኘው ገንዘብ አብዛኛውን የሚያውለውም አዲሲቱን ከተማውን ማለት፥ ባቢሎንን ለመሥሪያና ለማስዋቢያ ነው። ኤፍራጥስ አቅራቢያ በምትገኘው በዚህች አዲስ ከተማው ውስጥ ሆኖ፥ የነዳጅ ዘይትን አቅርቦትና ዋጋውን በመወሰን ብቻ በዓለም ዙሪያ የሚነሡና የሚወድቁ መንግሥታትን ይቆጣጠራል።

ሳዳም ሁሴን በ1990 እአአ ኩዌትን በወረሩ ጊዜ፥ በወታደራዊ ኃይል እሳቸውን የመቋቋም ብቃቱን እስኪያረጋግጥ ድረስ ዓለም የስድስት ወራት ጊዜ ወስዶበታል። ሳዳም ሁሴን ያን ጊዜ ወደ ሳውዲት ዓረቢያ ቢሻገሩ ኑሮ፥ የአውሮፓውያኑ እርሳቸውን የመቋቋም እርምጃ የተራዘመ ጊዜ ይወስድ ነበር። በዓለም ፍፃሜ ወቅት የሚነሣው የክርስቶስ ተቃዋሚ፥ በሁለት ምክንያቶች ሳቢያ የጦርነት አጻፋ አይወስድም። አንደኛ፥ በሌላ አካባቢ ይበልጥ አስቸጋሪ ጦርነት ይኖርበታል። ሁለተኛ፥ ሰፍራው በባቢሎን ንጉሥ ስለሚያዝበት፥ የጦር ኃይሉን ሳውዲት ዓረቢያ ውስጥ ሊያሰፍር አይችልም።

ሌሎቹን ጦርነቶች በድል ከተወጣ በኋላ ነው ጦሩን ወደ ባቢሎን የሚያዘምተው። የጦር ኃይሉ ውጊያውን ከሰሜን በመጀመር ወደ ባቢሎን ይዘልቃል። "ሕዝብ ከሰሜን ወጥቶባታል፤ ምድርዋንም ባድማ ያደርጋል" (ኤር. 50፥3)። ከሰባት ዓመቱ የክርስቶስ ተቃዋሚ የመጨረሻ ዘመቻዎች አንዱ፥ ችግር የፈጠረበትን ሰውና ከተማውን ማጥፋት ይሆናል። ይህ የዓለም መሪ፥ በዚህ ድርጊቱ ፍጹም የሆነ ኃይሉን እንዳያጠናክር እንቅፋት የሆነበትን መንግሥት ድል በማድረግ ላይ መሆኑን ያምናል። የሚያከናውነው ግን ዓላማውን ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ነው።

ራእይ ምዕራፍ 17 የሚያመለክተው፥ በመካከለኛው ምሥራቅና በክርስቶስ ተቃዋሚ መንግሥት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ነው። እግዚአብሔር ለዮሐንስ የገለጠለት፥ የመጨረሻው ዘመን ሁለት ኃይላት ዓለምን የሚቆጣጠሯት መሆናቸውን ነው። የባቢሎን ኃይል በኢኮኖሚና በገንዘቡ ረገድም ነው። የዓለምን ፍላጎት በማሟላት ሀብታም ትሆናለች። ይህን በማድረግም በዓለም ላይ የኢኮኖሚ የበላይነት ይኖራታል። የክርስቶስ ተቃዋሚ ግዛት ደግሞ ወታደራዊና ኢንዱስትሪያዊ ይሆናል። የሚቃወሙትን ሁሉ በመደምሰስ በሌሎች ላይ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ቁጥጥር ያደርጋል። የርሱ መንግሥት ደካማ ጎን፥ የባቢሎን የነዳጅ ዘይት ጥገኛ መሆኑ ነው። ለችግሩ የመጨረሻ "መፍትሔ" አድርጎ የሚወስደው፥ እንዲህ ያለ ችግር የምትፈጥርበትን አገር መውጋትና ማጥፋት ይሆናል። ባቢሎን ከጠፋች በኋላ፥ ነጋዴዎች ሁሉ ወደ አርማጌዶን የሚያመሩ ይሆናሉ።

> ምዕራፍ አስራ አምስት <

# አርማጌዶን፤ የመጨረሻ ግብ

አውቶቡሱ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ በሚያመራው ጠባብ መንገድ በዝግታ ሽቅብ ይጓዛል። በግራና በቀኝ ደግሞ የቀርሜሎስን የተራራ ሰንሰለት የመሠረቱት ተራራዎች ተሰልፈዋል። ከግብፅ ወደ ሜሶፖታሚያ በሚያመራው አውራ ጎዳና መዳረሻ ላይ እንዲያ ሆነው ሲታዩ በጸጥታ የቆሙ ጠባቂዎች ይመስላሉ። ከእነዚያ በጥንቱ የመካከለኛው ምሥራቅ ታሪክ ሁለቱን የታወቁ የሥልጣኔ አካባቢዎች ያገናኙ በነበሩና ያረጁ ጎዳናዎች ላይ፥ አያሌ የበረሃ ተጓዦች እንዲሁም ጀግናዎች ተጉዘው ባቸዋል።

ዛሬ ደግሞ በዕብራይስጥኛ መርካባህ (ሠረገላ) የተባለው አውቶቡሳችን ይህን ከ3,500 ዓመታት በፊት ቱትሞስ 3ኛ በተባለው ንጉሥ በተመዘገበለትና አስፈሪ በሆነው አቀበት ሽቅብ በመጓዝ ላይ ነን። የዚያ ንጉሥ የጦር አማካሪዎች፥ ንጉሡ አሁን እኛ ባለንበት አስቸጋሪ መንገድ እንዳይጓዝ እንዲህ በማለት መክረውት ነበር። “በዚህ እየጠበበ በሚሄድ መንገድ ለምን ትጓዛለህ? ድል አድራጊው ጌታችን (ንጉሡ) ልቡን በሚያረኩ ሌሎች መንገዶች ይጓዝ። እኛም በዚህ አስቸጋሪ መንገድ እንድንሄድ አታድርገን።” ንጉሡ ግን የጦር አዛዦቹን ምክር ችላ በማለት በግብፅ ላይ ያመፁ የከነዓን ከተሞችን ለመውጋት በሠረገላው ሽቅብ ተጓዘ። የእኛም የጉዞ መጨረሻ ቱትሞስ 3ኛ ወደመረጠው ወደ መጊዶ አቅጣጫ ነው።

ተራራውን እያቋረጥን ስንጓዝ፥ የጀዝሪል ሸለቆ ከፊት ለፊታችን ተዘርግቶ ይታየናል። በስተግራችን ጥንታዊቱ የመጊዶ ከተማ አለች። የዚህች ጥንታዊት ከተማ ፍርስራሽ ተራራው ላይ ሆኖ፥ ወደ ሰፊው ሸለቆ የሚዘልቀውን ጎዳና የሚጠብቅ ይመስላል። መጊዶን ድል ያደረጉ ወራሪዎች አንዱ ሌላው ባፈራረሳት ከተማ ላይ ሲገነባ ከጊዜ ብዛት ተራራው ከፍ እያለ ሄዷል። የከርሠ-ምድር ተመራማሪዎች ከተማይቱ ለሀያ አራት ጊዜ መወረሯን የሚያመለክቱና ሀያ አራት የተለያዩ የአፈር ንብብሮች አግኝተዋል። እነዚህ የአፈር ንብብሮች የዚህችን ስልታዊ ከተማ አስከፊ ታሪክ ድምፅ አልባ አስታዋሾች ናቸው።

ንጉሥ ሰሎሞን አሳንጾት በነበረው የውጭ በር ስናልፍ፥ ከእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ጠቢብ የነበረው ንጉሥ፥ የመጊዶንን ጠቃሚነት ተገንዝቦ እንደነበር ተረዳሁ። የነገሥት መጻሕፍትን ያዘጋጀው ሰው ስለ ንጉሥ ሰሎሞን በሚገልጥበት ጊዜ፥ ንጉሡ መናገሻ ከተማውንና

በግዛቱ የሚገኙ ሌሎች ሦስት ጠቃሚ ከተማዎችን "ሐጾርንም፥ መጊዶንም፥ ጌዜርንም" (1ኛ ነገ. 9፡15) ቅጥር ሠርቶባቸው እንደነበር አስገንዝቧል። በስፍራው በእስራኤላውያን የተሠሩ ታላላቅ ሕንጻዎች ትክክለኛ አገልግሎት ምን ነበር? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመሻት ምሁራን እስካሁን በመከራከር ላይ ናቸው። ሕንጻዎቹ ያገለገሉት ለበረትነትም ይሁን ለመጋዘንነት፥ የሚያስገነዝቡን አንድ ነገር ቢኖር፥ መጊዶ ከእስራኤል የክልል ማዕከሎች አንዷ መሆኗን ነው።

ቡድናችን የጌዜርን ሸለቆ ቁልቁል ለመመልከት ያመቸው ዘንድ ከኮረብታው በስተ ሰሜን ምሥራቅ ማዕዘን ላይ ተሰባሰበ። ከሸለቆው ሥር የተንጣለው የታቦር ተራራ በሩቁ ጭጋግ ውስጥ ይታያል። በስተቀኛችን ደግሞ አቅጣጫው ወደ ኮረብታው የሆነና በከርሠ-ምድር ቆፋሪዎች የተገኘ የከነዓናውያን መሠዊያ አለ። ይህ መሠዊያ ከሰሎሞን ዘመነ መንግሥት 1500 ዓመታት ቀደም ብሎ ጭምር፥ መጊዶ ጠቃሚ ስፍራ እንደነበረች አስታወሰን። መጊዶ የትኛውም እስራኤላዊ በበሯ ከመዝለቁ አያሌ ዘመናት ቀደም ብሎ የጌዜር ሸለቆ ዋና ስፍራ በመሆን አገልግላለች።

መጊዶ በቀርሜሎስ ተራራ መግቢያ ላይ የጌዜር ሸለቆ ስልታዊ ከተማ መሆኗ ብዙ ጎዘን አድርሶባታል። በከበባና ወረራ ተጠቅታለች። ለቁጥር የሚያታክቱ ወታደሮች በመግቢያዋ ደጅ ይሰበሰቡ ነበር። የተባበረችው እስራኤል ግዛት የመጨረሻ መሪ፥ ንጉሥ ሰሎሞን ከተማይቱን ከወራሪዎች ለመከላከል በአጥር ከልሏት ነበር። የይሁዳ የመጨረሻው ጥሩ ንጉሥ ኢዮስያስ የግብፅ ጦር ባቢሎናውያንን ለመውጋት በዚያ እንዳያልፍ በሚከለክልበት ጊዜ መጊዶ ላይ ነው የሞተው። "በእርሱም ዘመን የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ኒካዑ ከአሦር ንጉሥ ጋር ሊጋጠም ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ወጣ፤ ንጉሡም ኢዮስያስ ከእርሱ ጋር ሊጋጠም ወጣ፤ ፈርዖንም በተገናኘው ጊዜ በመጊዶ ገደለው" (2ኛ ነገሥት 23፡29)።

በዕብራይስጥ "ሀር መጊዶ" የሚባለው የመጊዶ ኮረብታ ወታደሮች ለጦርነት የሚከማቹበት ስፍራ ተምሳሌት ነው። የጌዜር ሸለቆ ወታደሮችን ለማከማቻና ለጦር መለማመጃነት አገልግሏል። የቀርሜሎስ ተራራ መተላለፊያ የእርሷ መሆኑ ከተማይቱ ወታደራዊ ጠቀሜታ እንዲኖራት አድርጓል። እግዚአብሔር የክርስቶስን ተቃዋሚና ሠራዊቱን በእስራኤል ላይ ለሚደረገው የመጨረሻ ጦርነት በሚያሰባስብበት ጊዜ፥ ጦሩ መጊዶ፥ በግሪክኛ አርማጌዶን በተባለው ኮረብታ ላይ መከማቸቱ ታዲያ ያስደንቃል? "በዕብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባለው ስፍራ አስከተቱአቸው" (ራእይ 16፡16)።

## የአርማጌዶኑ ጦርነት የዓለም ፍጻሜ ነው?

የኑክሊየር መሣሪያ ባለቤት ለመሆን በአገሮች መካከል የሚደረገውን እሽቅድምድም የሚቃወሙ ክፍሎች፥ ሕይወት ያለውን ፍጡር ሁሉ ሊያጠፋ የሚችለው አሠቃቂ የኑክሊየር አደጋ እንዳይቀሰቀስ አስጠንቅቀዋል። ሰብአዊ ፍጡርን ከገጸ ምድር የሚያጠፋውን ታላቅ ጦርነት ለመግለጥ "አርማጌዶን" በሚል ቃል ተጠቅመዋል። ይሁን እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስ "የአርማጌዶን ጦርነት" የሚለው ይህን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ የአርማጌዶን ውጊያ በዓለም ታሪክ የመጨረሻው ጦርነት መሆኑን አይገልጥም። ጦርነቱን ከዓለም ፍጻሜ ጋርም አያገናኘውም። እንደውም አርማጌዶን ላይ ውጊያ ይካሄዳል ብሎ በግልጥ አይናገርም። እግዚአብሔር ስለ አርማጌዶን የሚገልጠው ነገር ቢኖር፥ የዓለም ወታደራዊ ኃይላት የኢየሱስን ዳግም ወደ ምድር መመለስ በመቃወም ለውጊያ የሚሰበሰቡበት ስፍራ መሆኑን ነው። ራእይ ምዕራፍ 16ን በጥንቃቄ መመልከቱ በኢየሱስ ዳግም ምጽአት ዋዜማ በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ነገሮችን ለመገንዘብ ይረዳል። አርማጌዶን ላይ የሚደረገው የወታደሮች መከማቸት ከክንውኖቹ አንዱ ነው።

ራእይ ምዕራፍ 16 ውስጥ እንደተገለጠው፥ እግዚአብሔር የመጨረሻ የፍርድ ጽዋውን በምድር ላይ ያፈስሳል። እነዚህ ፍርዶች የሚከናወኑት፥ ኢየሱስ ዳግም ወደ ምድር ከሚመለስባቸው የመጨረሻ ሳምንታትና ቀናት በፊት ነው። ከመጨረሻው ፍርድ የሚቀድመው፥ መልአኩ በምድር ላይ የሚያፈሰው ስድስተኛ ጽዋ ነው (16፡12-16)። መካከለኛው ምሥራቅን እያቋረጠ ከቱርክ ወደ ፋርስ ባሕረ-ሰላጤ የሚፈሰው የኤፍራጥስ ወንዝ ይደርቃል። እግዚአብሔር ይህን ድንበር የሚያስወግደው፥ "ከፀሐይ መውጫ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲሰናዳላቸው" ነው። የዓለም ኃያላን ይሰባሰባሉ፤ የኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅም መሰባሰባቸውን ያፋጥነዋል።

ሰይጣን ተፈጥሯዊው መሰናክል ሲወገድለት፥ መንግሥታትን ሁሉ ይሰበስቡ ዘንድ ዲያብሎሳዊ መልእክተኞቹን ያሰማራቸዋል። "ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፥ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ፥ በእግዚአብሔር ቀን ወደሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ" (16፡14)። ሠራዊቱ የሚተመው ለጦርነት ነው፤ ይሁን እንጂ፥ ማንን ሊወጋ ነው የሚመጣው? ብዙ ሰዎች ጦሩ ከየስፍራው የሚሰባሰበው እርስ በርሱ ሊዋጋ ይመስላቸዋል። በመሆኑም የጦሩን አርማጌዶን ላይ መሰባሰብ ትልቁና የመጨረሻው የዓለም ጦርነት ነው ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እነዚህ ሠራዊቶች የሚሰባሰቡት እርስ በእርሳቸው ሊዋጉ ነው አላለም። የሚወጉት ሌላ የጋራ ጠላት ይኖር ይሆን?

ሰይጣንና ተከታዩ የሆኑት ሰዎች፥ ሠራዊቶቹ ይሰበሰቡ ዘንድ አጋንንትን ይልካሉ። ሠራዊቶቹ የሚመጡትም እንደ ተባባሪዎች እንጂ እንደ ጠላት ሆነው አይደለም። አርማጌዶን ከውጊያ ሜዳነት ይልቅ እንደ መዘጋጃ ስፍራነት ነው የሚያገለግለው። የመጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች ጥቅሶች የሚያመለክቱት፥ በምድራዊ ሠራዊቶችና በኢየሱስ መካከል የሚደረገው የመጨረሻ ጦርነት፥ ደቡብ እስራኤል በሚገኘው አርማጌዶን ላይ ሳይሆን፥ ኢየሩሳሌም ውስጥ መሆኑን ነው። አርማጌዶን፥ የምድር ሠራዊቶች መሪያቸው ለመጨረሻው ድል በሚያደርገው ዘመቻ ለመሳተፍ ይችሉ ዘንድ፥ ለመገናኛነት ነው የሚያገለግለው።

### የክርስቶስ ተቃዋሚው የመጨረሻ ቀናት

የሠራዊቶች አርማጌዶን ላይ መሰባሰብ የዓለም ታሪክ ፍጻሜ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ ዙፋኑ ላይ ለመቀመጥ ከመመለሱ በፊት፥ አንድ የመጨረሻ የፍርድ ጽዋ ወደ ምድር መፍሰስ አለበት። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ ራእይ 16፡17-21 ውስጥ የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ፍርድ አመልክቷል። የእግዚአብሔር ፍርድ የመጨረሻ ጽዋ ወደ ምድር በሚፈስበት ጊዜ፥ በሰማይ ካለው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ "ተፈጽሟል" የሚል ድምጽ ይሰማል። ይህ ፍርድ የእግዚአብሔር የቅጣት ፕሮግራም የሚያበቃበትና፥ ለኢየሱስ መምጣት መድረኩ የሚዘጋጅበት ነው።

የመጨረሻው ጽዋ ሁለት ዓይነት ሥቃዮችን ያመጣል። መጀመሪያ፥ እግዚአብሔር አጥፊ መቅሠፍቶችን በተከታታይ ወደ ምድር ይልካል። "መብረቅና ድምፅም፥ ነጎድጓድም ሆኑ፥ ትልቅም የምድር መናወጥ ሆነ፤ ሰው በምድር ከተፈጠረ ጀምሮ እንዲያ ያለ ታላቅ መናወጥ ከቶ አልነበረም. . . .። ደሴቶችም ሁሉ ሸሹ ተራራዎችም አልተገኙም። በሚዛንም አንድ ታላንት የሚያህል በረዶ በሰዎች ላይ ከሰማይ ወረደባቸው" (ራእይ 16፡18፥20-21)። እግዚአብሔር የተፈጥሮ ኃይልን በነዋሪዎቿ ላይ በሚያስነሣበት ጊዜ ዓለም የመጨረሻ የጣር ህቅታ ይይዛታል።

ከዚህ የመጨረሻ ጽዋ የሚወጣው ሁለተኛ ፍርድ የሚወርደው በባቢሎን መዲና ላይ ነው፥ "ታላቂቱም ባቢሎን የብርቱ ቁጣው ወይን ጠጅ የሞላበትን ጽዋ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች" (ራእይ 16፡19)። በሚቀጥሉት የራእይ መጽሐፍ ሁለት ምዕራፎች፥ ሐዋርያው ዮሐንስ ባቢሎን የክርስቶስ ተቃዋሚ በሆነው ሰውና በሠራዊቱ የምትጠፋበትን ሁኔታ ይገልጣል። ባለፈው ምዕራፍ እንደተመለከትነው፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚሆነው ሰውዬ የባቢሎን ገዢ ጥገኛ ይሆናል።

የዓለም ሠራዊት አርማጌዶን ላይ መሰባሰብ፥ “የበረሃው ዘመቻ ቁጥር ሁለት” ዋዜማ ይሆናል። የሚሰበሰበው ሠራዊት፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነውን ሰው ያሳዘነችውን ከተማ ለማውደም ወደ ባቢሎን ይዘምታል። ባቢሎንን ከደመሰሰ በኋላ፥ አይሁዳውያንን ለማጥፋት ወደ እስራኤል ይመለሳል። ያኔ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የሚመጣው።

የአርማጌዶን ውጊያ የመጨረሻው ጦርነት ሳይሆን፥ በተከታታይ ለሚሆኑ የመጨረሻ ጦርነቶች መንደርደሪያ ስለ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያመለክተን ሌላ ነገር አለ? ነቢዩ ዳንኤል የክርስቶስ ተቃዋሚ ስለሆነው ሰው የመጨረሻ ዘመን ፍንጭ ይሰጠናል። ይህ አንድ ነገር ይጠቁመን ይሆናል፥ ዳንኤል 11፡36-45 ውስጥ ነቢዩ የዚህን የኃጢአት ሰው ተግባር ይገልጣል።

የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚሆነው ሰው ራሱን ከፍ ከፍ እያደረገና ሐሰተኞቹን፥ “የአምባዎች አምላክ” እያከበረ በሥልጣን ገናና እንደሚሆን፥ ነቢዩ ዳንኤል ምዕራፍ 11፡36-39 ውስጥ ይገልጣል። የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚሆነው ሰው በመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት ብዙ ስልታዊ ዓላማ፥ ወታደራዊ ኃይልና ከፍ ከፍ ማለት መሆኑን እነዚህ ቁጥሮች ይጠቁማሉ።

ከምዕራፍ 11፡40 ጀምሮ ዳንኤል የሚያተኩረው፥ “በፍጻሜ ዘመን” በሚከናወኑ ነገሮች ላይ ነው። የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚሆነውን ሰውና የሠራዊቱን እንቅስቃሴ እንዲሁም የሚያካሂዳቸውን ጦርነቶች ነው ዳንኤል በእነዚህ ቁጥሮች የሚገልጠው። ቁጥር 41 ላይ እንደተገለጠው ይህ ሰው፥ “ወደ መልካሚቱ ምድር [እስራኤል]” ይገባል።*

የተቃዋሚው በፍጻው ዘመን አጋማሽ ላይ መምጣት፥ ቀደም ሲል ከእስራኤል ጋር ካደረገው ስምምነት የተነሣ፥ ለሰው ሁሉ ዱብ ዕዳ ወይም ድንገተኛ ይሆንበታል። ያ ሁኔታ በሚዳ ያሉ ወደ ቤታቸው የመመለሻ ጊዜ እንኳን አጥተው በፍርሃት እንዲሸሹ (ማቴ. 24፡15-21) ያደርጋቸዋል። ዳንኤል 11፡40-41 ውስጥ የተጠቀሰው ወረራ፥ ተቃዋሚው “ከሠረገሎችና ከፈረሶች ከብዙም መርከቦች ጋር” ስለሚመጣ አስቀድሞ የታወቀ ይሆናል። ዳንኤል 11፡41 ውስጥ የተጠቀሰው የ“መልካሚቱ ምድር” መወረር ከሠራዊቱ አርማጌዶን ላይ መሰባሰብ ጋር ተዛማጅነት አለው ብዬ አምናለሁ። የክርስቶስ ተቃዋሚ “ዓለም አቀፍ ግብረ ኃይል” ያሰባስባል። ይህን የሚያደርገው፥ ዓለምን እንዳይገዛ የሚቃወሙትን ሁሉ ከያሉበት

---

* አንዳንዶች ጦርነቱ የሚካሄደው፥ በመጨረሻው ሰባት ዓመት አጋማሽ ላይ፥ ይህ ተቃዋሚ ሰው ኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተ መቅደስ በመሄድ እግዚአብሔር ነኝ በሚልበት ጊዜ እንደሚሆን ይገምታሉ።

ለማጥፋት ነው። ሠራዊቱ አርማጌዶን ላይ ይሰባሰብና በስተደቡብ ወደ ግብፅና ወደ አፍሪካ ይጓዛል። "እጁን በአገሮች ላይ ይዘረጋል፥ የግብፅም ምድር አታመልጥም። በወርቅና በብርም መዝገብ ላይ፥ በከበረችም በግብፅ ዕቃ ሁሉ ላይ ይሠለጥናል፤ የሊቢያና የኢትዮጵያ* ሰዎችም ይከተሉታል" (11፡42-43)።

ይሁን እንጂ፥ አንድ ድል ሌላ ዓመፅን ያስነሣል። "ከምሥራቅና ከሰሜን ግን ወሬ ያውከዋል፤ ብዙ ሰዎችንም ይገድል ዘንድና ፈጽሞ ያጠፋ ዘንድ በታላቅ ቁጣ ይወጣል" (11፡44)። ከምሥራቅና ከሰሜን የሚመጡት ወሬዎች ምንድናቸው? የሚጠፉትስ እነማን ይሆኑ? ዳንኤል የሚገልጠው የክርስቶስን ተቃዋሚ የመጨረሻ የአገዛዝ ቀኖች ከሆነ፥ አስፈሪው ወሬ የሚመጣው ከባቢሎን ሊሆን ይችላል። የባቢሎን ገዢ ምናልባት በዓረባውያን ወንድሞቹ ጥፋት በመቆጣት የነዳጅ አደላውን ለማቋረጥ ያስፈራራ ይሆናል። ወይም ደግሞ የወደፊቱ ታይቶት፥ እንደሚመጣ ከሚያውቀው ጦርነት ራሱን ለመከላከል ዝግጁነቱን ያሳያል። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፥ ወሬው ግን የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚሆነውን ሰው ያስጨንቀዋል። ለዚህ ነው ሠራዊቱን ለሌላ ዘመቻ፥ ጥፋትና ሽብር የሚያዘምተው። ባቢሎን ከግብፅ "በስተምሥራቅና ሰሜን" ትሆናለች። መጽሐፈ ራእይ እንደሚተነብየው፥ ኢየሱስ ወደ ምድር ከመመለሱ በፊት የክርስቶስ ተቃዋሚ ድል የሚያደርጋት የመጨረሻ ከተማ ባቢሎን ትሆናለች።

የክርስቶስ ተቃዋሚ "ከምሥራቅና ከሰሜን" የሚነሣበትን ችግር ካስወገደ በኋላ፥ የመጨረሻ ዘመቻውን ይጀምራል። "ንጉሣዊ ድንኳኑንም በባሕርና በከበረው በቅዱሱ ተራራ መካከል ይተክላል" (11፡45)። ዳንኤል የክርስቶስ ተቃዋሚና ሠራዊቱ የሚሠፍሩበትን ቦታ ስም ባይጠቅስም፥ ሠራዊቱ በመጨረሻ የሚያጠቃውን ስፍራ እናውቅ ዘንድ በዝርዝር ይነግረናል። ስፍራው የሚገኘው በሜድትራኒያን ባሕርና "የከበረና የተቀደሰ ተራራ" ከተባለችው የኢየሩሳሌም ከተማ መካከል ነው። የክርስቶስ ተቃዋሚ የመጨረሻ መድረሻ እስራኤል ናት። የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚያደርገው የመጨረሻ የጥፋት ዘመቻ "ዘመቻ ኢየሩሳሌም" ተብሎ ሊሰየም ይችላል።

---

* በግሪክኛ በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ከግብፅ በስተደቡብ ጥቁር ዐባይና ነጭ ዐባይ እስከሚገናኙበት የነበረ አገርና መንግሥት ነው (ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር)። ሠራዊቱ ግብፅንና አፍሪካውያን ተባባሪዎቿን በመውጋት እጃቸውን እንዲሰጡ ያስገድዳቸዋል። ይህን በማድረግ በስተደቡብ ያለ ደጀኑን አስተማማኝ ያደርገዋል።

ዘመቻ ኢየሩሳሌም

የክርስቶስ ተቃዋሚ እስራኤልን እንደ የውጊያ መነሻ ስፍራነት በመጠቀም ግብፅንና አፍሪካን ለመቆጣጠር፥ እንዲሁም ባቢሎንን ለመደምሰስና የመካከለኛው ምሥራቅን ቀሪ ክፍል ለመያዝ ሠራዊቱን ያዘምታል። "የጎን ውጋት" የሆኑበትን እነዚህን አገሮች በሚገባ ካጠፋቸው በኋላ፥ ላለፉት ሦስት ዓመታት ተኩል ሊያጠፋ ይሞክረው ወደነበረ ጠላት ፊቱን ይመልሳል። ዘመቻ ኢየሩሳሌም የሚያተኩረው፥ የእስራኤልን መዲና ፈጽሞ በማፈራረስና በምድሪቱ ላይ ያሉትን የእስራኤል ቅሪቶች በማጥፋቱ ላይ ነው።

ይህን የዘመኑን የመጨረሻ ጦርነት ነቢዩ ኢዮኤልም ገልጦታል። መንግሥታት እስራኤልን ለመውጋት የሚያደርጉትን ዝግጅት ውብ በሆነ አገላለጥ እንዲህ በማለት ያቀርበዋል፦ "ይህን በአሕዛብ መካከል አውጁ፤ ለሰልፍ ተዘጋጁ፤ ኃያላንን አስነሡ፤ ሰልፈኞች ሁሉ ይቅረቡ ይውጡም። ማረሻችሁን ሰይፍ፥ ማጭዳችሁንም ጦር ለማድረግ ቀጥቅጡ፤ ደካማውም፥ እኔ ብርቱ ነኝ ይበል። እናንተ በዙሪያ ያላችሁ አሕዛብ ሁሉ፥ ቸኩላችሁ ኑ፥ ተሰብሰቡ፤ አቤቱ ኃያላኖችህን ወደዚያ አውርድ። አሕዛብ ይነሡ፥ ወደ ኢዮሳፍጥ ሸለቆም ይውጡ፤ በዙሪያ ባሉ አሕዛብ ሁሉ ላይ እፈርድ ዘንድ በዚያ እቀመጣለሁና" (ኢዩ. 3፡9-12)።

በእስራኤል ላይ የሚደረገው የመጨረሻ ጦርነት የሚጀምረው፥ መንግሥታቱ ኢዮሣፍጥ ሸለቆ ውስጥ ሲሰበሰቡ ነው። ምናልባት ምሥራቅ ኢየሩሳሌም ውስጥ፥ ማለት በከተማይቱና በደብረ ዘይት ተራራ መካከል በሚያልፈው የቄድሮን ሸለቆ ውስጥ ይሆናል።

ነቢዩ ዘካርያስም ኢየሩሳሌም ላይ በሚዘመተው በዚህ የመጨረሻ ጦርነት ላይ በማትኮር እንዲህ ብሏል፦ "አሕዛብንም ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ ለሰልፍ እሰበስባለሁ፤ ከተማይቱም ትያዛለች፥ ቤቶችም ይበዘበዛሉ፥ ሴቶችም ይነወራሉ፤ የከተማይቱም እኩሌታ ለምርኮ ይወጣል፥ የቀረው ሕዝብ ግን ከከተማ አይጠፋም" (ዘካ. 14፡2)። ይህ ውጊያ በታሪክ ውስጥ የሚከናወን ሌላ ጦርነት ሳይሆን፥ በእስራኤል ላይ የሚዘመት የመጨረሻ ጦርነት መሆኑን እንዴት እናውቃለን? ዘካርያስ ቀጥሎ ባሉት ጥቂት ቁጥሮች እንዲህ በማለት መልሱን ይሰጠናል፦ "እግዚአብሔር ይወጣል፥ በሰልፍም ቀን እንደተዋጋ ከእነዚያ አሕዛብ ጋር ይዋጋል። በዚያ ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ ዘይት ላይ ይቆማሉ፤ ደብረ ዘይትም መካከል ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ይሰነጠቃል፥ እጅግም ታላቅ ሸለቆ ይሆናል፤ የተራራውም እኩሌታ ወደ ሰሜን፥ እኩሌታውም ወደ ደቡብ ይርቃል። የተራሮችም ሸለቆ እስከ አፀል

ይደርሳል፤ ...አምላኬ እግዚአብሔርም ከቅዱሳኑ ጋር ይመጣል'' (ዘካ. 14፡3-5)። በዘካርያስ የተገለጠውና በኢየሩሳሌም ላይ የሚደረገው ጦርነት የሚያበቃው፥ ኢየሱስ ሕዝቡን ለመታደግ ወደ ምድር ሲመለስ ብቻ ነው።

## ንጉሡ በመምጣት ላይ ነው

''የአርማጌዶን'' ዘመቻ በምድር ላይ የሚደረግ የመጨረሻ ጦርነት አይደለም። እንደውም አርማጌዶን የሚለው ቃል እራሱ ጦርነትን አያመለክትም። ስሙ የሚገልጠው፥ ለውጊያ የሚዘጋጀው ሠራዊት ለመጨረሻ ጦርነት የሚሰባሰብበትን ግዙፍ ሸለቆ ነው። ሠራዊቱ ከዚያ ተነሥቶ አፍሪካን ድል ለማድረግ ወደ ግብፅ ይጓዛል። ከዚያም በሰባቱ ዓመታት ውስጥ የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነውን ሰው ስትቆጣጠረው የቆየችውን የባቢሎንን ከተማ ለማውደም ወደዚያ ይተማል። በመጨረሻም የእስራኤልን ሕዝብ ከምድር-ገጽ ለማጥፋት ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳል።

ዳንኤል፥ ኢዩኤልና ዘካርያስ በክርስቶስ ተቃዋሚና በክርስቶስ መካከል የሚደረገው ጦርነት የሚከናወነው ኢየሩሳሌም ላይ ይሆናል ነው የሚሉት። እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲል በታሪክ ውስጥ ጣልቃ እንደሚገባና፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ ኢየሩሳሌም ላይ የሚያዘምተውን ሠራዊት የሚያጠፋ መሆኑን ነው ሦስቱም ነቢያት የሚተነብዩት። በዘካርያስ ትንቢት መሠረት ጦርነቱ የሚያበቃው፥ መሢሑ ወደ ምድር ሲመለስና እግሮቹ ደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሲያርፉ ነው። ጦርነቱ የሚጠቃለለው፥ በኢየሱስ ዳግም ወደ ምድር መምጣት ይሆናል። በክርስቶስና በተቃዋሚው መካከል የሚደረገው የፍጻሜ ውጊያ ምንኛ አስፈሪ ይሆን?

ሐዋርያው ዮሐንስ ራእይ 19፡11-21 ውስጥ ባለው ክፍል ትክክለኛውን ጦርነት ይገልጠዋል። ጦርነቱ ሲጀመር ''ታይቶ የማይታወቅ'' መስሎ ነው ለዓለም የሚታየው። ዮሐንስ በአምባላይ ፈረስ ላይ የተቀመጠውን ተዋጊ-ኢየሱስን በመጀመሪያ ያስተዋውቃል። ሰማይ ተከፍቶና ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ ሠራዊት ታጅቦ ወደ ምድር ሲመለስ የሚታየውን አስፈሪ ግርማ ዮሐንስ ገልጦታል (19፡14)። ኢየሱስ ድል አድራጊ ነው፥ በልብሱ ላይ ''የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ'' የሚል ስም ተጽፎበታል (19፡16)።

ትእይንቱ ይለወጥና አንድ መልአክ የምድር አዕዋፍን ሁሉ ወደ ጦርነቱ ይሰበስባቸዋል። እነዚህ አዕዋፍ ከሁሉ የላቀ ምድራዊ ሠራዊት ከሰማይ ሠራዊት ጋር የሚያደርገውን ''ጦርነት ፍጻሜ'' ይመለከታሉ። ይህ ብቻም አይደል፥ ከጦርነቱ በኋላ ምድርን የሚሸፍነውን የሰዎች በድን ሥጋ እንዲበሉም ይጋበዛሉ።

ዮሐንስ ከዚህ ቀጥሎ የሚያሳየን፥ አምባላይ ፈረስ ላይ የተቀመጠውን የሚዋጉትን ተዋጊዎች ነው። "በፈረሱም የተቀመጠውን፥ ጭፍሮቹንም ይወጉ ዘንድ አውሬውና የምድር ነገሥታት ጭፍራዎቻቸውንም ተከማችተው አየሁ" (19፡19)። የክርስቶስ ተቃዋሚና ሠራዊቱ ዓለም ልታሰባስበው የሚቻላትን ኃይል ሁሉ ይወክላሉ። ወደ ኢየሩሳሌም መጥተዋል፤ ኢየሱስ በዙፋኑ ላይ ሊቀመጥ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ የመጨረሻ እንቅፋት የሚሆኑት እነርሱ ናቸው።

እስከዛሬ ከተደረጉት ሁሉ እጅግ የላቀውን ጦርነት ለመመልከት በግንባር ረድፍ ባሉ መቀመጫዎች ላይ አረፍ እንላለን። ተቀናቃኞቹ በየፊናቸው ብርቱዎች ናቸው። የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነው ሰውም ሰይጣን ሊያቀርበው ከሚቻለው ሁሉ የላቀና ዓለምን የሚቆጣጠራትን ከፉ መንግሥት የሚወክል ነው። ክርስቶስ ደግሞ እግዚአብሔር የሚያቀርበውና ከሁሉ የላቀ ሲሆን፥ አመጣጡም እንደ ታዳጊና ዓለምን ለመግዛት የእግዚአብሔር ሥልጣን እንዳለው ገናና ሆኖ ነው። ደወሉ ያቃጭላል፤ ተፋላሚዎቹም ወደ መፋለሚያው መድረክ መሀል ይመጣሉ። ውድድሩ የሚያበቃው በአንድ ምት ነው፦

> "አውሬውም ተያዘ፥ በእርሱም ፊት ተአምራትን እያደረገ የአውሬውን ምልክት የተቀበሉትን፥ ለምስሉም የሰገዱትን ያሳተ ሐሰተኛው ነቢይ፥ ከእርሱ ጋር ተያዘ፤ ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ። የቀሩትም በፈረስ ላይ ከተቀመጠው፥ ከአፉ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ፤ ወፎችም ሁሉ ከሥጋቸው ጠገቡ" (ራእይ 19፡20-21)። ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ነው የሚያበቃው።

ኢየሩሳሌም ላይ የሚካሄደው የአርማጌዶን ጦርነት፥ ታሪክ ከሚያውቃቸው ጦርነቶች ሁሉ በአጭሩ የተቀጨ ነው። ሠራዊቱ በሁለቱም ወገን እንደሚከማቹ ዮሐንስ ይገልጣል። በመልካምና በክፉ ኃይላት መካከል የሚደረገውን አስደናቂ ፍልሚያ ልንመለከት ነው። ይሁን እንጂ፥ አንድ ሰው የቱንም ያህል ኃያል ቢሆን፥ ከእግዚአብሔር ብርቱ ክንድ አንጻር ምንም አይደለም።

ነቢዩ ኢሳይያስ፥ ምድር ላይ የሚሰባሰበው ብርቱ ኃይል ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ሲነጻጸር የሚመስለውን እንደሚከተለው ይገልጠዋል፦ "እነሆ አሕዛብ በገንቦ እንዳለች ጠብታ ናቸው፥ በሚዛንም እንዳለች ትንሽ ትቢያ ተቆጥረዋል . . .። አሕዛብ ሁሉ በፊቱ እንዳልነበሩ ናቸው። ከምናምን እንደሚያንሱ እንደ ከንቱ ነገርም ይቆጠራቸዋል"

(ኢሳ. 40፡15፥ 17)። በእግዚአብሔር ኃይል ፊት የክርስቶስ ተቃዋሚና ሠራዊቱ በቅፅበት ይጠፋሉ።

የክርስቶስ ተቃዋሚና ረዳቶቹ ተይዘው ወደ ዘላለም ቅጣት ይጣላሉ። እግዚአብሔር ነኝ ይል የነበረው ሰው ፍጻሜ በዚህ ሁኔታ በውርደት ይደመደማል። ኢየሩሳሌምን ለመውጋት የተሰባሰበው ግዙፍ ሠራዊትም፥ ክርስቶስ አንድ ቃል ብቻ ሲናገር ወደ ሬሳነት ይለወጣል። የሠራዊቱ አባላት የያዙትን መሣሪያ ለመተኮስ እንኳን ዕድል አይኖራቸውም። አርማጌዶን ላይ የተጀመረው መሰባሰብ በኢየሱስ ድል አድራጊነት ያበቃል። እርሱም "የንጉሦች ንጉሥና የጌቶች ጌታ" የሚለውን ዘላለማዊ ክብር ይይዛል።

# > ክፍል አራት <

# ትንቢት፤ የነገዎቹ አርእስተ ዜናዎች የዛሬዎቹን ፍላጎቶች የሚያረኩት እንዴት ነው?

እውነት ሁሉ የእግዚአብሔር እውነት ይሆን ይሆናል፤ አንዳንድ እውነቶች ግን ከሌሎች ይልቅ ተግባራዊ የሚሆኑና አግባብነት ያላቸው ናቸው። የአንድ ክብ ነገር ዙሪያ ልክ 3.14159 ከክቡ አጋማሽ መሥመር ልክ ጋር ተባዝቶ ከሚሰጠው ቁጥር ጋር ተመሳሳይ መሆኑ የሕይወት እውነት ነው። የመሬት ስበት ኃያል ነገሮችን በተመሳሳይ ፍጥነት ወደ ምድር እንብርት እንዲወድቁ ማድረጉም የዚሁ ተመሳሳይ እውነት ነው። አንድ ሰው የቤቱን ጣሪያ ቀለም ለመቀባት በጣሪያው ጠርዝ በኩል እጁን ቢዘረጋ ከመጀመሪያው ይልቅ የሚያሳስበው፥ የኋለኛው እውነት ውጤት ነው።

የእግዚአብሔር ነቢያት፥ እግዚአብሔር ለፍጡራኑ ያለውን የወደፊት ዕቅድ ለማወጅ የጊዜን መጋረጃ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጠዋል። ከትንቢቶቻቸው ብዙዎቹ ኢየሱስ መጀመሪያ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ተከናውነዋል። ብዙዎቹ ትንቢቶች ግን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት ዳግም ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ የሚከናወኑ ናቸው። ትንቢት የእግዚአብሔር ቃል እውነት አካል ነው።

ብዙ ሰዎች ግን የወደፊት ሁኔታዎችን የሚገልጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለማጥናት አይፈልጉም። ለምን? ሁለት ምክንያቶች አሉ፤ እነሱም የተዓማኒነትና የጥቅም ጉዳዮች ናቸው።

ተዓማኒነት። እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች መናገሩን እንዴት አውቃለሁ? ብዙ ቅን ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የተጠቀሱ ትንቢቶችን በተመለከተ ያላቸው አመለካከት የሚስማማ አይደለም። እኔስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ሁኔታዎች የሚከናወኑ ስለመሆናቸው እርግጠኛ ልሆን እችላለሁ? እርግጠኛ ካልሆንኩ የትንቢቱን ክፍል "እንዳለ ትቼ"፥ እርግጠኛ የሆንኩባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብቻ አጠናለሁ።

ጥቅም። መጽሐፍ ቅዱስ ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች ቢተነብይ፥ ምን ይሁን ታዲያ? መጽሐፉ የሚተነብየው እኔ ከሞትኩ በኋላ ስለሚከናወኑ ነገሮች ስለሆነ፥ ትንቢትን ማጥናቱ ምን ይጠቅመኛል? ከዚያ ይልቅ፥ ዛሬ ለኢየሱስ እንዴት መኖር እንደሚገባኝ የሚነግሩኝን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ባጠና ይሻለኛል። ዛሬ ከአስቸጋሪ ነገሮች ጋር መታገሌን ትቼ ለምንድነው ስለ ወደፊቱ የማጠናው?

እግዚአብሔር በእርግጥ ስለ ወደፊቱ ተንብዮአል? ከሆነ ትንቢቱ ዛሬ ለኔ የሚሰጠኝ ጥቅም አለ? የምዕራቡ ዓለም ሥልጣኔ በተዓማኒነትና ጥቅም ጉዳዮች ተጠምዷል። በዚህ ሳቢያ ነው፥ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢቶች ላይ እንዲያተኩሩ እነዚህ ሁለት አስቸጋሪ ጠላቶች፥ ማለት የተዓማኒነትና የጥቅም ችግሮች የተደቀኑባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይኖረዋል? መልሱ አዎ እንደሚሆን አምናለሁ። ይህ የዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል፥ የነገዎቹ አርእስተ ዜናዎች የዛሬዎቹን ፍላጎቶች የሚያረኩበትን ሁኔታ ያሳያል።

> ምዕራፍ አስራ ስድስት <

# እግዚአብሔር በእርግጥ የወደፊቱን ሁኔታ ይተነብያል?

አንድ ጸሐፊ ምን ይላል፡-

"የብሉይ ኪዳን ትንቢታዊ ዘገባዎች ዓላማ ምንድነው? የሚመጡ ዘመናትን የዓለም ታሪክ ንድፍ ወይም ዕቅድ መግለጥ፥ ወይስ ለመሢሑ በእስራኤል ሕልውና ውስጥና ዘመን መምጣት ዝግጅት ማድረግ? ዓላማው በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዙሪያ የሚሆኑ ሁነቶችን መግለጥ፥ ወይስ እግዚአብሔር ሰውን ከኃጢአት ነጻ ለማውጣት ያለውን ዕቅድ ለመተግበር ክርስቶስ መጀመሪያ ወደ ምድር የሚመጣበትን ሁኔታ ለማከናወን የሚደረግ ዝግጅት? ሁለቱም ጥያቄዎች ውስጥ ሁለተኛዎቹ አማራጮች ናቸው ትክክሎቹ።"

እግዚአብሔር የወደፊት ሁነቶችን ለመተንበይ ይፈልጋል ወይስ ከላይ እንደተገለጠው፥ ለዘመናት ያለውን ዕቅድ ለማወቅ ስንሻ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በፈለግነው መንገድ እየተረጎምን ነው የምናነበው? ይህ ጉዳይ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ጠልቆ የሚገባና፥ መጽሐፍ ቅዱስን በምንፈታበት ወይም በምንተረጉምበት ዘዴ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን የሚያምን ሁሉ፥ ይህን ጉዳይ ልብ ማለት ይኖርበታል። የሚያሳዝነው ነገር ግን፥ ብዙ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢትን ጉዳይ ለመመርመር አለመድፈራቸው ነው።

ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሊጠቀሙበት አይፈልጉም። አንዳንዶቹም ያልተለመዱ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ትንቢቶችን ሲያነቡ ደስተኛነት አይሰማቸውም። ብዙዎቹ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የወደፊት ሁነቶችን ይተነብያል ወይስ አይተነብይም ብለው እንዲጠይቁ የሚያስገድዷቸውን ክፍሎች ሳያነቡ ማለፍን ይመርጣሉ። እንዲህ ማድረጉ "ለትምህርትና ለተግሣጽ፥ ልብንም ለማቅናት፥ በጽድቅም ላለው ምክር" (2ኛ ጢሞ. 3፡16) ይበጅ ዘንድ ከእግዚአብሔር ከተሰጠን ቃል ብዙው እንዲያልፈን ያደርጋል። እነዚህን ጠቃሚ ክፍሎች ከመዝለል ችግሩን መፍታቱ የተሻለ ይሆን ነበር።

### ብታምኑም ባታምኑም

ሮበርት ሪፕሊ የተባለ የሂሳዊ ምስሎች እውቅ ሠዓሊ የሥዕል ሥራውን የጀመረው በ1918 እአአ በሣለውና "ብታምኑም ባታምኑም" በሚለው ሥዕሉ ነው። እንግዳ፥ ያልተለመዱና ልዩ ሥዕሎችን ሥሏል።

አንዳንዶቹ ግራ የሆኑና የማይታመኑ ቢመስሉም፥ እውነት ነበሩ። ከሠዓሊው ሥራዎች የምናገኘው ትምህርት፥ አንዳንዴ እውነት ከልብ ወለድ ይልቅ እንግዳ ናት የሚለው ሳይሆን አይቀርም።

እግዚአብሐር ነቢያት ቃሉን እንዲጽፉ በመራቸው ጊዜ፥ ስለ ወደፊቱ እንዲተነብዩ ያስቻላቸው መሆኑን ለማመን እንችላለን? የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢታዊ ይዘት ለመመርመር የሚያስችል ተጨባጭ አሠራርስ ይኖራል? እግዚአብሔር ቃሉን በሰጠን ጊዜስ ወደፊት ሊሆን ያለውን ነገር ሊያሳውቀን መሻቱን የሚጠቁም ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን? አዎ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ለጥያቄዎቹ መልስ አለው።

## እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን እንደሚገልጥ ያሳውቃል

ነቢዩ ኢሳይያስ የኖረው፥ ፖለቲካዊና ሥነ-ምግባራዊ ቀውስ በሰፈነበት ዘመን ነው። እግዚአብሔር በነቢይነት የጠራው፥ ንጉሥ አዛርያስ በሞተበት ዓመት ነበር። የንጉሡ ኀምሣ ሁለት ዓመት የአገዛዝ ዘመን አቻ የሌለው ሠላምና ብልጥግና የሰፈነበት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ንጉሡን የሚገልጠው "በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አደረገ" (2ኛ ነገ. 15፥3) በማለት ነው። ይሁን እንጂ፥ መልካሙን አገልግሎቱን በአንድ የሞኝነት ድርጊቱ በከለው። በትዕቢት ተሞላና የካህናቱን ሥልጣን በመንጠቅ በቤተ መቅደስ መሠዊያ አጠነ። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር በለምጽ መታውና ቀሪ ዕድሜውን በብቸኝነትና በመገለል አሳልፎ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ740-739 ዓ.ዓ. በነበረው ጊዜ መካከል ሞተ።

በቀጠሉት አሥር ዓመታት ይሁዳ በነገር ሁሉ ስታሽቆለቁል ኢሳይያስ ተመለከታት። አገሪቱ በንጉሥ አዛርያስ ዘመን ከነበረችበት ብርቱ መንግሥትነት፥ ከአሻንጉሊትነት ብዙም ወደማትሻልበት ሁኔታ አሽቆለቆለች። ይህ የሆነው የንጉሥ አዛርያስ የልጅ ልጅ፥ አካዝ በነገሠ ጊዜ ነው። አካዝ የይሁዳን ነጻነት ለአሦር አሳልፎ ሰጠ። ይህን ያደረገው፥ በስተሰሜን ካሉ ጠላቶቿ የሚመጣባትን ጥቃት አሦር ትከላከልላት ዘንድ ነበር። አሦርም ለምትሰጠው "የመከላከል" አገልግሎት የሚገባትን ክፍያ ትሰጣት ዘንድ ይሁዳን አስገደደቻት። በዚህ መሠረት ይሁዳ ሉዓላዊነቷን አጣችና ሀብቷ ሁሉ በአሦር ተበዘበዘ።

ንጉሥ ሕዝቅያስ በአባቱ በአካዝ ምትክ ነገሠ። የኋላ ኋላ የአሦር ንጉሥ በሞተ ጊዜ፥ ሕዝቅያስ ከሌሎች የብዙ አገር ነገሥታት ጋር በመሆን ነጻነቱን አወጀና፥ በአሦር የተጣለበትን የገንዘብ ዕዳ መክፈሉን አቆመ።

አዲሱ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ዙፋኑን አገሩ ውስጥ ከነበሩ ተቀናቃኞች ሲከላከል ቆየና፥ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ703 ያመፁበትን መንግሥታት እንደገና ለመያዝ ወታደሩን አዘመተ። ዘመቻው ሁለት ዓመት ቢወስድበትም በ701 ዓ.ዓ. ሠራዊቱ ይሁዳን አጥለቀለቃት።

ኢሳይያስ የሰናክሬምን አሠቃቂ ወረራ እንዲህ በማለት በአጭሩ ገልጦታል፡- "በንጉሡ በሕዝቅያስ በአሥራ አራተኛው ዓመት፥ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ወደ ይሁዳ፥ ወደ ተመሸጉት ከተሞች ሁሉ ወጥቶ ወሰዳቸው። የአሦርም ንጉሥ ራፋስቂስን ከብዙ ሠራዊት ጋር ከለኪሶ ወደ ንጉሡ ወደ ሕዝቅያስ ወደ ኢየሩሳሌም ላከ" (ኢሳ. 36፡1-2)። ሌላ ጽሑፍ ውስጥ እንደተገለጠው ሰናክሬም እራሱ ወረራውን አስመልክቶ እንዲህ በማለት ይበልጥ ግልጥ የሆነ ትንታኔ ሰጥቷል፡- "አይሁዳዊው ሕዝቅያስ ቀንበሬን ለመሸከም አልወደደም፤ አርባ ስድስት ከተሞቹን፥ የተገነቡ ምሽጎቹን፥ አያሌ መንደሮችንና አካባቢያቸውን ከብቤ ድል አደረኳቸው። ...እርሱንም ጎጆዋ ውስጥ እንዳለች ወፍ አድርጌ መናገሻው በሆነችው ኢየሩሳሌም ውስጥ አሠርኩት"።

ንጉሥ ሕዝቅያስ ከሰናክሬም ማስጠንቀቂያ በደረሰው ጊዜ፥ ኃያል የነበረውን የአሦር ሠራዊት ለመከላከል መሞከሩ የሚያስከትልበትን አስከፊ ውጤት ተረዳ። በመሆኑም እውነተኛ የእምነት ሰውነቱን ያረጋገጠ እርምጃ ወሰደ፡- "ሕዝቅያስም ደብዳቤውን ከመልእክተኞች እጅ ተቀብሎ አነበበው፤ ሕዝቅያስም ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው" (ኢሳ. 37፡14)። የአረመኔውን ንጉሥ ዛቻ ለእግዚአብሔር ለማሳየት ነው ሕዝቅያስ የፈለገው። ከዚያም ለሰው የማይቻለውን ነገር ያደርግና ይሁዳን ይታደጋት ዘንድ እግዚአብሔርን እንዲህ ጠየቀ፡- "እንግዲህም አምላካችን አቤቱ፥ የምድር ነገሥታት ሁሉ አንተ ብቻ እግዚአብሔር እንደሆንህ ያውቁ ዘንድ ከእጁ አድነን" (ኢሳ. 37፡20)።

እግዚአብሔርም የሕዝቅያስን ጸሎት ሰማ፡- "የእግዚአብሔር መልአክ ወጣ፥ ከአሦራውያንም ሰፈር መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ገደለ" (ኢሳ. 37፡36)። ሰናክሬምም በነቃ ጊዜ የተመለከተው፥ ሰብአዊ ሠራዊት ሊያደርግ የማይችለውን እግዚአብሔር ማድረጉን ነበር። ገናናው የአሦር ሠራዊት ሙታኑን ከቀበረ፥ መጓሪያውን ከሰበሰበና የሠላም ስምምነት ከተፈራረመ በኋላ ከይሁዳ ወጣ። ይሁዳ እንደገና ለአሦር ግብር መክፈሏን ብትቀጥልም፥ ሕዝቅያስ የይሁዳ ምድር ንጉሥ መሆኑ ጸና። በአሦር ንጉሥ ላይ ያመፀና በዙፋኑ ላይ የቆየ ንጉሥ ሕዝቅያስ ብቻ ነበር።

ሕዝቅያስ በአሦራውያን ላይ የተቀዳጀው ታላቅ "ድል" ታዋቂነትን ቢያስገኝለትም፥ በአንጻሩ ግን የይሁዳን የመጨረሻ ዕድል

ዘጋው። የቀድሞው የባቢሎን ንጉሥ መሮዳክ ባልደን ወደ ሕዝቅያስ መልእክተኞችን ሰደደ። የመልእክተኞቹ ግልጥ አመጣጥ፥ ሕዝቅያስን እንኳን ከሕመምህ ተሻለህ ለማለት ቢሆንም፥ የፈለጉት ዋና ነገር ግን፥ ሕዝቅያስ የአሦርን ንጉሥ ድል ለማድረግና በዙፋኑ ላይ ሊቆይ የቻለበትን ምሥጢር ለማወቅ ነበር። መሮዳክ ባልዳን እንደ ሕዝቅያስ ዕድለኛ አልነበረም። ሰናክሬም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ703 ባቢሎንን በመውጋት መሮዳክ ባልዳንን አባሮት ነበር። በመሆኑም ቀሪ ዕድሜውን የገፋው ዙፋኑን ለማስመለስ ያልተሳካ ሙከራ በማድረግ ነበር።

መልእክተኞቹ ሕዝቅያስን በማወደስ እንዲህ የሚሉት መሆኑን ለመገመት ይቻላል፦ “ጤናህ የተሟላ ሆኖ በማግኘታችን እጅግ ደስ ብሎናል። ዓለም እንዳንተ የአሦርን እብሪተኞች የሚመክቱ መሪዎችን ትሻለች”። ከዚያም ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው የጉብኝታቸውን እውነተኛ ዓላማ እንዲህ ይገልጣሉ፦ “ሕዝቅያስ ጌታችን ሆይ! መሮዳክ ባልዳን ባቢሎን ያለውን ዙፋኑን ለማስመለስ በመጣር ላይ ነው። በመሆኑም ንጉሥ ሰናክሬምን ለመውጋት ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ እንሻለን። እስቲ ንገረን ሕዝቅያስ፥ አሦራውያንን ከምድርህ ለማባረር የቻልከው እንዴት ነው? የአሦርን ሠራዊት እንዴት ድል አደረክው?”።

ሕዝቅያስ ኢየሩሳሌም ውስጥ ያለውን ቤተ መቅደስ ለእነዚህ መልእክተኞች እያሳየ ስለ እስራኤል አምላክ ለመንገር እንዴት ያለ ድንቅ ዕድል ገጥሞት ነበር? ነገር ግን በመኩራራት መንፈስ ተሸፈነና ከእስራኤል አምላክ ክብር ይልቅ፥ የራሱን (የሕዝቅያስን) ክብር ገለጠላቸው፦ “ሕዝቅያስ ደስ አለው፥ ግምጃ ቤቱንም፥ ብሩንና ወርቁንም፥ ቅመሙንና የከበረውንም ዘይት፥ መሣሪያም ያለበትን ቤት ሁሉ፥ በቤተ መዛግብቱም የተገኘውን ሁሉ አሳያቸው፤ በቤቱና በግዛቱ ሁሉ ካለው ሕዝቅያስ ያላሳያቸው የለም” (ኢሳ. 39፡2)።

የሕዝቅያስ አሳዛኝ ኩራት የተገለጠው በ700 ዓ.ዓ. ነው። እግዚአብሔርም በሕዝቅያስ የሞኝነት ድርጊት ሳቢያ፥ በይሁዳ ላይ የሚመጣውን የፍርድ ትንቢት አስይዞ ኢሳይያስን ላከው፦

> “እነሆ በቤትህ ያለው ሁሉ፥ አባቶችህም እስከዛሬ ድረስ ያከማቹት ሁሉ ወደ ባቢሎን የሚፈልስበት ወራት ይመጣል፤ ምንም አይቀርም፥ ይላል እግዚአብሔር። ከአንተም ከሚወጡት ከምትወልዳቸው ልጆችህ ማርከው ይወስዳሉ፤ በባቢሎንም ንጉሥ ቤት ውስጥ ጃንደረቦች ይሆናሉ” (ኢሳ. 39፡6-7)።

ይህ ነበር በይሁዳ ምድር ላይ የተነገረ ግልጥ ትንቢት። ኢሳይያስ፥ አሦራውያን ያቃታቸውን ባቢሎናውያን የሚያደርጉት መሆኑን ገልጦ ይናገር የነበረው እግዚአብሔር በገለጠበት መሠረት ነው። ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን ወረው ከተማይቱን ይበዘብዛሉ። እግዚአብሔር ቀደም ብሎ የሕዝቅያስን ሕይወት ታድጎ ነበር። ከእርሱ የሚወለዱት ግን ወደ ባቢሎን ይማረካሉ።

የኢሳይያስ ትንቢት የተፈጸመው እንዴት ነበር? ኢሳይያስ ቃሉን በጽሑፍ ካሰፈረ ከአንድ ክፍለ-ዘመን በኋላ፥ ልክ ኢሳይያስ እንደተነበየው እግዚአብሔር ፈጽሞታል። የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ወረራት። ሠራዊቱ ሦስት ጊዜ ወደ ከተማይቱ ዘለቀ። በእያንዳንዱ ጊዜ ምርኮኞችንና የበዘበዘውን ነገር ወደ አገሩ አጋዘ። ነቢዩ ዳንኤል የኢሳይያስን ትንቢት በግልጥ ይጠቅሳል። ናቡከደነፆር ቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረውን ነገር ከመዝረፍ ባሻገር፥ "ከእስራኤል ልጆች ከንጉሥታቱና ከመሳፍንቱ ዘር" በምርኮ ወደ ባቢሎን ወሰደ (ዳን. 1፥3)፤ ልክ ኢሳይያስ ከመቶ ዓመት በፊት እንደተነበየው ማለት ነው።

ኢሳይያስ አይሁዶች በምርኮ ወደ ባቢሎን እንደሚወሰዱ እርግጠኛ ስለ ነበር፥ በመጽሐፉ ቀሪ ክፍል ለነዚሁ በምርኮ ለሚወሰዱ ሰዎች ሲናገር ነው የቆየው። ትንቢቱን የጻፈው በ700 ዓ.ዓ. ቢሆንም፥ ከዚያ በኋላ ስለሚከናወኑ አንዳንድ ሁኔታዎች ተንብይዋል።* ከእነዚህ ትንቢቶች በብዙዎቹ ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች የሚናገር መሆኑን ነው እግዚአብሔር የሚገልጠው። የኢሳይያስን ጽሑፍ ያንብቡና እግዚአብሔር የሚናገረው ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች መሆን አለመሆኑን ይረዱ።

ብቻውን አምላክ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲል ነው እግዚአብሔር ወደፊት የሚከናወኑ ነገሮችን አስቀድሞ የሚናገረው። ወደፊት የሚሆኑ ነገሮች እውቀት የሚኖረው፥ የዓለማት ሁሉ ገዢ የሆነ እውነተኛ አምላክ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ወደ ሐሰተኛና የአረመኔ አማልክት ዞር ብሎ እንዲህ ይላል፦ "እኔ ብቻ አምላክ የመሆኔ ማረጋገጫ ይሄው። በነቢዩ በኢሳይያስ ዘመን የሚሆኑ ነገሮችን እጽፋለሁ፤ እናንተም ነገሮቹ ተከናውነው ስትመለከቱ አስቀድሜ እንደተናገርኳቸው ታውቃላችሁ"። እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን ይገልጥና፥ ትንቢቶቹ መለኮታዊነቱን እንደሚያረጋግጡ ያስገነዝባል፦ "ያምጡ የሚሆነውንም ይንገሩን፤ ልብም እናደርግ ዘንድ ፍጻሜያቸውን እናውቅ ዘንድ፤

* ለምሳሌ ከተነበየ ከ114 ዓመት በኋላ የኢየሩሳሌም ከተማ በ586 ዓ.ዓ. ወደቀች።

የቀደሙት ነገሮች ምን እንደሆኑ ተናገሩ፥ የሚመጡትንም አሳዩን። አማልክትም መሆናችሁን እናውቅ ዘንድ በኋላ የሚመጡትን ተናገሩ" (ኢሳ. 41፡22-23)።

እግዚአብሔር፥ አማልክት ነን ለማለት የሚሹትን ሁሉ በመገዳደር፥ ሕዝቦች እንደ እስራኤል አምላክ ጠላትነት ለይተው እንዲያውቋቸው መሻቱን፥ ኢሳይያስ ከጥቂት ምዕራፎች በኋላ እንዲህ ገልጧል፦ "እንደእኔ ያለ ማነው? ይነሣና ይጥራ፥ ይናገርም፤ ከጥንት የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅልኝ፥ የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ" (ኢሳ. 44፡7)። እግዚአብሔር የወደፊቱን እናገራለሁ አደርገዋለሁም ይላል። የወደፊቱን የሚናገረው፥ ትንቢቱ በትክክል በተፈጸመ ጊዜ እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን ሕዝቡ ያውቅ ዘንድ ነው።

እግዚአብሔር የወደፊቱን እናገራለሁ ይላል። ታዲያ በዚህ የኢሳይያስ መጽሐፍ ክፍል በተለይ የተናገረው ምንድነው? እጅግ አስደናቂው ትንቢት የሚገኘው ኢሳይያስ 45 ውስጥ ነው።

> "እግዚአብሔር ለቀባሁት፥ አሕዛብንም በፊቱ አስገዛ ዘንድ፥ የነገሥታትንም ወገብ እፈታ ዘንድ፥ በሮቹም እንዳይዘጉ፥ መዝጊያዎቹንም በፊቱ እከፍት ዘንድ ቀኝ እጁንም ለያዝኩት ለቂሮስ እንዲህ ይላል...። ስለ ባሪያዬ ስለ ያዕቆብ፥ ስለ መረጥኩትም ስለ እስራኤል ብዬ በስምህ ጠርቼሃለሁ፤ በቁልምጫ ስምህ ጠራሁህ፥ አንተ ግን አላወቅኸኝም። እኔ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። ከእኔም ሌላ ማንም የለም" (45፡1፥4-5)።

ቂሮስ የተባለ አንድ ሰው አይሁዳውያንን ከባቢሎን ባርነት ነጻ የሚያወጣቸው መሆኑ ኢሳይያስ 45 ውስጥ ተተንብዮዋል። ይህ ትንቢት በኢሳይያስ ከተነገረ ከ160 ዓመት በኋላ የሜዶ-ፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ባቢሎናውያንን ድል በማድረግ አይሁዳውያን ወደ ምድራቸው እንዲመለሱ የሚፈቅድ ሕግ አወጀ።

ትንቢቱ አእምሮ ሊቀበለው ከሚቻለው በላይ ነው። እግዚአብሔር የወደፊቱን እንደገና በሚገልጥበት ክፍል፥ የትንቢቱንም ምሳሌ ያመለክታል። ይሁዳ በባቢሎን የምትያዝ መሆኗን ብቻ (ኢሳይያስ ቃሉን ከተነበየ አንድ መቶ ዓመት በኋላ የተፈጸመው) ሳይሆን፥ ቂሮስ በሚባል ድል አድራጊ አማካይነት ይሁዳ ነጻ የምትወጣ መሆኗንም ነበር እግዚአብሔር የተናገረው። የእግዚአብሔር ትንቢቶች ግልጥና ዝርዝር ሲሆኑ፥ እንደተናገረው በትክክል ተፈጽመዋል።

## የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት ሌሎች አምነዋል

በከፋ ድርቅ ይመታ ስለ ነበረ አንድ ኅብረተሰብ የተነገረ ታሪክ አለ። የበቆሎ ሰብላቸው በፀሐይ ንዳድ ሲጠወልግ ገበሬዎች በተስፋ መቁረጥ ይመለከቱ ነበር። ምድሪቱ ተሰነጣጥቃለች፥ አቧራው በአውሎ ንፋስ እየተነዳ በመስኩ ላይ ይሽከረከራል። ሰማይ ላይ ምንም ደመና ሳይታይ ሳምንታት አለፉ። ጭንቀትና ድንጋጤው እየከፋ ሲመጣ፥ ማኅበረሰቡን የምታገለግለው ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ድርቁን ያስወግድ ዘንድ ምዕመኑ ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልይ አወጀች። ለጸሎት የተወሰነው ዕለት ደረሰና ሕዝቡ ለጸሎት ወደ ቤተክርስቲያን መጣ። መንደሪቱ ለዝናብ ጥየቃ ጸሎት ሕዝቡን ባስተባበረችበት በዚህ ስብሰባ ላይ፥ ገበሬዎች ከባንክ ሠራተኞችና ከሌሎች የቢሮ ሰዎች ጎን ተቀመጡ። በዚህ ወቅት አንዲት ሴት ጃንጥላ ይዛ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገባች። ይህን ያዩ አንዳንድ ሰዎች "ምን ሊያደርግልሽ ነው ጃንጥላ የያዝሽው?" በማለት ጠየቋት። "ዝናብ እንዲዘንብልን በመጸለይ ላይ ስለሆንን ነዋ!" አለች ሴቲቱ። እግዚአብሔር የተጠየቀውን እንደሚፈጽም የሚያምን ልብ ነበራት።

እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን የሚተነብይ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጧል! ይሁን እንጂ፥ የተናገረውን እንደሚፈጽም ሰዎች አምነው እንደነበር የሚያመለክት አንዳች ማረጋገጫ አለ? እግዚአብሔር የሚናገረው ትንቢት ሊፈጸም ያለው ነገር ትክክለኛ ምሥል መሆኑ ገብቷቸዋል? ወይስ ቃሉ ግልጥ ያልሆነ እንቆቅልሽ መሰል ነገር ሆኖባቸዋል? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችለው አንድ መንገድ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የእግዚአብሔርን የትንቢት ቃል የተረዱበትን ሁኔታ መመርመር ነው። እስቲ የአንዳንዶቹን ጽሑፍ እያነበብን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈረን ትንቢት የፈቱበትን ዘዴ እንቃኝ።

መጀመሪያ የምንነበኘው፥ የባቢሎን ዙፋን አማካሪ የነበረውን ዳንኤልን ይሆናል። ዳንኤል የንጉሥ ናቡከደነፆር አማካሪ በመሆን አገልግሏል። ገና በልጅነቱ በምርኮ ወደ ባቢሎን ከተወሰደ በኋላ፥ ለዚህ ከፍተኛ ማዕረግ የበቃው፥ ለእግዚአብሔር በነበረው የማይናወጥ ታማኝነት ምክንያት ነው። አንድ የእግዚአብሔር ሰው የሆነ መሪ ሊኖረው የሚገባውን ባሕርይ የተላበሰ ነበር።

ምንም እንኳን የዕድሜውን አብዛኛውን ክፍል ያሳለፈው ከኢየሩሳሌም ርቆ ቢሆን፥ ከአምላኩ ግን ርቆ አያውቅም። ስለ ዳንኤል ግላዊ ሕይወት ያለን ጥቂት ዕውቀት፥ ዳንኤል ሕይወቱን በእግዚአብሔር

እምነት ላይ የመሠረተ የጸሎት ሰው መሆኑን ይገልጣል። ይህን የሕይወቱን ሁኔታ ጠላቶቹ እንኳን ተገንዝበውታል፡- ‘‘ከአምላኩ ሕግ በቀር በዚህ በዳንኤል ላይ ሌላ ሰበብ አናገኝበትም አሉ’’ (ዳን. 6፡5)። ዳንኤል የእግዚአብሔርን ቃል አንብቧል፥ አጥንቷል፥ ታዟል።

ዳንኤል ዕድሜው ከገፋ በኋላ የምናይበት ባሕርይ የጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል የማጥናት ልምድ ነበር። በመጽሐፉ ምዕራፍ 9 ውስጥ እንደምንረዳው፥ በጸሎት እንዲተጋ የሚያደርገው ጥልቅ ጉዳይ ከኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥ አግኝቷል። በሕይወቱ ላይ እንዲህ ያለ ለውጥ እንዲያመጣ ያደረገውና በኤርምያስ መጽሐፍ ያገኘው ነገር፥ በእግዚአብሔር በግልጥ የተነገረ ትንቢት ነበር።

ኢየሩሳሌም በባቢሎን የምትጠፋ መሆኑን ነበር ኤርምያስ ያወጀው። ኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ የነበረውን ፍርድ ባስታወቀበት የመጨረሻ ትንቢቱ እንዲህ ብሏል፡- ‘‘ይህችም ምድር ሁሉ ባድማና መደነቂያ ትሆናለች፤ እነዚያም አሕዛብ ለባቢሎን ንጉሥ ሰባ ዓመት ይገዛሉ’’ (ኤር. 25፡11)። ኢየሩሳሌም ለሰባ ዓመት በባቢሎን ትገዛለች! ከዚህ የፍርድ ጊዜ በኋላ ብቻ ነበር እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ እስራኤል ምድር የሚመልሰው።

በ605 ዓ.ዓ. በባቢሎናውያን በምርኮ ከተወሰዱት የመጀመሪያ ምርኮኞች አንዱ ዳንኤል ነበር። ባቢሎን በ539 ዓ.ዓ. በሜዶን ፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ ድል እስከትሆን ድረስ አይሁዳውያን በባቢሎን ምርኮኛነት ቆይተዋል። ዳንኤል 9፡1-2 ውስጥ እንደምንረዳው፥ ነቢዩ የኤርምያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር፡- ‘‘በከላዳውያን መንግሥት ላይ በነገሠ ከሜዶን ዘር በነበረ በአሕሻዊሮስ ልጅ በዳርዮስ በመጀመሪያ ዓመት’’። ዳርዮስ የቂሮስ ሌላ ስም ይሁን፥ ወይም በንጉሥ ቂሮስ የተሾመና በዚህ ስም የሚታወቅ ሌላ ሰው መጠሪያ፥ የታወቀ ነገር የለም። ግልጥ የሆነው ነገር ግን፥ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ538-537 በነበረው ጊዜ፥ ዳንኤል የኤርምያስን መጽሐፍ ያነብ የነበረ መሆኑ ነው። ዳንኤል ባቢሎን ውስጥ የኖረው ስድሳ ዘጠኝ ዓመታት ያህል ነበር።

የኤርምያስን ትንቢት በማንበብ ነው አይሁዳውያን በባቢሎን ምርኮ ለሰባ ዓመታት የሚቆዩ መሆናቸውን የተረዳው። እንዴት ነበር ዳንኤል ትንቢቱን የፈታው? ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን ባድማ የምትሆንበትን ትክክለኛ የጊዜ መጠን የሚያመለክት ግልጥ ንድፍ እንደሆነ አድርጎ ነው ትንቢቱን የተረዳው? ወይስ የኤርምያስ ትንቢት ኢየሩሳሌም ሥቃይ የሚደርስባት መሆኑን ብቻ የሚያስረዳና ግልጥ ያልሆነ መልእክት እንደሆነ አድርጎ?

"እኔ ዳንኤል የኢየሩሳሌም መፍረስ የሚፈጸምበትን ሰባውን ዓመት እግዚአብሔር በቃሉ ለነቢዩ ለኤርምያስ የተናገረውን የዓመቱን ቁጥር በመጽሐፍ አስተዋልሁ። ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኜ ስጾም እጸልይና እለምን ዘንድ ፊቴን ወደ ጌታ ወደ አምላኬ አቀናሁ" (ዳን. 9፡2-3)።

ዳንኤል በኤርምያስ አማካይነት የተላለፈውን የእግዚአብሔር ትንቢት አነበበ። ኢየሩሳሌምና የይሁዳ ሕዝብ በባቢሎናውያን እጅ የሚሠቃዩባቸውን ዓመታት የሚያመለክት ትክክለኛ ትንቢት መሆኑንም ተረዳ። ሰባዎቹ ዓመታት ወደ ፍጻሜ በመቃረብ ላይ ስለነበሩ፥ እግዚአብሔርን በጸሎት ይጠይቀው የነበረው "ከተማውንና ሕዝቡን" እንደ ነበረ እንዲመልስ ነው። ዳንኤል የእግዚአብሔርን ትንቢት የተረዳው፥ የባድማነቱ ዓመታት በግልጥ የታወቀ የጅማሬና የፍጻሜ ነጥብ ያላቸው መሆኑን የሚገልጥ እንደሆነ አድርጎ ነበር።

በኤርምያስ ትንቢት የተጠቀሰው የሰባ ዓመት የባቢሎን ምርኮ እንደተጻፈው ይፈጸማል በማለት ዳንኤል አምኗል። ስለ እስራኤል መንግሥት የተሰጠው ተስፋ ከመፈጸሙ በፊት ወደፊት ተጨማሪ 490 ዓመታት እንደሚያልፉ የሚያስረዳውን ትንቢት እግዚአብሔር በቀጥታ ለዳንኤል አሳወቀው። ከኢየሩሳሌም እንደገና መሠራት ጅማሬ፥ እስከ መሲሑ መምጣት ድረስ የሚኖረው ጊዜ 483 ዓመት ይሆናል። ከዚያ በኋላ ግን እግዚአብሔር በዘመኑ ቅደም ተከተል መካከል ክፍተትን ፈጠረ። በዚህ የጊዜ ክፍተት የሚከናወነው፥ የመሲሑ ሞትና የኢየሩሳሌም እንደገና መፈራረስ ነበር።

ከዚህ በኋላ ነበር በትንቢት የተነገሩት የእስራኤል የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት የሚጀምሩት፥ በአንድ ኪዳን መሆኑን እግዚአብሔር ለዳንኤል የገለጠለት። ኪዳኑ ለእስራኤል የሠላምና የጥበቃ ዋስትና የሚሰጥ ቢሆንም፥ ይህ የሰባት ዓመት የደኅንነት ጊዜ በአጭሩ ይቋረጣል።

"የሰባቱ ዓመት እኩሌታ ሲያልፍ፥ መሥዋዕትና ቁርባን ማቅረብን ይከለክላል፤ በቤተ መቅደሱም ማዕከላዊ ስፍራ ላይ አስጸያፊ የሆነ የጥፋት ርኩሰት እንዲቆምበት ያደርጋል" (ዳን. 9፡27- የ1980 ዓ.ም ትርጉም)። ከእግዚአብሔር ትንቢታዊ የጊዜ ሰሌዳ የመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመት ተኩል ጊዜያት የሚጀምሩት፥ "አስጸያፊ የሆነ የጥፋት ርኩሰት" በተባለውና ቤተ መቅደሱ ውስጥ በሚቀመጠው ነገር ነው። ዳንኤል ክንውኖችንና ጊዜያቸውን በግልጥ የሚያስታውቅ ይመስላል፤ እግዚአብሔር የፈለገው ግን እንዲያ እንዲሆን ነው? እኛስ ይህን ትንቢት

እንደ ትክክለኛ ንድፍ ወይስ ግልጥ እንዳልሆነ የእስራኤላውያን ችግር እንተርጉመው? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳን ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተናገረውን እናጢን።

ከዳንኤል ትንቢት ስድስት መቶ ዓመታት ያህል በኋላ፥ ኢየሱስ የትንቢቱን ትርጉም ለደቀ መዛሙርቱ ገለጠላቸው። ማቴዎስ 24 ውስጥ ነው ይህ የእስራኤል መሢሕ ሕዝቡ ወደፊት የሚመጣበትን ነገር ያስታወቀው። በእነዚያ የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት የሚፈጸሙ ነገሮችን በዝርዝር በመግለጥ የእስራኤልን የወደፊት ምስል አሳያቸው። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ተኩል ጊዜ የሚደርሰውን አጠቃላይ ችግር፥ ማቴዎስ 24፡4-14 ባለው ክፍል ውስጥ ለደቀ መዛሙርቱ ገልጧል። ከምዕራፍ 24፡15 ጀምሮ ግን፥ በተለይ በእስራኤል ላይ ችግር በሚያመጣ ነገር ላይ አተኮረ።

> "እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ አንባቢው ያስተውል፥ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ፥ በሠገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ. . . በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆ ናልና" (ማቴ. 24፡15-16፥21)።

ኢየሱስ "የጥፋት ርኩሰት" የሚለውን የዳንኤል ቃል ይጠቅስና፥ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን ያመለክታል። እነርሱም አንደኛ፥ የዳንኤል ትንቢት ገና የሚፈጸም መሆኑ ሲሆን፥ ይህ ትንቢት ከ600 ዓመታት ለበለጠ ጊዜ ያልተፈጸመ መሆኑ መልእክቱን ዋጋ ቢስ አላደረገውም፤ ገና ይፈጸማል። ሁለተኛ፥ የተጠቀሰው ነገር ዳንኤል እንደተነበየው በትክክል የሚፈጸም መሆኑን ነው ኢየሱስ የሚናገረው። የዳንኤል ትንቢት የተሸፈነና ስለ እስራኤል ክፉ ቀኖች የተነገረ አልነበረም። የሚናገረው ገና ሊፈጸም ያለውን የእስራኤል ታሪክ ነው። ያም እግዚአብሔር እንደተናገረው በትክክል ይፈጸማል።

ከዳንኤልና ከኢየሱስ በተጨማሪ፥ ሌሎችም ትንቢቶችን በተመሳሳይ ሁኔታ በመረዳት ገልጠዋል። ጳውሎስ እነዚህን የዳንኤልና የኢየሱስ ትንቢቶች ያውቃቸዋል፤ ትክክለኛነታቸውንም አረጋግጧል። የክርስቶስ ተቃዋሚ፥ "የጥፋትን ርኩሰት" ቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚያቆም ስለመሆኑ የተነገረውን ትንቢትም አምኗል። እንዲህ በማለትም ይገልጠዋል፡- "እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ፥ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው

ተቃዋሚ እርሱ ነው›› (2ኛ ተሰ. 2፡4)። ጳውሎስ ዳንኤል 9 እና ማቴዎስ 24 ውስጥ የተጠቀሰውን መልእክት በመጭመቅ፥ ቤተ መቅደሱን የማርከሱን ጉዳይ ዳንኤልና ኢየሱስ እንደተነበዩት በትክክል አመልክቷል።

ሐዋርያው ጴጥሮስም አንባቢዎቹ የእግዚአብሔርን ትንቢት በሚጠራጠሩ ሰዎች ወጥመድ እንዳይገቡ በማሳሰብ በጻፈላቸው መልእክት እንዲህ በማለት አስጠንቅቋቸዋል፡-

> ‹‹በመጨረሻው ዘመን እንደራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባቾች በመዘበት እንዲመጡ ይህን በፊት እወቁ፤ እነርሱም፥ የመምጣቱ የተስፋ ቃል ወዴት ነው?... ይላሉ። ...እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ! በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ። አንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም›› (2ኛ ጴጥ. 3፡3-4፥ 8-9)።

እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን የማይረሳ መሆኑን ነው ጴጥሮስ ለአንባቢዎቹ ያስገነዘባቸው። እግዚአብሔር ትንቢቱ እንዲፈጸም የሚያደርገው በራሱ የጊዜ ዕቅድ መሠረት ነው።

እግዚአብሔር ለዓለም እያንዳንዱን ዝርዝር የያዘ ትንቢት ይሰጣልን? ወይም በሌላ አባባል፥ የሚፈጽማቸውን ትክክለኛ ትንቢቶች ይናገራል? ለዚህ ጥያቄ ዳንኤል፥ ኢየሱስ፥ ጳውሎስና ጴጥሮስ የሚሰጡት መልስ ‹‹አዎ!›› የሚል ነው። ሁሉም የእግዚአብሔርን ቃል መረመሩ፤ ያልተፈጸሙ ትንቢቶችን ተመለከቱ፤ እናም እግዚአብሔር እንደተናገረው እንደሚፈጽም ጠበቁ። የእግዚአብሔርን ትንቢቶች እርግጠኛነት ተቀበሉ፤ እኛም እንዲሁ እናደርግ ዘንድ ይገባል።

## በትክክል የተፈጸሙ ትንቢቶች

መጽሐፍ ቅዱስ ወደፊት የሚከናወኑ ነገሮችን ይገልጣል፤ መጽሐፉን የጻፉ ሰዎች ደግሞ ትንቢቶቹ ልክ እግዚአብሔር እንደተናገረ ይፈጸሙ ዘንድ ጠብቀዋል። ታዲያ ትንቢቶቹ መፈጸም አለመፈጸማቸውን በሌላ ወገን የምናረጋግጥበት መንገድ አለ? እምነት አልባ በሆነችው ዓለማችን የሌሎች ምስክርነት በቂ አይደለም። ተጠራጣሪው ደቀ መዝሙር፥ ቶማስ፥ ‹‹የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ፥ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ፥ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም›› እንዳለው ማለት ነው (ዮሐ. 20፡25)። በሌሎች የተገለጡ ነገሮችን ከማመናችን በፊት ተጨባጭ ማረጋገጫ እንሻለን።

እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን መተንበዩንና ትንቢቶቹም መፈጸማቸውን የምናረጋግጥበት ነጻ መንገድ አለ? አዎ፥ አለ። እግዚአብሔር እንደተናገረ በትክክል የተፈጸሙና በመቶ የሚቆጠሩ ትንቢቶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። ሁሉንም ትንቢቶች ልንመለከታቸው ባንችልም፥ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ትንቢቶች እንዴት እንዳከናወናቸው ለመመልከት ያህል እስቲ ጥቂቶቹን እንመርምር።

- *ትንቢቱ መሲሑ ቤተልሄም ውስጥ ይወለዳል፡-*

"አንቺ ቤተልሄም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእስራኤልም ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል" (ሚክ. 5፡2)።

☆ ፍጻሜው፡- "ዮሴፍ ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ፥ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተልሄም ወደ ምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ. . . ወጣ። በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ" (ሉቃስ 2፡4-7)።

- *መሲሑ በአህያ ውርጫ ላይ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ይገባል፡-*

"አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በይ፤ እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፥ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል" (ዘካ. 9፡9)

☆ ፍጻሜው፡- "ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተፋጌ ሲደርሱ፥ ያን ጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፥ እንዲህም አላቸው፥ በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ፥ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ. . .። በነቢይ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ" (ማቴ. 21፡1-2፥4)።

- *መሲሑ የተናቀ ይሆናል፡-*

"የተናቀ ከሰውም የተጠላ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው እኛም አላከበርነውም" (ኢሳ. 53፡3)።

"ብዙም ውሾች ከበውኛልና፥ የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ" (መዝ. 22፡16)።

☆ ፍጻሜው:- "ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት፥ ከእሾህም አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ፥ በቀኝ እጁም መቃ አኖሩ፥ በፊቱም ተንበርክከው፥ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ሠላም ለአንተ ይሁን እያሉ ዘበቱበት፤ ተፉበትም፤ መቃውንም ይዘው ራሱን መቱት። ከዘበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፥ ልብሱንም አለበሱት፤ ሊሰቅሉትም ወሰዱት (ማቴ. 27፡28-31)።

♦ *የመሢሑን ልብስ ይከፋፈሉታል:-*

"ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ" (መዝ. 22፡18)።

☆ ፍጻሜው:- "ከሰቀሉትም በኋላ ልብሱን ዕጣ ጥለው ተካፈሉ" (ማቴ. 27፡35)።

♦ *በመሢሑ ላይ ገዳዮቹ ያላግጡበታል:-*

"የሚያዩኝ ሁሉ ይላገጹብኛል፤ ራሳቸውን እየነቀነቁ በከንፈሮቻቸው እንዲህ ይላሉ፥ በእግዚአብሔር ተማመነ፥ እርሱንም ያድነው" (መዝ. 22፡7-8)።

☆ ፍጻሜው:- "የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና፥ ቤተ መቅደስንም የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራው፥ ራስህን አድን፤ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ አሉት። እንዲሁም ደግሞ የካህናት አለቆች ከጻፎችና ከሽማግሎች ጋር እየዘበቱበት እንዲህ አሉ፥ ሌሎችን አዳነ፥ ራሱን ሊያድን አይችልም፤ . . . በእግዚአብሔር ታምኖአልና፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎአልና ከወደደውስ አሁን ያድነው" (ማቴ. 27፡39-43)።

♦ *መሢሑ ይገደላል:-*

"እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ። . . . በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ?" (ኢሳ. 53፡5-6፥8)።

☆ ፍጻሜው:- "ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ። እነሆም የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፥ ምድርም ተናወጠች፥ ዓለቶችም ተሰነጠቁ" (ማቴ. 27፡50-52)።

♦ መሢሑ ባለጠጋ መቃብር ውስጥ ይቀበራል፡-

"ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ፥ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፥ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር (ኢሳ. 53፥9)።

☆ ፍጻሜው፡- "በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለጠጋ ሰው ከአርማቴያስ መጣ፥ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ። . . . ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው (ማቴ. 27፥57፥59-60)።

♦ መሢሑ ከሞት ይነሣል፡-

"ምላሴም ሐሴት አደረገች፤ ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ታድራለች፤ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፤ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም" (መዝ. 16፥9-10)።

"እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል (ኢሳ. 53፥10)።

☆ ፍጻሜው፡- "መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው እናንተ አትፍሩ፥ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና እንደተናገረው ተነሥቷልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ" (ማቴ. 28፥5-6)።

ጴጥሮስ መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 16 ውስጥ ያለውን ቃል በመጥቀስ እንዲህ ይገልጠዋል፡- "ወንድሞች ሆይ፥ ስለ አባቶች አለቃ ስለ ዳዊት እንደ ሞተም፥ እንደ ተቀበረም ለእናንተ በግልጥ እናገር ዘንድ ፍቀዱልኝ፤ መቃብሩ እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ ነው። ነቢይ ስለሆነ፥ ከወገቡም ፍሬ በዙፋኑ ያስቀምጥ ዘንድ እግዚአብሔር መሀላ እንደ ማለለት ስለ አወቀ፥ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ አይቶ ነፍሱ በሲኦል እንዳልቀረች፥ ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ (ሐዋ. 2፥29-31)።

ተቃዋሚ ጠበቆች የግራ ቀኝ የክርክራቸውን ማጠቃለያ ለፍርድ ለተቀመጠው ሸንጎ አቀረቡ። ዳኛውም ወደ ኋላው ደገፍ ብሎ የክሱን ሁኔታ እንዲህ በማለት አስረዳ፡- "የሸንጎው አባላት ሆይ፥ ተግባራችሁ የቀረቡትን ማስረጃዎች ሁሉ መመርመርና በማስረጃው ክብደት መሠረት አንድ ውሣኔ ላይ መድረስ ነው። ከዚህ በኋላ ውይይታችሁን ለመቀጠል ከፍርድ ቤቱ ወደ ሸንጎው ቢሮ ታመራላችሁ። ዛሬ ከፊታችሁ ያለው ጥያቄ፥ "እግዚአብሔር በእርግጥ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን ይናገራል?" የሚል ነው"።

እግዚአብሔር ስለ ራሱ ተናግሮ፥ "ወደፊት ስለሚሆነው ነገር" ገልጧል (ኢሳ. 44፡7)። ዳንኤል፥ ኢየሱስ፥ ጳውሎስ እና ጴጥሮስ እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን የመግለጥ ችሎታ ያለው መሆኑን ያረጋገጡ ምስክሮች ናቸው። ከታሪክ የሚታየው ማስረጃም ምስክርነታቸውን አጽንቶታል። እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳን ውስጥ በመደጋገም ልዩ ልዩ ትንቢቶችን የተናገረ ሲሆን፥ እያንዳንዱ ነገር ልክ እርሱ እንደተናገረው ተከናውኗል። ታዲያ እርስዎ በቀረቡት ማረጋገጫዎች ላይ ተመሥርተው የሚሰጡት ብያኔ ምንድነው? አንድ የሥነ-መለኮት ተንታኝ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡- "እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ አያሌ ነገሮችን ገልጧል። ምንም እንኳን ከንውኖቹ በሺህ ለሚቆጠሩ ዓመታት ቢዘገዩ፥ ልክ እንደተተነበዩት ተከናውነዋል። እግዚአብሔር ጥበብን ሁሉ የተሞላ ልዑል አምላክ መሆኑን አረጋግጧል። ስለዚህ ማመን እንጂ ሌላ ምርጫ የለንም"።

## ትንቢትን የመገንዘቡ ሁኔታ ይጨምራል

መጽሐፍ ቅዱስ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን ቢገልጥም፥ ትንቢቶቹን በመረዳቱ ረገድ ግን አንድ ዋና እንቅፋት አለ። ይኸውም ስለ መጨረሻው ዘመን ትንቢት የተጻፉ አያሌ ገለጣዎች መከሠታቸው ነው። እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች የተናገረው ግልጥ ከሆነ፥ ለምንድነው የተለያዩ መግለጫዎች መኖራቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን ግልጥ ትንቢቶች በመቀበሉ ረገድ ክርስቲያኖች ሁሉ የማይስማሙት ለምንድነው?

ለዚህ ጥያቄ ተገቢ ስፍራ ልንሰጠው ይገባል። ክርስቲያኖች ትንቢቶችን በተመለከተ ብቻ ሳይሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጠቀሱ ብዙ ነገሮችም አይስማሙም። ስምምነት የእውነት ማረጋገጫ መስፈርት ቢሆን ኖሮ፥ "እውነት ምንድነው?" እያልን የጲላጦስን ጥያቄ የምናስተጋባ እንሆን ነበር። አለመግባባታችን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመራን እንጂ፥ ከእርሱ የሚያርቀን ሊሆን አይገባም። ቤተ ክርስቲያን እንደ ጥንቶቹ ቤሪያውያን ያለ ባሕርይ ያላቸው ብዙ አባላት ሊኖሯት ይገባል። እነርሱ እንዲህ ተብሎላቸዋል፡- "እነዚህም (የቤሪያ ሰዎች) በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፥ ነገሩ እንዲህ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ" (ሐዋ. 17፡11)።

ፍላጎታችን የእግዚአብሔርን ቃል እውነት መረዳት ነው። ይህ ፍላጎት ቢኖርም እንኳ፥ እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች

በተናገረው ቃል ላይ የተለያየ ግንዛቤ ያላቸው ቅን ክርስቲያኖች እናገኛለን። እንዲህ ያሉ ልዩነቶች ለምን ኖሩ? ሦስት ግልፁ ምክንያቶች አሉ።

የመጀመሪያውና ሰዎች ስለ መጨረሻው ዘመን ሁኔታዎች የማይግባቡበት ምክንያት፥ የእግዚአብሔርን እውነት ሙሉ በሙሉ የጨበጠ ማንም አለመኖሩ ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን ሊረዳው የሚገባ ነገር፥ ከእግዚአብሔር ቃል ገና ብዙ የሚማረው ነገር መኖሩን ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች አንድን የተለየ ጉዳይ በዝርዝር ባለማጥናታቸው ሳቢያ አለመግባባት የሚፈጠር መሆኑን ተገንዝቤያለሁ። ሌላው ያለመግባባት ምክንያት፥ እግዚአብሔር በዘመን ፍጻሜ ስለሚያከናውናቸው ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጠው ነገር ባይኖር እንኳን፥ እነርሱ ከሚኖራቸው ግምት የተነሣ የሚፈጠር ነው። አለመግባባቶች ብዙ ጊዜ ከግንዛቤ እጦት ይፈጠራሉ። ታዲያ ስሕተቱ የእኛ እንጂ የእግዚአብሔር አይደለም።

ሁለተኛውና ስለ ፍጻሜው ጊዜ ሁኔታዎች የማንግባባበት ምክንያት፥ ዛሬ ዓለም ውስጥ ከምናያቸው ነገሮች ጋር የማይጣጣሙ ትንቢቶችን ትክክለኛ እንደሆኑ አድርገን ለመቀበል አለመቻላችን ነው። ለምሳሌ፥ ስለ እሁኗ እስራኤል የተነገረው ትንቢት ከኀምሳ ዓመት በፊት በጣም እሩቅ ይመስል ነበር።

ለ2,000 ዓመታት እስራኤል እንደ መንግሥት አልኖረችም፤ እግዚአብሔር ግን ስለ እርሷ የወደፊት ሁኔታ የሚናገረው ነገር ያለው ይመስል ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ስለ እውነት ካለን ግንዛቤ ጋር ስላልተስማማ፥ ቃሉን በመቀበል ረገድ ችግር ነበረብን። ከ1948 እአአ ወዲህ ግን እስራኤል እንደገና እንደ መንግሥት ስለተመሠረተች፥ እግዚአብሔር ስለ እርሷ አስቀድሞ የተናገረውን መገንዘቡ ቀላል ሆ ኖልናል። ታዲያ ችግሩ የነበረው ከእግዚአብሔር ቃል ነው፥ ወይስ እግዚአብሔር የተናገረውን ለማመን አለመቻላችን?

የትንቢቶች ችግር በፍጹም የእግዚአብሔር ቃል አይደለም። ችግሩ እንዲሁ ሲታዩ የማይሆኑ በሚመስሉበት ጊዜ፥ የእግዚአብሔርን ትንቢቶች ትክክለኛ ትርጉም ለመቀበል ፈቃደኞች አለመሆናችን ነው። ለምሳሌ፥ እግዚአብሔር ስለ ባቢሎን የተናገራቸው ትንቢቶች ግልፁ ቢሆኑም፥ አሁን የምትታወቀው ባቢሎን በመጨረሻው ዘመን የምታከናውነው ድርሻ አላት ብለው ጥቂት ሰዎች በጥብቅ አስበዋል። በአሁኑ ጊዜ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ስለሚከናወኑ ነገሮች ካለን ግንዛቤ ጋር ስለማይዛመድ፥ ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ቃል ትርጉም

አልተቀበልነውም ነበር። ሳዳም ሁሴን ኩዌትን በወረሩና የዓለምን የነዳጅ ስርጭት ለመቆጣጠር ባስፈራሩ ጊዜ ግን፥ የእግዚአብሔር ቃል እርሱ እንደተናገረው በትክክል የሚፈጸም መሆኑን ተረዳን። የተለወጠው ምንድነው? የእግዚአብሔር ቃል፥ ወይስ በዓለም ስለሚከናወኑ ነገሮች እኛ ያለን ግንዛቤ?

ሦስተኛው፥ ስለ ፍጻሜው ዘመን የማይስማሙበት ምክንያት፥ ሊሆኑ ያሉ ነገሮች እስኪቃረቡ ድረስ ቃሎቹ ለሰዎች ግልጥ እንደማይሆኑ እግዚአብሔር መናገሩ ነው። ስለ እስራኤል መሢሕ ቀዳሚ ምጽአት የተነበዩ የብሉይ ኪዳን ነቢያትም ቢሆኑ፥ የተናገሯቸውን ቃሎች ትርጉም ሙሉ በሙሉ ተረድተው ነበር ለማለት አይቻልም፡-

"ለእናንተ ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት፥ ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፤ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ፥ ስለ ክርስቶስ መከራ፥ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ በምን፥ ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር" (1ኛ ጴጥ. 1፡10-11)።

ነቢያቱ፥ ማለት ኢሳይያስና ሚክያስ፥ ኢየሩሳሌም ውስጥ አብረው ምሳ ሲበሉ የሚያመለክት ምሥል በአእምሮዬ ለመገመት እችላለሁ። አንደኛው ነቢይ በመጨረሻ ከእግዚአብሔር የመጣለትን ራእይ ሲያነብ፥ ሌላው የሚሰማቸውን እንቆቅልሽ መሰል ነገሮች ለመገጣጠም እየሞከረ ራሱን ያካል። መሢሑ ቤተልሄም ውስጥ ሲወለድ፥ ለዓለም ኃጢአት ሲሠቃይ፥ ሲሞትና ከሞት ሲነሣ እንዲሁም የመጨረሻውን የእስራኤል መንግሥት ሲመራ የሚያሳይ ምሥል በአእምሯቸው ይመለከታሉ። ዝርዝሮቹን ሁሉ ግን ሊረዱ አልቻሉም። የተነገሩት ትንቢቶች መፈጸሚያ ሲደርስ ብቻ ነው ነገሮች ግጥምጥም ያሉት።

እግዚአብሔር ይህንኑ እውነት ለዳንኤል ነግሮታል። ዳንኤል የተመለከታቸውን ራእዮች ሁሉ እንዲመዘግብ ካደረገው በኋላ፥ "ዳንኤል ሆይ! የዓለም መጨረሻ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ መጽሐፉን ዘግተህ አሽገው፤ የትንቢቱንም ቃል በምሥጢር ያዝ፤ በዚያን ጊዜ ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይራወጣሉ፤ ምርምርና እውቀትም ይበዛል" ብሎታል (ዳን. 12፡4፥ የ1980 እእእ እትም መ.ቅ.)። የዳንኤል ጽሑፍ ይነበብ ይሆናል፤ ለብዙ አንባቢያን ግን "የታሸገ መጽሐፍ" ሆኖ ኖሯል። ቃሎቹ "በአሕዛብ ዘመን" ለሚኖሩ አይሁዳውያን የተላለፈ የተስፋ መልእክት ነበራቸው። አይሁዳውያን ግን የእግዚአብሔርን ትንቢት ትክክለኛ ትርጉም አልተረዱም። የትንቢቶቹ መፈጸሚያ ጊዜ ሲቃረብ ብቻ ነበር የመልእክቱ ትርጉም ግልጥ የሆነው። እግዚአብሔር "ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ

ይራወጣሉ፤ ምርምርና እውቀትም ይበዛል" ሲል፥ ይህንኑ ማስገንዘቡ ነበር። ይህን ሲናገር፥ የጉዞን ብዛት በመግለጥ ሰዎች የሚመራመሩት በአውቶሞቢል፥ በባቡር ወይም በአይሮፕላን ከስፍራ ስፍራ በመዟዟር ነው ለማለት ሳይሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስን እያገላበጡ የተለያዩትን ክፍሎች እያነጻጸሩ በማንበብ ነው ለማለት ነበር።

"የዘመን ፍጻሜ" ሲቃረብ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች የሚኖረን ግንዛቤ ማደግ አለበት። በዓለም የሚከናወኑ ነገሮች በመጨረሻ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ጋር በትክክል መገናዘብ ይጀምራሉ። የጠዋት ጋዜጦችና የምሽት ዜናዎች የዳንኤልን፥ የኢየሱስን ወይም የሐዋርያው ዮሐንስን ቃላት መምሰል ሲጀምሩ፥ ለትንቢት የተጋረደው ዓይናችን ይገለጣል። እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች ይናገራል፤ በዓለም የሚታዩ ክንውኖች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ትንቢቶች ጋር መመሳሰል ሲጀምሩም የእግዚአብሔር ትንቢቶች ግልጥ መሆን ይጀምራሉ።

> ምዕራፍ አሥራ ሰባት <

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶችን ማጥናት የሚኖርብኝ ለምንድነው?

ራሴን ግራ እጄ ላይ አስደግፌ በማጠናበት ኮሌጅ የሂሳብ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተቀምጫለሁ። በቀኝ እጄ የያዝኩትን የብዕር ጫፍ ቀደም ሲል እፊቴ ባለው ወረቀት ላይ በሠራኋቸው መስመሮችና ቅርፆች ላይ በማመላለስ ላይ ነኝ። የዚያን ዕለት ዓላማዬ ወይም ዕቅዴ ንቁ ለመሆን ነበር። ለአንድ ሳምንት ያህል "የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መግቢያ" የሚለውን ክፍለ ትምህርት ስከታተል ስለቆየሁ በጣም ስልችት ብሎኛል። ወጪና ገቢ የሚለው ትምህርት ለእኔ ምን ፋይዳ አለው? የሂሳብ ሠራተኛ ልሆን አይደለም። እግዚአብሔርን ለማገልገል ስላቀድኩ ዳላስ ሴሚናሪ ወደሚባለው ከፍተኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት ልገባ ነው። በመሆኑም ለመዝገብ አያያዝና ለሂሳብ ሥራ የሚያገለግሉ ጽሑፎችና መጻሕፍት ምንም አይጠቅሙኝም።

ስለቀሰምኩት የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መግቢያ ትምህርት እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። አዲሱ አገልግሎቴ የበጀትና ሌላም የሂሣብ ሥራ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ የነገረኝ የለም። ከሀያ ዓመታት በፊት ለእኔ ምንም ጥቅም የሌለው የመሰለኝ እውቀት፥ ላለፉት አሥር ዓመታት እጅግ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ለውጤታማ አስተምህሮ፥ ነገሮች ጠቀሜታ ወይም "ፋይዳ" ያላቸው መሆኑን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። የማስተምረው ነገር ያለውን ፋይዳና ጠቀሜታ ለማስገንዘብ ካልቻልኩ፥ ትምህርቴ ብዙ ሰዎችን የሚስብ አይሆንም። ዓላማችን "እውቀትን ስለ እውቀት" እንደመሆኑ ብዙ የማይጠቅሙ ግንዛቤዎችን በየዕለቱ እያጣራን እናስቀራቸዋለን። ለመቀበል የምንፈቅደው፥ የሚረባንን እውቀት ብቻ ነው።

በመኪና ወደ ሥራ የሚሄዱ ከሆነ፥ በጉዞዎ ብዙ መኪናዎችን ይቀድሙ ይሆናል፤ መኪናዎቹን ግን እምብዛም ልብ አይሏቸውም። ነገር ግን እስቲ አዲስ መኪና ይግዙና የሚሆነውን ይመልከቱ። ጎዳናው ላይ የእርስዎን የመሰሉ አውቶሞቢሎች ይመለከታሉ። እነዚህ አውቶሞቢሎች እርስዎ አዲስ አውቶሞቢል ስለገዙ በአንዳች አስማታዊ ነገር የመጡ ናቸው? አይደሉም፤ አዲስ የገዙት የአውቶሞቢል ዓይነት ለእርስዎ ዋና ነገር መሆኑ ነው። ከእርስዎ ጋር የተገናኘ ወይም የሚመለከትዎ ነገር ስለሆነ፥ የራስዎን የሚመስል መኪና የገዙ ሰዎችን ልብ ብለው መመልከት ይጀምራሉ።

ብዙ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የሚመለከታቸው አይመስላቸውም። "እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ቢናገርም እንኳን፥ ከእኔ ወይም ከሕይወቴ ጋር ምን ያገናኘዋል?" ይላሉ። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ከዓለም ካወጣት በኋላ ስለሚሆኑ ነገሮች ማጥናቱ ለምን ያስፈልጋል? በፍጻሜው ዘመን የሚሆኑ ነገሮች እኔ በምድር ላይ ሳለሁ ካልተከናወኑ፥ ከሞትኩ በኋላ እግዚአብሔር ስለሚያደርገው ነገር ምን አስጨነቀኝ? መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናቴ የሚያስገኝልኝ ፋይዳ አለ? ወይስ ፋይዳ ቢስ በሆነ ነገር ነው አእምሮዬን በመሙላት ላይ ያለሁት?

እግዚአብሔር ትንቢትን የተናገረው አእምሯችንን በእውቀት ለመሙላት ሳይሆን፥ ልቦናችንን ለመቀየር ነው። ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን ለማወቅ ያለንን ጉጉት ለማርካት ሲል ትንቢት የተናገረበት ጊዜ የለም። ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች በተናገረ ጊዜ ሁሉ፥ ሕይወትን የሚመለከቱ ነገሮችን ትንቢቱ ውስጥ ይጨምራል። የሚናገራቸው ትንቢቶቹ "አሁንና ለዚህ" የሚሆን ምክር አለባቸው። ትንቢቶቹ ዛሬ ለሕይወታችን ለውጥ እንዲያመጡ እግዚአብሔር የሚፈልግ ስለመሆኑ የሚያስረዱ አራት ምሳሌዎችን እንመልከት።

## ትንቢት ምስጋናን ያመነጫል

ሐዋርያው ጳውሎስ፥ ሮሜ ምዕራፍ 9-11 ውስጥ ባለው ክፍል እግዚአብሔር ለእስራኤል ወደፊት ያለውን ፕሮግራም ይገልጣል። እስራኤል የእግዚአብሔርን የተስፋ በረከት ስላልተቀበለች፥ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን በኩል አሕዛብን ለመባረክ ይህን እምቢታዋን ተጠቀመበት። ("የበረሃ ወይራ ቅርንጫፍ" የተባሉት) አሕዛብ፥ ("ከቅርንጫፎች አንዱ ቢሰበር") የተባለች እስራኤልን ተክተዋል (ሮሜ 11፥17)። ከዚህ ለጠቅ አድርጎ ግን፥ እግዚአብሔር እስራኤልን የሚያድናት መሆኑን ሲገልጥ እንዲህ ብሏል፡- "የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው፤ እንዲሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል" (ሮሜ 11፥25-26)።

መቼ ነው እስራኤል እንደገና እንደ ብሔር የምትሰበሰበው? ጳውሎስ ኢሳይያስ 59 ውስጥ ያለውን ቃል ጠቅሶ፥ "መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል" (ሮሜ 11፥26፥ ኢሳይያስ 59፥20ን አሳጥሮ በመግለጥ) ይላል። ኢሳይያስም ሆነ ጳውሎስ እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባላት ትንቢት የሚፈጸመው ከኢየሱስ ዳግም ምጽአት ቀጥሎ ነው ይላሉ። ሮም የነበሩት የጳውሎስ መልእክት አንባቢዎች ግን፥ እግዚአብሔር እስራኤልን እንደገና ወደ በረከት ምድር ሳይመልሳት ሞተዋል። ታዲያ ይህ ትንቢት የጳውሎስን መልእክት ላነበቡ ለነዚያ ሮማውያን ምን ፋይዳ ነበረው- ለኛስ?

ጳውሎስ እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ምድሯ የሚመልስበትን ሁኔታ ከገለጠ በኋላ፥ እግዚአብሔርን በመዝሙር እንዲህ አመስግኖታል፦ "የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም" (ሮሜ 11፡33)። እግዚአብሔር የወደፊቱንም ዘመን የሚቆጣጠር መሆኑን መረዳቱ ጳውሎስን በምስጋና እንዲንበረከክ አስገድዶታል። እግዚአብሔር ለሚመጡት ዘመናት ያለውን ፕሮግራም መረዳቱ ጥበብን፥ እውቀትንና የዓለማትን አምላክ ኃይል ወደ ማስተዋል ይመራናል። ትንቢት ወደፊት ወደሚሆኑ ነገሮች ማመልከት ብቻ ሳይሆን፥ ዘመናትን ወደሚቆጣጠረው እግዚአብሔር ገናናነትም ይጠቁመናል።

## ትንቢት ያበረታታል

ጳውሎስ የመጀመሪያ ደብዳቤውን ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች የጻፈው፥ በተቃውሞ ግፊት ከከተማይቱ ከወጣ በኋላ ነበር (ሐዋ. 17፡1-9)። በስፍራው የቆየው የተሰሎንቄን ቤተ ክርስቲያን በመመሥረት ለጥቂት ጊዜ ቢሆንም፥ ስለ ፍጻሜው ዘመን ሁኔታዎች ሳያስተምራቸው አይቀርም። አንደኛና ሁለተኛ የተሰሎንቄ መልእክቶች ስለ ኢየሱስ ዳግም ምጽአትና ስለ ፍጻሜው ዘመን ሁኔታዎች አያሌ ትምህርቶች አሏቸው። የአንደኛ ተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፎች ሁሉ የሚያበቁት፥ የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት በማመልከት ነው።

ጳውሎስ ከተለያት በኋላ የደረሱት ብዙ ነገሮች ተሰሎንቄ ውስጥ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ያስቸግሯት ነበር። ብዙ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት የሞቱ ሲሆን፥ የሙታን ዘመዶች ከሟች ወገኖቻቸው ጋር "ለመገናኘት እንችል ይሆን?" የሚል ጥያቄ በአእምሯቸው ተፈጥሮ ነበር። በሕይወት ያሉትም በጊዜው የስደት ፈተና ውስጥ ማለፍ ነበረባቸው። ጳውሎስን በሌላ ስፍራ የተቃወሙት አድማ ፈጣሪዎች፥ ተሰሎንቄ ውስጥ የተጀመረውን አዲስ የወንጌል ሥራም ሊያዳፍኑት ፈለጉ። አንዳንድ አማኞች የሰባት ዓመቱ የፍዳ ዘመን የመጣ እስኪመስላቸው ድረስ ቀኖቹ እጅግ አስቸጋሪ ሆነው ነበር። ይህ የታሰ ባቸው፥ ቀደም ሲል እግዚአብሔር ፍርዱን በምድር ላይ ስለሚያፈስበት "የጌታ ቀን" ጳውሎስ ነግሯቸው ስለነበር ነው። "ወደ ፍዳው ጊዜ ገብተው ነበር እንዴ?"

ጳውሎስ እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች የተናገረውን ትንቢት በማደግ ላይ ለነበረች ለዚያች ቤተ ክርስቲያን አስገንዝቧታል። በሞት የተለዩ ክርስቲያኖች ስለሚጠብቃቸው ነገርም 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13-18 ውስጥ እንዲህ በማለት ገልጦላቸዋል፦

"ጌታ ራሱ በትእዛዝ፥ በመልእክትም አለቃ ድምፅ፥ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን" (1ኛ ተሰ. 4፡16-17)።

ኢየሱስ የሞቱትንም ሆነ በሕይወት ያሉትን ለመውሰድ እንደሚመጣና ወደ ላይ እንዲነጠቁ እንደሚያደርግ ጳውሎስ ተንብዮአል። ሁሉንም ወደ ሰማይ ይወስዳቸዋል።

የተሰሎንቄ ሰዎች በመጪው "የጌታ ቀን" በምድር ላይ እንደማይኖሩ ጳውሎስ ቀጥሎ ባለው ምዕራፍ ገልጦላቸዋል፡-

"ሠላምና ደኅንነት ነው ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል። ከቶም አያመልጡም። እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ፥ ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም። . . . እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ" (1ኛ ተሰ. 5፡3-4፥9)።

ጳውሎስ የጌታ ቀን ገና አልመጣም፤ በሚመጣበት ጊዜ ግን በመንፈሳዊ ጭለማ ለሚመላለሱት ድንገተኛ ይሆንባቸዋል ይላል። የተሰሎንቄ አማኞች "የብርሃን ልጆች" ስለነበሩ ለሚመጣው የቁጣ ቀን አይጋለጡም።

ጳውሎስ ወደፊት የሚሆነውን ትንቢታዊ እውነት ለተሰሎንቄ ሰዎች ይነግራቸዋል። ወደፊት ምድርን ስለሚያጥለቀልቃት የመከራ ጊዜም ከገለጠላቸው በኋላ፥ ከመከራው ቀደም ብሎ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ከምድር የሚወስዳት መሆኑን አስረዳቸው። እግዚአብሔር ይህን የተናገረው፥ አእምሯቸውን ለመሙላት ያህል ብቻ አይደለም። ጳውሎስ ከእያንዳንዱ ትንቢታዊ ክፍል ለጥቆ እንዲህ ይላል፡- "ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ" (1ኛ ተሰ. 4፡18)፤ "ስለዚህ እናንተ ደግሞ እንደምታደርጉ እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፥ አንዱም ሌላውን ያንጸው" (5፡11)። እግዚአብሔር ይህን ትንቢት የተናገረው ሕይወታቸውን ለመለወጥ ነው።

የወደፊቱን ማወቅ በኢየሱስ ላመኑ ሁሉ መጽናናትን የሚያስገኝላቸው መሆን አለበት። አሁን ችግር ውስጥ እንገኝ ይሆናል፤ እግዚአብሔር ዓለማትን ሁሉ የሚቆጣጠር መሆኑንም ከትንቢት እንረዳለን። ለዓለማትም ሆነ ለእኛ አሳብ ወይም ዕቅድ አለው።

እግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕጣችንን የወሰነ መሆኑን ማወቃችን፥ አሁን ያለብንን ፈተና እንቋቋም ዘንድ ብርታት ይሆነናል።

## ትንቢት ጽናትን ይሰጣል

የማያቋርጥ ስደታቸውን አስመልክቶ አሁንም ጥያቄዎች ይነሡ ስለነበር፥ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ሁለተኛ ደብዳቤ ጻፈ። በጊዜው አንድ ሰው ከጳውሎስ የተጻፈ በማስመሰልና፥ የፍጻሜው ዘመን የቀረበ መሆኑን በመግለጥ አንድ ሐሰተኛ ደብዳቤ የጻፈ ይመስላል። ለዚህ ነው ጳውሎስ እንዲህ ሲል የጻፈው፡- "ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰብሰባችን፥ በመንፈስ ወይም በቃል ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት፥ የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ፥ ከአእምሯችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ፥ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን" (2ኛ ተሰ. 2፡1-2)።

ከእነርሱ ጋር ተሰሎንቄ ውስጥ በቆየ ጊዜ ያስተማራቸውን ግልጥ ትምህርት ነው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የሚያስታውሳቸው። "ገና ከእናንተ ጋር ሳለሁ ይህን እንዳልኋችሁ ትዝ አይላችሁምን?" (2፡5) ይላቸዋል። ቀደም ሲል የነገራቸውን ነገሮች ነው በአጭሩ የሚገልጥላቸው። ከቁጥር 3-4 ባለው ንባብ ውስጥ ደግሞ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ እግዚአብሔር ነኝ ስለሚለው "የዓመፅ ሰው" ይነግራቸዋል። ከቁጥር 6-12 ባለው ክፍል እንዲሁ እግዚአብሔር ከልካዩን ከፉ ካስወገደ በኋላ ስለሚኖረው መንፈሳዊ ትግል ያስረዳቸዋል። ሰይጣን ዓለምን ለማታለል ስለሚሠራቸው ምልክቶችና ድንቆችም ያስገነዝባቸዋል። ኢየሱስ ተገልጦ ይህን "የዓመፅ ሰው" እስኪያጠፋው ድረስ፥ የተዘረዘሩት ነገሮች የሚቀጥሉ መሆናቸውንም አረጋገጠላቸው።

ጳውሎስ በምድር ላይ ሊመጣ ያለውን ችግር ለአንባቢዎቹ ከገለጠ በኋላ፥ የእነርሱ ፍጻሜ ግን የተለየ መሆኑን እንዲህ በማለት ያስረዳቸዋል፡- "እኛ ግን የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፤ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጧችኋልና (2ኛ ተሰ. 2፡13)። ጳውሎስ ለስለስ ባለ ቋንቋ ለአንባቢያኑ የሚያስረዳቸው፥ እነርሱ በእግዚአብሔር ቀን ውስጥ የማያልፉ መሆኑን ነው። ምክንያቱንም ሲገልጥላቸው፥ ያ ዕለት የሚመጣው፥ ባልጠረጠረና በማያምነው ዓለም ላይ ስለሆነ ነው ይላቸዋል። በኢየሱስ ያመኑ፥ ፍጻሜያቸው ከማያምኑት የተለየ ነው። የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ስደት ቢገጥማቸውም፥ የዚያኔው ስደት በፍጻሜው ዘመን በዓለም ላይ የሚመጣው መከራ አልነበረም።

ጳውሎስ በተሰሎንቄ ቆይታው ብዙ ጊዜውን ያሳለፈው፥ ስለ ፍጻሜው ዘመንና ሐሰተኛው ክርስቶስ ስለምንለው ሰው በመግለጥ መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን በመከራው ጊዜ የማትኖር ከሆነ፥ ወደ ዝርዝር ጉዳይ መግባቱ ለምን አስፈለገ? እነዚህ የተሰሎንቄ አማኞች በአስቸጋሪ ጊዜ እንዲጸኑ ነው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ፕሮግራም እንዲህ በማለት የሚገልጥላቸው፡- "ከአእምሯችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ፥ እንዳትደነግጡም" ብሎ በማሳሰብ ነው የሚጀምረው (2ኛ ተሰ. 2፡2)። የፍርሃት ተጠቂዎች እንዳይሆኑና እንዲጸኑ፥ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ያውቁም ዘንድ ይፈልጋል። "ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ" (2ኛ ተሰ. 2፡3)። ጳውሎስ የዚያን ክፍል ትምህርቱን የሚያጠቃልለው፥ ያለንበትን ጊዜ ለመረዳት ትንቢት ጠቃሚ መሆኑን አጠንክሮ በመንገር ነው። "እንግዲያስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ፥ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ" (2፡15)።

1991 (እአአ) እንደገባ፥ ዓለም መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮችን በድንጋጤ ትመለከት ነበር። ሳዳም ሁሴን ሦስተኛውን የዓለም ጦርነት ይጀምሩ ይሆን? ለጦርነቱ መርዛማ ጦር መሣሪያዎች ይጠቀሙ ይሆን? የኑክሊየር መሣሪያ ይኖራቸው ይሆን? የቀድሞዋ ሶቪየት ኅብረት መንግሥትስ እርሳቸውን በመርዳት፥ የሳዳም ሁሴን ተቃዋሚ በሆኑት የተባበሩት ኃይላት ላይ ድንገተኛ ጥቃት ይሰነዝሩ ይሆን? ጦርነቱስ ተባብሶ ምድርን ወደሚያጠፋት የኑክሊየር ጦርነት ያመራ ይሆን? ጦርነቱ ወዴት ያመራ እንደ ነበር የዓለም ሕዝብ ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም። ሰዎች ግን ብዙ አስገራሚ አሳቦችን ሰንዝረዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር የሚናገረውን የሚያውቁ ግን ፍርሃት አልነበረባቸውም። እግዚአብሔር ለዓለም ዕቅድ አለው፤ ዓለም በርሱ ዕቅድ መሠረት እንጂ፥ "በድንገተኛ" የኑክሊየር አደጋ አትወድምም።

የእግዚአብሔርን ዕቅድ መገንዘቡ በክፉ ቀኖች ጽናትን ይሰጣል። እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን በተመለከተ አቅጣጫ አሳይቶናል። እርግጥ ነው፥ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን ሁሉ አናውቅም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በወሰነው የመጨረሻ ዘመን የሚከናወኑ ዋና ዋና ነገሮችንና አድራጊዎቹን የመለየት በቂ እውቀት አለን። እውቀታችን ከመስመራችን እንዳንወጣ ሊጠብቀን የሚችልና በቂ ነው።

## ትንቢት ቅድስናን ያፈራል

ሐዋርያው ጴጥሮስም ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች ተናግሯል። 2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ውስጥ፥ "በቅዱሳን ነቢያት ቀድሞ የተባለውን ቃል፥

በሐዋርያቶቻችሁም ያገኛችኋትን የጌታንና የመድኃኒትን ትእዛዝ እንድታስቡ'' (2ኛ ጴጥ. 3፡2) በማለት ለአንባቢዎቹ ያሳስባል። ምን የሚሉ ቃላትን ነው እንዲያስቡ የሚፈልገው? ከቁጥር 3 በመጀመር ስለ ''መጨረሻው ዘመን'' ወይም ስለ ''ጌታ ቀን'' ይገልጣል። ገና ሊፈጸሙ ስለሚገባቸው የመጨረሻ ትንቢቶች ነው አንባቢዎቹን ያስታወሳቸው።

ምንም እንኳን ትንቢቶቹ የተነገሩት ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ስለ መጨረሻው ዘመን የተናገረው ዕቅድ እንደሚፈጸም ጴጥሮስ ለአንባቢዎቹ ነግሯቸዋል። ይሁን እንጂ፥ ለምንድነው እግዚአብሔር ትንቢቶቹን ከመፈጸም የዘገየ የሚመስለው? ''ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው፥ ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል'' (3፡9)። በመጨረሻው ዘመን የሚሆኑ ነገሮች ገና ያልተከናወኑበት ምክንያት፥ እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ይቀበሉት ዘንድ ዕድል ሊሰጣቸው ስለ ፈለገ ነው።

እግዚአብሔር ታጋሽ ቢሆንም፥ ትዕግሥቱ በመጨረሻ ዘመን በዚህ ኃጢአተኛና የተበላሸ ዓለም ላይ ሊሆን ያለውን ዕቅዱን አይገታውም። ጴጥሮስ በዘመናት ወደፊት ዘልቆ፥ መኖሪያችን የምንላትን መሬት የወደፊት ዕጣ ሲገልጥ እንዲህ ይላል። ''ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፥ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፥ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል'' (2ኛ ጴጥ. 3፡10)። እግዚአብሔር በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት በሰው ዘር ላይ የመጨረሻ ፍርዱን ከሰጠ በኋላ ይህችን ዓለም ለዘላለም ያጠፋታል (ራእይ 20፡11-15)። አሁን ያሉትን ዓለማት የሚተካቸው ምንድነው? እግዚአብሔር ''ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር'' (2ኛ ጴጥ. 3፡13) ይፈጥራል።

ጴጥሮስ እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የማይከናወኑ ነገሮችን በዝርዝር የሚገልጠው ለምንድነው? የገለጠው እውነት ለአንባቢዎቹ የሚኖረው ተገቢነትስ ምንድነው? የትንቢቶቹን ተገቢነት በመልእክቱ ውስጥ በሦስት የተለያዩ ጊዜያት ገልጧል። በእያንዳንዱ ጊዜ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን አሁን ከሚኖራቸው ተገቢነት ጋር አገናኝቷቸዋል። ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች የሚኖረን እውቀት በአሁኑ ሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይገባል።

የመልእክቱን የመጀመሪያ ተገቢነት 2ኛ ጴጥሮስ 3፡11-12 ውስጥ እንዲህ ገልጦታል፦ ''ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ፥ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኮላችሁ በቅዱስ ኑሮ

እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል?”። ትንቢት የግል ቅድስናን ሊያፈራ ይገባል። እግዚአብሔር በዓለም ላይ እንደሚፈርድና እኛም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንደምንቀርብ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (2ኛ ቆሮ. 5፥10)። በዚህ ዓለም ያለ ነገር ሁሉ የሚጠፋ መሆኑንም የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል። ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን ማወቃችን ትክክለኛው ተስፋችን ላይ እንድናተኩር ይረዳናል።

ዩኒቨርስቲ ውስጥ በምማርበት ጊዜ፥ ድንገተኛ ፈተና ማቅረብ የሚወዱ ብዙ መምህራን ነበሩኝ። በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ በማንኛውም ሰዓት፥ “አንድ ገጽ ወረቀት አውጡና ስማችሁን ከራስጌ ጻፉ” የሚለውን የማይወደድ ቃል መስማት የተለመደ ነበር። ለምንድነው አንዳንድ አስተማሪዎች እንዲህ ያለውን ፈተና መስጠት የሚወዱት? ምክንያቱም ብዙ ተማሪዎች እንዲህ በድንገት የሚጠየቁ መሆናቸውን ካልተረዱ፥ የሚፈለግባቸውን የክፍል ሥራና ምንባብ እንደማያከናውኑ ከልምድ ያገኙት ግንዛቤ አለ።

እግዚአብሔርም ስለሚመጣው የዘመን ፍጻሜ ፈተናውና፥ የፈተናው ውጤት ስለሚኖረው ዘላለማዊ ጠቀሜታ አስታውቋል። የደኅንነትን የምሥራች የመስማት ዕድል ያልገጠማቸው ወይም በክርስቶስ ያላመኑ ሰዎች የዘላለም ሞት ፍርድ አለባቸው። ለክርስቶስ ከማገልገል ይልቅ፥ ደስታቸውን ብቻ የሚሹ ክርስቲያኖችም ሥራቸው ይመዘናል፥ ለፍርድም ይቀርባሉ። የመጨረሻው የፍርድ ቀን የሚመጣ መሆኑን ያወቁት የጴጥሮስ መልእክት አንባቢዎች፥ በቅድስና ለመኖርና የወንጌሉን የምሥራች ላልሰሙት ለማድረስ ተነሣሥተዋል።

ጳውሎስ፥ በሁለተኛው የተገቢ ሁኔታዎች ማስገንዘቢያ መልእክቱ እንዲህ ብሏል፡- “ስለዚህ ወዳጆች ሆይ ይህን እየጠበቃችሁ ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ሆናችሁ በሠላም በእርሱ እንድትገኙ ንቁ” (2ኛ ጴጥ. 3፥14)። ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች የሚኖረን እውቀት በዛሬ ሕይወታችን ላይ ለውጥ ማምጣት አለበት። በሚቀጥለው ወር የምታገባ መሆኗን የምታውቅ ሙሽራ፥ የመጨረሻውን ዕለት ያለ ዝግጅት አትጠብቅም። የጋብቻዋ ዕለት እርግጠኛነት የዕቅድና የድርጊቶቿ መሪ ይሆናል፤ ስለዚህ የመጨረሻው ዕለት ሲመጣ የተዘጋጀች ሆና ትገኛለች። እኛም ለመጨረሻው ዕለት ዛሬ ዝግጅት እንጀምር ዘንድ፥ እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች አስገንዝቦናል።

ጴጥሮስ፥ 2ኛ ጴጥሮስ 3፥17 ውስጥ ለአንባቢዎቹ የሰጣቸው የመጨረሻው የተገቢ ሁኔታዎች ማስገንዘቢያ እንዲህ ይላል፡- “እንግዲህ እናንተ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ፥ በዓመፀኞቹ

ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ"። ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች ማወቃችን ከስሕተትና ከመታለል ይጠብቀናል። እግዚአብሔር በትንቢት የተናገራቸውን ለመፈጸም ዛሬ በዓለም ውስጥ የሚሠራ መሆኑን ያምናሉ? እምነትዎ የጸና ለመሆኑ ማረጋገጫው፥ የሚናገሩት ነገር ሳይሆን የአኗኗር ሁኔታዎ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ትንቢቶችን ለምንድነው የምናጠናቸው? ዓላማችን የሚታዩ ቻርቶችንና ግራፎችን በመሥራት አእምሮአችንን በእውነቶች መሙላት ነው? እንዲያ ከሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን ትንቢት እግዚአብሔር ባቀደው መንገድ አይደለም የምንጠቀምበት። እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን የገለጠልን ሕይወታችንን ለመለወጥ ነው። ትንቢትን መቀበል ያለብን በፍርሃት፥ እንዲሁም የሚሆኑ ነገሮችን የሚገልጥና የሚፈጽመውን የዓለማት አምላክ ድንቅ አሠራር በማድነቅ መሆን አለበት። የሕዝቦችን ዕጣ ወይም ዕድል የሚያከናውን አምላክ የሕይወታችንን ዝርዝር ጉዳዮች የሚሠራ መሆኑን ስንረዳ፥ መጽናናትና ብርታት ሊሰማን ይገባል። ይህ የእግዚአብሔር ሥራ በዙሪያችን ለሚፈጠሩ ሁኔታዎች አንበገርም የማለት አቅምን፥ ጽናትና እድገትን የሚሰጠን መሆን አለበት። በመጨረሻም እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርገውን መረዳታችን በቅድስና እንድንኖር ሊያነሣሣን ይገባል፤ ምክንያቱም ለምንጠየቀው ነገር መልስ ለመስጠት አንድ ቀን እፊቱ እንቆማለን።

> ምዕራፍ አሥራ ስምንት <

# ቢሆንስ ታዲያ?

ያለሁበት ቡድን የዮርዳኖስን ምድረ በዳ ቁልቁል ከሚመለከተው ኮረብታ አናት ላይ ሲደርስ፥ ፀሐይ ወደ ምዕራብ አዘቅዝቃ ነበር። ከሸለቆው የሚነሣው ጥቁር ጥላ ከብርሃን ጋር እየተፎካከረ፥ ሽቅብ ወደ ይሁዳ ኮረብታ የሚወጣውን ጠመዝማዛና ጎርበጥባጣ ገደል ፈካ፥ ጠቆር በማድረግ ላይ ነው። ደረቅና ቀዝቃዛ ንፋስ የተሸሸገውን ጥላ ካንቀላፋበት ለመቀስቀስ ወደ ቋጥኛማው ሸለቆ ያፏጫል። ኃይለኛው የቀትር ፀሐይ ብርሃን በወጣባቸው ጊዜ ይበልጥ ይነጡ የነበሩት ኖራማ ኮረብታዎች፥ አሁን የምሽት ጨረር አርፎባቸው ወርቅማ ነሐስ መስለዋል። ሌሎቹ ባዶና ሕይወት አልባ ኮረብታዎች ደግሞ ቋጥኝና ድንጋይ ለብሰዋል።

ባለንበት ተቀምጠን፥ በነዚህ የእስራኤል ምድር ኮረብታዎች አናት ላይ አሸጋግረን በመመልከት ላይ እንዳለን፥ አስጎብኛችን አንድ መቅረፀ ድምፅ አወጣና ከፈተው፤ መቅረፀ ድምፁም የእስራኤል መሢሕ ከመምጣቱ ሰባት መቶ ዓመታት በፊት በነቢዩ በኢሳይያስ የተናገረውን ትንቢት በመዝሙር እንዲህ አሰማን፦ “አጽናኑ ሕዝቤን አጽናኑ፥ ይላል አምላካችሁ። ለኢየሩሳሌም ልብ ተናገሩ፤ የተቀጠረችበትን ወራት እንደ ተፈጸመ፥ ኃጢአቷም እንደ ተሠረየ፥ ከእግዚአብሔርም እጅ ስለ ኃጢአቷ ሁሉ ሁለት እጥፍ እንደተቀበለች ወደ እርሷ ጩኹ” (ኢሳ. 40፡1-2)። የእስራኤል መሢሕ ሠላም ይዞ የሚመጣ መሆኑን እግዚአብሔር አስቀድሞ ተናግሯል። መቼ ነበር መሢሑ የሚመጣው ታዲያ?

የእግዚአብሔር ፕሮግራም እና የእስራኤል ደኅንነት የሚጀምርበት ጊዜ ምልክቶችን ኢሳይያስ እንዲህ በማለት ገልጦታል፦ “የአዋጅ ነጋሪ ቃል፥ የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጎዳና በበረሃ አስተካክሉ። ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፥ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማውም ይቃናል፥ ሰርጓጉጡም ሜዳ ይሆናል” (ኢሳ. 40፡3-4)። አሁን የዮርዳኖስ ምድረ በዳ ላይ አፍጥጬ ሳለሁ ነው የኢሳይያስን ትንቢት የተረዳሁት።

እግዚአብሔር የማይቻል የሚመስልን ነገር እንኳ ለእስራኤል ሊያደርግላት ቃል ገብቶላታል። ሕዝቦቹን ሊያድን ይመጣ ነበር፤ የሚከለክለውም አልነበረም። የዮርዳኖስ ምድረ በዳ ውስጥ የነበሩ ተደጋጋሚ መሰናክሎች እንኳን አላቆሙትም። ተራራ፥ ሸለቆ ወይም ጠመዝማዛ ቦታዎች አላገዱትም። ይሁን እንጂ፥ መቼ ነው የእግዚአብሔር ፕሮግራም መጀመር የነበረበት? በምድረ በዳው የ“አዋጅ ነጋሪ ቃል” ነበር የጀመረው።

ኢሳይያስ ትንቢቱን ከተናገረ ሰባት መቶ ዓመታት በኋላ "ዮሐንስ፥ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በምድረ በዳ እየሰበከ መጣ" (ማቴ. 3፡1)። ያለሁበትን ምድረ በዳ በጥሞና እየተመለከትኩ፥ የዮሐንስ ድምፅ ከንፋስ ጋር ተዋሕዶ ሽንተረሩን ሲያቋርጥ የሚሰማ ይመስለኛል። ኢሳይያስ የተናገረውን ትንቢት ዮሐንስ በትክክል ፈጽሞታል። "በምድረ በዳ የሚጮኽ ድምፅ" ነበር።

አውቶቡሳችን ላይ ተሳፍረን ወደ ኢየሩሳሌም የሚያመራውን ዳገታማ ጉዞ ጀመርን። ከተማይቱ መዳረሻ ላይ ያለውን የመጨረሻ ኮረብታ ከመውጣታችን ቀደም ብሎ ነበር ጨለማው አካባቢውን የሸፈነው። የጉዟችን አባላት ከጥቂት ጊዜ በፊት ስላደመጡት ቃል እውነትነት እያሰላሰሉ በጸጥታ ተቀምጠዋል። አውቶቡሳችን ኮረብታው አፋፍ ላይ ወጥቶ የኢየሩሳሌም ከተማ ስትታየን፥ አስጎብኛችን "መሲሑ" ከሚለው የመዝሙር መልእክት አንድ የመጨረሻ ክፍል፥ "ሃሌሉያ! የዚህ ዓለም መንግሥት የጌታችንና የልጁ የክርስቶስ ስለሆነ ለዘላለም ይነግሣል" የሚለውን አሰማን። ዮርዳኖስ ምድረ በዳ ውስጥ በነበርንበትና፥ ኢየሩሳሌም በደረስንበት ጉዞ መካከል በነበረው ግማሽ ሰዓት ውስጥ፥ ስለ ክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት ትንቢት በተነገረበትና የዳግም ምጽአቱ መዳረሻ እስከሆነበት ወቅት ድረስ ያለውን ጊዜ በአሳብ ተጓዝነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ መጥቶ ነበር። እንደገናም ወደ ምድር ይመጣል። ሕዝቦችን በብረት በትር የሚገዛ የይሁዳ አንበሳ ሆኖ ነው ዳግም የሚመጣው። ኢየሱስ ወደ ምድር በሚመለስበት ዋዜማ የተከናወኑ ዋና ዋና ነገሮችን በዚህ መጽሐፍ በቀረበ ጽሑፍ መርምረናል።

## ጠቅለል ሲደረግ

አሁን በዓለም የሚሆኑ ነገሮችን ስንመለከትና መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ቃል ጋር ስናነጻጽራቸው፥ እግዚአብሔር ረጅምና አስደናቂ የሆነውን ታሪክ የመጨረሻ ክንውን በፍጥነት በመሥራት ላይ መሆኑን እመለከትና እደነቃለሁ። የመጀመሪያ ምልክታችን ሕዝቧ ከ1900 ዓመታት ስደት በኋላ ተመልሶ ሕልውና ያገኘችው እስራኤል ናት። እግዚአብሔር ለዘመናት ባለው ፕሮግራሙ ውስጥ እስራኤል መካከለኛውን ስፍራ ይዛለች። ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ለመውሰድ በአየር ሲመጣ፥ እስራኤል በክንውኑ መድረክ መካከል ትገባና የመሪ አቀንቃኝነት ሚናዋን ትቀጥላለች። ድርጊቱ የሚጀምረው፥ ከመጀመሪያ አንሥቶ

የምትጠብቀውን እውነተኛ ሠላም ለእስራኤል በሚሰጠው የሠላም ስምምነት መፈረም ነው። ያ ሠላም፥ በኋላ በሚፈጠሩ ሁኔታዎች ይፈርሳል።

በዘመኑ ፍጻሜ እስራኤል ስለሚገጥሟት ሁኔታዎች መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የሚገልጠው ነገር አለ። በአካባቢው ክንውን ውስጥ የሚገቡ ሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ መንግሥታትም በነቢያት ተጠቅሰዋል። ዘመናዊቱ ኢራቅ ውስጥ የምትገኘው ባቢሎን፥ በምጣኔ ሀብት የመሪነት ስፍራን ይዛ ብቅ ትላለች፤ ይህ ምናልባት ነዳጅ ዘይትን በመቆጣጠር ሊሆን ይችላል። ኢራን፥ ሊቢያ፥ ሱዳን ምናልባትም ቱርክ በፍጻሜው ዘመን አጭር ሚና ይኖራቸዋል። በዚሁ መሠረት እስራኤልን በድንገት ይወሯታል፤ ወረራው ግን በእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ይከሽፋል።

በአሜሪካን መንግሥት ድንገት መውደቅ ሳቢያ የተፈጠረውን የኃይል ክፍተት ለመተካት፥ አንድ የአውሮፓውያን ኅብረት ይፈጠራል። የአሜሪካን መንግሥት በፍጻሜው ዘመን የመሪነት ሚና አይጫወትም። ይህ የሚሆንበት ምክንያት አልተነገረንም።

ይህ የአውሮፓውያን ኅብረት የዓለም ሠላም አምጪነትና ጠባቂነት ሚናን መጫወት ይጀምራል። የኅብረቱ የመጨረሻ መሪ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ ያውጅና ስገዱልኝ ይላል። እስራኤላውያን አንሰግድልህም ሲሉት፥ ሊያጠፋቸው ይሞክራል። በሰይጣን ስለሚታገዝ ምንም የማይገታው ብርቱ ይመስላል። መጨረሻው ግን ፈጣንና ፍጹም ይሆንና፥ ኢየሱስ መንግሥቱን ለመመሥረት ወደ ምድር ሲመለስ፥ ከነሕይወቱ ወደ እሳት ባሕር ይጥለዋል።

እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን በመግለጥ ላይ ነው። እንደ ዕድል ነጋሪ፥ ወይም ጠንቋይ የሰዎችን ስሜት ለመሳብ ሲል አይደለም ትንቢት የሚናገረው። የዓለማት አምላክ እርሱ ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲል፥ ወደፊት የሚሆኑ ዋና ዋና ነገሮችን በቅድሚያ ተናግሯል። በእርሱ ማመንን እንድንማርና እሳቡ እስኪፈጸም እየጠበቅን ቅዱስ ሕይወት ለመኖር ይቻለን ዘንድ፥ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን አስታወቀን። በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱት ነገሮች እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ከገለጣቸው ትንቢቶች ጋር እስከተመሳሰሉ ድረስ መከናወናቸው አይቀርም።

የእርስዎ ስፍራ የት ነው? አማራጭ ቁጥር 1

*ራእይ መጽሐፍ ውስጥ እንደተመዘገበው፥ እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚከናወኑ ነገሮች አስደናቂና ሰፊ ትንቢት ለሐዋርያው ዮሐንስ*

ገልጦለታል። ዮሐንስ፥ በመጽሐፉ ከአራተኛው ምዕራፍ ጀምሮ አንባቢዎቹን ሊያስቡት ከሚቻላቸው ነገር ሁሉ በላይ ወደሆኑ የወደፊት ነገሮች ይወስዳቸዋል። ወደፊት ስለሚመጣው አስቸጋሪ ጊዜ፥ የችግሩን ዋና ዋና ተሳታፊዎች፥ ኢየሱስ የራሱን መንግሥት ለመምራት የሚመለስ መሆኑን፥ በዓለማት ላይ ስለሚበየነው የመጨረሻ ፍርድ እና በዘመናት ሁሉ የነበሩ ቅዱሳን የሚኖሩባት ኢየሩሳሌም ያለችበት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ስለ መመሥረቷ ይገልጣል።

ዮሐንስ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን ካስገነዘበ በኋላ፥ በመጽሐፉ የመጨረሻ ምዕራፍ ስለ አሁኑ ዘመን ይገልጣል። ለአንባቢያኑ ያስተላለፋቸው የመደምደሚያ ቃላት፥ የኢየሱስ ዳግም ምጽአት ከሕይወታችን ጋር ያለውን ግንኙነት እንድንመዝን ያስገድደናል። የዮሐንስ የመጀመሪያ ትኩረት፥ በትንቢት የተነገሩ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር እንደተናገረው የሚከናወኑ መሆኑን ማስገንዘብ ነው። "እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነት ናቸው፤ የነቢያትም መናፍስት ጌታ አምላክ በቶሎ ሊሆን የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ እንዲያሳይ መልአኩን ሰደደ" (22፡6)። ከዚያ ለጠቅ በማድረግ ኢየሱስ ክርስቶስ በመልአኩ አማካይነት፥ "እነሆም በቶሎ እመጣለሁ፥ የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው" (22፡7) ብሏል።

ነቢያት የተናገሯቸው ትንቢቶች ይፈጸማሉ። ኢየሱስም ዳግም ወደ ምድር ይመለሳል። እግዚአብሔር ይሆናሉ ያላቸው ነገሮች ሁሉ ይሆናሉ። ታዲያ በዚህ የእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የእርስዎ ስፍራ የት ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ለመውሰድ ሲመጣ፥ እርስዎንም ወደ መንግሥተ ሰማያት ይወስድዎታል? መንግሥተ ሰማያት የዘላለም ስፍራ ስለ መሆኑስ እርግጠኛ ነዎት?

ዮሐንስ፥ ማንኛቸውም ነገሮች እግዚአብሔር እንደተናረ የሚፈጽሙ መሆኑን ከመሰከረ በኋላ፥ ወደ መልእክቱ አንባቢዎች መለስ በማለት፥ ማድረግ የሚገባቸውን እንዲያደርጉ ዕድል ይሰጣቸዋል። መጀመሪያ የሚያተኩረው፥ ስለ ወደፊት ዕጣቸው እርግጠኞች ወዳልሆኑት ሰዎች ነው። እነዚህ ሰዎች ምዕራፍ 21 ውስጥ በዮሐንስ የተጠቀሰችው ዘላለማዊት የኢየሩሳሌም ከተማ ነዋሪዎች መሆን አለመሆናቸውን አያውቁም። እንዲህ እያለ ነው ዮሐንስ ለእነዚህ ሰዎች ተስፋ የሚሰጣቸው:- "መንፈሱ [የእግዚአብሔር መንፈስ] እና ሙሽራይቱም [ሙሽራ የተባለችው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ 21፡9-10] ና ይላሉ። የሚሰማም ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወት ውኃ እንዲያው ይውሰድ" (22፡17)።

እርስዎ ለእግዚአብሔር ጥሪ በዚህ አኳኋን መልስ ሰጥተዋል? ሁላችንም አጥፍተናል፥ የእግዚአብሔርንም ትእዛዛት ተላልፈናል። ሮሜ መጽሐፍ ውስጥ ጳውሎስ፥ "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል" (ሮሜ 3፥23) በማለት ያስገነዝበናል። ሰው ሁሉ ስለሚያጠፋ፥ እግዚአብሔር አንዳንድ አስቸጋሪ በታዎች ላይ ወደ መንግሥተ ሰማያት የማስገቢያ ነጥቦቹን ዝቅ ያደርጋል ብለን እንገምት ይሆናል። እርሱ ግን መስፈርቶቹን ዝቅ አያደርግም፤ ቃሉም "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና" (ሮሜ 6፥23) ይላል። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የሆነ ሰው ብቻ ነው በራሱ ችሎታ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የሚችል።

እግዚአብሔር ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንድንሆን ይፈልጋል። ነገር ግን ኃጢአት ስለሠራን ለዚያ ኃጢአት መቀጣት አለብን። ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንኖር ዘንድ፥ የኃጢአታችን ዕዳ የሚከፈልበትን መንገድ እግዚአብሔር ሊያዘጋጅ ይችላል? "ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቶአልና፥ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" (ሮሜ 5፥8)። ኢየሱስ ሰውም፥ እግዚአብሔርም ስለሆነ ፍጹም ነው። ፍጹም ሕይወት ኑሮ የመስቀል ላይ ሞት ሞቷል። ስለ ክፉ ሥራዎ ለርስዎ የሚገባዎትን ቅጣት በመስቀል ላይ ከፍሎልዎታል።

የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ዋጋ፥ ሊከፍሉት ከሚቻልዎ እጅግ የላቀ ነው። እግዚአብሔር ግን ራሱ የመግቢያ ዕዳዎን ከፍሎ ዘላለምን ሊሰጥዎ እጆቹን ዘርግቷል። ለዚህ ነው መንፈሱና ሙሽራይቱ "ና!" የሚሉት። የዘላለም ሕይወት ሊገዛልዎ እግዚአብሔር ራሱ ዋጋውን ከፍሏል። ሊያደርጉት የሚገባ ነገር "የሕይወት ውኃ ስጦታን በነጻ መውሰድ ነው"።

ዛሬ የዘላለም ሕይወትን እንዴት ሊያገኙ ይችላሉ? መጀመሪያ፥ ኃጢአተኛ መሆንዎንና በራስዎ መልካም ሥራ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የማይችሉ መሆንዎን ይገንዘቡ። ሁለተኛ፥ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ የኃጢአትዎን ዕዳ ለመክፈል በመስቀል ላይ መሞቱን ማመን አለብዎት። ከሞት የመነሣቱ እውነት የሚያረጋግጠው የእርሱ ቤዛነት በቂ መሆኑን ነው። ሦስተኛ፥ ለዘላለማዊ ዕጣዎ ወይም ሕይወትዎ በኢየሱስ ይመኑ፤ የዘላለም ድነት ተስፋዎንም በርሱ ላይ ያድርጉ። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጸሎት በመጸለይ አሁኑኑ ይህን ለማድረግ ይችላሉ፦

*"ጌታ ሆይ ኃጢአተኛ መሆኔንና ፍጹም ከሆነው መንገድህ የወጣሁ መሆኔን አውቃለሁ፤ ኃጢአት ከአንተ እንደ ለየኝም እገነዘባለሁ። ስለ*

ኃጢአቴ በመስቀል እንዲሞት ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ምድር የላክኸው መሆንህን አምናለሁ። የኃጢአቴን ዕዳ ለመክፈል ሲል በመስቀል ላይ በሞተልኝ በኢየሱስ አምናለሁ። እባክህ በደሌን ይቅር ብለህ የዘላለም ሕይወትን ስጠኝ፤ አሜን"።

ይህን ጸሎት ከልብዎ ከጸለዩ፥ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት እንኳን በደህና መጡ እንልዎታለን። ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛቸው መሆኑን ለሚያምኑ ሁሉ፥ የዘላለም ሕይወት የሚሰጣቸው መሆኑን እግዚአብሔር እንዲህ በቃሉ አረጋግጧል፦ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር እንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐ. 3፥16)። በእግዚአብሔር ሊታመኑ ይችላሉ።

ይህን ጸሎት ከጸለዩ፥ ጥቂት የመጨረሻ አሳቦች ልስጥዎ። መጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስዎን ማንበብ ይጀምሩ። የኃጢአትዎን ዕዳ ለመክፈል ስለሞተልዎ፥ ስለ ክርስቶስ ይበልጥ ለመረዳት፥ ከአዲስ ኪዳን፥ የዮሐንስ ወንጌልን በማንበብ ይጀምሩ። ሁለተኛ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን የምታምንና የምታስተምር አንድ ጥሩ ቤተ ክርስቲያን በአቅራቢያዎ ይፈልጉ። ቤተ ክርስቲያኒቱ ፍጹማን የሆኑ ሰዎች የሚከማቹባት አይደለችም፤ ሕመምተኞች ፈውስ ፍለጋ የሚሄዱበት ሆስፒታልን ትመስላለች። ሰዎች መንፈሳዊ ፈውስ ወይም መስተካከል የሚያገኙባት ናት። ለቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ክርስቶስን ለመቀበል መወሰንዎን ይንገሯቸውና፥ በክርስትና ሕይወትዎ ለማደግ የሚረዳዎ ትምህርት ወይም መመሪያ ይሰጡዎ ዘንድ ይጠይቋቸው።

## የእርስዎ ስፍራ የት ነው? አማራጭ ቁጥር 2

ትንቢት ገና በክርስቶስ ካላመኑት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ዮሐንስ ለአንባቢዎቹ ከገለጠ በኋላ፥ በክርስቶስ ላመኑት አሳብ በማካፈል መልእክቱን ያጠቃልላል። እንዴት ነው ታላቁ የትንቢት እውነት በአማኞች ላይ ተጽዕኖ የሚኖረው? ራእይ 22፥20 ውስጥ እንዲህ በማለት ራሱ መልስ ይሰጣል። "ይህን የሚመሰክር [ኢየሱስ ክርስቶስ] አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል"። ኢየሱስ ከርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊወስዳቸው የሚመጣ መሆኑን አማኞች ማስታወስ አለባቸው። በእግዚአብሔር ትንቢታዊ አጀንዳ ውስጥ ይህ ሁለተኛው ክንውን ነው። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ለመውሰድ በአየር የመምጣቱ ጊዜ፥ ዳግም ወደ ምድር ከመምጣቱ ጋር ሊምታታ አይገባም። የመጀመሪያው አመጣጡ 1ኛ ተሰሎንቄ 4 ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን፥ በማንኛውም ጊዜ ሊሆን የሚችል

ነው። ሁለተኛው አመጣጥ፥ ከሰባት ዓመቱ መከራ በኋላ የሚከናወን ሲሆን፥ እስራኤልን የሚመለከቱ ብዙ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችም ይፈጸሙበታል።

ኢየሱስ በማናቸውም ሰዓት ሊመጣ የሚችል መሆኑን በርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ያስገነዝባል። ዮሐንስ ዳግም በኢየሱስ ያመኑ ሁሉ ሊናገሩ የሚገባቸውን ቃል በመጥቀስ፥ "አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና" ይላል። የእግዚአብሔር የትንቢት ቃሎች፥ ትኩረታችንን ከችግራችን ላይ አንሥተን ወደ ሰማይ እንድናዞር ያስገድዱናል። ሕይወት ዛሬ አስቸጋሪ በሆነበት ሁኔታ ለዘላለም አይኖርም። ኢየሱስ በማንኛውም ባልተጠበቀ ጊዜ የመለከቱን ድምፅ በማሰማት መጥቶ፥ ከዚህ አስቸጋሪ ዓለም ይወስደንና ከርሱ ጋር ለዘላለም እንኖራለን።

ከአንድ ክፍለ ዘመን ቀደም ባለ ጊዜ ቺካጎ (አሜሪካ) ውስጥ የኖረ አንድ ክርስቲያን ጠበቃ ብዙ ችግሮች ገጥመውት ነበር። ሆራሺዮ ስፓፈርድ የተባለ ይህ ሰው ቺካጎን ባጋያት ቃጠሎ ሳቢያ ከባድ መሰናክል ገጠመው። ንብረቱን እንደገና እስኪያስተካክል ድረስ ሚስትና ልጆቹን ለእረፍት ወደ አውሮፓ ላካቸው። ቤተሰቦቹ ወደ ለንደን በመጓዝ ላይ እንዳሉ መርከባቸው ግጭት ደረሰባትና ሰጠመች። ከአደጋው የተረፈችው ባለቤቱ ብቻ ናት። ልጆቹ በረዷማው ውቅያኖስ ውስጥ ሰጠሙ።

ስፓፈርድ አሳዛኙን ዜና እንደሰማ ወደ አውሮፓ ተጓዘ። የተሳፈረባት ጀልባ የተጓዘችው፥ ልጆቹ የሞቱበት አደጋ በደረሰበት አቅራቢያ ነበር። አደጋውን እያስታወሰ በኀዘን፥ በብቸኝነትና በሥቃይ ቢሠቃይም፥ ከክርስቶስ ጋር ካለው አንድነት የተነሣ ተጽናና። በሥቃይ ረመጥ ውስጥ ሆኖ "ነፍሴ ሠላም ናት" በሚል ርእስ ቀጥሎ ያለውን መዝሙር ጻፈ።

> "ሠላም እንደጅረት ቢያጅበኝ፥
>
> ኀዘን እንደ ባሕር ማዕበል ቢያስፈራራኝ፥
>
> ዕድል ፋንታዬ ምንም ይሁን፥
>
> መልካም ነው፥ ነፍሴ ሠላም ናት" ማለትን አስተማርከኝ።

እንዲህ ባለ ፈታኝ ጊዜ ስፓፈርድ በነበረው ሠላም ተደንቄአለሁ። የግጥሙን የመጨረሻ ስንኝ ልብ ብዬ ተመለከትኩ። በዙሪያው ያለው ነገር ሁሉ በፈራረሰ ጊዜ፥ በጸጥታ እንዲጸና የረዳው፥ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት እውነት ነበር። ስፓፈርድ የተመሠረተው 1ኛ ተሰሎንቄ 4 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር መለከት ድምፅ ሲሰማ፥ ጌታ ራሱ ከሰማይ የሚመጣ መሆኑን በገለጠው ቃል ላይ ነው። ይህ ሰው፥ በጽሑፉ ራእይ

22፡20 ውስጥ ያለውን ቃልም ጠቅሷል። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ ኢየሱስ ቶሎ የሚመጣ መሆኑን ከገለጠ በኋላ "አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎ ና" ብሏል። ይህን አሳብ ነው የስፓፈርድ ግጥም የያዘው።

ይህ ሰው ለምን እንዲህ ያለ ችግር እንደደረሰበት አልተረዳም። ነገር ግን "ሁሉን ለበጎ" እንደሚያደርግ ተስፋ በሰጠ አምላክ እምነት ነበረው። እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ በማስተካከል ላይ መሆኑን ትንቢቱን የሚፈጽምበት ዕለት በመምጣት ላይ መሆኑን አውቋል። ስለ እግዚአብሔር የወደፊት ፕሮግራም የነበረው ግንዛቤ፥ በክፉ ቀናት ሁሉ በእርሱ እንዲታመን አደረገው።

እርስዎም ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን እንዳይፈሩ ነው የምጸልይልዎ። ይህ የትንቢት ጥናት፥ እምነትዎ፥ ታሪክን በሚቆጣጠረው በእግዚአብሔር እንዲጸና ይረዳዎታል ብዬ አምናለሁ። ቃላችን ቀጥሎ ካለው የስፓፈርድ ቃል ጋር የሚመሳሰል ይሁን፡-

"ጌታ ሆይ፥ እምነት ገሐድ የሚሆንበትን ጊዜ አፋጥን ደመናት እንደወረቀት ይጠቅለሉ

መለከት ይሰማ፥ ጌታም ይውረድ

አሜን! ነፍሴ ሠላም ናት!"

# አባሪዎች

የሚፈልጉትን ጥቅስ/አርእስት በተመለከተው ገጽ ባያገኙት፥ ከገጹ በፊትና ኋላ ያሉትን ገጾች ይመልከቱ።

# የእንግሊዝኛ ቃላት ዝርዝር

## የሰዎች ስም

| | |
|---|---|
| ሀርትዝል፥ ቲዎዶር | Hertzl፥ Theodore |
| ሐሺም ራፋሳንጃኒ | Hashemi Rafsanjani |
| ሀንድል | Handel |
| ሂትለር፥ አዶልፍ | Hitler፥ Adolph |
| ሊዲያ | Lydia |
| ሌኒን | Lenin |
| ሙዓመር ጋዳፊ | Muammar Qaddafi |
| ሙስጠፋ ከማል አታቱክ | Mustafa Kemal Ataturk |
| ሜኢር፥ ጎልዳ | Meir፥ Golda |
| ሞዋያድ ሰይድ | Mouyad Said |
| ሳዳም ሁሴን | Saddam Hussein |
| ስሚዝ፥ ጆሴፍ | Smith፥ Joseph |
| ስታሊን፥ ጆሴፍ | Stalin፥ Joseph |
| ስፓፈርድ፥ ሆራሽዮ | Spafford፥ Horatio |
| ሻህ | Shah |
| ራሚ ካውሪ | Rami Khouri |
| ሬገን፥ ሮናልድ | Reagan፥ Ronald |
| ርትሜየር፥ ሊን | Ritmeyer፥ Leen |
| ቂሮስ | Cyrus |
| ቡሽ፥ ጆርጅ | Bush፥ George |
| ባር ኮክባ | Bar Kokhba |
| ቤጊን፥ ሚናሂን | Begin፥ Menachem |
| ቤከር፥ ጄምስ | Baker፥ James |
| ቤን ጎርዮን | Ben Gurion |
| ቱርጋት ኦዛልን | Turgut Ozal |
| ቱትሞስ 3ኛ | Thutmose III |
| ታይተስ | Titus |
| ቻርልስ ደጎል | Charles de Gaulle |
| ቻምበርሌይን፥ ኔቪል | Chamberlain፥ Neville |
| ናፖሊዮን | Napoleon |
| ኔሮ | Nero |
| ኖቤል | Nobel |
| አል-ሳውድ | Al-Saud |
| አያቶላ ኮሆሚኒ | Ayatollah Khomeini |
| አርጤክስስ | Artaxerxes |
| አብዱላህ | Abdullah |
| አንዋር ሳዳት | Anwar Sadat |
| አውግስጦስ ቄሳር | Augustus Caesar |
| አያቶላ ሩሆላ ሆሚኒ | Ayatollah Ruhollah Khomeini |
| አሚር ታሂር | Amir Taheri |
| አብዱል አዚዝ ኢብን ሳውድ | Abdul Aziz Ibn Saud |
| ታሪክ አዚዝ | Tariq Aziz |
| ኦቶ | Otho |
| ኪሲንጀር፥ ሔንሪ | Kissinger፥ Henry |
| ካርተር፥ ጂሚ | Carter፥ Jimmy |
| ካውፍማን፥ አሼር | Kaufman ፥ Asher |
| ክሊንተን | Clinton |
| ኮለምበስ | Columbus |
| ዝቪ | Zvi |
| የልሲን፥ ቦሪስ | Yeltsin፥ Boris |
| ድሬይፈስ | Dreyfus |
| ዶላን፥ ዴቪድ | Dolan፥ David |
| ጃክ ድሎርስ | Jacques Delors |
| ጆሴፈስ | Josephus |
| ጋማል አብዱል ናስር | Gamal Abdel Nasser |

ጋልባ Galba
ጎርባቾቭ፥ ሚካኤል Gorbachev፥ Mikhail
ፀረ-ክርስቶስ Anti-Christ
ቪቴሊየስን Vitellius
ቬስፓስያን Vespasian

## የህብረተሰብ ክፍሎች፡ ሕዝቦችና ድርጅቶች

ሚዶ-ፐርሺያ Medo-Persians
ሞርሞንስ Mormons
ሰርባውያን Serbs
ሱኒ Sunni
ሲሜሪያውያን Cimmerians
ሲቲያን Scythian
ሺያት Shiite
ባዝ Ba'ath
የአውሮፓ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን European Economic Community
ኦፔክ OPEC (Organization of Petroleum Exporting Countries)
ኢንቲፋዳ Intifada
ኦቶማን Ottoman
ኩርድስ Kurds
ኪሜሮይ Kimmerioi
ክሮሾች Croats
ዋህቢ Wahabi
ጊሚራይ Gimirrai
የፍልስጥኤም ነጻ አውጭ ድርጅት PLO (Palestinian Liberation Organization)

## የቦታ ስሞች

ሊቢያ Libya
ሉቱዋኒያ Lithuania
ሉክሰንበርግ Luxembourg
ላቲቪያና Latvia
ሎከርቢ Lockerbie
መሳዳ Masada
መጊዶ Megiddo
ሜሪላንድ Maryland
ሚግዶል Migdol
ሞልዳቪያ Moldavia
ሳዑዲ አረቢያ Saudi Arabia
ስሎቬኒያ Slovenia
ስኮትላንድ Scotland
ሮማንያ Romania
ቡልጋሪያ Bulgaria
ባስፓራስ Bosporus
ባለዓለት ጉልላት Dome of the Rock
ባስክ Basque
የቤተ መቅደስ ተራራ ታማኞች Temple Mount Faithful
ቤሩት Beirut
ቤልጂየም Belgium
ብራሰልስ Brussels
ቱርክሜኒስታን Turkmenistan
ታጂክስታን Tajikistan
ታቦር ተራራ Mt. Tabor
ቴል አቪቭ Tel Aviv
ቶቦልስክ Tobolsk
ቺካጎ Chicago
ቼርኖቤል Chernobyl
ቼኮዝላቫኪያ Czechoslovakia
ኔዘርላንድስ Netherlands
አርማጌዶን Armageddon
አማን Amman

| | |
|---|---|
| አስዋን | Aswan |
| አስቶኒያ | Estonia |
| አርሜንያ | Armenia |
| አዘርባጃን | Azerbaijan |
| ኡዛቤክስታን | Uzbekistan |
| ኢራቅ | Iraq |
| ኢራን | Iran |
| ኢስታምቡል | Istanbul |
| ኤሊያ ካፒቶሊና | Aelia Capitolina |
| ኩዌት | Kuwait |
| ኪርጊስታን | Kyrgyzstan |
| ካዛኪስታን | Kazakhstan |
| ካርሜል ተራራ | Mt. Carmel |
| ክሮሽያ | Croatia |
| ዩጎዝላቪያ | Yugoslavia |
| ዩክሬን | Ukraine |
| ዮርዳኖስ | Jordan |
| ያድ ቫሽም | Yad Vashem |
| ዳአርዳኖሊስ | Dardanelles |
| ጄዝሬል | Jezreel |
| ጆርጂያ | Georgia |
| ግዮን ምንጭ | Gihon Spring |
| ፉጥ | Put |
| ፋርስ ባሕረ-ሰላጤ | Persian Gulf |
| ካስፒያን ባሕር | Caspian Sea |
| ፋኦ ፔኒንሱላ | Fao Peninsula |
| ፔንሲልቫንያ | Pennsylvania |
| ፖላንድ | Poland |
| ቬትናም | Vietnam |

### ጥቃቅን

| | |
|---|---|
| የመከር በዓል | Feast of Ingathering |
| ማርሻል ፕላን | Marshall Plan |
| ሮሽ ሀሽና | Rosh Hashanah |
| ስከድ | Scud missile |
| ስፑትኒክ | Sputnik |
| የበረሃው ማዕበል ዘመቻ | Operation Desert Storm |
| የናዚ መንግስት ጭፍጨፋ | Nazi Holocaust |
| ኒውዮርክ መጻህፍት | New York Times |
| ኖቤል የሰላም ሽልማት | Nobel Peace Prize |
| አቺሌ ላውሮ | Achille Lauro |
| ኤል አክሳ | El-Aksa |
| የፋርስ ቋንቋ | Farsi |
| የኩርድ ቋንቋ | Kurdish |
| ኮለምበስ ዴይ | Columbus Day |
| ዋርሶ የጦር ቃል ኪዳን | Warsaw Pact |
| ዮም ክፑር በዓል | Yom Kippur |
| የዳስ በዓል | Feast of Tabernacles |
| የድንኳን በዓል | Feast of Booths |
| ፕሬስትሮይካ | perestroika |

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማውጫ


ዘፍጥረት
ም. 1-11 ... 14
2 ፥ 7 ... 31
3 ፥ 1-7 ... 71-72
10 ፥ 2-5 ... 86
11 ፥ 3 ... 92
11 ፥ 30 ... 16
12 ፥ 2-3 ... 15
12 ፥ 3 ... 22፥ 75
12 ፥ 4 ... 16
ም. 12-14 ... 15
13 ፥ 14-17 ... 16
ም. 15 ... 15፥ 17
15 ፥ 2-3፥ 6 ... 16
15 ፥ 4-5 ... 15-16
15 ፥ 9-17 ... 17
15 ፥ 18 ... 17፥ 23
15 ፥ 19-21 ... 23
19 ፥ 24 ... 135
ም. 37 ... 72፥ 153
37 ፥ 31-35 ... 39
49 ፥ 20 ... 92

ዘጸአት
3 ፥ 2 ... 17
19 ፥ 18 ... 17
ም. 20-40 ... 24
40 ፥ 35 ... 24

ዘሌዋውያን
25 ፥ 1-5 ... 38
ም. 26 ... 19፥ 70
26 ፥ 33፥ 42፥ 44 ... 19
26 ፥ 33-35 ... 38

ዘኁልቍ
9 ፥ 15-16 ... 17
13 ፥ 29 ... 23
23 ፥ 19-20 ... 20
ም. 34 ... 24
34 ፥ 2 ... 23
34 ፥ 3-12 ... 24

ዘዳግም
ም. 28 ... 20፥ 70
28 ፥ 63-64 ... 19
28 ፥ 64-65 ... 70
ም. 30 ... 38
30 ፥ 3 ... 20
ም. 33 ... 91
33 ፥ 24 ... 91

ኢያሱ
10 ፥ 11 ... 135
11 ፥ 1-3 ... 23
ም. 14-21 ... 24

1ኛ ነገሥት
4 ፥ 20-21 ... 21
6 ፥ 38 ... 65
9 ፥ 15 ... 173

2ኛ ነገሥት
15 ፥ 3 ... 185
23 ፥ 29 ... 173
25 ፥ 2-4 ... 28

2ኛ ዜና
2ኛ ዜና 36 ፥ 21 ... 40

ነህምያ
2 ፡ 3፥ 5 ............ 41

ኢዮብ
1 ፡ 6-12 ............ 72
2 ፡ 1-7 ............ 72
42 ፡ 5-6 ............ 39

መዝሙር
22 ፡ 7-8 ............ 196
22 ፡ 16 ............ 195
22 ፡ 18 ............ 196
ም. 105 ............ 22
105 ፡ 8-11 ............ 22

ኢሳይያስ
ም. 1 ............ 54
1 ፡ 2፥ 15፥ 18፥ 23 ............ 54
ም. 2 ............ 55
2 ፡ 2 ............ 115
2 ፡ 4 ............ 54፥ 131
ም. 7-12 ............ 55
7 ፡ 14 ............ 55
9 ፡ 6፥ 7 ............ 55
11 ፡ 6-9 ............ 54-55
ም. 13 ............ 106
13 ፡ 19 ............ 107
ም. 13-14 ............ 112
14 ፡ 1 ............ 107-108
36 ፡ 1-2 ............ 186
37 ፡ 14፥ 20፥ 36 ............ 186
39 ፡ 2፥ 6-7 ............ 188
40 ፡ 1 ............ 211
40 ፡ 15፥ 17 ............ 180-181
41 ፡ 22-23 ............ 188
44 ፡ 7 ............ 189፥ 197
ም. 45 ............ 189
45 ፡ 1 ............ 128
45 ፡ 1፥ 4-5 ............ 189
53 ፡ 3 ............ 195
53 ፡ 4-6 ............ 70
53 ፡ 5-6፥ 8 ............ 151፥ 196
53 ፡ 9 ............ 196
53 ፡ 10 ............ 197
ም. 59 ............ 203
59 ፡ 20 ............ 203
59 ፡ 21 ............ 131

ኤርሚያስ
25 ፡ 11 ............ 191
25 ፡ 11-12 ............ 38
29 ፡ 10 ............ 38
30 ፡ 3 ............ 74
30 ፡ 7 ............ 74-75
ም. 30-33 ............ 74
31 ፡ 31-34 ............ 131
50 ፡ 3 ............ 170
50 ፡ 4-5፥ 40 ............ 108
ም. 50-51 ............ 106፥ 112
51 ፡ 25 ............ 115

ሕዝቅኤል
3 ፡ 26-27 ............ 27
24 ፡ 1-2፥ 15-27 ............ 27
29 ፡ 10 ............ 127
33 ፡ 22 ............ 28-29
ም. 33-48 ............ 24
ም. 36 ............ 31፥ 33
36 ፡ 24፥ 28 ............ 29
36 ፡ 25-27 ............ 29-30
36 ፡ 33-34 ............ 30
ም. 36-37 ............ 37፥ 52
ም. 37 ............ 33
37 ፡ 3 ............ 30
37 ፡ 10-12 ............ 31
37 ፡ 14 ............ 31፥ 33
37 ፡ 16 ............ 32
37 ፡ 21-22 ............ 31-32

ም. 38 ........................ 85፥ 86
38 ፡ 2 ........................ 84
38 ፡ 2-3፥ 6 ........................ 126
38 ፡ 5 ........................ 127
38 ፡ 6 ........................ 85
38 ፡ 8፥ 11 ........................ 51፥ 130
38 ፡ 14፥ 19-22 ........................ 134
38 ፡ 22 ........................ 134-135
38 ፡ 23 ........................ 135
ም. 38-39 ........................
............ 52፥ 84-85፥ 87፥ 126-127
ም. 39 ........................ 24
39 ፡ 22 ........................ 131
39 ፡ 25 ........................ 24፥ 52፥ 131
39 ፡ 29 ........................ 52፥ 131
ም. 40-43 ........................ 24
43 ፡ 5 ........................ 24
43 ፡ 13-44፡31 ........................ 24
ም. 48 ........................ 25

ዳንኤል
ም. 1 ........................ 145
1 ፡ 3 ........................ 188
ም. 2 ........................ 115፥ 145-150
2 ፡ 4 ........................ 145
2 ፡ 32 ........................ 148
2 ፡ 34 ........................ 148
2 ፡ 35 ........................ 115
2 ፡ 36 ........................ 146-147
2 ፡ 38 ........................ 147
2 ፡ 38-39 ........................ 115
2 ፡ 39፥ 40 ........................ 148
2 ፡ 40-45 ........................ 112
2 ፡ 43 ........................ 155
2 ፡ 44 ........................ 115፥ 145
ም. 2-7 ........................ 145-146፥ 153
ም. 3-4 ........................ 146
ም. 4-5 ........................ 149
ም. 5 ........................ 146
5 ፡ 30-31 ........................ 148
ም. 6 ........................ 146
6 ፡ 5 ........................ 191
ም. 7 ........................
......... 42፥ 64፥ 73፥ 145-146፥ 149
7 ፡ 4፥ 5 ........................ 149
7 ፡ 6 ........................ 150
7 ፡ 7 ........................ 150፥ 154
7 ፡ 14 ........................ 145
7 ፡ 16 ........................ 147
7 ፡ 23-27 ........................ 112
7 ፡ 24 ........................ 154
7 ፡ 25 ........................ 42፥ 73፥ 154
7 ፡ 27 ........................ 151
ም. 8 ........................ 145-148
8 ፡ 20፥ 21 ........................ 148
ም. 9 ........................
............ 38፥ 41-42፥ 46፥ 62፥ 150
9 ፡ 1-3 ........................ 191
9 ፡ 3፥ 11፥ 15-19 ........................ 39
9 ፡ 17-18 ........................ 39
9 ፡ 19፥ 23፥ 24 ........................ 39
9 ፡ 25 ........................ 40-41፥ 151
9 ፡ 26 ........................
.................. 43-44፥ 52፥ 151፥ 152
9 ፡ 26-27 .... 112፥ 153፥ 160
9 ፡ 27 ........................
.............. 42፥ 44፥ 46፥ 52-53፥ 62
ም. 11 ........................ 101፥ 162
11 ፡ 36 ........................ 101
11 ፡ 36-45 ........................ 176
11 ፡ 37፥ 38 ........................ 163
11 ፡ 40 ........................ 101
11 ፡ 40-41 ........................ 177
11 ፡ 40-42 ........................ 163
11 ፡ 41 ........................ 101፥ 102
11 ፡ 42-43 ........................ 102፥ 177
11 ፡ 44 ........ 102፥ 103፥ 177
11 ፡ 45 ........................ 102፥ 177

12 ፡ 1 ........74
12 ፡ 4 ........199

ኢዮኤል
ኢዮኤል 3 ፡ 9-12........178

ሚክያስ
5 ፡ 2 ........195
ም. 7 ........18
7 ፡ 11፥ 19 ........18
7 ፡ 20 ........18፥ 22

ሐጌ
ሐጌ 1 ፡ 15........66

ዘካርያስ
3 ፡ 1-2........72
ም. 5 ........111
5 ፡ 5-11........112
5 ፡ 7-8፥ 11 ........111
9 ፡ 9 ........43፥ 195
14 ፡ 2 ........178፥ 179
14 ፡ 3-5........179

ማቴዎስ
2 ፡ 7-8፥ 16-18 ........72-73
3 ፡ 1 ........212
4 ፡ 1-11........73
4 ፡ 17 ........148
16 ፡ 1-4........6
16 ፡ 21-23........73
21 ፡ 1-2፥ 4 ........195
ም. 24 ........193፥ 194
24 ፡ 2፥ 3፥ 4-33፥ 51 ........45
24 ፡ 4-14........193
24 ፡ 4-31........45
24 ፡ 6-7........80
24 ፡ 21-22........75
24 ፡ 15........193
24 ፡ 15-16........46፥ 62
24 ፡ 15-21........177፥ 193
24 ፡ 30........75
24 ፡ 31........131
25 ፡ 13፥ 36፥ 42፥ 44........46
26 ፡ 28፥ 53........70
27 ፡ 22........44
27 ፡ 25........70
27 ፡ 28-31፥ 35፥ 39-43፥
57፥ 59-60 ........196
28 ፡ 5-6 ........196

ማርቆስ
9 ፡ 24........16
14 ፡ 21........75

ሉቃስ
1 ፡ 54-55 ........22
2 ፡ 4፥ 6 ........195

ዮሐንስ
3 ፡ 16........216
13 ፡ 21-30........73
13 ፡ 34........75
19 ፡ 15........150
20 ፡ 25........194

የሐዋርያት ሥራ
1 ፡ 6-8 ........75
2 ፡ 29-31 ........197
17 ፡ 1-9 ........204
17 ፡ 11........198

ሮሜ
3 ፡ 23........215
5 ፡ 8........215

6 ፡ 23 ............ 215
ም. 9-11 ............ 203
11 ፡ 17፥ 25-26፥ 33 ...... 203

1ኛ ቆሮንቶስ
13 ፡ 1-13 ............ 75

2ኛ ቆሮንቶስ
5 ፡ 10 ............ 208
11 ፡ 14 ............ 162

ገላቲያ
5 ፡ 22 ............ 75

1ኛ ተሰሎንቄ
ም. 4 ............ 216፥ 218
4 ፡ 13-18 ............ 204
4 ፡ 13-5፡11 ............ 133
4 ፡ 16-17 ............ 204፥ 205
4 ፡ 18 ............ 205
ም. 5 ............ 50
5 ፡ 2-3 ............ 50
5 ፡ 3 ............ 7
5 ፡ 3-4፥ 9፥ 11 ............ 205

2ኛ ተሰሎንቄ
2 ፡ 1-2 ............ 205
2 ፡ 2 ............ 63፥ 206
2 ፡ 3 ............ 160፥ 206
2 ፡ 3-4 ............ 63፥ 205
2 ፡ 4 ............ 194
2 ፡ 5 ............ 205
2 ፡ 6-12 ............ 206
2 ፡ 9-10 ............ 164
2 ፡ 13 ............ 206
2 ፡ 15 ............ 206-207

2ኛ ጢሞቴዎስ
3 ፡ 16 ............ 185

ዕብራውያን
6 ፡ 13-17 ............ 18
11 ፡ 13 ............ 21


1ኛ ጴትሮስ
1 ፡ 10-11 ............ 199


2ኛ ጴትሮስ
1 ፡ 20-21 ............ 8
ም. 3 ............ 207
3 ፡ 2፥ 3 ............ 207
3 ፡ 3-4፥ 8-9 ............ 194
3 ፡ 9፥ 10 ............ 207
3 ፡ 11-12 ............ 208
3 ፡ 13 ............ 207
3 ፡ 14፥ 17 ............ 208


1ኛ ዮሐንስ
2 ፡ 18 ............ 160

ራእይ
ም. 1 ............ 153
1 ፡ 19 ............ 153
ም. 2-3 ............ 153
3 ፡ 10 ............ 133
ም. 4 ............ 153፥ 214
4 ፡ 1 ............ 153
ም. 4-19 ............ 153
6 ፡ 2 ............ 163-164
7 ፡ 4 ............ 153
ም. 11 ............ 153
ም. 12 ............ 43፥ 64፥ 71-72
12 ፡ 1 ............ 72፥ 153


12 ፡ 4 ............................ 72
12 ፡ 5 ............................ 72-73
12 ፡ 6 .............. 42፣ 64፣ 73
12 ፡ 9 .............. 64፣ 71፣ 72
12 ፡ 13 ............................ 73
ም. 12-13 ............................ 64
ም. 13 ..................... 42፣ 154
13 ፡ 1 ............................ 154
13 ፡ 2 ............................ 160
13 ፡ 4 ............................
............ 64፣ 154-155፣ 165፣ 169
13 ፡ 5 ..................... 42፣ 154
13 ፡ 5-7፣ 11፣ 12 ............ 64
13 ፡ 14-15 ............................ 65
ም. 16 ............................ 174
16 ፡ 12-16 ............................ 174
16 ፡ 16 ............................ 173
16 ፡ 17-21 ............................ 175
16 ፡ 18፣ 20-21 .... 175፣ 176
16 ፡ 19 ................ 110፣ 112
ም. 16-19 ............................ 110
ም. 17 ............................
........... 109፣ 110-111፣ 112፣ 115
17 ፡ 1 .................. 111፣ 114
17 ፡ 2 ............................ 109
17 ፡ 3 .................. 114፣ 169
17 ፡ 4 ............................ 109
17 ፡ 5 ............................ 112
17 ፡ 6 ............................ 109
17 ፡ 7 ........... 112-113፣ 169
17 ፡ 9-10 ............. 113፣ 115
17 ፡ 15 ............................ 114
17 ፡ 16 ....... 103፣ 109፣ 170
17 ፡ 17 ............................ 109
17 ፡ 18 ............................
......... 109፣ 112፣ 116፣ 155፣ 170
17 ፡ 17-18 .. 110፣ 115፣ 169
ም. 18 ........... 109፣ 110-111
18 ፡ 2 .................... 109፣ 112
18 ፡ 3 ........... 92፣ 109፣ 116
18 ፡ 5፣ 6፣ 8 ................. 109
18 ፡ 9 ...................... 116-117
18 ፡ 10 ............................ 109
18 ፡ 11 ............................ 170
18 ፡ 12-13 ............................ 92
18 ፡ 16 ............................ 109
18 ፡ 17 ............................ 92-93
18 ፡ 17-19 ............................ 93
18 ፡ 19 ............................ 170
18 ፡ 24 ............................ 109
19 ፡ 1-3 ............................ 110
19 ፡ 11-21 ............................ 180
19 ፡ 20-21 ............................ 180
20 ፡ 11-15 ............................ 207
ም. 21 ............................ 214
21 9-10 ............................ 215
ም. 22 ............................ 214
22 ፡ 6፣ 7 ............................ 214
22 ፡ 17 ............................ 215
22 ፡ 20 ............................ 218


ሶርያ
(የፈረንሳይ የሞግዚት
አስተዳደር)
ቤይሩት
ታላቅ ባሕር
ደማስቆ
ጢሮስ
ኃይፋ
ቴል አቪቭ
አማን
ኢየሩሳሌም
ጋዛ
ቤርሳቤህ
ፍልስጥኤም
ሲና
የእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር
1920-1946
ኤላት
አካባ
የኤላት
ባሕር ሰላጤ
ሳዑዲ ዓረቢያ


ሶርያ
(የፈረንሳይ የሞግዚት
አስተዳደር)
ቤይሩት
ታላቅ ባሕር
ደማስቆ
ጢሮስ
ኃይፋ
ቴል አቪቭ
አማን
ኢየሩሳሌም
ጋዛ
ቤርሳቤህ
ከዮርዳኖስ ማዶ
ሲና
የእንግሊዝ የማከፋፈል እቅድ
1946
ኤላት
አካባ
የኤላት
ባሕር ሰላጤ
ሳዑዲ ዓረቢያ




የአሁኗ እስራኤል — 2003 እ.ኤ.አ.


ጥቁር ባሕር
ሮማንያ
ቦዝኒያ
ዩጎዝላቪያ
ቡልጋሪያ
መቄዶንያ
አልባንያ
ግሪክ
ጆርጂያ
አዘርባጃን
አርሜንያ
የካስፒያን ባሕር
ቱርክ
ኢራን
ሶርያ
ኢራቅ
ቀርጤስ
ቆጵሮስ
ሊባኖስ
ታላቅ ባሕር
እስራኤል
ዮርዳኖስ
የሱዌዝ ቦይ
ሲና
ሊቢያ
ግብፅ
ሳውዲ ዓረቢያ
ኩዌት
የፋርስ
ባሕር-ሰላጤ
[redacted]